ስብሀት ገ/እግዚአብሔር

# እነሆ ጀግና!



# ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- |
| 1. ታከለ ታገለ | 1 |
| 2. ቴዎድሮስ | 20 |
| 3. ማህትማ ጋንዲ | 47 |
| 4. አብርሃም ሊንከን | 59 |
| 5. ጋሊሊዮ፣ ማርቲን ሉተርና ጆርዳኖ ብሩኖ | 63 |
| 6. ኤድጋር አላን ፖ | 72 |
| 7. ኮናን ዶይል | 77 |
| 8. ዮሀን ቮልፍጋንግ ገተ | 81 |
| 9. ቼሆቭ | 85 |
| 10. ጀግናው በላይ ዘለቀ | 88 |
| 11. ካስትሮ | 101 |
| 12. ቼ ጉዌቫራ | 107 |
| 13. ሆ ቺ ሚን | 114 |
| 14. ማኦ ዜዱንግ | 117 |
| 15. ደጎል | 121 |
| 16. ዣን ፖል ሳርትርና ሌሎቹ | 129 |
| 17. ማርክ ትዌን | 133 |
| 18. ገማል አብድል ናስር | 136 |

# ክፍ 1 ል

# ታከለ ታገሰ

## (ከልጅነት እስከ አርበኝነት)



በግምት የዛሬ ሃያ ዓመት አንድ ጓደኛዬ እንዲህ ሲለኝ አስታውሳለሁ።

«ታከለ ወልደ ሐዋርያት የሚባል ሰይጣን አለ ባክህ!» («ሰይጣን» ሲል በብልሀትና በጉብዝና ከሰው በላይ የሆነ ማለት ነው።) እኚህን ሽማግሌ ንጉስ እረፍት ነሣቸው። እንኳን ነፃ ሆኖ ደቅርና ተግዞ ወይም ታስሮም ቢሆን ይፈሩታል። አንድ ጊዜማ ቢጨንቃቸው በግቢያቸው ውስጥ አሰሩት። ታዲያ አንድ ሌሊት ተኩስ ሰምተው ከእንቅልፋቸው ይነሳሉ ሽሜ። የተኩሱን ምክንያት ማንንም ከመጠየቃቸው በፊት የታሰረውን ታከለን ስልክ ደውለው እንዲህ አሉት። «ታከለ! እዚቾው አብረን እንሞታለን እንጂ አታመልጠኝ!»

«እንዲህ ከፈሩት ለምን አይገድሉትም?»

«ታከለን የገደልክ ዕለት አለቀልህ። ሦስት ቀንም አትቆይም ብለዋቸዋል!»

«እነማን?»

«ጠንቋዮች:: ደሞ ጠንቋዮቹን እንዲህ እንዲሉ የነገራቸው ማን መሰለህ? ታከለ ራሱ።»

ሥዩም ስብሐት የደጃዝማች ታከለ ደቀ መዝሙርና የቅርብ ተባባሪ ሆኖ 14 ዓመት ያህል አሳልፏል:: እዚህ ፁሑፍ ውስጥ የሚገኘውን አብዛኛውን የነገረኝ እሱ ነው:: በሚነግረኝ ጊዜ ይህን እገሌ ናቸው የነገሩኝ፤ ይህን ደጃዝማች ራሳቸው ናቸው የነገሩኝ፤ ይህ ሲሆን እዚያው አብሬአቸው ነበርኩ፤ እያለ ነው ያጫወተኝ:: ደጃዝማች ታከለን ያወቁዋቸው አብረዋቸው የሠሩ አብረዋቸው የተዋጉ፣ እና ለሥዩም ስብሐት ያጫወቱት ጥቂቶቹን ብቻ ለመጥቀስ ያህል እነሆ ::

- ብላታ ኪዳነ ማርያም አበራ .... የቅርብ ወዳጃቸው

- ሻለቃ ሙሉሰው ምትኩ ..... አብረዋቸው የዘመቱ::

- ፊታውራሪ ኃይሉ ከብረት ...... ወንድሙ ከሳቸው ጋር የዘመተ::

- አቶ ሰይፉ ድባቤ .... የልጃቸው ባል::

- ራስ ውብነህ ተሰማ፣ ደጃዝማች ብሬ ዘገየ፣ ደጃዝማች አየናዬ ቸኮል እና ደጃዝማች በላይ መኮንን - በአርማጨሆ አብረዋቸው የዘመቱ አርበኞች

- አያሌ የሆለታ ገነት ልጆች

- ደጃዝማች ገብረ መስቀል ሀብተማርያም - በሱዳን ስደተኛ የነበሩ::

- ፊታውራሪ ወልደ ጊዮርጊስ ተድላ ነገዶ::

- አቶ ህሩይ ረዳ - ኬንያ ስደተኛ የነበሩ::

- ደጃዝማች መኮንን ደስታ - የትምህርት ሚኒስትር የነበሩና እጅግ የተደነቀላቸው ምሁርና አገር ወዳድ

- እና ቀኛዝማች ገብረ እግዚአ ስብሐት - ገና ስዩም ከደጃዝማች ጋር ላይ ሳይወቅ በፊት አስደናቂ አድርገው የነገሩትና ከሩቅ ፍቅር ያሳደሩበት::

ሆኖም ይህ ፅሑፍ እንደ «ታሪክ» ሊነበብ አይገባውም:: ደጃዝማች ታከለን ከብዙ ተከታዮቻቸው አንዱ በምን ዓይን እንደሚያያቸው ለማሳየት እንደተፃፈ ሊቆጠር ይገባዋል:: እንግዲያው ምን ዋጋ አለው? መነሻ ሊሆን ይችላል:: ሌሎችም ደጃዝማች ታከለን በቅርብ ያወቁ አብረዋቸው የሠሩ፣ አብረዋቸው የተዋጉ በየበኩላቸው የሚያውቁትን ቢፅፉ ተጠራቅሞ፤ ተስተያይቶ፤ የሚቃረኑበት ቢኖር እሱ ተመርምሮ ተጣርቶ ታሪክ ይሆናል::

ታከለ ወልደ ሐዋርያት (ከእንግዲህ «ደጃዝማች» የሚለውን ልተወው ነው፣ ታከለ ከማዕረግና ከሹመት በላይ ነውና) የሀገር ቅርስ ነው:: ከማንም በፊት ከገዛ ሕይወቱም በፊት አገሩን የሚያስቀድም ታላቅ ሰው ነው::

እኔ በበኩሌ ስለታከለ በሰማሁ ጊዜ ደስታ፣ አድናቆት፣ ኩራት ነው የተሰማኝ:: ከንግዲህ ወዲያ በኢትዮጵያዊነቴ ከሚያኮሩኝ ከጥቂቶቹ ታላላቅ

ኢትዮጵያውያን መሀል ታከለ አንዱ ይሆናል። ይህ ዓይነቱ ሀብት ለሌሎች ቢያስተላልፉት የማይቀንስ ስለሆነ - እንዲያውም ተላቶፈም በ እየበዛ ስሄዱ እየበዛ የሚሄድ ስለሆነ - ታከለን ለሌሎች ማስተላለፍ ራሱ ደስታን የሚያሰኝ ነው።

(የታሪክ ተማሪዎችና ምሁራን ይህን ለሁፍ እንደምታነቡ ተስፋ አለኝ። የቆክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል። «ጊዜ» የሚሉት ሌባ ሳይወስደብን ታከለ ወልደ ሐዋርያት «አባ ሰላም - የፈሪ ባላ» የተባለውን ሀብታችንን ሰብስቡልንና በመፅሐፍ አትሩልን። ያሁንና የመጪው ትውልድ መብትም ነው፤ የናንተ ግዴታም ነው።)

ሥዩም ስብሐት ስለታከለ ወልደሐዋርያት ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማው ያስራ አምስት፤ ያሥራ ስድስት ዓመት ልጅ ሆኖ ደሴ በሚማርበት ጊዜ ነበር። በ1934 ዓ.ም. (ያን ጊዜ እሱ የሚያደንቀውና ጀግና ነው የሚለው «የሚያመልከው» በላይ ዘለቀን ነበር። አጤ በጉልበቱ! የኖሊያን ሙቅሶቶ!) ንጉሱ ለጉብኝት ይመጣሉ ተብሎ በደሴ ብዙ ዝግጅት ሲደረግ ሰንብቷል። ታድያ እሳቸው ሆዬ፤ እንደዛሬ ደሴ የገቡ እንደ ነገ ወደ አዲስ አበሯቸው!

ምነው ምን ነካቸው ቢባል፡ «ታከለ ወልደ ሐዋርያት አሊጋ ሊገለብጥ ሲል ተያዘ» ተባለ።

ሥዩም ስብሐት አደገ። ለትምህርት ወደ አውሮፓ ሄደ። እንደ አብዛኛው ተማሪና ወጣት ምሁር ሁሉ፤ የኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ለኢትዮጵያ አይበጅም፤ ለውጥ ያስፈልጋል ብሎ ያምናል። ከዚህም ጋር ንጉሡን በጣም ይጠላቸዋል። በላይ ዘለቀን አስገድለውበታላ!

«ስዊስ፣ ኢንግላንድ፣ በፖለቲካ ዓይናችንን ከፈትን» ያላል ሰዩም፤ «ወጣት ነን፤ ልበ ንፁህነት አለ፤ ሀሳባችን ለጊዜው ይፈነጫል.. ግን ያ ሀሳባችን በተግባር ይተረጎማል ወይ? አናውቅም።»

እነ ሥዩም ስብሐት ወደ አገራቸው ተመለሱና ሁኔታውን ቃኙ።

«እኛ እፍኝ አንሞላም። በዚህ ላይ ንጉሡ ከሕዝቡ ከልለውናል።»

«ካቶሊኮች ናቸው - አገራቸውን አያውቁም - ያባቶቻቸውን ወግ ይንቃሉ» በሚል ፕሮፓጋንዳ ሕዝቡ እንዳይቀርበን አድርገዋል።

ስለዚህ ወጣቶቹ አንድ ሰው ያስፈልጋቸዋል - ያ ሰው በአንድ በኩል ሕዝቡ የሚያውቀው፤ የሚያከብረው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወጣቶቹ ምሁራን እንደ ተራማጅ የሚቆጥሩት መሆን ይኖርበታል። ይህን ሰው ፍለጋ ጀመሩ።

ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የፀጥታ ዳይሬክተር የሰዩም ጓደኛው ነው። «ደጃዝማች ታከለ በጣም ግሩም ሰው ናቸው» እያለ ይነግረዋል።

በዚህ መሀል የባንክ ሰራተኛ እንቅስቃሴ ብቅ ይላል። «እኛ በመጠንኛ

ደሞዝ መሥራት የምንችለውን ሥራ የውጭ ዜጎች ብዙ ደሞዝ ይበሉበታል። ሥራውን እኛ እንረከብ» ባዮች ናቸው።

ባለስልጣኖቹ «ይህን ሁሉ ሰራተኛ ማነጋገር አንችልም። የሚወክሉዋችሁን ጥቂት ሰዎች ምረጡና እነሱ ያነጋግሩን» ይላሉ፤ ሰራተኞቹም እሺ ብለው ሰባት ሰው ይወክላሉ።

ሰባቱ እንደቀንደኛ አድመኞች ተቆጥረው፣ እንዲገረፉ፣ እንዲታሠሩና እንዲጋዙ ይታቀዳል። ታከለና ወርቅነህ ገበየሁ ሲያድኗቸው ይፈልጋሉ። ግን የሚያደርጉት ይጨንቃቸዋል። አንድ ላይ ይመካከራሉ (ያን ጊዜ ታከለ ከእስራት ተፈትተው ያገር ግዛት ምክትል ሚኒስትር ናቸው - ማለትም የወርቅነህ አለቃ።)

ታከለ «አባ ሰላም» ለጃንሆይ ደብዳቤ መፃፍ ነው ይሉታል። «በግርማዊነትዎ ብርታትና ጥረት ተምረው አገራቸውን ለማገልገል ደርሰው ፈረንጅ የያዘውን ስራ እኛ ኢትዮጵያውያን እንችለዋለን ስላሉ፣ ማለት ግርማዊነትዎ ባርቆ አስተዋይነቱ የተከለው አሁን ለፍሬ በመድረሱ፣ አሁን እነዚህን መቅጣት የአሳሳችን ምክር መስማት ይመስላል። በመማር ላይ ያሉትና የተማሩት ኢትዮጵያውያን እንደዚሁም የውጭ ዜጎች ግርማዊነትዎ ትምህርትንና ችሎታን ኮትኩቶ ያሳድጋል እያለ ሳለ፣ አሁን እነዚህ ትምህርትም ሙያም አለን በማለታቸው ቅጣት ቢደርስባቸው...» እያለ በረዥሙ ፅፎ ሲያበቃ ከተመልካች ብሎ መጨረስ ነው። ምሁራን ከሆኑት ጓደኞችህ አንዱ አይፅፍልህም?»

ወርቅነህ ሥዩም ስብሐትን ይህን ደብዳቤ ፃፍልኝ ይለዋል። ይፅፍለታል። ታከለ ደብዳቤውን አንብበው ሲያበቁ የፃፈውን ሰው አምጣልኝ ይሉታል ወርቅነህን። ቢሮአቸው ይወስድላቸዋል። ያስተዋውቃቸውና ይዉ፡ል።

«ተባረክ!» ይሉታል ሥዩምን «ኃይለ ሥላሴን እንዲህ እያታለልን ነው የኖርነው።»

ንጉሡ «ተመልካች» የላከውን ደብዳቤ አንብበው በባንክ ሠራተኞች ላይ የተሠነዘረባቸው ቅጣት ቀርቶ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ያደርጋሉ።

ጥበበኛው፣ ዘዴኛው፣ በህዝብ ዘንድ የተከበረው ታከለና መሪ ይፈልግ የነበረው ወጣት ሥዩምም ይተዋወቃሉ። ቀስ በቀስ ይቀራረባሉ። ሥዩም እንደ አባቱ፣ እንደ መሪው፣ እንደ አስተማሪው ሊያያቸው ይጀምራል። ታዲያስ? ታከለ ወልደ ሐዋርያት አንዳችም የውጭ አገር ትምህርት አልነበረውም።

ታከለ ወልደ ሐዋርያት ቁመቱ ምናልባት አንድ ሜትር ከሰማንያ ሳንቲም ይሆናል። ከሩቅ ሲያዩት ሙሉ ሰውነት ያለው ይመስላል፣ ቀረብ ሲሉት ግን ቀጠን ያለ ነው። ሰውነቱ ንቁ ነው። በምቾት፣ በድሎት ያልሰነፈ። ጠይም ነው። አገጩ ሰፋ ያለ። ዓይኖቹ ይጫወታሉ።

...የግዛመቹ ኩትልቁ ትልቅ፣ ከትንሹ ትንሽ የማይሆኑ ሰው ናቸው።

ከፊታቸው ቆመህ የፈለግከውን የመሰለህን ልትናገር ትችላለህ፤ ገሪታቸው ይጋብዝሀል:: በሌላ በኩል ደግሞ የክብርና የግርማ ወሰን አለኝ፤ ማንም ሊያልፋት የማይችል::

«የመብል ሰው አይደሉም፤ ስትበላ ደስ ታሰኛቸዋለህ:: ብርንዶ ቁርጡን አይደፍሩትም፤ በትንሹ ብቻ:: መጠጥም አይወዱም:: ለሥነ ስርዓቱ፤ ለወጉ ያህል ብቻ አንድ ብርጭቆ ያህል ይጠጣሉ፤ አብሯቸው ላለው ሲሉ::»

«መንቀባረር የለችም፤ እንደ ተራ ሰው ናቸው፤ ሂያጅ አይደሉም:: እንዳገራችን መኳንንት እቁባት፤ ቅምጥ አያውቁም:: ሁለት ጊዜ አግብተዋል:: የመጀመሪያ ሚስታቸው ወይዘሮ ፋናዬ ወልደ የሱስ ከሳቸው ጋር አርበኛ ነበሩ:: ሞቱ:: ሁለተኛ ሚስታቸው ወይዘሮ አካለወልድ አማኑኤል የንጉሡ ያክስታቸው የልጅ ልጅ ናቸው::»

ታከለ የገንዘብ ፍቅር የለበትም:: እንዲያውም ወዳጆቹ «ታከለና ገንዘብ አይተዋወቁም» እያሉ ይቀልዱበታል::

አንዷ ሴት በወሬ በወሬ «በመቶ ሃያ ሺህ ብር ቤት አሠርቼ» ስትል ታከለ በመገረም «ድንጋይ ለማከማቸት ይህን ያህል?!» ብሏታል::

ገንዘብ የሚወድ ሰው በታከለ ዓይን ደካማ ነው፤ ለገንዘብ ተገዝቶ አገሩን ሊረዳ አይችልም::

ታከለ የሚወደው አገሩን ነው:. ኢትዮጵያን:: ጥልቀቱም ስፋቱም ወሰን የሌለው ፍቅር፤ ለጀብዱም ለትህትናም የሚዳርግ ፍቅር፤ ለሹመትም ለእስራትም የሚያበቃ ፍቅር፤ ለተንኮልም ለቀጥተኛነትም የማይመለስ ፍቅር፤ እስከ ሞት የማይለወጥ ፍቅር::

አንዳንዴ ታከለ ስመመን መሳይ ይይዘውና የተኛ ይመስላል - ብንን ይልና ታዲያ፤ ራሱን እየነቀነቀ «አገሬን ኢትዮጵያን፤ አገሬን ኢትዮጵያን ተፈሪ ተጫወተባት!» ይላል::

ታከለ የኖረውም የሞተውም ለኢትዮጵያ ነው:: ከልጅ ኢያሱ ይሻላል ብሎ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ይበጃል በማለት የተፈሪ ታማኝ ጭፍራ ሆኖ አገለገለ! ተፈሪን ዙፋን ላይ ካስቀመጡት አንዱ ሆነ:. አንዲት ቀን ሳያርፍ ለኢትዮጵያ ሲዋጋ አምስት ዓመት አሳለፈ:: ለኢትዮጵያ ጉዳ ሆኖ ስላገኘው ተፈሪን ከዙፋኑ ለማውረድ ሲታገል፤ ሲታሠር፤ ሲጋዝ፤ ሲፈታ፤ ሲሾም፤ ሲዶልት፤ ሲጠረጠር፤ ሲያዝ፤ ሲታሰር፤ ሲፈታ፤ ሲሾም፤ ሲዶልት፤ እድሜውን ሙሉ ለኢትዮጵያ ሲዋጋላት ኖረ፤ እየተታኮሰላት ሞተ::

ታከለ ወ/ሐዋርያት የተወለደው በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ በቃጅማ ቁርቁራ የእነ ልብነ ደንግል አዝማች ራስ ወሰን ሰገድ ከግራኝ ጋር ሲዋጉ የሞቱበት ስፍራ ናት፤ ቢሾፍቱ አጠገብ::

የታከለ አባት አለቃ ወልደ ሐዋርያት የዜማና ያቋቋም ሊቅ ነበሩ። ታከለም አቋቋምና ዜማ፣ መፃሕፍትን ጠንቅቆ ያስኪደ (የተማረ) ነው። ፍትሐ ነገሥቱንም የጡቀዋል። ዝቋላና እንጦጦ ራጉኤል ነው የተማረው።

ታከለ ያደገበት አካባቢ ገና በወጣትነቱ ንቃት ሳይሰጠው አልቀረም። እነማን ነበሩ? አቶ ሠርፀ መድህን - በጊዜው ሀብታምና የፖለቲካ ሰው። አቶ ተስፋ ጊዮርጊስ-የፈረንሳይ ለጋሲዮን አስተርጓሚ፣ ኢትዮጵያ የመንግስታት ማህበር (ሊግ - ኦቭ - ኔሽንስ) አባል እንድትሆን ሚና የተጫወቱ። ፍቅረ ማርያም አባ ተጫን የታከለ አብሮ አደግና የቅርብ ጓደኛ ነው፤ አብረው ጉግስ እየተጫወቱ ነው ያደጉ። አፈወርቅ ወልደ ሰማያት (ኦጋዴን የወደቀው ጀግና)።

ታከለን «የፖለቲካ መምህሬ ከዚህ ዓለም ኑሮ ጋር ያስተዋወቀኝ» የሚሉት ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ነበሩ። ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ምሁርም አገር ወዳድም ነበሩ። የኢትዮጵያ መንግስት አስተዳደርን የመሠረቱ እሳቸው ናቸው ይባላል።

ልጅ ኢያሱ ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ወዳጅነት እያጠናከሩ ሲሄዱ ጊዜ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ እንዲህ ማለት አመጡ፣ «ኢያሱ የኢትዮጵያ የቅርብ ጠላት ያህል ነው። ኢትዮጵያን ያጠፋታል። ተፈሪ የሩቅ ጠላትዋ ነው፤ በሩቅ ጊዜ ያጠፋታል። አሁን የቅርቡን ጠላት በሩቁ ማስወገድ። እሱ ደሞ ተራውን ይጠብቅ።» ታከለ ይህን ያምናል ስለ ልጅ ኢያሱ። ስለ ራስ ተፈሪ «የሩቅ ጠላት» መባል ግን ውስጡን ይቆረቁረዋል። «እንደ ራስ ተፈሪ ዘመናዊ እና ለኢትዮጵያ የሚያስብ ማን አለና!» ብሎ ያስባል።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የታከለን ንቁና አስተዋይ መሆን ያዩና የምስጢር ፀሐፊያቸው ያደርጉታል። ራስ ተፈሪ ካሸነፉ በኋላ፣ ማለት «የቅርቡ ጠላት በሩቁ ጠላት ከተወገደ በኋላ» ነጋድራስ ገብረ ሕይወት በድንገት ታመው ሞቱ። እድሜያቸው ሠላሳ አንድ ዓመት ከአሥር ወር ነበር።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝን በቅርብ በማወቁና በሀገር ወዳድነታቸው በመማረኩ ምክንያት ለታከለ የውጭ ትምህርት መማር በቀጥታ አገር ወዳድነትን የሚያስከትል ይመስል ነበር። ወደ እርጅናው ከደረሰ በኋላ እንኳ አንዳንዴ በመገረም፣ «እነ እንጊሊዝ የተማሩ ሆነው እንዴት ለተፈሪ ሲሉ አገራቱን ይጉዷታል?» ይላል።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፉዲስ አበባን ማዘጋጃ ቤት በሚያቋቁሙበት ጊዜ ታከለ በፀሐፊነት ተቀጥሮ ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ልጅ ኢያሱ መጡና ብላቴን ጌታን፣ «ለደጃች ገብረ እግዚአብሔር ደብዳቤ መላክ እፈልጋለሁ፤ ፀሐፊ ጥራልኝ» አሉዋቸው። ታከለን አስጠሩላቸው።

«ይኸ ውርጋጥ ነው፤ ምን ይችላል ብለህ ነው?»

«ግድ የለም ትም ይችላል።»

ልጅ ኢያሱ «በል ፃፍ» አሉና ጉዳዩን በፍጥነት ተናግረው ሲያበቁ፣ ታከለ ወደ ቢሮው ተመልሶ ደብዳቤውን ፅፎ አመጣላቸው፣ አነበቡት። ቀደዱት። «በል እንደገና ፃፈው እዚሁ ቁጭ ብለህ» አሉት። ፃፈው፣ አነበቡት።

«ስንት ነው ደሞዙ?» አሉዋቸው ብላቴን ጌታን።

ነገሯቸው። ሦስት አሞሌ ጨውና አንድ ሦስት ብር ትሆናለች - ትንሽ ነች። «ጎሩይ» አሉ ልጅ ኢያሱ «እነዚህ በሰሩት እናንተ ትሾሙበታላችሁ፣ ደሞዝ ትዝቁበታላችሁ።» የታከለ ደሞዝ በልጅ ኢያሱ ትዕዛዝ ተጨመረለት።

ታከለ ለራስ ተፈሪ ፍቅር አድሮበታል። አሁን እኛ «ተራማጅ» የምንለው ዓይነት አገር ወዳድ ስለመሰሉት። እሳቸው ደሞ በበኩላቸው ሊያገለግሉዋቸውና ሊጠቅሙአቸው የሚችሉ ወጣቶችን እየሰበሰቡ ነው።

«ታከለ፣ ይህች የምትወዳት አገርህ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ዘመናዊ ሆና ለምታ ታያታለህ» እያሉ ተስፋ ያሳድሩበታል።

ታከለ ለልዑል ራስ ተፈሪ የማያደርግላቸው ነገር አልነበረም። በፕሮፓጋንዳና መኳንንቱን በማግባባት ይረዳቸዋል። በታማኝነት በመላላክም፣ በሌላ ስራም። «የባርያ ነፃ ዳሬክተር» አድርገው ሾሙት። ባርያን ነፃ የማውጣት ሥራውን እያቀላጠፈ ብዙዎቹን ወግ አጥባቂዎች ሳያስቀይም አልቀረም።

አንድ ቀን ንግሥት ዘውዲቱ አስጠርተው እንዲህ አሉት፣ «ታከለ፣ አንተንኳ ጨዋ የጨዋ ልጅ ትመስላለህ። እናቱ ሌሊት ስትፈጭ የምታድር ይመስል ባርያ ነፃ! ባርያ ነፃ! እያልክ ለአሽከሮቼ አገልጋይ በማሳጣት ምነው አስቸገርከን?!»

አልጋወራሽ ታማኝ አገልጋያቸውን ከመንግሥት ጥላቻ ገለል ለማድረግ ታከለን የምዕራብ ኢትዮጵያ ገበያዎች ምክትል ሹም አድርገው ላኩት። ባርያን ነፃ ለማውጣት የበለጠ እድል አገኘ። ስራውን በትጋት ሲሰራ ከዋናው ሹም ጋር ተጋጨ። ሰውዬው ለግል ጥቅማቸው የቆሙ በመሆናቸው ታከለ አብሯቸው ሊሠራ አልቻለም።

«ስማ አንተ! ከአመድ ጋር ጠርጌ አሽቀንጥሬ ነው እምወረውርህ!» አላቸው ይባላል።

አልጋ ወራሽ ታከለን ከዚያ አነሡት። የከፋ ተጠባባቂ አገረ ገዥ አድርገው ሾሙት።

አሁን እንግዲህ ብዙ ዓመታት እንዘልልና፣ አንድ ቀን ሥዩም ስብሐት ከቦንጋ ወደ ጅማ በመኪና ሲሄድ፣ አንድ ሽማግሌ ታመው ከልጃቸው ጋር ወደ ጅማ ሲሄዱ ግቡ እኔም ወደዚያው ነኝ ይላቸዋል። ልጃቸው እየስተረጐመለት ሽማግሌውን ይጠይቃቸዋል። ገዥዎቻችሁ እንዴት ናቸው? ይላቸዋል። እንዲህ ይሉታል ሽማግሌው፣

«ያኔ አንተ አልተወለድክም:: አንድ ገዥ ነበረን ሀቀኛና ትክክለኛ ዳኛ የሆነ። ልጅ ታከለ ይባል ነበር:: እሱ ተሹሞ መምጣቱን ስንሰማ (አባቴ የቦንጋ ንጉስ ነው) ጦር ከተትንና ቦንጋ ወንዝ ላይ መሽገን ጠበቅነው በጅማ በኩል ይመጣል ብለን:: እሱ ግን በጎሬና በረሚራ በኩል ዞሮ በጀርባችን ቦንጋ ከተማችን ገብቶ ቁጭ! ይህን ስንሰማ እኛም ተመለስንና ቤተ መንግስት ገባን፤ የሚያደርገውን ለማየት::

ቤተ መንግስት መጣና አደግድጎ እጅ ነሣ:: «እንግዲህ መገፋት፣ መበደል፣ መጨቆን፣ መጉሳቆል የለም፤ ባርያ የለም!» አለን:: ልክ እንዳለው ሆኖ አገኘ ነው:: ጉቦ አያውቅ ማዳላት አያውቅ:: እጅ ንሱኝ የለ ሙክት ጉትቱልኝ የለ:: ነገር አይጓተትብን፤ ትክክለኛውን ውሳኔ ማግኘት ነው እንጂ:: ብቻ ምን ልበልህ፤ የእኩልነትና የፍትህ ኑሮን ያስገኘልን ገዥ ነበር:: ጥሩ መሆኑን ሲሰሙ ጊዜ ነው መሰለኝ፣ በሁለት ዓመቱ አንስተው ወሰዱብን::»

ሥዩም ይህን ሲያጫውተኝ «ሞንሲኞር ባርለሲና የተባለ የካቶሊክ ጳጳስ፣ አኪም ቦሩን (በኋላ ራስ ደስታ ሆስፒታልን) የሰራው፣ እሱ ስለ ኢትዮጵያ የጻፈው መፅሐፍ «ታከለ ለከፋ የፍርድና ርትእ አስተዳደር መዘርጋቱንና ብልህ አስተዳዳሪ እንደ ነበረ ዘርዝሮ ፅፎታል» አለኝ::

ታከለ ከከፋ ወደ አዲስ አበባ የተመለሰበት ምክንያት ደጃች ባልቻ ለተፈሪ አልታዘዝም እያለ የሚያንገራግርበት ጊዜ በመሆኑ አልጋወራሽ ታማኞቻቸው አጠገባቸው እንዲሆኑ በመፈለጋቸው ነው::

ታከለ ያገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ፀሐፊ ሆነ:: (ሚኒስትሩ ጌታቸው አባተ።) ከታከለ ተግባሮች አንዱ ያገር ግዛት ሚኒስቴር አፈ ጉባኤ ሆኖ፣ ልዩ ልዩ ሂስ ሲሰነዘር መልስ መስጠት ነበር:: በዚህ ሳቢያ ብርሃንና ሰላም የተባለ ጋዜጣ ውስጥ ታከለ የፃፏቸው ፅሁፎች የጋዜጠኝነት ችሎታ እንደነበረው ያሳያሉ ይላሉ፣ ያነበቧቸው ሰዎች::

ንግስት ዘውዲቱ አረፉ:: አልጋ ወራሹ መንገስ፤ ዘውድ መድፋት ፈሩ:: መሰናክል ሆኜ ልቆይ የሚል ሀሳብ ነበራቸው:: ታከለ ግን ያለ ዘውድ መግዛት አስቸጋሪ ነው ብለው ከተከራከሩዋቸው አንዱ ነበረ:: ኃይለ ሥላሴ ዘውድ ደፉ::

እንግዲህ ታከለ ሲያልምለት፣ ሲመኝለት፣ ሲለፋለት የነበረው ጊዜ ደረሰ:: ለኢትዮጵያ ልማትና እድገት የሚጥርና የዘመኑ ሥልጣኔ ለኢትዮጵያ አስፈላጊ መሆኑን የሚያምን ንጉሥ የነገሠ መሰለው:: ይለፋ ጀመር ታከለ፣ ይጣደፍ ጀመር:: በዚህ በኩል ባርያ ፊዕሞ ነፃ መውጣት አለበት፣ በዚያ በኩል ትምህርት ቤት መከፈት አለበት፣ በዚያኛው በኩል ደሞ ሌላ ዘመናዊ ዕቅድ መመሥረት አለበት ማለቱን ቀጠለ::

ገባው ታከለ ወልደ ሐዋርያት የኢትዮጵያ ፍቅረኛ። ለካ ለኢትዮጵያ መሳሪያ ሆንኩ ሲል ለተፈሪ ኖሯል መሳሪያነቱ። ተራ ሰው ቢሆን ኖሮ «እንግዲህ ሞከርኩ አልሆነም» ብሎ መጠጥ፣ ሴትና ገንዘብ ወደ ማሳደድ ይገባ ነበር። ግን ታከለን ከአብዛኛው ሰው የሚለየው ጠባይ ቢኖር ዛሬ ስለተሸነፈ ትግሉን ያለማቋረጡ ነው። ልጅ ኢያሱ ለኢትዮጵያ አይበጅም ብሎ ባመነበት ሰዓት ልጅ ኢያሱን ለማስወገድ በሙሉ ልቡናውና በሙሉ አቅሙ ታገለ። አሸነፍኩ ሲል ዘወር ብሎ ያያል - ከእጅ አይሻል ዶማ! ሆነ። ያለፈው አለፈ። ታከለ በሕይወቱ እስካለ ድረስ ሁሉ ነገር ያልፋል። የማያልፉት ኢትዮጵያና ታከለ ለሷ ያለው ፍቅር ናቸው። እንግዲያው ተፈሪም ማለፍ አለበት። ነገር ግን ተፈሪን እጥላለሁ ማለት ኢትዮጵያን እስካልጐዳ ድረስ ብቻ ነው። ምክንያቱም ተፈሪም ያልፋል፣ ታከለም ያልፋል፣ የምትዘልቀው ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ስለዚህ የታከለ ዓላማ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ የሚከተለው ይሆናል፣

* * *

## (ከአርበኝነት መልስ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ)

«ኢትዮጵያን ሳልጐዳ ተፈሪን ማስወገድ ከቻልኩ፣ ዋጋው የኔ ሞት ቢሆንም እከፍለዋለሁ። ተፈሪ በሚወድቅበት ሰዓት ኢትዮጵያም ጉዳት የሚደርስባት ከሆነ ግን ተፈሪ እንዳይወድቅ ዋጋው የኔ ሞት ቢሆንም እከፍላለሁ።»

በዚህ መመሪያ ታከለ አባ ሰላም «የፈሪ ባላ» ሕይወቱን እንዴት እንዳሳለፈ በሚቀጥለው ፅሑፍ እንተርካለን።

ኅዳር 1973

ብላታ ታከለ ወልደ ሀዋርያት ሲነሳ አዲስ አበባ ድብልቅልቋ ወጥቶ ነበር። ከአምስት ዓመት አርበኝነት ሲመለሱ አፄ ኃይለ ሥላሴ ቀድመውት ከገቡ ወር ሆኗቸዋል። ግን የከተማው ፀጥታ ገና አልተረጋጋም። ተኩስ ሳይሰማ አይውልም አያድርም።

ከንጉሡ ጋር የገባው የእንግሊዝ ጦርና አምሥቱን ዓመት በዱር በገደል ሲዋጋ የነበረው የኢትዮጵያ አርበኛ እንደ መፋጠጥ ብለዋል። እንግሊዞቹ «ጣልያን የተወው ሀብት ለኛ ይገባናል፣ የሞትንበት ነውና» ባይ ናቸው። ከዚህም ከዚያም ይዘርፋሉ። አርበኞቹ እንግሊዝ ምን እንደሚፈልግና የንጉሡና የእንግሊዞቹ የውስጥ ስምምነት ምን እንደሆነ ሊያውቁ አልቻሉም።

ንጉሡ የደፈረሰውን ፀጥታ የሚያረጋጋላቸው ሰው አስፈለጋቸው፣ ስልጣናቸውን ለማጠናከር ፋታ ያሻቸዋልና። «እኛን ነው እንጂ የሚጠላን፣ ባገር ጉዳይ የማይጠረጠር ነው» ብለው ታከለን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባና የሸዋ አውራጃ ገገር ብለው ሾሙት። እሳቸው የሾሙት ለራሳቸው ጥቅም ብለው ነው፣ እሱም ሹመቱን የተቀበለው ለራሱ ጥቅም ብሎ ነው። ለታከለ

«ጥቅም» ማለት ዓላማውን ከግብ የሚያደርስለት ወይም ለማድረስ የሚረዳው ማለት ነው። በዚህን ጊዜ የሱ አላማዎች ሦስት ነበሩ። አንደኛ፣ ፀጥታ መስፈን አለበት (ሕዝቡ አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደል የተጉዳው ይበቃዋል)። ሁለተኛ፣ እንግሊዝ የኢትዮጵያን ነፃነት አረጋግጦ መውጣት አለበት። ሶስተኛ፣ የተፈሪ ሥልጣን በሕገ መንግስት ሊገደብ ይገባዋል የሚሉት ነበሩ።

ከንቲባው ከተማውን ለማረጋጋት አስፈላጊውን እርምጃ ወሰደ። አርበኛው መጥቶ «እረ እንግሊዞች እንዲህ በደሉን» ሲለው፣ ታከለ ቆጣ ይልና፣ «እሱ ያንገበከው ምንድነው?» ይለዋል። «እሱማ ጣልያንን መግደያ ነው» ሲለው «ይኸስ ከበደለህ ያው አይደል!» ይላል ታከለ። አመራርና እምነት አጥቶ ይተራመስ የነበረው የከተማው ሕዝብ ተረጋጋ፣ ፀጥም አለ።

ታከለ በአንድ መሳሪያ፣ በአንድ ዘዴ አይወሰንም። የእንግሊዝን ወታደራዊ ክፍል ከዲፕሎማቱ ለማለያየት ጥረት አድርጓል። ወታደራዊው ክፍል ጀግንነቱን ስለሚያውቅለት ይህ ሙከራው በመጠኑ ሳይሳካ አልቀረም፣ ግን እንግሊዝኛ ቋንቋ ባለመቻሉ አጥጋቢ ውጤት እስከ ማግኘት አልደረሰም።

የታከለ ሹመት እንግሊዞችና ኢትዮጵያ ከሚመክሩበት ጉባኤ ወንበር አስገኝቶለታል፤ ማለት ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ስጋቱ አልቀረለትም።

ስለዚህ፣ ምናልባት «እንግሊዝ የኢትዮጵያ ሞግዚት ትሁን፣ ከንጉሱ ጋር ተዋውቀናልና» የሚሉበት ጊዜ ቢመጣ መከራከሪያ ማዘጋጀት አስፈለገ። ታከለ እንደሱው ከሚያስቡና ከሚሰጉ አገር ወዳዶች ጋር ተመካከረና ተስማማ። ያገር ሽማግሌዎች ከየወረዳውና ከየአውራጃው ወደ ዋናው ከተማ እንዲመጡ ተደረገ። ህዝቡ የመረጣቸው ባለመሆናቸው «ፓርላማ» ሊባሉ ባይበቁም፣«ፅንስ ፓርላማ» ልንላቸው እንችላለን። እነሱ ወስነው «ኢትዮጵያ ሞግዚት አትሻም» ካሉ፣ የንጉሡን ውሳኔ ህዝቡ ሽሮታል ብሎ ለመከራከር ይቻላል። (እንግሊዝ በፓርላማ ምን ያህል እንደምታምን አንባቢ ያስታውስ።) ጥር 1934 እንግሊዝ ለኢትዮጵያን የግዛት ነፃነት አውቃለሁ ስትል የመጀመሪያውን ውል ፈረመች።

እንግዲህ ፀጥታውም ተረጋጋ፣ እንግሊዝም መውጣቱ ሆነ። የታከለ ቀዳሚ ዓላማዎች ሁለቱም ከሞላ ጎደል ግባቸውን መቱ ማለት ነው። ምንም እንኳ በነዚህ ጉዳዮች ንጉሡም ቢተባበሩ ከንግዲህ ግን ታከለ ተባባሪ ሊሆናቸው አይችልም፤ ተፃራሪ እንጂ። በዚች ከንቲባ ሆኖ ባገለገለባት አጭር ጊዜ ውስጥ እንኳን ተፃራሪነቱን አሳይቷል። አንደኛ፣ ቤትና ቦታ ቢሰጡት እምቢ አልቀበልም ብሏል። ሁለተኛ፣ የንጉሡ ባለሟሎች እየመጡ ይህ ቤት ወይም ይህ ቦታ ለኔ ይገባኛል ሲሉት «አሀ! ለካ ሞትንላት ተንከራተትንላት የምንለው እቺን ኢትዮጵያን ቀለድ ጥለን ልንከፋፈላት ነውና!» እያለ በዙ ቂም አትርፏል። «እቺ ባቄላ ያደረች እንደሁ አትቆረጠምም» ሳይሉ አልቀሩም አፄ። ምክንያት ፍለጋ ጀመሩ።

ምክንያቱን የአፄ ሰላዮች እፍል ውሀ ሚዳ አገኙላቸው። እዚያ ሜዳ ውስጥ (ያን ጊዜ ጫካ የከለለው ሰዋራ ስፍራ ነው) እንደ ሺ. አምስት መቶ የሚሆኑ የከተማው ባለኔ ጉረምሶች በእንጨት ምስል ጠመንጃ የወታደር ስልት ልምምድ ያደርጋሉ። አሰልጣኙ በቀለ ተክለ ሚካኤል ይባላል። ጉዳዩ ሲመረመር የመለመላቸውም፣ ስንቃቸውን የሚችላቸውም ታከለ ወልደ ሐዋርያት ነው፣

ታከለ የተያዘ ዕለት፣ ተከታዮቹን በመፍራት የእንግሊዝ ታንኮችና ወታደሮች የከተማውን ፀጥታ ለማረጋገጥ ወጡ።

ለህዝቡ የተወራው፣ «ታከለ ወልደ ሐዋርያት የሐንስ ኢያሱን ለማንገስ ሲዶልት ተያዘ» ተብሎ ነበር:: (ሰዩም ሰብሐት ስለ ታከለ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማው ይህን ጊዜ ነበር::) የታከለ ሀሳብ ግን ሌላ ነበር። ሺ. አምስት መቶውን አሰልጥኖ ሲያበቃ አምስት መቶውን ክብር ዘበኛ ውስጥ፣ ሺውን ጦር ሠራዊት ውስጥ እንዲቀጠሩ ያደርጋል:: የራሱን ሰዎች ንጉሡ ሠራዊት ውስጥ አስርጉ ያስገባል ማለት ነው:: ቀጥሎ፣ ሌሎች አስፈላጊ ዝግጅቶች ከተሟሉ በኋላ (በተለይም የእንግሊዝ ጦር ከኢትዮጵያ ምድር ጨርሶ ከወጣ በኋላ) አጼ ኃይለ ሥላሴን አስገድዶ፣ ሥልጣናቸውን የሚወስን ህገ መንግስት እንዲያውጁ ያደርጋል:: ሀሳቡ ይህ ነበር እንጂ ከዙፋናቸው ለማውረድ አላቀደም:: እርግጥ ነው፣ ጣልያን ሲባረር እሳቸው ተመልሰው እንዳይነግሱ ለማድረግ ሞክሮ ነበር:: አሁን ግን ተመልሰዋል፤ ሥልጣን ጨብጠዋል:: ሕዝቡም ለጊዜው በፕሮፓጋንዳና በወረት ተሸንፏል:: ስለዚህ አሁን ተፈሪን መሻር የአገሪቱን ፀጥታ ማደፍረስ ነው:: ፀጥታውን አረጋጋለሁ በሚል ሰበብ መግባቱ አይቀርምና፣ እንግሊዝ እንዲህ ዓይነት ሰበብ አግኝቶ ከገባ ደግሞ ተመልሶ አይወጣም:: ስለዚህ ተፈሪ እዙፋኑ ላይ መቆየት አለበት:: የታከለ እምነት እስከ 1940 ድረስ ይኸው ይሆናል::

ከላይ እንደተጠቀሰው ታከለን አስይዘው የወነጀሉና ክሱን ያነበቡ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሀንስ ነበሩ:: ታከለ እስራት ተፈርዶበት ከዚያ ሲወሰድ፣ «ወልደ ጊዮርጊስ» አላቸው «እኔ ታከለ ነገ እወጣለሁ:: አንተ ግን የወደቅክ እለት የት ትገባለህ?» ራስ ካሳ ንጉሡን እንዲህ አሉዋቸው ይባላል «በሽሽታችን ጊዜ ቦርሳ ተሸካሚያችን ለነበረ ለወልደ ጊዮርጊስ ብለህ ታከለን ያህል ሰው ታስራለህ?»

«ተንኮሉን ክፋቱን እኛ ነን የምናውቀው!» አሉ ንጉሡ «ከራስ በላይ ንፋስ»:: ታከለ በንጉሡ ግቢ ጨለማ ቤት ውስጥ ታሠረ፣ ንጉሡ የታከለን ቤት ለደጃዝማች መስፍን ስለሺ ሰጡዋቸው:: ደጃች መስፍን ቤቱን ለመረከብ ድሄዱሉ ታዲያ፣ በአራቱም ማዕዘን መትረየስ ተጠምዷል:: ወይዘሮ ፋናዬ የታከለ ባለቤት አርበኛ ሳሉ ጥልያንና ባንዳ የፈጁበት መትረየስ መሆኑን ደጃች መስፍን ያውቃሉ::

አበ ኃይለ ማርያም አቸምየለህ (የአባ ሀና ረዳት) ንጉሡን «ግርማዊ

«ሴትየዋ (ወይዘሮ ፋናዬ) እልኸኛ ናቸው፤ አውቃቸዋለሁ። ተኩስ ከፍተው የከተማውን ፀጥታ ሊያደፈርሱት ይችላሉ። ገና በደምብ ሳይረጋጋ። ምናለ ቤቱ በእጃቸው ቢቆይ? እባክዎን?» እንዲህ በመለመንና በማባበል እሺ አሰኙዋቸው፣ ንጉሡ ትእዛዙን አነሱ።

እንግዲህ አባ ኃይለማርያም ከታከለ ጋር ዘምተዋል። ታዲያ አንዳንድ ቀን ንጉሡ ይጠሩዋቸውና «በንዲህ ያለ ቦታ ውጊያ ላይ እንዴት አደረገ?» ይሉዋቸዋል። ሲነግሩዋቸው በተመስጦ ያዳምጡና፣ ታሪኩ ሲያልቅ ራሳቸውን እየነቀነቁ፣ «አይ ወንድ! አይ ጀግና! ምነው ምንቸገረው እኔና እሱ ብንስማማ!?» ይላሉ ንጉሡ።

በጨለማ ቤት መታሰሩ የታከለን ዓይን እንደጐዳው ሲያውቁ ጊዜ ወደታች ግቢ ተዛውሮ ከበላይ ዘለቀና ከማሞ ወልደ ሚካኤል ጋር ታሠረ።

ይህ ማሞ ወልደ ሚካኤል የራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት የልጅ ልጅ ነው። የታወቀ ባንዳ ነው። ታከለንም በላይ ዘለቀንም ወግቷቸዋል። ግን በባንዳነቱ አያፍርም።

አርበኞችና ባንዳው አብረው ታሥረው ሳሉ አንድ ቀን ማሞ ወልደ ማካኤል እንዲህ አለ ይባላል። «መቸም ተፈሪ ለገንዘብ ስግብግብ ነው። ጣሊያን የደበቀው ገንዘብ አለ፣ ቦታውን አውቀዋለሁ ብዬ ልኬበታለሁ። በሱሪዬ እጥፋት ባሊላ ቦምብ ይዤ እገናኘውና እዚያው እሰናብተዋለሁ! ከዚያ ብሞትም አይቆጨኝ።»

ታከለ ተሸበረ። በሀሳቡ ታየው - ተፈሪ በባሊላ ቦምብ ብትንትኑ ሲወጣ ... እኔ እነግሥ እኔ እነግሥ ሽኩቻ ሲመጣ... እርስ በርስ ጦርነት ሲለኰስ ... በኦጋዴን ያለው የእንግሊዝ ጦር ቀድሞ ሲደርስ.. ሌላ የእንግሊዝ ጦር ሲደርስ... ይህ ሁሉ እየታየው እያስጨነቀው እንቅልፍ ሽልብ እንኳ ሳያደርገው ነጋ።

ጧት፣ እሥረኞቹ ወደ ሽንት ቤት ለመሄድ ወረፋ ሲጠብቁ፣ ታከለ በድንገተኛ ሆድ ቁርጠት ይጨነቅ፣ ይታጠፍ፣ ይወራጭ ጀመር። ለሽንት ቤት ቅድሚያ ሰጡት። ሲወጣ የዘብ ኃላፊውን ጠቀሰው። የዘብ ኃላፊው እየደገፈ ወደ ሽንት ቤት ሲወስደው ታከለ በሹክሹክታ «ጃንሆይን ስትላቸው፣ ከማሞ ጋር እንዳይገናኙ - ብሏል ታከለ በላቸው። ባስቸኳይ!» አለው።

ንጉሡ ከማሞ ጋር ሳይገናኙ ቀሩ። ምናልባት ታከለ ባይልክባቸው ኖሮ ይገናኙት ይሆናል። ይኸ ግን ለታሪካችን ልዩነት አያመጣም። ታከለ ኢትዮጵያ እንዳትቆስልበት ወይ ነፃነቷን እንዳታጣበት ሲል፣ የአሳሪውን ንጉሥ ህይወት ይጠብቃል። ያውም የዓይኑን ብርሃን ያደበዘዘበትን ንጉሥ!

ሎርድ ደላዋር በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል ሊደረግ ለታሰበው ሁለተኛ ውል ድርድር በመጣ ጊዜ ታከለ ከእስራት ወጥቶ ደጃች ሀብተ ሥላሴ ቤት በቁም እሥር እንዲቀመጥ ተደረገ። ዓይነተኛውን አርበኛ እሥሮ ላገሪቱ ነፃነት መደራደር ከትዝብት ይጥላል ብለው ሳያስቡ አልቀሩም ንጉሡ።

በ1937 መጀመሪያ ላይ ሁለተኛው ውል ተፈረመ። እንግሊዝ የኢትዮጵያን

ሙሉ ነፃነትዋን አወቀችላት፤ ታከለም ከሦስት ዓመት እስራት በኋላ ነፃነቱን አገኘ:: እረ! ምክትል አፈንጉሥ ሆነ!

በአፈ ንጉሥነቱ ብዙም አልቆየ:: አሁንም ሳይዶልት አይቀርም ተብሎ ተጠረጠረ:: ከከተማው ለማራቅና ከተከታዮቹና ከአበሮቹ ለመለየት ሲባል «ደጃዝማች» ተብሎ የቦረና ነጌሌ አውራጃ ገዥ ሆነ::

ለአውራጃ ገዢው ታከለ «ራስ አደፍርሰው ባንተ አውራጃ ጉዳይ አይገባብህም» ተብሎ ተነግሮታል:: ጠቅላይ ገዢው ራስ አደፍርሰው ደግሞ «ታከለን በጥንቃቄ እየተከታተልክ!» ተብለዋል:: ስለዚህ በሁለቱ መሀል ንትርክ ሆነ::

ታከለ ጉሳ ለጉሳ ሊያዋጋ ነው ተብሎ ተከሰሰ:: ታከለን ለሚያውቁት ሰዎች ይኸ ክስ «አያጅቦ፣ ሳታመኻኝ ብላኝ» የሚለውን ምሳሌ ሳያስታውሳቸው አልቀረም:: ግን መቸስ ታከለ ታከለ ነውና፣ ለንጉሡ አስጊ የሆነ ዝግጅት ቢያደርግ አይገርምም... እንዲያውም ባያደርግ ይገርማል እንጂ! ንጉሡ ሰውየውን ያውቁታልና (እሱ ከሚያውቃቸው እኩል ያውቁታልና) ምናልባት ሊሸፍት ይሆን እንዴ? ብለው በመፍራት ጦር አዘዙበት:: የጦር አዛዥ ሻለቃ ፅጌ ዲቡ (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል) ለታከለ ገብተዋል ተብለው ስለተጠረጠሩ፣ በኰሎኔል ተስፋ ደስታ አዝማችነት ሌላ ጦር ተላከ፡

በመካከሉ ግን የሽምግልና ጉባኤ ተላከበት:: «ፍርድ ከተሰጠኝ አዲስ አበባ እመጣለሁ» አለ:: አውሮፕላን ተላከለት:: መጣ:: ታሠረ:: ለፍርድ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲቀርብ፣ ፕሬዚዳንት የነበረው እንግሊዛዊ ዳኛ አቦት፣ «ወንጀሉ ሳይረጋገጥ መታሰር ከህግ ውጭ ነው:: ሰውዬው ከቀረበበት ክስ ነፃ ነው» ሲል ፈረደለት::

ታከለ ነፃነቱን ተጐናፅፎ ወደ ቤቱ ሲሄድ ተያዘ:: አፍንጮ በር አጠገብ ወደ ነበረው ወህኒ ቤት ተወሰደ፣ ራሱን ተላጨ:: ታሠረ:: ሌሊት በወህኒ ቤቱ ሁከት ተነሳ፣ ታከለ ወደ ንጉሡ ግቢ ተወስዶ ታሠረ::

ጥቂት ሰንብቶ ታከለ ወደ ተጉለት ተወስዶ ቆላ ውስጥ ታሰረ:: ለአምስት ዓመት ያህል ከተፈሪ ጋር የሚደረገው ፍልሚያ ጋብ አለ::

ቢትወደድ ነጋሽ የኍሐንስ ረምሀ፣ ፊታውራሪ ተወልደ ብርሃን አካሉ፣ ሙቶ አለቃ በቀለ አናሲሞስ፣ አለቃ ፈጠነ፣ ቀኛዝማች ከበደ ይመር እና ሌሎች ሆነው ዙፋን ሊገለብጡ ሲያሴሩ መሀላቸው ከነበሩት ጥቂቶች ከድተው ምስጢሩን ሸጠውባቸው ተያዙ:: ሴረኞቹ ታከለን ከታሠረበት አውጥተው በአመራር ስራው እንዲሳተፍ ሊያደርጉት አስበው ነበረ ተብሎ ለንጉሡ ተነገራቸው:: በጊዜው ባለስልጣን የነበረ አንድ የታከለ ዘመድ ጉዳዩን እንዲያጣራ ወደ ተጉለት ቆላ ተላከ:: (ግን አንድ የታከለ ወዳጅ የሆነ ከፍተኛ ባለስልጣን ይህን ስላወቀ አስቀድሞ ልኮበት አስጠንቀቀው ታከለን::)

የተላከው ዘመዱ ሲመጣ ታከለ «የተላከበትን ላቅልልልህ። ማስታወሻህን አውጣና ፃፍ» አለው። (አንባቢ ነገሩ እንደገባው «ቢትወደድ» የሚለው ሹመት ለንጉሥ ታማኝ ወታደር ባለሙዋል እንጂ ለፀሐፊና ለደብተራ ወይም ለቤተ ክህነት ሰው የማይሰጥ መሆኑን ያስታውሱ።)

ፀሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን ሕዝቡ «ቢትወደድ» ይላቸው ጀመር። እቴጌ ጣይቱም በዚህ ተናደው ገብረ ሥላሴ ራሱን ቢትወደድ በማሰኘት ትልቁን ሹመታችንን አርክሶታል ሲሉ ከአፄ ምኒሊክ ፊት ከሰሱዋቸው። አፄ ምኒሊክም አስጠርተው «እንዴት አንተ? ያልሰጠንህን ሹመት ቢትወደድ እየተባልክ ትጠራበታለህ?» ቢሉዋቸው «ጃንሆይ! እነሱ ቢጠሩኝ እኔ መቸ ወይ አልኩ?» ብለው መለሱላቸው። ዘመድየው ይህን ፅፎ ሲጨርስ፣ ታከለ «ይህን ስጣቸው ለጌታህ» አለው።

ንጉሡ መልእክቱን አነበቡ። ራስ አበበ በኋላ ለታከለ ሲነግሩት «በሕይወቴ ሙሉ ጃንሆይ ይህን ያህል ሲስቁ አይቼ አላውቅም «አየህ ነገረን ከ! እያሉ ሳቁ።»

ወድያውኑ ታከለ እሥራቱ ተሻሻለለት። ደጋ ወደ ሆነውና መጠነኛ የህክምና ርዳታም ሊያገኝ ወደሚችልበት ወደ ደብረ ብርሀን ተዛወረ። ጥቂት ቆይቶ ወደ ሆለታ ተዛወረና በከተማው መዛወርም ስለተፈቀደለት በጎች ያረባ ጀመር። (በነገራችን ላይ፣ «ሆለታ» ማለት በኦሮምኛ «በጎች» ማለት ነው።)

ይሽ ሁሉ ሲሆን ታከለ አዲስ አበባ ካሉት ተከታዮቹና አበሮቹ ጋር መላላኩ ስላላቋረጠ ከሩቅም ቢሆን የፖለቲካውን ሁኔታ ይከታተል ነበር።

በ1946 ንጉሡ ለመጀመሪያ ጊዜ አሜሪካ ሲሄዱ ሆነ። ታከለ ተፈታና ባገር ግዛት ሚኒስቴር አማካሪ ሆነ፣ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ውድቀት መድረሱን ገመተ። በ1947 ንጉሡ አውሮፓን ሲጎበኙ አሁንም ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ አብረዋቸው ሄዱ። ሲመለሱ ከፀሐፊ ትዕዛዝነት ተሽረው የአሩሲ ጠቅላይ ግዛ ተብለው «ተሾሙ»። ታከለ ያገር ግዛት የአስተደዳር ምክትል ሚኒስትር ሆነ።

ይህ ምን ማለት ነው? ባንድ በኩል ንጉሡ ወልደ ጊዮርጊስን ሲቀጡዋቸው ለጠላታቸው ለታከለ አሳልፈው ሰጡዋቸው። አሁን አለቃቸው ስለሆነ እንደልቡ «ሊከረክማቸው» ይችላል። ዋናው ቁም ነገር ግን እነሆ ወልደ ጊዮርጊስ አሥራ አራት ዓመት ሙሉ ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ የራሳቸውን ሰዎች የት የት እንደተከሉ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ምናልባት ሁከት ቢያስነሱስ? ስለዚህ የሁኖታውን ኃላፊነት የሚረከበው ሰው ችሎታም እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ ከወልደ ጊዮርጊስ ጋራም ምንም ቢሆን የማይተባበር ሰው መሆን ይኖርበታል።

ታከለ ሁኖታውን በማገባ ጠበቀላቸው፣ በ1948 የኢዮቤልዩ በአላቸውን

ሲያከብሩም የፀጥታ ችግር አልገጠማቸውም። ቀደም ሲል በሐሳ ትዕዛዝ ታከለን እንዲታረቅ ብለውት ነበር። ከአማላጆቹ አንዱ ጓደኛው ብላታ ኪዳነ ማርያም አበራ «ሰውዬውስ ከልቡ ነው። ለምን አማትታረቀው?» አሉት።

«እንኳን አሁን ጥለኛዬ ሆኖ ሊታረቀው፣ ወዳጅ ቢሆንም አጠላው ነበር። የንጉሥ ባለሙዋልን ወዳጅህ ካደረግከው፣ የጨነቀው እለት ይሰዋሀል!» አለ ታከለ።

ሆኖም ታከለ «የወደቁ» ጠላቱን ለማስቃየት ይህን ያህል ፍላጎትም አልነበረው፤ ጊዜም አልነበረው። የቆመ ጠላት እያለ... አሁን እንግዲህ የዓለም ሁኔታ ተለውጧል፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቂት ብጥብጥ ቢነሳ እንግሊዝ ከጉዳይ አትጥፈውም። ስለዚህ ታከለ ተፈሪን «ሊመክረው» ይችላል።

የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ እንዲቋቋም ከጣሩት መካከል አንዱ ታከለ ነው። መፈንቅለ መንግስት ሲደረግ ከተማውን መቆጣጠሪያ እንዲሆነው። በሌላ በኩል ደግሞ ብሔራዊ ጦር እንዲቋቋም ጥረት ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ አዛዦቹንም ለመውሰድ ሞከረ። ያገር ቤቱን ፀጥታ ለማስከበር እንዲያስችለው። የሁለቱም የጦር ኃይሎች አዛዥ መኮንኖች አብዛኛዎቹ የሱ ሰዎች እንዲሆኑ አደረገ። ከዚህም ጋር የፖሊስ አዛዥ ጀኔራል ፅጌ ዲቡ የታከለ ታማኝ ተከታይ ነበሩ።

ግን አሁንም ተፈሪ ለትንሽ ቀደመው። «አፈ ንጉሥ ታከለ» አለና ነገር ማዛትና ጦር ከማቋቋም አውጥቶ፣ ይግባኝ ማዳመጥና የነገር ፋይል ማገላበጥን አሸከመው። ታከለ በአንድ እጁ ሲሰራው የነበረውን ንጉሡ አፈረሱበት። በሌላ እጁ ሲሰራው የነበረውን ግን እንኳን ሊያፈርስበት ገና አልነቃበትም።

ከ1948 አንስቶ ታከለ ወደ ወጣቱ ትውልድ ማትኮር ጀምሯል። የፖለቲካ ስሜት ካላቸው ወጣቶች ምሁራንና በወታደሩ ዘንድ ተወዳጅ ከሆኑ ወጣት መኮንኖች ጋር መገናኘት ጀመረ።

ታከለ ከወጣቶቹ ምን ተማረ? ትንተናን። ህዝቡ ለዘለቄታ እንዲጠቀም ከተፈለገ ተፈሪን ማግለል ወይም ስልጣኑን መገደብ አይበቃም፣ የግፍ አገዛዝን የማያከሂድ ሥርአትን መዘርጋት ያስፈልጋል። አዲሱ ሥርአት ኃይሉንና ሥልጣኑን ከጥቂቶች እጅ መንጭቶ በብዙኃኑ እጅ የሚያገባ መሆን ይኖርበታል። ስለዚህ የመጀመሪያ ተግባሩ መሬቱን ለሕዝቡ መልሶ ማስረከብ ይሆናል፣ ወዘተ..

ወጣቶቹስ ከታከለ ምን ተማሩ? እንደ አስተዋይነታቸው ይለያያል። ስዩም ስብሐት የተማረውን አንዳንዱን ለመጠቀም ያህል...

ወጣቶቹ ተሰብስበው ሲወያዩ ወይም ሲከራከሩ ታከለ ዝም ብሎ ማዳመጥ ነው። ሲነታረኩም ሲጨቃጨቁም ዝም። ስለ አንድ መሰረታዊ ነጥብ ለወራት ሲከራከሩ ይችላሉ። ዝም ብሎ ማዳመጥ። ለምን? ጠባያቸውንና የአስተሳሰብ ስልታቸውን፣ ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን ለመገመት ነው።

በ1952 መጨረሻ ግድም፣ አንድ የጊዜውን ሁኔታ የሚያውቁ ሰውዬ ሥዩም ስብሐትን፣ «ጃንሆይ መስኮብ ሊሄዱ ነው፤ ግን አንድ የርስዎ ዘመድ አለ፣ ትተውት እንዳይሄዱ ፈሩ» አሉት (ሥዩም በሀሳቡ ታከለ ደጋግሞ የተናገረውን ሰማ፣ «ፈረንጅ አገር ብሄድ... አብዳለሁ ኢትዮጵያ ያልደረሰችበትን ሳይ!»)

«ንጉሥ የሚያስፈራ ዘመድ ካለኝማ ይንገሩኝ ልኩራበት» አላቸው ሥዩም ያላወቀ ለማስመሰል:: «አወቅ እስቲ» አሉት:: ጥቂት ስሞች ጠራላቸው:: «ደጃዝማች ታከለ» አሉት::

«የ መሀይም!?» አለ ሥዩም:: ድምፁ ውስጥ በነገሩ መገረሙና ለታከለ ያለው ንቀት ይሰማል:: አፊቱም ላይ ይታያል:: ሰውዬው እየተቆጡ፣

«ታከለ ነው መሀይም? ሊቁን መሀይም አሉት?» አሉ::

ሥዩም እየተፀፀተ፣ «አይ እንደሱ ማለቴ አይደለም ኧረ!» አላቸው:: ቀጠል አድርጎም «ከድፍረት አይቁጠሩብኝና፣ እኚህ ጃንሆይ ምነው ምነው መካሪ አጡ? እስቲ ታከለ ለራሱ አምስት ዓመት ተዋግቶ፣ ብዙ ዓመት አገልግሎ፣ አስራ ሁለት ዓመት ታስሮ ተንከራቷል:: ደክሞታል:: ኑሮ ሰልችቶታል:: የቀረችው እድሜ ትንሽ ናት፣ እሷን በሰላም ሊያሳልፉት ይፈልጋል:: እንዲያው ከመሬት ተነስተው ባይነካኩት ምናለበት? ሰውዬው ከሞት ጋር ተቆራኝቶ ተፋጦ የኖረ ሰው ነው:: ሞት አይፈራም:: እንዲህ ሲነካኩት አንድ ቀን ብድግ ብሎ ስተት ብሎ ጉብቶ በደረታቸው ቢቆጥርባቸውስ? ድፍረቱን፣ ተኳሽነቱን፣ ሞት ያለ መፍራቱን ታውቃላችሁ:: ይተውት ብላችሁ ብትመክሯቸው ምነው?»

በሦስተኛው ቀን ታከለ ሥዩምን በስልክ ይጠራዋል:: ቤቱ ሲሄድ፣ ታከለ የቀልድ ለጥ ብሎ እጅ እየነሳ፣ «እግዜር ይስጥልኝ ከመስኮብ ስላስቀሩኝ» ይለዋል:: ቀና ብሎ እየሳቀ «ስድቡም ደርሶኛል» አለ ራሱን እየነቀነቀ፣ የገዛ ደቀ መዝሙሩን የማድነቅም የመውደድም ስሜት በተቀላቀለበት ድምፅና ፈገግታ::

በ1953 ንጉሡ ብራዚል ሆነው በአዲስ አበባ መፈንቅለ መንግሥት መሞከሩን ሰሙ:: ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከመወሰን በፊት አንድ ጥያቄ ጠየቁ፣ «ታከለ አለበት ወይ?» የለበትም ሲሉዋቸው «እንግዲያስ እንመለስ» አሉ:: ተመለሱ::

እነ ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ እንደተሸነፉ፣ ታከለና አንድ አምስት የሚሆኑ እሱ የሚተማመንባቸው ሰዎች ሁናቴውን ገመገሙ::

አንድ ቀን በጊዜው በጣም ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ሰው ወደ አፈንጉስ ታከለ መሥሪያ ቤት ሔዶ አስጠራቸው (ይህን ካየሌ ዓመታት በኋላ ፀሐፊ ትዕዛዝ ራሳቸው ናቸው ለሥዩም ስብሐት የነገሩት) ሊጠራው የመጣውን ሰውዬ ታከለ «ጥራው?!» ብሎ በዓይኑ ገረፍ አደረገው::

ባለሥልጣኑም ከመኪናቸው ወርደው ወደ ታከለ ቢሮ ገቡ:: ሊመክሩት መምጣታቸው ነው:: በዚህ በታህሳስ ግርግር የተነሳ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፣ ነገሩ በጣም ተባብሷል፣ አይበጥብጡ፣ ሊሉት ይሞክራሉ እሳቸው:: እሱ ግን በመስኮቱ ብቅ ያለች አንዲት ወፍ ያጫውታል፣ ጫጩት እንደሚጠራ ሰው

ይጠራታል፡፡

«ምነው ቢሰሙኝ?!» አለ ሰውዬው፡፡

«ስማህ» አለ ታከለ «እመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ ነን፡፡ ሰው ወደ ፀሐይ መውጫ ይነሳል እንጂ ወደ መጥለቂያዋ አይነሳም፡፡ አሁን ሥራ አለብኝ፡፡ በል ደህና ዋል፡፡»

ጄኔራል መንግስቱ ንዋይን የአስተዳደር አቤቱታ ሲያቀርብ (የፍርድ ሳይሆን የአስተዳደር) አፈ ንጉሥ ታከለ ፊት አመጡት፡፡ በሰንሰለት ታስሯል፡፡ ታከለ፣ «ሕግ ሳይፈርድበት በሰንሰለት አይታሰርም፡፡ ፍቱት!» ብሎ አስፈታው፡፡

የጄኔራል መንግስቱ አቤቱታ፣ ሲፈርዱ ከተመረጡት ዳኞች ከአንደኛው ጋር የግል ግጭት ሳይኖረን አልቀረምና ይለወጥልኝ የሚል ነበር፡፡ አፈንጉሥ ታከለ ምክንያትህ የህጉን አንቀፅ የሚያጠግብ አይደለም... ብሎ ወሰነ፡፡ (እንደ አጋጣሚ ሆኖ፣ ሁለቱ ዳኞች ሞት ሲፈርዱበት፣ አይነተኛ ምስክር በቂ እንዳልሆነ ተችቶ «እሥራት እንጂ ሞት አይገባውም» ብሎ ለጄነራል መንግስቱ የፈረደለት ይኸው «ይለወጥልኝ» ብሎ የአስተዳደር አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ ነው፡፡)

ሁለተኛው የጄኔራል መንግስቱ አቤቱታ፣ «የውጭ አገር ጠበቃ ላስመጣ ይፈቀድልኝ» የሚል ነበር፡፡ አፈ ንጉሥ ታከለ፣ «በንዲህ አይነት ከባድ የወንጀል ክስ የውጭ አገር ጠበቃ ለማስመጣት ሕጉ አይፈቅድልህም....» ሲል ወሰነ፡፡

ታከለ ወልደ ሐዋርያት ጄኔራል መንግስቱን ለብቻው አቢሮው ዘግቶ ከግማሽ ሰዓት በላይ አነጋግሮታል፡፡ ምን ተባባሉ ይሆን? የሚያውቅ የለም፡፡ ሆኖም፣ ይህን የመሰለ ውሳኔ ያስተዳደርና የስነ ስርዓት ስለሆነ በዶሴ ተውጦ መቅረት ሲኖርበት፣ ሆን ተብሎ የታከለን ስም በማስመሰል ለማጉደፍ እንዲስፋፋ ተደረገ፡፡

ጄኔራል መንግስቱ ፍርዱን ተቀበለ፡፡ ወደ ጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ይግባኝ አልልም አለ፡፡ እፄ ኃይለ ሥላሴ መኳንንትና ሚኒስትሮች ባሉበት ታከለን አስጠርተው ይግባኙን ተመልከት አሉት፡፡

«መመልከት አለብህ» ብለው ድርቅ አሉ ንጉሡ፡፡

«እንግድያውስ ፍርዱን ልንገርዎ» አለ ታከለ፣ «አይነተኛ ምስክር የተባለው በዳኛ ተተችቶበታል፣ የምጨምርበት የለም፣ የሚያጠግብ ምስክር አይደለም፡፡ ተከሳሹ በጦር መሳሪያ መንግሥት ለመገልበጥ መነሳቱን አምኗል፡፡» እዚህ ላይ የወንጀለኛ መቅጫ አንቀፅ ይጠቅስና «ቅጣቱ ከሀያ ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት እስከ ሞት ሊሆን ይችላል፡፡ እንደቀረበው ምስክር ፍርዱን መደልደልና ማሻሻል የዳኛ ፋንታ ስለሆነ፣ እኔ የምፈርደው ሃያ ዓመት ፅኑ እሥራት ብቻ ነው፡፡»

«ገባን፡፡ እኛም የፈለግነው ይህን ለማወቅ ነው!» አሉ ንጉሡ፡፡

እሳቸውስ የፈለጉት ባንድ በኩል ከመንግስቱ ነዋይ ደም ንፁህ ነኝ፣ ሁለተኛ፣ ፍርድ ቤት ሞት ፈረደበት ለማለት ነበር፣ አልሆነላቸውም፡፡ የሞት

ፍርዱን ራሳቸው ማስደቅ ግድ ሆነባቸው። ሴላ የፈለጉት ታከለ በመንግስቱ ነዋይ ላይ እንዲፈርድና፣ ስለ ፈረደ ህዝቡ እንዲንቀው ነበር። ......

ሰኔ 1953 ዓ.ም. አንድ ቀን ሥዩም በመኪና ታከለን ቢሸኙቱ ይወስደዋል። ንጉሡ ጠርተውታል። ታከለ ለሶስት ሩብ ጉዳይ የገባ በሰባት ሰዓት ወጣ። ይህን ሁሉ ሰዓት ታከለና ተፈሪ በቆይታ ነበሩ። የመጨረሻው ቆይታቸው ነበር። ሥዩም ሲያየው ታከለ እንደ ማዘንም እንደ መበሳጨትም እንደ መሸበርም ያለ ይመስላል። ከዚህ ቀደም እንዲህ ሆኖ አይቶ አያውቅም።

ይህ ከሆነ በኋላ አንድ ቀን ታከለ ሥዩም ስብሐትን ወደ ሰበታ ወሰደው። አንድ እርሻ መሀል ቆመው መነጋገር ጀመሩ።

«የኔ መታሰር የተረጋገጠ ነው» አለ ታከለ «ወጣቱን የሚወክልላቸውና የሚያጠግባቸው ያስፈልጋል። አንተን መርጫለሁ። ሌሎቹ አብዛኞዎቹ እንኳን እኛን፣ የሌለበትንም ያስይዛሉ። ባንተ ብቻ ነው እርግጠኛ ልሆን የምችለው።»

ስዩም ደነገጠ። ግን ፅዋው የሱ መሆኑ ገባው።

ታከለ፣ «ይህን ሲጠይቁህ ምን ትመልሳለህ? እንዲህ ሲሉህስ?» እያለ ለምርመራው አዘጋጀው።

ነሐሴ 1953። አንድ ቀን ሥዩም ኃይለኛ እንፍሉዌንዛ ይዞት ተኝቶ ሳለ ታከለ ከቢሮው ደወለለት። «ተጠራሁ። በርታ። አይዞህ ልጄ። ሥጋት አይግባህ። መጨረሻችን እንዳይመስልህ። በል ደህና ሁን» አለው።

ሩብ ሰዓት ሳያልፍ መጥተው ሥዩምን ወሰዱት።

ታከለ በቀጥታ በኤሮፕላን ወደ ጐሬ ተወስዶ ታሠረ። ሥዩም ስብሐት 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ከባድ ወንጀል ምርመራ ተወሰደ። ምርመራ ላይ እንዳለ በጣም ታመመ። ሀኪም የአንጀት ቁስል እንዳለበት መሰከረ። ሀምሳ ቀን ሆስፒታል ተኛ። ወደ ምርመራው ተመለሰ። ምርመራው ሳያልቅ ወደ ጂማ ተጋዘ። ከዚያ ወደ ሚዛን ተፈረ። ሦስት ወር ቆይቶ፣ ህመሙ ሲጠናበት ጊዜ ወደ ጂማ ተላከ።

ታከለ ጐሬ እንደተጋዘ ኩላሊቱን ታመመ። ወደ ጂማ አመጡት ለህክምና። እንዳይገናኙ ብለው ስዩምን ወደ አዲስ አበባ። ከዚያ ወደ አሰላ አሩሲ (አርሲ)። ገዢው ዳንኤል አበበ አማላጅ ሆነውና አሰላ አንድ ዓመት ከስምንት ወር ከተጋዘ በኋላ፣ በጠቅላላው ከሶስት ዓመት እሥራትና ግዞት በኋላ «ምህረት» ተደረገለት።

ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ታከለ በየጊዜው ያለማቋረጥ የኪስ ገንዘብ ይልክለታል። ሥዩም «ምህረት» ይደረግለት እንጂ «ጥጋቡ ገና ስላልበረደለት» ሥራ ተከለከለ። እንደምንም ተፍጨርጭሮ እስኪቋቋም ድረስ ታከለ ገንዘብ መላኩን አላቋረጠም። አንድ ቀን የስዩም ሠራተኛ ልብሶቹን በሙሉ ስርቆበት ጠፋ። ልብሶቹ በተሰረቁ በአምስተኛው ቀን ግሩም የሆነ ሱፍ ጨርቅ (ሶስት ሜትር ከሩብ) ደረሰው። ከመቶ ሀምሳ ብር ጋር ስማበፊያ። ሱፉ ታከለ የሚለብሰው አይነት ነው፤

መንግሥት ቤት ገብቶ ጥቁር ሱፍ ሙሉ ልብስ በሙስቴዮ ይዞ መጥቶ አለየኝ።
«እስካሁን አለ ይኸው ልሁ» አለኝ።

በ1955 ታከለ ጅማ እያለ ልጁ አስገዶች በጠና ስለታመመች ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተፈቀደለት። አረፈች። ቀበረ። ከዚያ ወደ ሰበታ ሄደ፤ በቁም እስር። ሥዩም በድብቅ እየሄደ ይገናኙ ጀመር። ጫካ ስለሆነ ምቹ ነው። ተቋርጦ የነበረውን ጥረታቸውን ቀጠሉ።

ጣልያን የተባረረበትን ሃያ አምስተኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ፣ ታከለ ከአራት ዓመት ከዘጠኝ ወር እስራት በኋላ ተፈታ። በድምሩ አሥራ ሰባት ዓመት በእሥራት አሳልፏል ማለት ነው።

የታከለ ሰዎች በየጠቅላይ ግዛቱና በየወረዳው እየሄዱ ሁኔታውን እያጠኑ እየተመለሱ በነገሩት መሠረት፤ ሁኔታው የትጥቅ ትግል እንደሚጠይቅ ተገነዘበ። ከሌሎች ጋር ግምባር መፍጠር አስፈለገ። ታከለ አዲስ አበባ እንዲቆይ፤ ሥዩም ከሌሎች የኃይለ ስላሴ ተቃዋሚዎች ጋር ለመነጋገርና ግምባር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ለማጥናት እንዲዘዋወር ተወሰነ። ሥዩም ታከለን ተሰናብቶ ሄደ። ከሰባት ዓመታት በላይ እስኪያልፍ ድረስ አልተመለሰም። ታከለንም በህይወት አላገኘውም።

ግምባር የመፍጠሩ ሙከራ አልተሳካም። ታከለም አረጀ። ተስፋ እየቆረጠ የሄደ ይመስላል፤ ምክንያቱም መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር መመካከር ጀመረ። ምስጢሩ ወጣ። በንጉሡ ላይ አደጋ ሊያስጥል ነው ተባለ።

ሰኞ ህዳር 7 ቀን 1961 ወደ ስምንት ሰዓት ላይ ሊይዙት መጡ። እጄን አልሰጥም አለ። ተኩስ ተከፈተ። ጥይት አለቀበት፤ ራሱን ገደለ። ሰበታ አቦ፣ አባቱና እናቱ ከተቀበሩበት ተቀበረ።

«ጀኔራል ገድሏል እያስመሰከረ።
ጣልያንንም ገድሏል እያስመሰከረ።
እንበሳው ታከለ ራሱን ሲገድል ማነው የነበረ?»
ብሎ አንጐራጉሮ አንዱ

«ጃንሆይ የልጅ ኢያሱና የደጃዝማች ታከለ ስም ሲነሳ ፀጉራቸው ይቆማል» ይላሉ የሚያውቁ ሰዎች። ከነዚህ አዋቂዎች ውስጥ አንዱ ለሥዩም ስብሐት ሲያጫውቱት እንዲህ ብለውታል፤ «ደጃዝማች ታከለ ቢሞቱ፣ ጃንሆይ እርማቸውን ለማውጣት ወደ መቃብራቸው ቀርበው አፈር አይበትኑም።»

«ምነው?»

«አይ! ታከለ እድል የገጠመው እንደሆነ ድንገት እንዳይነሳ ብሎ ነው ይገባል ብለው ይፈራሉ!»

ጥር 1973

# 2

# ቴዎድሮስ



በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ስለቤተ መንግስትና ስለቤተመቅደስ በአያሌው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ አፈታሪክ በአመዛኙ ለትክክለኛነቱና እርግጠኛነቱ የሌሎችን የታሪክ ዘርፎች ማረጋገጫና ማዳበሪያ የሚጠይቅ ነው:: ይሁንና አንድ አፈታሪክ በዘመኑ የነበረውን ማኅበራዊ አስተሳሰብና ግንኙነት የሚፈነጥቅ በመሆኑ በአንድ ጐኑ በመዘክርነቱ በሌላው ገፅ ደግሞ ለበለጠ ምርምርና ጥናት መነሻነቱ የሚጠቅም ስለሚሆን በአፈታሪክ የምንረከበውን ሁሉ እንደታሪክ መዘክርነት ይበልጥ በሚያገለግለን መንገድ ለመጠቀም ጊዜና ቦታን እንዲሁም የታሪክ አጋጣሚን መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል::

የዳግማዊ ቴዎድሮስ ታሪክ አስደናቂና ማራኪ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል:: ለልቦለድ ደራሲያን፣ ለቴአትር ደራሲያንና ለገጣምያን ፃፉኝ ግሩኝ የሚል በመሆኑ ለኪነት ሰዎች የፈጠራ ሐሳብ ምንጭ ሆኖአቸው ቆይቷል::

እዚህ ውስጥ የምታነቡትን አብዛኛውን የነገሩኝ ብላታ ዱሬሳ አመንቴና አቶ ስዩም ስብሐት ናቸው:: ብላታ ዱሬሳ «የአፄ ቴዎድሮስ ጋሻ ጃግሬ የነበሩ ሽማግሌ ሰው ናቸው ያጫወቱኝ» ብለው ነበር የነገሩኝ (መሬት ይቅለላቸውና)::

ትክክለኛውና ሙሉው የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ በሊቃውንት ተመርምሮ፣ ተዘጥሮ፣ ተፅፎ እስኪቀርብላችሁ ድረስ ይህ አፋዊ ታሪክ ለቅምሻ ያህል

ይኸውላችሁ፡፡

## ጊዜው - ዘመነ መሳፍንት

ከስሑል ሚካኤል በኋላ የጎንደር ነገሥት ደከሙ፡፡ በየክፍለ ሀገሩ የነበሩት መሣፍንት በየፊናቸው አፈነገጡ፡፡ ግብር አልከፍል አሉ፡፡ አፄ ተክለ ጊዮርጊስም («ተፍፃሜተ መንግሥት») ቢቸግራቸው ከርብ (ወንዝ) በላይ ያለውን በጌምድርን እንደ ሌላው አገር ሁሉ ግብር ክፈል አሉት፡፡ (ከዚያ በፊት፣ ማለት ከአስራ ስምንተኛው ምዕት መጀመሪያ በፊት - ከርብ በላይ ያለው በጌምድር ግብር ከፍሎ አያውቅም ነበር፡፡)

ኃይንቴው ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ ከርብ በላይ በጌምድርን ወክሎ አፄ ዘንድ ይሄድና እንዲህ ይላቸዋል «እኛ በጌምድሮች ንጉሥ «ተነሳ!» ሲለን፣ ልጃን ሚስቴን ሳይል ሳንል፣ እግራችንን ለጠጠር፣ ግንባራችንን ለፀሐይ፣ ደረታችንን ለጦር የምናበረክት ነን እንጂ፣ እንደ ሌላው አንገብርም፡፡ ስለዚህ፣ አባክዎን ጃንሆይ፣ የግብር ትዕዛዙን ያንሱልን፡፡»

አፄም ሲመልሱ፣ «እናንተ ለቤተ መንግስቱ ቀረብ ስለምትሉ በቁጥር ትበዛላችሁ እንጂ፣ ለኔ ሌላውም ኢትዮጵያዊ ይስለፋል፡፡ ስለዚህ እንደ ሌላው መገበር አለባችሁ» ይላሉ፡፡ አፄና ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ እልህ ተጋቡ፡፡

ኃይሉ እሸቴ ወደ ደብረ ታቦር ተመልሶ፣ ሕዝቡን ሰብስቦ፣ «በጌምድር! ምኑን አለሁ ትላለህ!» ይላቸዋል፣ «እንደ ሴት ቀሚስ ልበስ! ንጉሤ የምትላቸው ገባር አደረጉህ፡፡»

ሕዝቡ፣ «ምን ይበጃል?... የመሰለህን አድርግልን፡፡ አፋችን አንተ ነህ» ይሉታል፡፡

«ንጉሡ ምክራችንን ካልተቀበሉ ሥልጣናቸውን መወሰን አለብን» ይላል ኃይሉ እሸቴ፣ «እኛ እንደራሴ እንመርጣለን፡፡ ሥልጣኑን ከንጉሱ ተረክቦ እሱ ያስተዳድረናል፡፡ ንጉሡ ዘውዳቸውን ይዘው አርፈው ይቀመጡ፣ ቀለብ እንሰፍራለን፡፡»

ሕዝቡ፣ «አንተ ነህ አውራችን» አለ፡፡ ኃይሉ እሸቴ ግን ጉባኖችና ተቀናቃኞች ሲኖሩበት ስለሚችሉ፣ ያደርስኛል፣ ለጊዜው ግን ሌላ ልጠቀም በማለትና የህዝቡን መከፋፈልና መድከም በመፍራት «የኔ ይቅደና፣ ለጊዜው ራስ ዓሊን (የየጁን) ብንመርጥ ይሻላል» አለ፡፡

(የየጁ ገዢዎች ወረሴህ - ወረሼህ - የሚባሉ ቤተሰብ ናቸው፡፡ እንዲጋባሚ ሆኖ የዘመነ መሳፍንት የመጀመሪያው «እንደራሴ» ራስ ዓሊ የሚባሉ ወረሴህ ናቸው፡፡ ስለዚህ እንዲያስቱ በማለት ራስ ዓሊ «ትልቁ» እና ራስ ዓሊ «ትንሹ» ይባላሉ፡፡)

ራስ ዓሊ ትልቁ የሕዝቡን ጥሪ እንደሰሙ የየጁ ጭና ከተማ ከነበረው

ከመርጦ ተነስተው ፈረስ እየለዋወጡ ያለማቋረጥ በመጋለብ የአሥር ቀኑን መንገድ በሶስት ቀን ገስግሰው ደብረ ታቦር ደረሱ። ኃይሉ እሽቴም ምን ሊያደርጉ እንደሚፈለግባቸው በህዝቡ ፊት ነገራቸው። እጅ ነስተው ውክልናውን ተቀበሉ።

ራስ ዓሊ ጎንደር ሔደው አፄ ተክለ ጊዮርጊስን፤ «እኔ እንደራሴዎ ነኝ» አሉዋቸው «እርስዎ ቀለብ እየተሰፈረልዎ ዘውድዎን ይዘው ይኑሩ። ጦሩን የም መራ ግን እኔ ነኝ። ይህ የህዝቡ ቃል ነው።»

አፄ «በጓምድር የጅህን ይስጥህ!» ብለው ተራገሙ። ግን እምቢ ለማለት አቅም አልነበራቸውም።

እንግዲህ ከአርባ ሃምሳ ዓመት በፊት ስሁል ሚካኤል በግል ብልጠትና ጥረት ይዘውት የነበረውን ሥልጣን፤ ራስ ዓሊ ትልቁ በሕዝብ ግፊትና በአዋጅ ጨበጡት። በዚህ አኳኋን ለሰባ ስድስት ዓመት የገነነውን «ዘመነ መሣፍንት» ተብሎ የሚጠራውን የኢትዮጵያ ታሪክ ምዕራፍ ከፈቱ።

ራስ ዓሊ በመጀመሪያ ኃይሉ እሽቴን ራስ ወርቅ እንዲያስር አስደረጉ። ግዛት ግን አልሰጡትም። እንዲያውም ሕዝቡን ሊያስነሳ እንደሚችል አይተዋልና ፈሩት - ሊያጠፉት ያደቡ ጀመር። እሱም ነቃባቸውና ሸሸ።

እንግዲህ የሚቀጥሉት ሰባ ስድስት ዓመታት መሣፍንቱ «እኔስ እንደ ራስ ዓሊ ሥልጣን መያዝ አልችልም እንዴ? ማን ከማን ያንሳል!» እያሉ ዕድላቸውንና ጉልበታቸውን ለመሞከር ቆርጠው የተነሱ ይመስል የሁከት፤ የብጥብጥ፤ የብዙ ውጊያ ዓመታት ሆኑ። ሥልጣኑን እነራስ ጉግሣ፤ እነራስ ወልደየስ፤ እነራስ እገሌ እነራስ እንቶኔ ተነጣጠቁት።

በራስ ዓሊ ትንሹ ዘመን ጦርነቶቹ ጋብ አሉ፤ አገሩ ረጋ አለ። መጠነኛ ሰላም ሰፈነ። መሣፍንቱም አብዛኛዎቹ ያመት ግብር ወደ ጉንደር ይልኩ ጀመር። ይሁን እንጂ መሣፍንቱ - ይልቁንም ከጉንደር ራቅ ያሉት - ኃይላቸው ከፍ ያለ ነበር፤ በሚገዙት አገርም የሞትና የሕይወት ሥልጣን ነበራቸው።

ይህ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ዘመን ለኮሎኒያሊዝም ዓላማ አመቺ ሆነ። የአውሮፓ መንግስታት ከማዕከላዊው መንግስት ከጉንደር ሳይሆን፤ በቀጥታ ከሸዋ መስፍን፤ ከትግሬ መስፍን፤ ከባህረ ነጋሽ እና ከሌሎቹ መኳንንት፤ መሣሪያ መሸጥ፤ በንግድና በሚስዮን ስም እግራቸውን ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት ጀመሩ። ደግነቱ ኢምፔሪያሊዝም ገና መልክ አልያዘም ነበር እንጂ፣ ማዕከላዊው የጉንደር መንግስት የሌለ ያህል ነበር።

የራስ ዓሊ ትንሹ ቤተመንግስት አካባቢም ሌሎቹ ግዛቶች በሚልኩላቸው ግብር እጅግ ጠግቦ ተዝናና፤ ግብረገብ ችላ ተባለ።

አገሩ ሥርዓት አጣ። የመሣፍንቱ ውጊያ ቢቀርም፤ ሽፍታ በየቦታው ስለሚነሳ አገሬው ሠርቶ መብላት ተሳነው። ለሕዝቡ የሚያስብ ታጣ። ፍትሕና

ርትዕ ጨርሶ ጠፋ:: እንደራስ ዓሊ ትንሹም ያገር ጉዳይ ከመከታተልና ችሎት ተቀምጠው ከመፍረድ ይልቅ ደብረ ታቦር ወርደው ጃንሜዳ ላይ በመከዳ ተመቻችተው ለጉግስ ጨዋታ ድንኩላ ፈረስ ማግረጥ የስርክ መዋያቸው ሆነ::

ከልዩ ልዩ የአውሮፓ አገሮች መልእክተኞች «የንግድ» ውል ሊፈራረሙ ወደ ጐንደር መጥተዋል:: ለምሳሌ ያህል የእንግሊዝን ሙከራ እንመልከት:: ፕላውደን የተባለው የእንግሊዝ መልእክተኛ ራስ ዓሊ ፊት የንግድ ውሉን ረቂቅ ለማንበብ ከሁለት ዓመት በላይ ደጅ ከጠና በኋላ፤ በመጨረሻ ደብረ ታቦር ጃንሜዳ በመከዳ እየተንፈላሰሱ በሚዝናኑባት ሰዓት የውሉ ረቂቅ ሲነበብላቸው በግማሽ ልብ እየሰሙ ፈረሶቹን ሲመለከቱ፤

«ምነው በሙሉ ልብ ቢያደምጡኝ፤ ይህ ውልኮ ለሁለቱም አገሮቻችን ጠቃሚ ጉዳይ ነው» ብሎ ቢያመለክት፤

«ምነው ፕላውደን! በኔና ባንተ ዕድሜ እንደሆን አንድ እንግሊዝ ነጋዴ በኢትዮጵያ ወይም አንድ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ በእንግሊዝ አገር ሲነግዱ አይችሉም» ብለው ወደ ፈረስ መመልከታቸው ተመለሱ::....

እንደዚህ በአገሪቱ ሁኔታው ሲበላሽና እየባሰበት ሲሔድ፤ ሕዝቡ ዘንድ አንድ ሐሳብ ሥር ይሰዳል «ትልቅ ነበርን፤ ትልቅም እንሆናለን» የሚል ሐሳብ:: የሕዝቡ መጉላቀልና የገዥዎቹ መጋጨት አንዳንዶቹን ሐቀኞች ሰዎች አስቆጥቶ የሕዝቡን ብሶት በመወከል እንዲነሱ ስለገፋፋቸው፤ ተስፋ በትንቢት ስም ባገሩ አስተጋባ:: «ንጉሥ ይነሳል:: ስሙንም ቴዎድሮስ ይላል:: ኢትዮጵያም ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ የሰላምና የምሕረት አገር ይሆናል:: አርባ ዓመት ይነግሣል» እየተባለ ተነዛ፤ ተዛመተ::

## ልጅ ካሣ

የቋራው ደጃች ኃይሉ ልጅ አልባ ነበሩ:: ዘመኑ በሚፈቅደው ደንብ «ለዘር የምታበቃቸው» ወላድ ሴት ይፈልጉ ነበር::

ከጐጃምና ከጐንደር ባላባቶች የሚወለዱ ወይዘሮ አትጠገብ የሚባሉ አንዲት ሴት ነበሩ:: (በዚያን ዘመን ኮሶም ሆነ ሌላ መድኃኒት የሚያቀምሱ የቤት እመቤቶችና የታወቁ ሴት ወይዛዝርት ናቸው:: «እጃቸው ፍቱን ነው፤ ያሽራሉ» ይባላል:: በዚያን ዘመን መድኃኒት ማወቅና ማቅመስ ከሴት ባልትና አኩል የሚከበርና የሚያስመሰግን ሙያ ነው:: መድኃኒቱን ቀምሶ የሻረው ሰው፤ መድኃኒቱን ላቀመሱት ወይዘሮ እንደ ውለታ ምልክት ወይም በመታሰቢያ መልክ ስጦታ ይሰጣቸዋል እንጂ በዘመናችን እንደምናደርገው በገበያ መሰዋወጥ የታወቀ አልነበረም:: የአፄ ቴዎድሮስ እናትም እንዲህ ዓይነት እውቀትና ሙያ ነበራቸው:: ወላት ግን ሲሳደብ እውነት ለመናገር ሳይሆን ለማንቋሸሽ ነውና፤ ጠላቶቻቸው አጓን «የኮሶ ሻጭ ልጅ» አሉዋቸው::)

በሕልሟ በቅሎዬ ወግ ሰቃዋን እንደተጫነች አንተ ተተምጠህባት አየሁ። ስለዚህ የሚሆንህን ፈልግ፤ ብለው አስናበቱት።

ልጅ ካሳ ስሜንን ለቆ በደምቢያ አድርጐ ወደ ጉጃም ተሻገረ። ለተጓጓዙ ደጃዝማች ጐሹ አደረ። ደጃች ጐሹ ደምቢያንም መጠቅለል ያፈልጉ ስለነበር፤ የደጃች ክንፉ ጉባን (ተቀናቃኝ) ሊሆን የሚችል ሰው ማግኘታቸውን ምንልባት አልጠሉም። ስለዚህ ካሳን ባለሟል አደረጉት።

ካሳ ጉበዝ የጦር ሰውም ይሁን፤ ቅን አገልጋይም ይሁን፤ ታማኝ ባለሟልም ይሁን፤ አሁንም አንዳች ሹመት ወይ ሽልማት አላገኘም። ሹመት በስጡት የሚያስፈራ መስሏቸው ይሆን? ከዚህም ጋር ካሳ በእድሜና በማስተዋል እየበሰለ ሲሄድ አንድ ዕውነት በየሄደበት ተደንቅሮ ያፈጥበት ነበር፤ ይኸውም ዕውነት - ባገሪቱ ብጥብጥና ሕግ የለሽነት ነግሷል፤ አገሬው የመኳንንቱና የሽፍቶቹ መጫወቻ ሆኗል፤ ከሽፍቶቹ የማይሻሉት መኳንንት በሹመት የተተከሉበትን ባላገር እህሉንም ሚስቱንም እንዳሰኛቸው ይዘርፋታል። ካሳ ይሕ ሁኔታ አንገሸገሸው። ሁሉንም ጥሎ ወደ ቋራው ገባ። ወንበዴ ወይም ሽፍታ ሆኖ ተቀመጠ።

## «አባ ታጠቅ ካሳ»

ከእንግዲህ የጐንደርም ሆነ የሌላ ሥልጣን በቋራ ሊረጋገጥ አልቻለም። ከቋራም አልፎ ተርፎ በመላው ደምቢያ ጠረፍ ስሙ ተነሳ፤ «ካሳ ካሳ» ይባል ጀመር። ይኸን ጊዜ አጐቱ ደጃች ክንፉ ሞተው ስለነበረ፤ ሕዝቡ ያጐቱን ተማስ አወረሰውና «ደጃች ካሣ» ይለው ጀመር።

የጐንደር ቤተ መንግሥት ስጋት ገባው፤ ምክንያቱም «ካሳ ትንቢት ያለ ነው የተነሳው፤ መላ ኢትዮጵያን ጠቅልሎ አርባ ዓመት ይገዛል የተባለው እሱ ነው» እየተባለ ሊወራ ጀምሯልና።

ንጉሡ «ፃድቁ ዮሐንስ» ውሎዋቸው ከመሰሐፍትና ከሊቃውንት ጋር ነው። ራስ ዓሊ ትንሹም ለስሙ «እንደራሴ» ይሁኑ እንጂ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ጉግስና ሌላ ሌላ ደስታ በማሳደድ ነው። ዕውነተኛው ሥልጣን በራስ ዓሊ እናት በእቴጌ መነን እጅ ነው።

እቴጌ መነን ዋዛ የፖለቲካ ሰው አልነበሩም። ካሳ አደገኛ መሆኑ ገብቷቸዋል። «ምከሩ እንጂ፤ ይህን ቀለኛ ምን ብናደርገው ይሻላል?» ይሉ ጀመር።

በጦር ወግቶ ማጥፋት ነው ተባለ። በጦር መሪነቱ የታወቀውና የሚመካው ደጃች ወንድ ይራድ፤ «ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ እኔ አሳየዋለሁ!» ሲል ፎከረ። እቴጌ መነንም «ወንድይራድ፤ እሱን ያቸነፍክ እንደሆን ልጄን ተዋበችን እስጥሀለሁ» አሉት። ተዋበች የልጃቸው የራስ ዓሊ ልጅ ናት። እንደሰማቸ እጅግ የተዋበች ናት። ወንድይራድ እሷን እያየ ወኔውንና ድል የማድረግ

ፍላጐቱን እንዲጨምር ሲባል ተዋበች አብራው እንድትዘምት ተደረገ።

እንዳጋጣሚ - እንዴት እንደሆነ አይታወቅም - ደርቡሾች ከሱዳን ሰወረራ መጡ። ካሣ ደርቡሾቹን ለመግጠም የተዘጋጀ መሰለ። ግን «ፈርቶ» እያፈገፈገ ሄደ፣ ደርቡሾቹ እየተጠጉ መጡ። ካሣ አሁንም በስላቤ እያፈገፈገ እነ ደጃች ወንድይራድ ሠራዊት አጠገብ ሲደርስ ወደ ጐን ተፈተለከ (ከደርቡሾቹና ከነወንድይራድ ሠራዊቶች መሐል ሠራዊቱን አሾልኮ አወጣ።) ደርቡሹና ወንድይራድ ገጠሙ፣ ተጨፋጨፉ፣ ብዙ ሰው አለቀ፣ ወንድይራድ ሸሸ። ደርቡሽ ድሉን መቀጠል ተስኖት ወደ መጣበት ተመለሰ።

ከደርቡሾቹ የተረፈውን ሲዘርፍ ካሳ ወደ ጦር ሜዳው መጣ። አንድ የቆሰለ ወታደር ተዋበችን ደርቡሾች እንደማረኩዋት ነገረው።

ካሳ ከዚያ የገሰገሰ ደርቡሾችን ሰናር ላይ ደረሰባቸው። ድንገት አደጋ ጣለባቸው። ተዋበች ታስራ፣ ከብሯን ሲደፍሩዋት ሲታገሉዋት ደረሰ። ካንዱ ደርቡሽ ጩቤ መዛ (መቸም የደርቡሾች ጩቤ ሜቶ መርዝ የተቀባ ነውና) የገዛ እናትዋን ስትወጋና ካሳ ሲደርስ እኩል። አስጣላት። ቶሎ በጊዜ ደሙን ከእናትዋ ላይ አስመጠጠላትና መርዙ ሳይጎዳት ቀረ። እዚህ ላይ የካሳና የተዋበች ፍቅር ተጀመረ። (በኋላ፣ አፄ ቴዎድሮስ ከነገሡ በኋላ፣ እቴጌ ተዋበች ሹሩባቸው እናታቸው ዘንድ ስለሚቋረጥ ጠባሳዋን ባዶ ቦታ በወሰባ ይሸፍኑዋት ነበር ይባላል።)

ካሳ ተዋበችን ወደ አያትዋ ወደ እቴጌ መነን ሸኛት። ደምቢያን ስጥተንሃል አሉት። ታርቆ ገባ። «ባለ ትንቢት» ነውና በወዳጅነት ማሰር ይሻላል በማለት ተዋበችን ዳሩለት።

ካሳ ከጐንደር እንዲቀመጥ ተደረገ። የደምቢያ ግዛትም ለደጃች ጐሹ ተሰጠበት።

እንግዲህ ካሳና እቴጌይቱ በጥርጣሬ ዓይን ይተያዩ ጀመር። እሱም ጊዜ እስኪያመች ታማኝ ሎሌ መምሰል መርጧል፣ እሳቸውም ጠርጥረውት «ይህ ቀጣፊ ቆለኛ» ይሉታል፣ ታማኝነቱንና ተገዥነቱን ለመፈተን ያህል በየጊዜውና በየስበቡ ክብሩን ይነካኩበታል። እንደ ምንም እየገባ የቋራን ግዛት እንዲሰጡት አደረገ።

ወደ ቋራ ለመሄድ ከመነሳቱ በፊት ካሳ መጠጣት ስለነበረበት በደንቡ መሰረት እቴጌይቱን «ተሰናበታቸው»። ያን ዕለት ተዋበች ከሳቸው ጋር ነበር የዋለችው። የእልፍኝ አሽከሮች ይመጡና እቴጌን «ደጃች ካሳ ተሰናብተዎል። ምን እንላከላቸው?» ይላሉ። «ደሞ ለዚያ ቀጣፊ ቆለኛ አንድ ገንቦ ጠላ፣ አምስት እንጀራና አንድ ታላቅ መች አነሰው?» ይላሉ እቴጌ።

የታዘዘለት ላንድ ተራ ወታደር የሚሰጥ ነው። አንድ ደጃዝማች ግን

ከነአሽከሮቹ ነው የሚበላ። ስለዚህ እቴጌ መነን ሆኑ በሰው አጥረዱት ካሳን ተዋበች በጣም ተናደደች። በፍጥነት ሄዳ ሁኔታውን ለካሳ ነገረችው። ዝም አለ። የስንበቱ ሲመጣ ተዋበች በቁጣ «መልስህ ውስጥ!» አለች። ካሳ ግን «ተው ግድ የለም» ብሎ ተቀበለ። ታላቁን እንዳለ አገልግል ውስጥ ከተተ። ሰሰተን ሚስቱንና አገልግሉን ይዞ አሽከሮቹን አስከትሉ ከጐንደር ወጣ። በሦስተኛው ቀን ቋራ ጠረፍ ደረሱ።

እዚያ ካሳ አገልግሉን ከፈተ። ያን የገማውን ታላቅ ቆራረጠ። በቀልክነት እስከ መጨረሻው ለመዋጋት ተማማሉ። ከእንግዲህ ካሳ ከዙፋን ላነሰ ነገር እንደማይመለስ አገር አወቀ።

እቴጌ መነን ላኩበት። እምቢ አልመጣም አለ። ደጃች ወንድይራድ የሦስት ደጃዝማች የሚያህል ሠራዊት ይዞ ዘመተበት። ካሳ በሽፍትነቱ ጊዜ አምስቱን አገሬው ወዶለት ኖሮ፣ አሁን በሙሉ ከተተለት። ካሳ ጦሩን አፋፍ ላይ አዘጋጅቶ ድንኳኑን ተክሎ ጠበቀ። ደጃች ወንድይራድ እያስፎከረ - «የካሳ ሽፍታ ልጅ እጄን ቢስም ይሻለዋል» እያሰኘ - መጣ። ካሳ ከደርቡሾቹ የማረከው የሚተፋ መነሰር አለው። በሱ ያየል።

ተዋበች ካሳን፣ «ተኛ ይከጦሀል። ሲደርሱ እቀሰቅስሀለሁ» ተለምናለች። የት ሲደርሱ እንደምትቀሰቅሰው አመላክቷት ይተኛል።...

«ታጠቅ! ታጠቅ ደረሱ!» ብላ ቀሰቀሰችው። ከዚያ ወዲህ የፈረስ ስሙ «አባ ታጠቅ» ሆነ።

ካሳ በተላሉ ድል አደረገ። ወንድይራድ ተማረከ። «ወንድ መሆን ነው እንጂ. አስቸጋሪው ወንድይራድ፣ መሳደብ ቀላል ነው። እኔ እያለሁልህ ለምን የወንድ እናት ትሰድባለህ?» ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት ኮሶ! እንቆቆ! ቀጨሞ አያጠጣ ወንድይራድን በቁርጠትና በተቅማጥ ገደለው።

ካሳ የወንድይራድን ወታደሮች ምን እንዳላቸው ለትውልድ አልተላለፈም። ብቻ አብዛኞዎቹ ግልብጥ ብለው ለሱ ገቡለት፣ እጥፍ ድል ሆነለት።

ሰኔ 1975

## «አፄ ቴዎድሮስ ዳግማዊ»

አባ ታጠቅ ካሣ ደጃች ወንድይራድን ድል ሲያደርግ ጊዜ እቴጌ መነን እርቅ ጠየቁ። በቋራ ግዛቱ ላይ ደምቢያን ጨመሩለት። እዚያ ሄዶ ተቀመጠ።

እንግዲህ እቴጌ መነን ቀደም ሲል ደምቢያን ለጉጃም ገዢ ለደጃዝማች ጉሹ ሰጥተዋቸው ነበር። አሁን ታድያ ደጃች ጉሹ «ለምን ግዛቴን ያጠፋብኛል?» ብለው እቴጌን ቢጠይቁ፣ እቴጌይቱ «መች ስጠነው? በጉልበቱ ነው እንጂ. የወሰደው» ሲሉ ይመልሱላቸዋል። ደጃች ጉሹም ይናደዱና «የኔ ውርጋጥ አሳየዋለሁ!» ብለው ይዘምቱበታል።

ካሣ ለደጃች ጉሹ «እባክዎን እንካስ፤ እቴጌ ሊያጋቡኝ ፈልገው ነው እንጂ ፍርጠውንም የምበዩ ወደዚህ ነው፤ ከጉዳም አይደለም» ብሎ ላከባቸው፤ አሻፈረኝ ብለው በመቱበት፡፡ ካሣ ሲዋጋቸው በገደሉም እንዳያዋቱ እንዳያቆስሉ ብዙ ጥንቃቄ ወስዶ ነበር፡፡

በጦርነቱ ዋዜማ የደጃች ጉሹ አዝማሪ፣

«የንዋ በባልንጂ መች ይዋጋል ካሣ

ወርደህ ጥመድበት በሸምብራው ማሣ» እያለ ሲዘፍን አደረ፡፡

በጦርነቱ ደጃች ጉሹ በጦር ተወግተው ሞቱ፡፡ ያልወደቁትና ያልሸሹት ወታደሮቻቸው አሁንም አብዛኛዎቹ ለካሣ ገቡለት፡፡

ካሣ ድንኳኑን ተክሎ ዳባውን ለብሶ ለደጃች ጉሹ ሞት ሰባት ቀን ሀዘን ተቀመጠ (እንዲህ ዓይነት ሰውም ነበር፡፡)

በጦርነቱ ዋዜማ የሰደበውን አዝማሪ በካጋታው አስጠርቶ ለምን ሰደብከኝ? ቢለው፤ አዝማሪው፣

«አወይ የግዜር ቁጣ፣ አወይ ያምላክ ቁጣ፣

አፍ ወዳጁን ያማል የሚሠራው ቢያጣ

ሽመል ይገባዋል ያዝማሪ ቀልባጣ» ሲል መለሰ፡፡

ካሣም «ትክክል ፈርደሀል» አለና በሽመል አስደብድቦ አስገደለው፡፡ (እንዲህም አይነት ሰው ነበረ ካሣ፡፡)

ራስ አሊና እቴጌ መነን በካሣ ላይ ዘመቱ፡፡ አዘዞ አጠገብ ተዋጉ፡፡ እቴጌይቱ ጭናቸውን በጦር ተወግተው ቆስለው ተማረኩ፡፡ ራስ ዓሊ ሸሽቶ የጁ ገባ፡፡

ካሣ በድል አድራጊነት ጎንደር ሲገባ፣ ሕዝቡ በጭብጨባ በእልልታ ተቀበለው፡፡ «ስምህን ንገረን! ስምህን!» ሲሉት «ስሜን ስሜን (አገር) እነግራችኋለሁ» አላቸው፡፡ የስሜኑን ደጃች ውቤ ሳሸንፍ እነግራችኋለሁ ማለቱ ነበር፡፡

ደጃች ውቤና አባ ታጠቅ ካሣ ስሜን ደረስጌ አጠገብ ተጋጠሙ፡፡ ደጃች ውቤ ድል ሆነው ተማረኩ፡፡

እንግዲህ ደጃች ውቤ ደረስጌ ማርያምን ሊነግሱባት አቅደው ሲበዛ አንቆጥቁጠው ነበረ የሠሩዋት፡፡ ታዲያ ካሣ ይህን አይቶ «እንዴ! ሊያዝኑዋት ኖሯልንዴ እንዲህ ያንቆጠቆጡዋት?» ብሎ ቀለደባቸው ይባላል፡፡

የደጃች ውቤ ዕቃ ቤት ሰባት ቀን ሙሉ ሲዘረፍ አላለቀም ይባላል፡፡ እና ካሳ በመገረም፣ «ብልህ ይመስሉኝ ነበር፣ ደጃዝማች፣ ምን ሊያደርጉልዎ ነው ይህን ሁሉ ሀብት ያከማቹት?» ብሎ ጠየቃቸው፡፡

«አያ! ለክፉ ቀን ይሆነኛል ብዬ ነበራ!» አሉት፡፡

ከት ብሎ ስቆ፣ «ለርስዎ ከዚህ የከፋ ቀን ምናለ? ምነው አልደረሰልዎ?» አላቸውና፣ አብረውት ወደ ነበሩት ሌሎች ሰዎች ዞር ብሎ፣ «ለከፋ ቀን ተብሎ የተከማቸ ሀብት ለከፋ ቀን ከደረሰ፣ የታለ ክፉ ቀን?» አለ። (አለቻ ጥልቅ ፍልስፍና)

ኮማ ደረሰኜ ማርያም ባባ ሰላማ እጅ «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ቴዎድሮስ ዳግማዊ» ተብሎ ሲቀባ፣ ዘውዱን ከጳጳሱ እጅ ነጥቆ ራሱ ደፋው ይባላል። (ወይስ የናፖሊዮንን ታሪክ ለጥፈውበት ይሆን?)

ዳግማዊ ቴዎድሮስ መጀመሪያ ያወጁት የባርያን ነፃነት ነበር። አዋጃቸው ምን ያህል በስራ ላይ ዋለ? ለሚለው ጥያቄ ግን መልስ አናገኝለትም።

ራስ አሊ ወረሴህ (ወረ ሼህ) በመሆኑና የጁ የወረሴሆች አገር በመሆኑ አገሬው ያቅፈኛል ብሎ ነበር ወደዚያ መሸሹ። አፄ ቴዎድሮስ ከደረስጌ ተነስተው በጉንደር አድርገው ወደ የጁ ዘመቱ። ራስ አሊ ድል ሆኖ ሸሽቶ በረና ጫቀታ አፋፍ ሄዶ ተቀመጠ። አባርረን እንውጋው ሲሉዋቸው አፄ ቴዎድሮስ ንቀው ተውት። ወደ ደብረታቦር ሲመለሱ የሚከተለውን ተቀኙ።

«አሊ ባለ ክንዱ ጋሻውም ወደቀ

የጨነበውንም የጁንም ለቀቀ»

በዚህ አኳኋን ዘመነ መሳፍንት አከተመ።

አፄ ቴዎድሮስ የእስላምንና የክርስቲያንን (የፀጋውንም የቅባቱንም) ሊቃውንት ደብረ ታቦር ጃን - ሜዳ ሰበሰቡ።

በእስላሙ ህብረተሰብ እጅግ የተከበሩ ሊቅ (አገራቸው ኩሬብ የሆነ) ሼክ ሁሴን ጂብሪል የተባሉ ነበሩ። በክርስቲያኑ በኩል ደግሞ መምህር አካለ ወልድ የተባለ ወጣት ሊቅ በአስተሳሰቡ አፄ ቴዎድሮስን ማርኳቸዋል። እና ንጉሡ ሰሎሳቱም ለ ቃውንት አንድ ሰንጋ ላኩ። ሰንጋውን የወሰደላቸውንም አሽከር፣ «የሚያደርጉትን ሁሉ ተመልከተህ መጥተህ እንድትነግረኝ» ብለው አዘዙት።

እንግዲህ ሰንጋውን ማን ያረደው? ሼክ ሁሴን ጂብሪል ተጨነቁ። መምህር አካለ ወልድ፣ «ምነው ተጨነቁ! እርስዎ ነዎት ታላቅ፣ ይባርኩት» አላቸው።

ቢስሚላሂ ብለው አረዱት። ተበልቶና ተካፈሉት። መምህር አካለወልድ ድርሻውን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በስመ አብ ብለው ባርከው በሉት። ጉድ ተባለ።

ሰንጋውን ያመጣው ሰውዬ በታዘዘው መሠረት ወደ ንጉሡ ተመለሰና የሆነውን ሲነግራቸው፣

«መምህር አካለ ወልድ በስመ አብ ብለው ሲባርኩት ጊዜ እንደ አዲስ ደመ ነፍ ብሎ ፈሰሰ» አላቸው።

«እሱን ተውውና፣ ዘላ አልበላም?» አሉት

«ዘሱ»

«የማሪል እንየ አካልየ

ይቀኑል እንደ ዘበርዩ» አሉ አፄ ቴዎድሮስ በአድናቆት::

በርግጥ ግን ዘመኑ ነውና፤ ሃይማኖት አፄ እንደተመኙት አገር ማስተባበሩ ቀርቶ የሚከፋፍል ሆነ፡ ስለዚህ፣ «ሃይማኖትህን በጉያህ! አገርና እኔ ግን የጋራ ነን» ብለው ትዕዛዙን በተኑት::

አፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት ለማረጋገጥ ወደ ወሎ ለመዝመት ተገደዱ:: ጉምቢ በተባለ ነፋሻ ስፍራ ከወይዘሮ ወርቂት ጦር ጋር ረዥም ጊዜ የወሰደ ውጊያ ተደረገ:: አልተሸናነፉም::

የወይዘሮ ወርቂት አዝማች የሆነው ደጃች ወልደ ሚካኤል ለአፄ ቴዎድሮስ እንዲህ ሲል ላከባቸው:-

«በኔና በርስዎ ኃጢአት ይኸ ሁሉ ሰው ከሚያልቅ፣ እኔና እርስዎ ፍልሚያ እንግጠም:: ያሸነፈ ሁሉቱንም ሠራዊት ይጠቅልል::» አንድ ተራ ደጃዝማች እንዴት እንዴት አባቱን ቢደፍረን ነው ከንጉሠ ነገሥቱ ልፋለም የሚለው፣ ብሎ በመናደድ ገብርዬ መልዕክተኛውን ሊሰይፈው ሲል፣ አፄ ቴዎድሮስ ከንዴቱን እየያዙ፣

«ተውኮ ገብርዬ! ወንድን ወንድ ልግጠም ሲል እንዴት መልዕክተኛውን ልግደል ትላለህ?» ይሉትና፣ እሺ ነገ ጧት ይዋጣልን፣ ብለው መልስ ይልካሉ::

በኋላ ሲናገሩ አፄ ቴዎድሮስ፣ «እንደዚያች ሌሊት የረዘመብኝና የፈራሁበት ጊዜ አላውቅም» ብለዋል ይባላል::

አይነጋ የለም ነጋ፣ ሁለቱ ሠራዊት ግምባር ለግንባር ተሰለፉ:: ካሣና ወልደሚካኤል በየበኩላቸው ጋሻና ጣምራ ጦር ይዘው ፈረስ ላይ ወጡ:: በፍቁ ተፋጠጡ:

«እርስዎ ይወርውሩ» አለ ወልደ ሚካኤል

«ቆማጣ ቆመጥማጣ! አዝገኸኛለሁ አንቺ ወርውሪ!»

ወልደሚካኤል ወረወረ:: ከሸፈ:: ካሣ ወረወረ:: ወጋው፣ ከፈረሱ ላይ ከነከሰው::

ጋልበ ደርሶ የጠሩን አወጋግ ቢመለከት ጦሩ ሰውዬውን ከመውጋትም አልፎ በስቶት ግማሹ ያህል ከጀርባው ወጥቶ ይታያል:: «ምንኛ በፈራ ነው እንዲህ የበሳሁት?!» አለ ካሣ በመገረም:: (እንዲህ ደፍሮ «ፈራሁ» ለማለት ምን ያህል ጀግንነት ይጠይቃል? የካሳን ያህል::)

ወይዘሮ ወርቂት ሸሽታ ቆላ ሸዋ ገባች:: ወሎ ገበረ:: አፄ ቴዎድሮስም ሆኑ ስርአትን ለጥተው እንደ ሁሌ ደምባቸው ከገሬው ባላባቶች አንዱን ሹመው፣ ወደሸዋ ቀጠሉ::

የሸዋው ንጉስ ኃይለ መለኮት በድንቱ ከመዩረታ በፊት በደንዛዛኛ ህመም ሞቱ:: አፄ ቴዎድሮስ ሸዋን ድል አድርገው አቶ በዛብህን ሾመው፣ የንጉስ ኃይለ መለኮትን ያስራ አንድ ዓመት ልጅ አቤቶ ምኒልክን ይዘው ወደ ጉጃም ቀጠሉ::

ጉጃምን አስገብረው ግዛቴን ለመስፋት ለተድላ ጓሉ ሰጥተው፣ ወደ ጉንደር ቀጠሉ:: ገና ጉንደር ሳይደርሱ ታዲያ ጉጃም ሸፈተ ተባለ:: «ማንን ይዞ ተነሳ?» ቢሉ፣ ፊታውራሪ ደሪ፣ ልጁ ችኩል፣ እና የልጁ የምንትዋብ ባል ናቸው መሪዎቹ አሉዋቸው::

«አስልጪው ቀጥቅጪው በመጣ፣

ጉጃም ከፉ ሰው ደሮ·ሚሉ አመጣ» ብለው ገጠሙና፣ «አዙር ፈረስ!» ብለው ወደ ጉጃም ተመለሱ::

## ምንትዋብና ካሣ

በመደበው ካሣ አስደናቂ ህይወት ውስጥ ሶስት ሴቶች ጉልተው ይታያሉ:: እነርሱም፣ ብዙ መከራ አይተው ያሳደጉት ወላጅ እናቱ ወይዘሮ አትጠገብ፣ ፍቅረኛው ጓደኛውና የተከሊል ሚስቱ እቴጌ ተዋበች፣ እና ለአስራ ሶስት ወይም ለአስራ አራት ዓመታት ያህል ፋታ ሳትሰጥ ያሳደደችውና ያስቸገረችው ጠላቱ፣ የጉጃምዋ ወይዘሮ ምንትዋብ ናቸው:: የዚች የምንትዋብና የካሣ ታሪክ ንጉሡን አፄ ቴዎድሮስን ሳይሆን ሰውየውን ካሣ ኃይሉን ምን አይነት ሰው እንደነበረ ስለሚያሳይ ይኸው ለብቻው አሰፍረዋለሁ::

አፄ ቴዎድሮስ አዙረው ተመልሰው፣ ሸፍቶ የነበረውን የጉጃም ጦር ወግተው ድል አድርገው፣ ፊታውራሪ ደሪንና ልጃቸውን ችኩልን በስቅላት ቀጡዋቸው:: እነዚህ የወይዘሮ ምንትዋብ አባትና ወንድም መሆናቸው ነው፣ ባሏ ደግሞ በውጊያው ተገድሏል:: እና ወይዘሮ ምንትዋብ ሶስት ኃዘን ተደራርቦ የቴዎድሮስ እጅ ቢመታት እንዲህ ስትል እንጉራጉረች:-

«ጠጅም አያምረኝም፣ ድሮ ጠጥቻለሁ፣
ስንጋም አያምረኝም፣ ቋንጣ ሰቅያለሁ፣
ቢሻኝ ከወንድሜ ካባቴ በላለሁ::
ሺ ብረት በግራው፣ ሺ ብረት በቀኙ፣
ሺ ፈረስ ከኋላው፣ ሺ ፈረስ ከፊቱ፣
ይህን ሳታይ ሞተች ካሳ ሻጭ እናቱ::
አንድ እግር በርበሬ መንቀል ተስኗችሁ፣
አቀጥሉ፣ ሰብልበ፣ ፈጅቶ ይግደላችሁ::
ይህንን ቢሰማ ያጉራል ላመሉ፣
ማናት ቢላችሁ፣ ምንትዋብ ናት በሉ::»

ንጉሡ ነገሥቱን አይሰድቡ ስድብ የሰደበቻቸው ወይዘሮ ምንትዋብ ተደዛ ከፊታቸው ቀረበች። «እስቲ ድገሚው!» ተባለች።

ሳትፈራ! ሳትመነታ! እንዲት ስድብ ሳትገድፍ ደገመችው።

ሳቀ ካሣ! «አንቺ ቆማጣ ቆመጥማጣ! በኔ ኪሳራ መንግሥት ለማየት ልትዘሪ?... ልቀቁት ትሂድ! ነፃ ነች። በህይወት እስካለች ድረስ ቀለብ ስፈሩላት። አባቷን! ወንድሟን! ባሏን ገድዬባት እንግዲያው ልታመሰግነኝ ኖሯል?» ካሳ ምን ዋዛ ነው?

ግና ምንትዋብስ ምኗ ዋዛ ነው? ወደ ጉንደር ተከተለችው። እስከ እለተ ሞቱ አልተወችውም። በሄደበት ተከተለችው! በግጥምም በተራ ንግግርም እየሰደበችው! ባለበትም በሌለበትም እየሰደበችው።

ግና ካሳስ ምኑ ዋዛ? ታገሳት! ቻላት! ዝም አላት። ዘመኑ መንግስቱ በሙሉ የውጊያ ነበርና! እሷም በሴትነት ጥበብዋ ከቅርብ ተከታዮቹ በእጅዋ ያስገባቻውን አስገብታ! በሚስጥርና በድንገት ሲዘምት ሲያቅድም ቀድማው ትሰማና (አንዳንዱን)! ቀድማው በግጥም ይፋ እያወጣችበት እያሰናከለችው! እንሳቀቅም አለችው! እሱም ቀለብዋን በወቅቱ እያስፈረላት ቻላት።

እሷ ስታሳድደው እሱ ሲችላት እመጨረሻው ሰዓቱ እመቅደላ ደረሱ። ሽጉጡን ጠጥቶ ሞተ። ካሳ ምኑ ዋዛ ነው? ግና ምንትዋብስ ምንዋ ዋዛ? ያን ጊዜ በጉጃም በገዳይነቱ የገጠመችበትን ያህል! አሁን በሟችነቱ ገጠመችለት። ያውም ራሳውን አልለቅ ብላ እየተጠመጠመችበት! «ደም እምባ» እያለቀሰችለት፡-

«መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ!
የሴቱን አናውቅም! ወንድ አንድ ሰው ሞተ
አባቴን! ወንድሜን! ልጄን ቢገድሉብኝ ነበር መናደዴ
ባሌን ቢገድሉብኝ ነበር መናደዴ
ጨከኑ በራስዎ! ይቅር አለ ሆዴ።
ማረከን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው!
ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኙዋቸው!
ምን ይሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው?
ለወሬ አይመቹም ተንኮለኛ ናቸው።»

በዱብዳ የልብ ስቃይ ተነስቶ ከዚች ከምንትዋብ እኩል ግጥሙን ሊያንቀረቅረው የሚችል ማን ነበር? ካሣ ራሱ። ስለዚህም የመጨረሻው የጀግና ድርጊቱን በድንቅ ግጥም ለትውልድ እንድታስተላልፍ ሲባል ካሣና ምንትዋብ ተገናኙ። እንደዚህ አይመስልም? የካሣ የህይወት ታሪክ በዛዛት እንደዚህ ነው የሚመስል። አንድ ሰው ቢጋጥሚ ተወልዶ የኖረው ሳይሆን! ተከታይ ትውልዶችን ለማስደነቅ! ለማስደሰት! ለማኩራት! ለማሳሰብ! አርአያ ለመሆን ከላይ ታትዶ የተኖረ ይመስላል።

## አዲስ ዓይነት መሪ

የአፄ ቴዎድሮስ መነሻና መሰረታዊ አላማ በመሳፍንቱ የስልጣን ሽሚያ የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያ መልሰ አንድነቷን ማረጋገጥና፣ ጠረፎችዋን የያዘውን ቱርክን አባርሮ የጥንት ታላቅነትዋን ማደስ ነበር:: ለዚህም የመጀመሪያ እርምጃ የያዙትን አገር ማረጋጋት፣ ከዚያም ከውጭ መንግሥታት ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ እና ዘመናዊ ፋብሪካዎችን (በተለይም የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎችን) ማቋቋም መሆኑን ተገንዝበው ጥረታቸውን ወደዚሁ አዋሉት::

የያዙትን አገር ማረጋጋትን በሚመለከት አንደኛ፣ ሽፍታና ወንበዴን ማጥፋት፣ ሁለተኛ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ የኃይል መሰረት የሆነውን የመሬት ስሪት መለወጥ የግድ አስፈለገ::

አፄ ቴዎድሮስ፣ «ልዩ ዘብ ላቋቁም ነውና፣ ሽፍትህ በዱር በገደሉ ከምትንከራተት፣ በኋላ ስትያዝ ከምትሰቀል፣ ና ግባ ይሻልሀል፣ ቀለብ እሰፍርልሃለሁ» ብለው አዋጅ አስነገሩ::

ሽፍታና ወንበዴው እየተሰገበገበ እየተንጋጋ መጣ:: ሽፍታ የነበረ ንጉሥ የሽፍታ ነገር ይገባዋል ብሎ ሳይሆን አይቀርም፣ እየተያዘ እንደ ወንጀሉ መጠን ተቀጣ::

ከዚያ በኋላ፣ ምን ያህል አመፅ በሳቸው ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ቢበዛ፣ ሕዝቡ ግን ከሽፍታ ከወንበዴ አረፈ::

አገሪቱን እስከ መከፋፈል ያህል ኃይል የተሰጣቸውን የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን የባላባቶቹን የመሬት ይዞታ ስፋት ለመቀነስ አፄ ቴዎድሮስ የሚከተለውን አወጁ፣

(ቃላቱን ሳይሆን ፍሬ ነገሩን እፅፋለሁ)

1. ውርስ እንደቀድሞው ለበሁር ልጅ ብቻ መሆኑ ቀርቶ፣ የተወለዱ ልጆች ሁሉ እኩል ይወርሳሉ::

2. ዲቃላም ልጅ ነው:: መወለዱ ከተረጋገጠ፣ እቤት ከተወለዱት እኩል ይወርሳል::

3. ሴት ልጅም ከወንድ ልጅ እኩል ትወርሳለች::

4. ሹመቱንና ሽልማቱን ግን ንጉሠ ነገሥቱ ላሰኛቸው ይሰጡታል::

አፄ ቴዎድሮስ ወታደር ሲባል የንጉሠ ነገሥቱ ነው እንጂ እንደ ቀድሞው የደጃዝማቾቹና የራሶቹ የግል ወታደራቸው አይደለም፣ አሉ:: ራሶም ሆነ ደጃዝማች የወታደሮቹ አለቃ እንጂ አሳዳሪ አይደለም:: አሳዳሪው ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ናቸው:: በዚህ ዘመን አባባል አፄ ቴዎድሮስ የሚሊቴሪ አስተዳደርን ማዕከለዊ አደረጉ::

ይህን ሁሉ ካረጉ በኋላ መስፍንቱና መኳንንቱ ቢነሱባቸው ምን ይገርማል፤ የሚገርመውስ ባይነሱባቸው ነበር። ከጊዜያቸው በፊት ተወለዱ፤ የዘመኑ ሰው እንኳን ሊቀበለው ሊገባው የማይችል ለውጥ ለማካሄድ ሞከሩ። እኛ የኋለኞዎቹ ዘመናት ትውልዶች ነን ያፄ ቴዎድሮስ ሙከራ ሊገባን የሚችል። ከልብ ብንሞክር።።

አፄ ቴዎድሮስ «ለሰራዊቱ ምን እናብላው?» ብለው ቢያስቡ፤ ባንድ በኩል፤ ቤተክርስቲያን ብዙ ርስት አላት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተግባርዋ ርስት ከማከማቸትና ከማስተዳደር የተለየና የራቀ መሆን አለበት።

ንጉሠ ነገሥቱ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን ጉዳይ ሲያነሱባቸው ጊዜ፤ «የቤተ ክህነት ሀብት ያባቶችዋ የሌዋውያን ነው፤ አይነሳም፤ የእግዚአብሔር መብለ ነው» ሲሉ መለሱ።

አፄም፤ «ዳዊት በተራበ ጊዜ የቤተ መቅደስን መብለ እንደበላ አታስታውሱምን?» አሉ፤ «እኔና ወታሮቼም ተርበናል።»

ለያንዳንዷ ቤተክርስቲያን ለአንድ መሪጌታና ለአምስት ቄስ ቀለብ የሚበቃ መሬት ብቻ እየተውለት፤ የተረፈውን መሬት በሙሉ አፄ ወረሱት። ከዚያ ቀጥር ትርፍ የሆነውን ቀሳውስትና ደባትር «ተከተሉኝ» አሉት። ወታደር ሁን አሉት።

እና ቤተክህነትስ አፄ ቴዎድሮስን ብትጠምዳቸው ምን ይገርማል? የሚገርመውስ ባትጠምዳቸው ነበር። አፄ ቴዎድሮስ ካለፉ በኋላ እንኳን ቂም የተጠረሰ ይመስል፤ ከሳቸው በፊትም፤ ከሳቸው በኋላም ለነገሡ ነገሥታት ሁሉ ቤተክርስቲያን በስም ጠርታ ፀሎት ስታደርግ፤ የአፄ ቴዎድሮስ ስም ግን አይጠራም ነበር ይባላል። (ምክንያቱ ግን መሬት ስለወረሱባት ተቀይማ ሳይሆን፤ ራሱን የገደለ ሰው ፍትሀትም ፀሎትም አይገባውም የሚል እምነት ስላላት ሊሆን ይችላል።)

የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት በሚመለከት፤ ለምሳሌ ያህል ፕላውደን የተባለው የእንግሊዝ ልዑክ ከራስ አሊ ጋር የንግድ ውል ለመፈራረም ሁለት ዓመት ሙሉ ደጅ ከጠና በኋላ ውሉን ሲያነሳባቸው እንኳ ምን ያህል ቀልድኛነት እንዳሳዩ ባለፈው ተመልክተናል።

አፄ ቴዎድሮስ እንደ ነገሡ ፕላውደን ያለ እንኳች ደጅ ጥናት ሊያነጋግራቸው ቻለ። የንግድ ውሉንም በአረብኛ ሲያነብላቸው አፍጠው ቆመው በሙሉ ሰምተው እንዳበቃ፤ የመጨረሻው አንቀፅ፤ «አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ በእንግሊዝ ምድር ወንጀል ቢፈፅም፤ በእንግሊዝ ፍርድ ቤት ይፈረድበታል። አንድ የእንግሊዝ ዜጋ በኢትዮጵያ ምድር ወንጀል ቢፈፅም፤ አሁንም በእንግሊዝ ፍርድ ቤት ይፈረድበታል» ይላል።

አፄ ቴዎድሮስ «ፓስፖርቱን እንደገና ራስ አሊ አልተፈራረሙበትም» አሉ

እተወዋለሁ:: ነገር ግን፣ የመጨረሻውን እንቆቅ ስንመለከት፣ እኩልነታችን የቱ ላይ ነው? አገሬን ላስከብር እንጂ ለውጭ ላስገዛር አልተነሳሁም» ብለው ውሉን እምቢ አሉ::

ፕላውደንም ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ራፖር (ዘገባ) ሲልክ እንዲህ ብሎ ይደመድማል፤

«... መመልከት ያለብን ቴዎድሮስ እምቢ ማለታቸውን ሳይሆን፣ እምቢ ያሰኛቸው ምክንያት ያው የተነሱበት የአገራቸው ክብርና ኩራት መሆኑን ነው:: ይህንንም ተረድተን ውሉ የሚስተካከልበትን ማሰብ ይኖርብናል:: ይልቁንም ማጤን የሚኖርብን እነ ራስ አሊ ያን ያህል ጊዜ ካገላበጡኝ በኋላ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በጥሞና ሰምቶ አዳምጦ ሲያበቃ፣ ወዲያው እሺ ወይም እምቢ የሚል ቁርጥ ያለ መልስ የሚሰጥ መሪ መነሳቱ ተበሩ የሚያሳድርብን መሆኑን ነው::»

የቴዎድሮስ ዳግማዊ ታሪክ በመጠኑም ቢሆን የታወቀ ነው:: እኔን የሚያስደንቀኝና «ምነው ስለሱ ብዙ ብዙ ባወቅኩ!» የሚያሰኘኝ የሰውየው የካሣ ባህሪይ ነው:: እኔን በዘመናት ርቀት ይህን ያህል ያስደነቀኝ ይኸ ካሣ የሚሉት ሰውዬ አብረውት የኖሩትን ምን ያህል አስደነቃቸው? - እስከ መጨረሻው፣ እስኪሞቱለት ድረስ:: ከነሱ ጋር የነበረውን ግንኙነት ስንመለከት ነው ሰውዬው የሚታየን:: ተዋበችን፣ ዮሐንስ ቤልን እና እነ ገብርዬን በየተራ እዩዋቸው እስቲ:: ለካሣ ምኑ ነበሩ? እሱስ ምናቸው ነበረ?

## ተዋበችና ካሣ

«ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ ይቀዳሉ» የሚለው ተረት እንደተዋበችና ካሣ ላሉት የሚነገርላቸው ነው::

ተዋበች የካሣ ዓይነት ሰው ነበረች:: ከመዋረድ መሞትን የምትመርጥ! ደርቡሾች ማርከዋት ክብርናዋን ሊደፍሩ ሲሉ፤ የደርቡሾች ጨቤ ጫፉ ላይ ገዳይ መርዝ እንዳለው በማወቅዋ፣ የአንዱን ጩቤ ሳያስበው በፍጥነት መዘዘችና የገዛ አናትዋን ወጋችው:: ካሣ በጊዜ ደርሶ ባያስጥላትና ደምዋን አስመጥጦ መርዙን ባያስወጣላት ኖሮ ሞታ ነበር:: ውርደትን ከመቀመስ ይልቅ ሞትን መቅመስ መምረጥዋን ሲያይ ካሣ ምንኛ አደነቃት ይሆን? ልዩ ውበትን ከልዩ ሰብአዊ ኩራት አጣምሮ የሰጣት ሴት! ያኔ ሳይሆን አይቀርም የሷ ፍቅር ያደረበት:: እንደዚያ ሳታስበው ደርሶላት ከውርደቱም ከሞቱም ያስጣላትን ጀግና እሷም በዚያች ሰዓት ልትወደው ሳትጀምር አልቀረችም::

ተዋበች እንደ ካሣ ቆራጥ ነበረች:: ካገባች በኋላ አያትዋ እቴጌ መነን ክብሩን ስለነኩባት እንዲሸፍት ሳታደፋፍረው ሳትገፋፋው አልቀረችም:: አብራውም ሸፈተች:: እስከ እለተ ሞትዋ ድረስም፤ እንደ ሕሊናው ወይም እንደ

ጥላው አይነት ምንም ቢሠራና የትም ቢሔድ ተለይታው የማታውቅ የፍቅር ቁራኛው ሆነች።

ተዋበች ለካሣ የሕልሙም የዕድሉም ተካፋይ የሆነች ውብ ሚስት ነበረች። ምግቡን እሷ ራሷ ነበረች የምታበስልለት። ከውጭ እንደመጣ በተልባ ፈትፍታ ታጉርሰዋለች። በሰላም ጊዜ ሆነ በዘመቻ ተለይታው አታውቅም። እና - ወደ ወሎ ዘምተው ሳለ ተዋበች በንዳድ (ወባ) በሽታ ሞተች። ምን ያህል እንዳዘነ፣ ምን ያህል እንዳጉደለችው ለመግለፅ ከመሞከር ይልቅ ዝም ማለት ይመረጣል። አስከሬንዋን ወደ መቃብር ሲከተል ካወረዳቸው የለቅሶ ቅኔዎች በጣም የሚታወቀው ተዋበች ለካሣ ምን እንደ ነበረች ይጠቁመናል።

«እጅግ ሥር አዋቂ ትናንትና ሞተች
መድኃኒቱን ምሳ ታበላኝ ነበረች።
እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ
እቴጌ ተዋበች ሚስትን ናት ገረድ?»

ሚስቱም፣ እናቱም፣ ገረዱም፣ ጓደኛውም፣ ፍቅረኛውም የነበረችው ተዋበች ከሞተችበት በኋላ ነው ካሣ የተለወጠው። ምን አለ ካሣ፣ ተዋበች ምንኛ ታላቅ ሰው እንደ ነበረች ለኛ ሊያመለክተን የሚችል?

«እግዚአብሔር ሲወድህ ሁለት ነገር ይሰጥሀል። ከሰዎች መርጦ መሪ አለቃ ያደርግሀል። ለዚህ ሥራ አብራህ የምትሰለፍ ታማኝ ሚስትም ይሰጥሀል። እኔንም ይወደኝ ነበረ፣ አሁን ግን ተጣልቶኛል።»

ከተልባ ፍትፍቱ ጋር ትእግስትን፣ ተስፋን፣ ደስታንና ፍቅርን ትመግበው የነበረችው ተዋበች ስትሞትበት ጊዜ፣ ካሣ ድፍረትን፣ ቁራጥነትን (ለሚጠሉት «ጭካኝነት») እና የጦር ስልትን ብቻ የተጐናፀፈ የቀድሞው ካሣ ግማሽ ሆኖ ቀረ።

የተዋበች ሞት ያጐደለው ካሳን ብቻ ሳይሆን፣ በወቅቱ የኖሩትን ኢትዮጵያውያንም ጭምር ነው።

ምነው የካሣን ዓይነት የቅኔ ተሰጥዎ በኖረኝና ስለተዋበች በተቀኘሁ!... ግን የተቀኙላትም አሉ፣ የሚቀኙላትም ይመጣሉ። ዘር ተቀብሮ በአበሰ ነው ሊበቅልና ገና ስንትና ስንት ጥበብ ታፈራለች!!!።

ካሣ ማመን እስኪያስቸግረን ድረስ ከጊዜው ቀድሞ የኖረና፣ በዚህም የተነሳ ተከታዩን ጊዜ የለወጠ ይሁን እንጂ፣ ባንዳንድ ነገር ግን የዘመኑ ሰው ነበረ። የዘመኑ ሰው ባይሆንማ በዘመኑ ውስጥ ያን ያህል ታላቅ ሚና ለመጫወት የሚያስችለውን ያህል የሰው ብዛት ሊያስከትል ባልቻለ ነበር።

ካሣን የኖረበት ዘመን ሰው ከሚያደርጉት ባሕርዮቹ አንዱ ሃይማኖተኛ

በሠፈው ስንመለከተው ደግሞ ቤል የነፃነት አርበኛ ነው እንላለን:: ለዚህም ነው ለቴዎድሮስ ያደረው::

ዘረኛውን ዓይነት ፈረንጅ ስንሞግተው ደግሞ እንዲህ ብለን አፉን እናስዘጋዋለን፤ «የቤል ዓይነቱ ሰው በአንድ አገር ይወሰዳል እንጂ በአንድ አገር አይወሰንም:: ከፈለገ መላው ዓለም አገሩ ቢሆንም በመላው ዓለም ለመኖር ስለማይቻል፤ የፈለገውን አገር ሊመርጥ ይችላል:: ቤል ለገዛ ምክንያቱ ኢትዮጵያን መረጠ:: ኢትዮጵያም አመነችውና ተቀበለችው:: የንጉሠ ነገሥቱ የልብ ጓደኛና ታማኝ ባለሟል ሆነ:: እሱም እምነቱን ከቶም አላጓደለም:: ንጉሠ ነገሥቱን ከሞት ለማስጣል ሲል ዓይኑና ልቡናው እያወቀ የገዛ ሕይወቱን ቤዛ ሰጠ::....

ስለዚህም እንደማንኛውም ሐቀኛ ኢትዮጵያዊ፤ ኢትዮጵያዊ ሆነ:: ኢትዮጵያዊ የሆነውና ለኢትዮጵያ የሞተው ተወልዶ ሳይሆን ተመርጦ ነውና ልዩ ምስጋና ሞገስ ይገባዋል::

የካሳ ከብዙዎች አንዱ ችሎታ ወይም ተሰጥኦ የሰውን ልክ ማወቁ ነው:: የቤልንም ልክ በትክክል አውቆት ነበር:: እኛ ከኛ ዘመን በኋላ ታሪኩን የሰማነው ሰዎች የቤልን ልክ ያወቅነው አሟሟቱ ስለገለፀልን ነው:: ካሣ ግን ቤልን በህይወት አይቶ ነው ልኩን ያወቀው፤ ለዚህም ነው ሊቀ መኳስ አድርጎ የሾመው::

ሊቀ መኳስ ምን እንደሆነ እኔም አረጋግጬ ላላውቅም ብቻ ከተግባሮቹ አንዱ በጦር ሜዳ ልክ የንጉሡን የመሰለ ፈረስ ላይ ተቀምጦ፤ ልክ የንጉሡን የመሰለ ልብስ ለብሶ፤ ልክ እንደ ንጉሡ መዋጋት ነው:: በዚያን ዘመን ባገራችን ንጉሥ ከተገደለ ወይም ከተማረከ ጦር ስለሚፈታ፣ ድል ሲሆን - በጠላት በኩል ሲታይ የውጊያው ዋና ዓላማ ንጉሡን መግደል ወይም መማረክ ነው:: በንጉሡ ወገን በኩል ደግሞ ጠላት ንጉሡን አገኘሁ ሲል ሊቀ መኳሱን እንዲያገኝ ማሳሳት ነው:: ስለዚህ «ሊቀ መኳስ» መሆን ቀልድ አይደለም:: ለፈሪ ሰው የሚሆንም አይደለም:: :

ተዋበች ከሚስትነቱም ከእቴጌነቱም አልፋ ካሣን በየጦር ሜዳው ጭምር እንዳልተለየችው ሁሉ፤ ሊቀ መኳስ ቤልም ከጦር ሜዳው አልፎ ካሣን በሄደበት አብሮት እየሄደ ይጠብቀው ነበር:: በጉዞ ላይም ይሁን በዘመቻ ላይ፤ ካሣ ድንኳን ውስጥ ሲተኛ ቤል የሚተኛው ልክ እድንኳኑ በር ላይ ነበር:: ጠላትም ይሁን ወዳጅ ቤልን ሳይሻገር ካሣጋ ሊደርስ አይችልም ነበር:: ማለትም፤ በጦር ሰዓትም ይሁን በሰላም ሰዓት (ካሣ ላይ የታወቀ የጠረኛ አደጋ ሊደርስበት በሚችልበት ጊዜም ይሁን ያልተጠረጠረ ሥውር የከሐዲ አደጋ ሊደርስበት በሚችልበት ጊዜም ይሁን) ቤል የካሳ ጋሻው ነበር::

ካሣ የሠው ልክ አዋቂ ብቻ ሳይሆን፣ እነዚያ ልካቸውን አውቆ ያስጠጋቸው ሰዎችም የሱን የሰው ልኩን የሚያውቁለት፤ አውቀውም እስከመጨረሻው

የሚከተሉት፤ ሐይወቱንም ለቆመለት ዓላማ ሙቶ በሙቶ የሚሰጡለት ዓይነት ሰው ነበር።...

ካሣ ሃሳቡ የነሙቶችም ነበሩበት። አስቢያማ ወደ ጉድ ወደ ጭራቅ እንጂ «ሙሉ ሰው» ባልሆን ነበር። ከጉዮስቶቹ አንዱ የጉንደር ከተማ ናሪዎችን በሙሉ በአንድ አጠቃልሉ እንደሰነፍ ማየቱ ነበር። እና ጉንደር ዋና ከተማ እንደ መሆኗ መጠን፤ ለተቀረው አገርም የሰንፍና አርአያ ነው ብሎ መጥላቱ ነበር። ከጉዶስቱ ጋር የተጣመረው ጥንካሬው ደግሞ ከዚህ ስንፍና አድናቸዋለሁ ብሎ ማመኑ ነበር።

«ጉንደር! ጉንደር! ሥራን ብቻ ሳይሆን በሠራኸው መኩራትን ጭምር ሰማስተማር እናትህ ሆድ ድረስ እከተልሀለሁ» አለ ይባላል አንድ ጊዜ።

ካሣ በደከመት ሰዓት ሰልኸኝነቱና ንጾሑ ገነሬለበትና «ይህን ግንብ አንጋጠ እየተመለከተ ነው ጉንደሬ ሰነፍ ሆኖ የቀረው። አቃጥልልኝ!» ብሎ ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር። እሳቱም መቀጣጠል ጀምሮ ነበር። እኛ የማናውቀው ነገር ሀሳቡን አስለወጠውና እሳቱን እንዲያጠፉ አዘዘ።...

...እኔ ቴዎድሮስም፤ መኳንንቶቻቸውም የጦር አዛገቻቸውም ጉንደር ሰንበተው ነበር። ጨሬቃ በሌለበት አንድ ሲሊትም አገር ጤና ብለው አብዥ ምኽ ተኝተው ወይም ሲተኙ እየተዘጋጁ ነበር። እና ታዲያ ምን ይሆንላችኋል? የካሳ ጥላቻው ዛር ወይ አጋንንት ይመስል ድንገት ተነሳበት፤ አፄ ቴዎድሮስ «ተነስ! ጉንደርን ለቶን መሄዳችን ነው» የሚል ዱብዳ የሌሊት ትእዛዝ ሰጡ። ሠራዊቱ ተነሳ። ካሣ እንደ ልማዱ ፊት ፊት ሲሄድ ዮሐንስ በል ደረሰበትና፤ «ጃንሆይ፤ ለመኳንንቶችዎና ለተከታዮችዎ ተወክዬ ነው የመጣሁትና ይናቱዳ ልኝ ልናገር» አለው።

«ተናገር» አለው ካሣ።

«ይህን ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ለብሶ ያደፈጠ ጠላትንስ እንተወው፤ ፈረስዎ ራሱ በዚህ በጭለማ አንድ ትንሽ አውሬ ቢያስበረግገውና ቢወድቁብንስ?»

«እና ምን አድርግ ትሉኛላችሁ?»

«ሲሆን አደረን በበርሃን መሔድ በተሻለ። አለዚያ ግን ጥማሻችን ከፊት ጥማሻችን ከኋላ እንሁንና ጃንሆይ መሀል ሆነው እንጓዝ።»

«ስለተጨነቃችሁልኝ እግዚሀር ይስጣችሁ» አለ ካሳ፤

«ነገር ግን አንድ ነገር እወቁ። ልመራ እንጂ ልመራ አልመጣሁም።» (መሪ እንጂ ተመሪ ልሆን አልመጣሁም።) እሱም ፊት ፊት ሲሔድ፤ እነሱም ሲጨነቁ አደሩ።

ዮሐንስ በል የአፄ ቴዎድሮስ ሊቀ መኳስ በየትኛው ጦር ግዳ ከማን ጋር ሲቆጉ እንደ ሞተ ወይ አልተነገረኝም ወይም ረስቼዋለሁ። (ደቅርታ!)

ስለአሟሟቱም ሁለት ዓይነት «ታሪክ» ሰምቻለሁ።

1. ከወዳጆ የተወረወረ ጦር ካሣን ሲወጋው ሲል አጅቶ ዘለለና ካሣን ተቀ ሰውነቱ ከለለው። ጦሩ በልቱ ወጋው።

2. በጦር ሜዳ ሳይሆን በሰላም ጊዜ አንዱ የመሳፍንት ነጋሪ ለንጉሡ ነጋሪ በቅርቡ የተሠራ አዲስ ዓይነት ጠመንጃ አሳያቸው። እሳቸውም ጠመንጃውን ለመሞከር ሊተኩሱት ከደረታቸው ሲያስጠጉት፤ ቢል «ደቀርታ ጃንሆይ፤ ይፍቀዱልኝና ቀድሜ ልሞክረው» አላቸው። ምነው ቢሉት፤ «አንድ ነገር ቀፈፈኝ» አላቸው። (ጠመንጃውን ሰጡት። ከደረቱ አስጠግቶ ለመሞከር ተኩሰው። ለካ መሣሪያው የተንከል ኖሮ፤ ቃታውን ሲስቡ ጥይቱ የሚተኮሰው በሰደፉ በኩል ወደ ፊት ሳይሆን፤ በሰደፉ በኩል ወደኋላ ኖሮ ቢል የሆዱ ደረቱን በጥይት መትቶ ወደቀ። ይህ ሁለተኛው አይነት አሟሟት አልመሰለህ ስለሆነ ነው እስጡሬዋለሁ።)

በጥይት ይሁን በጦር ያጠራጥረናል እንጂ ቢል በለሱ ንዝቶ የካሣን ሞት እንደምተስት ግን እርግጠኛ ነገር ነው። የቢል ሞት ካሣን አስቆጣው - እንዲያውም በዚያች ሰዓት አሳበደው ልንል እንችላለን። የተቀጋቸውን ሠራዊት ድል ካደረጉት በኋላም ካሣ በጭካኔ አስፈጀው። አንድም ሰው አላስተረፈ። አላስቀረውም።

የተቀበሩና የቢል ጎዘን ተደራርበ ካሣን ከፉኛ ጉዳው። ከሰው ሁሉ ተለይቶ ለብቻው ቁጭ ይልና ዓይኖቹን አንድ ቦታ ላይ ተክሎ ለብዙ ሰዓት ይተክዛል። ወይም በገናውን እየደረደረ ብዙ ብዙ ያንጐራጕራል።

ለብቻው ሆኖ ይጠጣ ጀመር። ከሰካርም አልፎ ብዙ እንዳይሠራና ለምርምር መስራት እስኪያቅም ይጠጣ ጀመር። ግን የካሣ ዓይነቱ ጠንካራ ሰው ድር ድር ምርኩዙን ወድያ አሽቀንጥሮ መጣሉ አይቀርም። ካሣም ከአንድ ሰሞን ወዲ በኋላ መጠጡን እርግፍ አርጎ ተወው።

[illegible]

## ካሣና እነ ገብርዬ

«ካሣና ገብርዬ» ስንል - ሰው ካልቆሽ በነተቀር ካሣን እንደሚያውቀው እናውቃውለና - ገብርዬ፣ ገሰሞ፣ አለሜ፣ እንግዳና ሌሎችም በርካታ ያሉ ጓደኞች፣ ካሣን የተከተሉት ነገ እንደሚነግስ እንዲ ሲያውቁ፣ ሲጠራጥሩ በሚደቸትበት ሰዓት መሆኑን እንርሳ። ይሁንና ተከተሉት። ለምን ተከተሉት?

ዘመኑ መሳፍንት ለኢትዮጵያ የጭለማ ሰዓት መሆኑን በናስታውስ - ካሣን የተከተለች ሽማ፣ ኩራዝ፣ ወይም ሚስ መሰይ፣ ከጭለማ የተሻለ መብራት ብቻ፣ የያዘ በመሆኑቸው መሆን አለበት። እኛ እንዲህ እናስባለን እንጂ እነሱ ግን የተከተሉት እንደኛ ከሩቅ በሐሳብ ተመርተው ነው። «ካሣ» ስለሆነ ብቻ ነው።

ለጥቅም ብለው ግን አልተከተሉትም፤ በሁነኛ የምናረጋግጠው ነገር ግን

መጨረሻ ላይ እንዳልተሳካለት የስታውቅ ነበር። ያኔ ይከዱት ወይም ጥለውት ይሄዱ፣ ወይም ለጠላቶቹ ይሸጡት ነበር። እነሱ ግን ድል የማድረግ ተስፋ እንደሌለው ካወቁም በኋላ አንድ በአንድ እስኪወድቁ ድረስ ተዋጉለት። ለምን? እዚያ ላይ ነው ምስጢሩ፤ እዚያ ላይ ነው ተአምሩ። እና «ነገሩ ገብቶሀል ወይ? ምስጢሩን ታውቀዋለህ ወይ?» ብትለኝ፤ እንኳን እኔ እዚህ ሆኜ ሳሰላስለው ይቅርና፤ እነሱም እዚያ ሆነው ሲኖሩትና ሲሞቱ ምስጢሩ የገባቸው አይመስለኝም። ካሣም ራሱ ተአምሩን ኖረው እንጂ ያወቀው አይመስለኝም።

ስለዚህ፣ በማላውቀው ገብቼ አልፈትፍትና፤ ሲወርድ ሲዋረድ ደርሶኝ የሰማሁትን አፈ - ታሪክ በአፈ - ታሪክ ደንብ አንድ በአንድ (ማለት መልክ ለማስያዝ ወይም ትርጉም ለመስጠት ሳልሞክር) ለአንባቢ ላስተላልፍ። እነሆ!

እነ ገብርዬ ከካሣ ጋር ዘላቂ ግንኙነታቸው እሱ ከነገሰ በኋላ አልተለወጠም ታዛዥነት ሳይቀነስ ጓደኝነት ነበራቸው።

ለነሱ ከአፄ ቴዎድሮስ ይበልጥ ጉልቶ የሚታያቸው ያን የገማውን ስጋ በልተው ሲማማሉ የነበረው ካሣ የጉበዝ አለቃ ነበር። ስለዚህ በምክር ሰዓት «ይህን ያልናቸው እንደሆነ ጃንሆይ ይከፋቸዋል፤ ይደናግጣሉ። ይቀየሙናል» ሳይሉ፣ የመሰላቸውን በቀጥታ ነበር የሚናገሩት።

ጓደኞቸው በመሆኑ ያስኩሉት ነበር። ... አፄ ቴዎድሮስ ስራም ብስጭትም እየበዛባቸው እየተጻከሙ ሄዱ። ባለሟሎቻቸው ተቸገሩ። «እኝህ ሰውዬ አንድ ሁለት ዓመት ካላረፉ በሽታ ላይ ይወድቃሉ። ልጃቸውን መሸሻን ይዘን ገለል እናድርጋቸውና አርፈው ይቀመጡ እንበላቸው»።

«ከዚያ በኋላ እንመልሳቸዋለን» ተባባሉ። «ነገሩስ ባልከፋ፤ ግን ገብርዬ ካልተጨመረበት ጉዳዩ አይሳካም» በማለት ገብርዬን ጠየቁት። «ጨርሶ ለመሻር እስካልሆነ ድረስ፣ እሺ» አለ።

አጤ ቴዎድሮስ ምን እንደተማከሩ ደረሱበት። መሳፍንቱንና መኳንንቱን ሰብስበው፣ እመሀላቸው አንፈራጠው ቆሙና፣

«እኔን ለማግለልና መሸሻን ይዞ ለመነሳት ዶልታችኋል ማለት ስለሰማሁ ነው የሰበሰብኳችሁ»። አሉዋቸውና፣ ገብርዬን እያዩ፣ «አይደለም ገብርዬ!» አሉት።

«ጃንሆይ፣ እርስዎን ለመጉዳት ሳይሆን «እረፍት እንዲያገኙ» ብለን ነው»

«አንተም? ገብርዬ? አንተም!» አለው ካሣ።

ገብርዬ ተፀፅቶ ከካሣ እግር ወድቆ ይቅርታ ለመነ።

«አዬ! ገብርዬ፣ አንተኮ የኔ ገብርዬ ነህ። መሸሻ ቢነግስ የራሱን ገብርዬ ነው የሚፈልገው» ብሎ አሰናበታቸው።

የታሰረም የለ፣ የታዘለም የለ፣ ጉዳዩም ሁለተኛ ተነስቶ አያውቅ። ካሣም

በተባርዩ በጭራሽ አልተለወጠበትም።

ካሣ ስንቢያ በመጀመሪያ ላይ አበረውት ለተነሱት ታማኝ ነበር።... አንድ ጊዜ ገለሞ ደምቢያን እንዲወጋ ተላከ። (ደምቢያ የግራር አገር ነው።) አንድ ጊዜ ጦርነት ገጠመ ሸሸ፣ ግን አሬጋዊት መጣ፣ አረሆ ታድያ ሲተሳጣው፣ ንጉሱ ፊት እንዲህ ስትል ዘፈነች፣

«አይሸሽም ሲሉ ገለሞ ሸሸ፣

የደምቢያን ግራር እያበላሸ»

ካሣ ታዲያ ዓይኛው ስለተሰደበበት የንጉሥ ክብሩን ረስቶ ብድግ አለና፣ «አሰ! በዙበት እንዲ ገለሞስ አልሸሸም!» አለ።

አፄ ቴዎድሮስ ለንጉባርዩ ተገቢ ወይም ትክክል የማይመስላቸውን ነገር ካደረጉ ወይም ሲያደርጉ ካዩ፣ እነሱ ያለ አንዳች ፍርሀት ለካሣ ይነግሩታል።

አሁንም በየትኛው የጦር ሜዳ እንደሆነ እንጃ፣ አፄ ቴዎድሮስ ሲመለከቱ ዋግ ስዩም ተድላ ከሁሉ ቀድሞ ወደ ውጊያው ሲገባ ያዩታል። እና ውጊያው መሀል ገብተው እየተዋጉም ይህን ዋግ ስዩም በአይን ይከታተሉታል። ሀይለኛ ጀግና መሆኑን ይገነዘባሉ።

ከዚያ በኋላ ዋግ ስዩም ተድላ ከቤተ መንግስት እንዳይለይ ተደረገ።

«አገሬ ደርሼ ልመለስ» ቢል፣ «ቤተሰቦቼ ናፈቁኝ» ቢል ጃንሆይ ፈቃድ ከለከሉት። እሱ ፈቃድ እየለመነ፣ እሳቸው እየከለከሉት ሶስት አራት አመታት አለፉ። እንጉባርዩ ትዕግስታቸው አለቀ። ተናገሩ።

«ዋግ ስዩም ተድላ ጃንሆይም እኛም ደጋግመን በጦር ሜዳ አይተነው የምናውቀው ጀግና ነው። እና ደጋግሞ «አገሬ ደርሼ ልመለስ» ሲል ሲለምን ጃንሆይ ያለ አንድ ምክንያት «እምቢ» አሉት። ለምን?»

«ፈራሁት! ከማለት የበለጠ ምን ምክንያት አለ?» አላቸው ካሣ ባጭሩ። መይሳው ካሣ ከጀግኖቹም ሀቀኞቹ! ምነው አይከተሉት! ሟችና ተዋጊ እስከሆነ ድረስ ምነው ሰው አይዋጉለት! አይሞቱለት!

«ምነው እስከ ሞት ድረስ - እርግጠኛ፣ ዓይኑን አፍጥጦ የሚመጣ ሞት ድረስ - - ምነው? እስከዚያ ድረስ ይዋጉለታል» ቢሉ... «ቀድመውትም ቢሞቱ እሱም እስከ ሞት ድረስ እንደሚዋጋ እርግጠኛ በመሆናቸው።» ይላል።

በመጨረሻ ጦርነት፣ ካሣ መቅደላ አምባ ላይ ሆኖ ሲያዋጋና ሲዋጋ፣ መልእክተኞች ተራ በተራ እየመጡ፣ «እገሌ ወደቀ» ይሉታል።

«ጠፀቀ?» ይልና ወዲያ - ንጹቱን አምቆ ...

በዚያች በጓመስ መሀል ሰዓት የኮማውን የውርደት ስጋ አብረውት ተምሰው «እስከ መጨረሻው የማሉት የልብ ጓደኞቹ በየፊናቸው፣ በየሰዓታቸው መሞታቸውን፣ ግን ሁሉም ለዚያው ዓላማ መሞታቸውን፣ ሲሰማ ሲያዝን፣ ሲሰማ፣ ሲናደድ ቆየና፣

«ፊታውራሪ ገብርዬ ወደቁ» አለው መልክተኛ።

«ገብርዬ ሞተ?» አለ ካሣ።

«አዎን ሞቷል»

«ሰኔ አዚጋጅቶ ሲጠብቀኝ ነው» አለና ካሣ - ሽጉጡን ጠጥቶ ሞተ።

«የተቀረው ዝምታ ነው» - ሼክስፒር እንዳለው።

የጉጃምዋ ወይዘሮ ምንትዋብ አሉት እንደሚባለው ግን፣ የተቀረው ዝምታ ሳይሆን መመስከር ነው። እና ወይዘሮ ምንትዋብ አስራ ሦስት ወይም አስራ አራት ዓመት ሙሉ የጠሉትን፣ የንቋሸሹትንና የሰደቡትን ካሳ ኃይሉን ሬሳውን አልለቅ ብለው እየተጠመጠሙበት ወደ መቃብር ሲከተሉት ምን ብለው መሰከሩ?

«የትግሬንም ንጉስ ሲንቁ ሲንቁ»
የላስታንም ንጉስ ሲንቁ ሲንቁ
የጉጃምን ንጉስ ሲንቁ ሲንቁ
የሸዋንም ንጉስ ሲንቁ ሲንቁ
ወንድ ያለ ራስዎ ገድለውም አያውቁ።

ይህ አፈታሪክ ልብ ወለድ ቢሆን ኖሮ እዚህ ላይ ማብቃት ነበረበት። የካሳ ቴዎድሮስ ህይወት ግን ኪነት ሳይሆን ኑሮ በመሆኑ የማይያያዙ ጥቂት ነገሮችን ከዚህ በታች አሰፍራለሁ። እንደ ምራቂ እንቁጠራቸው።

1. ሚስዮናውያን በብዛት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር። አፄ ቴዎድሮስ ሰበሰቧቸውና «ምን ጥበብ ታስተምሩናላችሁ?» አሉዋቸው።

«ቃለ - እግዚአብሔርን»

«ስንቱን ክርስቲያን ያልሆነ አገር አልፋችሁ፣ ከናንተ ቀድሞ ክርስትናን ለተቀበለ ህዝብ ምን ቃለ እግዚአብሔርን ታስተምሩታላችሁ? ንሳ እስሜ፣ እዚያው ጆልባቸው ድረስ ሽኝልኝ። የቅድስት አገሬንም ትቢያ ይዘው እንዳይሄዱ መጫሚያቸውን አራግፍልኝ።»

ብዙዎቹ ሚስዮናውያን ተባረሩ። አንዳንዶች ግን «መድፍ እንስራለን» ስላሉ ተዋቸው። እንፍራዝና ጋፋት ላይ አስማሩዋቸው።

2. እቴጌ ተዋበች ከሞቱ በኋላ አፄ ቴዎድሮስ የደጃዝማች ውቤን ልጅ ወይዘሮ ጥሩ ወርቅን አገቡ።

ተዋበች ካሣን ታግዘውና ታስደስተው የነበረውን ያህል ጥሩወርቅ

ታስቸግረውና ታበሳጨው ነበር። ትደፍረውም ነበር።

አንድ ቀን ካሣ በእልፍኝ ጋቢ ብቻ አጣፍቶ (ከጋቢው ስር ግን እርቃን ሲጋውን ሆኖ) ከገብርዬ ጋር ሲወያይ፣ ጥሩ ወርቅ መጣችና ታመናጭቀው ጀመር። ታገላት። ስድብ ጀመረች። ገዛም አላት። በመጨረሻ አንድ የማይሆን ስድብ ስለተሳደበች ገብርዬ «በልጭ!» አለበትና ሰይፉን መዘዘ። አንገቷን ሊቀላት ክንዱን አነሳ።

ካሳ ቀድሞት እጁን ያዘው። ይህን ሲያደርግ ጋቢው ከላዩ ስለወደቀ እርቃን ሲጋውን ቆመ።

«ተው! ተው! ገብርዬ» አለ ካሣ፣ «አጦር ሜዳ ታጥቄ እምታውቀኝ አንተ ነህ። እሷስ የምታውቀኝ ሱሪዬን አውልቄ ነው።»

3. አንድ ቀን አፄ ቴዎድሮስ ሲተክዙ ቆይተው መኳንንቱን፣ «እረ ለመሆኑ፣ ከመካከላችሁ ሚስቱን ገዝቶ የሚኖር ማነው?» ሲሉ ጠየቁ።

«እኔ!» አለ አንዱ መኮንን።

«እንዴት አድርገህ?» አሉት አፄ።

«እንዲያው ገና ሲያት፣ አቃውራታለሁ»

«ተው፣ ተው፣ ተው። ሌላስ?» አሉ አፄ።

«እኔ!» አለ ሌላው «ገና ስንተያይ፣ አኪኪ ዘራፍ! እልባታለሁ።»

ሌሎችም ልዩ ልዩ ዘዴያቸውን ተናገሩ። አፄ ሁሉንም «ከንቱ ነው» አሉ። በመጨረሻም አንዱ ባላገር ብጤ፣ «እኔ ነኝ! ሚስቴን ገዝቼ ምኖር» አለ።

«እንዴት አድርገህ?»

«እንዳሻሽ ብዬ»

«አንቺ በውነት ገዛሽ!» አለ ካሣ።

4. አፄ ቴዎድሮስ ሥጋ ደዌኛን እየሰበሰቡ ያቃጥሉ ነበር። ደብረ ታቦር ጉጆ ሲሰራ ያድራል። ቀን ደዌኞቹ እጉጆው ውስጥ ይ[illegible]ሩና እሳት ይለቀቅባቸዋል። (ካሳ ከሞከራቸው ብዙ ስራዎች አንዱ ሥጋ ደዌን በዚህ ዓይነት ከምድረ ኢትዮጵያ ማጥፋት ነበር።)

አንድ ቀን ዝናብ እየጣለ ካሣ ከሩቅ በመነፅር ደዌኞቹ ወዳሉበት በኩል ሲመለከት አንድ ትንሽ ልጅ ከዝናቡ ለመጠለል ወደ አንድ ጎጆ ሲገባ አየው። ልጁ ወደ በሩ መጣ አሰና እናቱን በእጁ ምልክት «ነይ! ተጠለይ» አላት።

ካሣ ነገሩ ከነከነውና ጉዳዩን ለማጣራት በፍጥነት ወደ ነሱ ሄደ።

«ልጁ ምን አለሽ?» ብሎ ቢጠይቃት «ያው እሱ እንደመሰለው ነው።» ለነሱ መቃጠያ መሆኑን ባለማወቁ መጠለያ አደረገው ሳይፈራ።

ካሣ ምርር ብሎት «ወይ ለዚህ ሕዝብ ልብ አትሰጠው፣ ወይ እኔን

አትገድለኝ። ምን አረግኩህ? አንተ አምላኩ፡» አለ።

ተሰብስበው የነበሩትን ደቂቆች ማረቻቸው። ከዚያ ወዲያም ደቂቆችን ማቃጠሉን ተወው።

5. አባ ቴዎድሮስ ከቤተ ክህነት ጋር ተጠማምደው ነበር። ከአንድ ቄስ ጋር የሆነ ክርክር ይዘው ሳለ፣

«እረ ለመሆኑ» አሉት፣ «ታቦት አጠገብ ስትደርስ ጥምጥምህን የምታወልቅ ለምንድነው?»

«የእግዚአብሔር ማደሪያ በመሆኑ»

«እኔስ እግዚአብሔር የቀባኝ ንጉስ ማደሪያው አይደለሁም?»

ቄሱ ጥምጥማቸውን ሲያወልቅ ሲል «ተወው! ተወው!» አሉት። «እንዲሁ መልካም ጠባይ ላስተምርህ ብዬ ነው።»

መቅደላ ላይ ስጋ ወደሙ አስመስለው የዘሆን ሀሞት ሲያጠጡዋቸው ሲሉ፣ አባ ቴዎድሮስ «ክርስቶስ ለራሱ ተቀብሎ ነው ያቀበለ» አሉዋቸው፣ «ዘሉ! ራሳችሁ መጀመሪያ ተቀበሉ።»

ቄሶቹ ሀሞቱን ጠጥተው ሞቱ።

ካሣ በዚህ ተናዶ እዚያ ያሉትን ካህናት ሁሉ ቤተልሔም ውስጥ አጉሮ ዘግቶባቸው ሄደ።

እሳት ተነሳ። (በትርምስምሱ ይሁን ወይስ እነሱ «ይታዘንልናል» ብለው ያቀጣጠሉት አይታወቅም።) እየገሰገሰ መጥቶ አሽከር ለንጉሡ ይነግራል።

«ታድያ ምን ይደረግ?» ይላል ካሣ።

«እናውጣቸዋ!»

«እግዚአብሔር ወርዶ ሲፈርድ አትፍረድ! ነው የምንለው?» አለ ካሣ።

ካህናቱ በቃጠሎው ሞቱ።

6. አባ ታጠቅ ካሣ ከደጃዝማች ውቤ ጋር ለመዋጋት ሠራዊቱ ወደሰሜን ሲጓዝ «ዘረፋ የለም» ብሎ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር።

በጉዞ ላይ እንዳሉ «አቤት! አቤት!» የሚል የሴት ድምፅ ተሰማ። ሹማምንቱ የነገሩን ጠባይ ያውቁታል። «አቤት!» ያለ ሰው በቀጥታ ወደሱ ካልቀረበ እንደሚቀጣቸው ያውቃሉ።

«የማንን እንባ ልንጠብቅ የመጣን መሰላችሁ?» ይላቸዋል።

«ደካማውን አቤት ሲል ካልሰማነውማ ምኑን ሰው ሆንነው?»

ስለዚህ «አቤት!» ያለችውን ሴት ወድያው አቀረቡለት። ጉስቁል ባልቴት ናት። «ተናገሪ!» ስትባል።

«ባል የሌለኝ ድሀ ባልቴት ነኝ» አለች።

«ያለችኝን አንዲት ዶሮ ይኸ የርስዎ ወታደር በላብኝ። አሁን እነዚህ የኋን ጫጩቶች ምን ላድርጋቸው?»

በሁቴቶ ሽፍንው የነበረውን ስትገልጠው፣ ትርሜት ውስጥ አንድ አስራ አምስት የሚሆኑ ጫጩቶች - በትርቡ የተፈለፈሉ።

ካሣ ቆጣ ይልና፣ «አንቺ ቆማጣ ቆመጥማጣ!» ይላታል ባልቴቲቱን፤

«እንኪን ዶሮሽን ላምሽን ለምን አይበላም ላንቺ ክብርሽ ነው!»

ወደ ወታደሩ ዞር ይልና በፈገግታ «ይቺ አሮጊት ትቃጥራለች ወይስ እውነት ዶሮዋን በልተሃል?» ይለዋል።

«በልቻለሁ ጌታዬ» ይላል።

«እንግዲያው እውነታቸውን ነዋ እሚጌቱ እነዚህ ጫጩቶች ከናታቸው ተለይተው ሊያድጉ ስለማይችሉ ከናታቸው ቀላቅላቸው»

«እሺ አልገባኝም ጌታዬ»።

«በላቸው እዚሁ አይኔ እያየ በላቸው! ደሞ በሞት ያለመቀጣትህ ተመስገን በል።» ወታደሩ እዚያው ቆሞ ጫጩቶቹን በላቸው፡

ካሣ ለባልቴትዋ ለመጦሪያ የሚበቃ ንብረት ካሳት።

«መይሳው ካሣ! ዘመድ ከዘመድ አደባላቂ!» የተባለው በዚህ ነው።

7. «ሲባስቶፖል» የተባለውን ትልቁን መድፍ መቅደላ ተራራ አቀበቱን እየገፉ ሲያወጡ፣ አፄ ቴዎድሮስ ከተራው ወታደር እኩል ላብ በላብ ሆነው ሲገፉ ያየ አንድ ወታደር ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ይባላል።

8. የመቅደላው ጦርነት ሊያልቅ አቅራቢያ ጄኔራል ናፒየር ለአፄ ቴዎድሮስ «ደሱ የኛ ነው እጅዎን ይስጡ!» ሲል ላከባቸው። የካሳ መልስ እንዲህ የሚል ነበር፦ «ለሰንደል ላይ የነጭ አህያ እጅ አያርፍም። እሳት ነው ያቃጥልሀል!» ካሣ - ቴዎድሮስ እንዲህም እንዲያም አይነት ሰው ነበር።

ጥቅምት 1976

# ❧ 3 ☙

# ማሀትማ ጋንድሂ

# *Mahatama Gandhi*



የጋንድሂ መንፈሳዊ ቅድመ አያቱ ማሀቪራ ሳይሆን አይቀርም:: ማሀቪራ በስድስተኛው ምዕት ከክርስቶስ በፊት ማለትም በጊታ ቡድሀ ዘመን የኖረ የጃይን ሃይማኖት ተከታዮች ሀያ አራተኛና የመጨረሻ ነብይ ነው:: ስሙም «ታላቁ ጀግና» ማለት ነው:: (ሂንዱዊዝም ቡድሂዝም ጃይኒዝም - እነዚህ ሶስቱ ናቸው በህንድ አገር የበቀሉ ታላላቅ ሃይማኖቶች::)

ማሀቪራ የንጉስ ልጅ ነበረ:: አግብቶ አንዲት ሴት ልጅ ከወለደ በኋላ፣ እድሜው ሰላሳ ዓመት ሲሆን ዓለም በቃኝ ብሎ መነነ:: ለአስራ ሁለት ዓመት ሰውነቱን በፆምና በሌሎችም የዚያን ጊዜ ዘዴዎች እያጉሳቆለ እንዳይሞት ያህል ብቻ ለምኖ እየበላ ሀቅን ሲፈልጋት ኖረ::

ማለትም «ማን ነኝ? ከየት መጣሁ? ወዴት እየሄድኩ ነው?» ለምትለው እንቆቅልሽ ጥያቄ አጥጋቢ የምትሆን መልስ ፍለጋ ሲጓዝ በእኛ አገር እንደሚታመነው በነሱ አገርም «ነፍስን ለመጥቀም ስጋን - መጉዳት» የሚል እምነት ነበር አሁንም አለ፣ የነገን አናውቅም:: ይህ የአላማ ፅናት የመንፈስ ጠንካራነት ሀቁቱ ዘንድ አደረሰው:: ተገለፀችለት:: ከዚያ ሲያስተምራት ኖረ:: (ለጋንድሂ ታሪካችን የሚያስፈልገንን እንቀንጭባለን::)

«አሂምሳ» ሲተረጎምም ፍጡራን ሁሉ ወንድማማቾችና እህትማማቾች ስለሆኑ እንዳንጎዳቸው ጥንቃቄ መውሰድ አለብን:: ስለዚህ መሬት መሬቱን እያየን እየተጠነቀቅን ነው:: ትንኟን ቂጫጭ፣ ትል የመሳሰሉትን ትንንሽ ሰዎች የለበሱትን በእሳት፣ በዋጋ ግን እኩያዎቻችን የሆኑትን ነፍሳት ጨፍልቀን እንዳናጠፋቸው እየተጠነቀቅን ነው:: እንደዚሁም ወደ ውስጥ ስንተነፍስ ሳናጠቃቸው ትንንን እና ከስም ያነሱትን ኢምንት በራሪ ነፍሳትን ውጠን እንዳናጠፋቸው አፍንጫችንን በስስ ሻሽ እንሸፍናለን ሻሹ እንደ ወንፊት ያገለግላል - አየሩ ይገባል ነፍሳቱ ውጪ ይቀራሉ:: አሂምሳ! እንደ ነፍሳት ያሉትን ኢምንት ፍጡራን ሳናይ ከምግባችን ጋር ልንበላቸው ስለምንችል፣ ከመሸ በኋላ መብላት ክልክል ነው (ይህ እንግዲህ በሻማና በጧፍ ዘመን ነው - ኤሌክትሪሲቲ ሌሊቱን እንደ ቀን ሳያበራው በፊት::)»

በምድሪቱ ላይ የሚንፏቀቁ የሚርመሰመሱትን ጥቃቅን ፍጡራን - እንዲሁም መሬት የሚኖሩትን - ሳናይ እንዳናጠፋቸው ለመጠንቀቅ ስንል፣ እርሻ ማረስን አትክልት መትከልን እርም ብለን ትተነው በንግድ ዓለም ተሰማርተናል:: በተጨማሪም ወይን ጠጅ ማር፣ ፍራፍሬ ስራስር እርማችን ነው::

ሲሶቹን ፍጡራን እንዳንጎዳቸው ከመጠንቀቅም አልፈን፣ ሲቻለን እንከባከባቸዋለን:: አንድ የጃይን ሃይማኖት ተከታይ ሲሞት አይቀበርም:: እንደ ሲሶቹ ሕንዶችም ሬሳው አይቃጠልም:: እንግዲያማ? በጣም ከፍ ተድርጎ የተሰራ፣ ስሩቱ ግን የጎጆ የሚያክል ግንብ አለ:: እላዩ ላይ አንድ ሠራተኛ አለ:: ቀንጨራ ቢላዋ መሳዮች ናቸው መሳሪያዎቹ:: ስራውስ? የጃይንን ሬሳ መበለት፣ ልክ እንደ ሉካንዳ ቤት ማለት ነው:: ሥጋውን እየቆራረጠ እየበለተ እየበለተ ለአሞራዎች መጋበዝ:: እነሱም ለምደዋልና እድሜ ለማህቢራ የእለት ሲሳያችንን ለሚሰጠን እያሉ እየንገበገቡ ናቸው የተለመደው ብልት እተለመደው ስፍራ አስቀምጦ ቅላቸው ድረስ:: ከዚያ ሽው ብለው ይወርዱና ላፍ አርገውት ይበርራሉ - ማህቢራን እያመሰገኑ:: የኛ ጉረምሶችም እንዲህ ሳይሉ አይቀሩም፤ በጭፈራ::

«ያ ማህቢራ! ያ ማህቢራ

እየበላ

በሰው ላሞራሉ»

ፍጡራንን እንዳንጎዳ መጠንቀቅ:: በድርጊት ብቻም አይደለም:: እንዳንጎዳቸው የምንጠነቀቀው በንግግርም (ስድብስ እርግማንስ) በሃሳብም:: ድርጊት... ንግግር... ሀሳብ... እነዚህ ሶስቱ የተያያዙ ናቸውና::

(«አሂምሳ» በዚያኛው ክፍለ ዘመን በፖለቲካው ትግል ዓለም ጋንዲ መሪያው ሲያረጋውስ እንዴት ሆነ ይሄ አሂምሳ?...)

... ማህቪራ መጀመሪያ አንድ ልብስ ብቻ ነበረው። ከዚያም ራቁቱን መሄድ አመጣ። መጀመሪያ የጀይን ሃይማኖት አትብሉ የሚለውን ከመብላት ይቆጠብ ነበር። ከዚያም ምንም ምንም አልበላም አለ። ሰልክሃና ሪበመ (Sallkhana) ማለትም ቁጭ አለና ከንግዲህ አንድ መብላት የለም ብሎ ወሰነ በውሳኔው ፀንቶ በራብ ሞተ (እኔም በመጀመሪያ ይህንን ማመን አስቸግሮኝ ነበር። ብዙ ጊዜም የማስብበት ነው። ለምን በገዛ ፈቃዱ በራብ ሞተ? ምናልባት ድንገት ወለል ብሎ ታየው ይሆን እንዴ፣ እፅዋትም እንደኛው ፍጡራን መሆናቸው? እራሱን ለማኖሪያ ሌላ ፍጡር ላጠፋ? አይሆንም! «አሂምሳ!» ምናልባት?)

አንዳንዴ ለራሴ እንዲህ እላለሁ? ጋንዲሂ ማለት ማህቪራ እንደገና ተወልዶ ይሆን እንዴ? ማን ይከለክለዋል? ሕንዶች እንደሆኑ እየተመላለሱ መወለድ ደንባቸው ነው።

ሞሀንዳስ ጋንዲሂ በቦምቤይ ከተማ ለሁለት ዓመት ጥብቅና ሞከረ። ያን ያህልም አልተዋጣለትም። ከዚያ ለስራ ወደ ደቡብ አፍሪካ ተላከ፣ እሱ ሳያውቀው ከዕጣ - ከፋሉ ጋር ቀጠሮ ነበረውና።

ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት ሲገባ «ጥምጥምህን አውልቅ!» ተባለ። በጥፊ የመቱት ያህል ደነገጠ። ጥምጥምክ አውልቀው የሚባል አይደለም። እንኳን ፍርድ ቤት መቅደስ ቢገቡ አውልቅ አይባልም። አንድ በሉልኝ።

አንድ ቀን ማታ ጋንዲሂ አንደኛ ማዕረግ የባቡር ትኬት አስቆረጠ። ጥቂት ቆይቶ ቲኬት መርማሪ መጣ። ህንድ ደፍሮ አንደኛ ማዕረግ ቦታ ገብቶ ተቀመጠ! አስወጣልኝ! ገፍትረው አስወጡትና ባቡሩ መንገዱን ቀጠለ። ጋንዲሂን በጨለማው በብርድ እየተንቀጠቀጠ ትተውት ሄዱ። ሁለት አትሉም?

ሁኔታዎች እንዲህ ሊቀጥሉ አይችሉም። ግን እንዴት እንለውጣቸዋለን? በትጥቅ ውጊያ ሊሆን አይችልም መቼስ። «አሂምሳ!» ስርአቱ ነው እንጂ. ግለሰቦች ጠላታችን አይደሉም። ታጥቀን ስንዋጋ ደሞ የሚሞቱት ግለሰቦች ናቸው። ስለዚህ...

...1894 (በፈረንጆች) ጋንዲሂ «የናታል ህንዳዊ ኮንግረስ ፓርቲ» የሚባል ድርጅት መሠረተ። (ናታል የደቡብ አፍሪካ አንዷ ክፍለ ሀገር ነው) እነሆ ዳዊት ተነሳ! ጎልያድን ምን ይዋጠው? (በተለይ ለወጣት ደራሲያን በትንሹ። የመጨረሻዎቹ ቃላት ትርፍ ኮተት ናቸው፣ ምክንያቱም የጋንዲሂን ወይም የማህቪራን ወይም የኢየሱስን ያህል ድንቅ ታሪክ ስትተርክ ቃለ አጋኖ ወይም ቃለ አድናቆት መጨመር ማርን የበለጠ ለማጣፈጥ ስኳር እንደ መጨመር ያህል ይሆናል።)

ጋንዲሂ ለእንግሊዝ መንግስት ሁለት ጊዜ ውለታ ውሎለታል። በ[illegible]

አፍሪካው ጦርነት (የሆላንድ ተወላጆች እንግሊዝ አይገዛንም! የራሳችንን ሀገር ነፃ እናወጣለን ብለው የተዋጉለት) እና እንደዚሁም በዙሉ አመፅ ጦርነት ጊዜ ጋንዲ ብሪቲሽ ራጅን (የእንግሊዝ አገዛዝን) ደግፎታል። የምን ጦር ነው እሱ? አሂምሳ! የተዋጊዎቹን ቁስለኞች የሚያክም የአምቡላንስ አገልግሎት አደራጀ።

በ1894 ጋንዲ Indian Opinion (ህንዳዊ አስተያየት) የሚባል ጋዜጣ ማሳተም ጀመረ። ዓላማው - የደቡብ አፍሪካ ኗሪ ህንዶችን መብቶች ለማስከበር።

በ1896 የትራንስቫል ክፍለ ሀገር መንግስት እዚያ የሚኖሩ ሕንዶች ሁሉ ወደ ሰፈራቸው ፖሊስ ጣቢያ እየሄዱ የጣት አሻራቸውን እንዲያስመዘግቡ የሚል ህግ አወጀ። (ወንጀል የፈፀመ ሰው ብቻ ነው አሻራው እንደዚህ የሚመዘገበው።)

ሞሀንዳስ ጋንዲ ሁለት ሺ ወንዶችና ሴቶች ህንዶችን በተቃውሞ ሰልፍ አስወጣቸው። ያ ህገ - ወጥ አዋጅ ተሻረ። ድል አንድ።

በሚቀጥሉት ስምንት ዓመታት ጋንዲ ያለ ትጥቅ ትግል - በሰላማዊ እምቢታ ብቻ - የደቡብ አፍሪካን ህንዶች መብቶች አብዛኛዎቹን ለማስከበር ቻለ። ይሄ ትግል እየተካሄደ እያለ፤ ሞሀንዳስ ጋንዲ የደቡብ አፍሪካን ህንዶች ኑሮ ሲያሻሽል የራሱን የግል ኑሮም እየለወጠ ነበር። በየተራ ቆሻሻ ጠራጊ፤ ጫማ ሠሪ፤ ገበሬ፤ የህትመት ሠራተኛ እየሆነ ሠራ። በመጨረሻም ጥብቅናውን ተወውና ዓለም በቃኝ ብሎ በድህነት ለመኖር ወሰነ - ጀመረ - ቀጠለ - ፈፀመ - እስከ እለተ ሞቱ።

በ1915 ወደ አገሩ ሲመለስ፤ ዝናው ቀድሞት ደርሶ ተናኝቶ ኖሮ የጀግና አቀባበል ተደረገለት። ራቢንድራናት ታጎር የተባለው የሕንድ ታላቁና ተወዳጁ የመንፈሳዊ - ኪነታዊ መፅሀፍት ደራሲ «ማህተማ ናቸው» ሲል አወጀ። ትርጉሙም «ታላቅ ነፍስ» ማለት ነው። ማህተማ ጋንዲ ሆኖ ቀረ።

በሚያዝያ 1915 ማህተማ ጋንዲ የመጀመሪያውን ሳትያግራሀ አሽራም (Satyagraha Asharam) መሰረተ። «ከሀቅና ከፍቅር ወይም ከሰላማዊነት የሚመነጭ ኃይል ገዳም» ማለት ነው። መስራች አባላት ሀያ አምስት። ዓላማቸው - «ሀቅን፣ ፍጡራንን ያለመጉዳትን፣ ግብረ ስጋ እርም ብሎ መተውን፣ ፍርሀት አልባ መሆንን፣ ራስን መቆጣጠርን» እነዚህን እሴቶች (ክቡር ዋጋ ያላቸውን) በነብሳቸው ውስጥ እየኮተኮቱ ማዳበር። ይህ የግለሰቡ ነብስ ዓላማ ሲሆን የህብረት አላማቸው ደግሞ፡-

ሀ. የሹድራ ቋሚ መደብ አባላት ሥራቸው ለሌሎቹ ሦስት የተከበሩ ዘላቂ መደቦች የሚሆኖቱ ሆኖ፣ እነሱን ደግሞ በእጅ መንካት እንኳ ያረክሳል ሲባልና ድርጊት ሲሠራ ቆይቷል። ከእንግዲህ ግን ሹድራም ሰው ነው። ይህ እምነታችን በ… ሰው ሕንድ እስኪሰፍን እንታገላለን - ዱላ ሳናነሳ።

ለ. በእጅ የተፈተለና የተሸመነ ብቻ ነው የምንለብሰው (የበርሚንግሀም ኢንግላንድ ፋብሪካዎች የሚልኩት ልብስ የህንድን ፈታይና ሸማኔ እንጀራ እየዘጋ ነበርና ነው::)

ሐ. ለጉሮ የሚያስፈልገንና በሀገራችን የማይገኝ ካልሆነ በስተቀር የውጭ እቃ አርማችን ነው::

ለሚቀጠሉት ሁለት ዓመታት ማህትማ ጋንድሂ ሕንድን እየዞረ ጉበኛት:: እንግሊዝ በአብዛኛው ለራሱ ሲል ይሁን እንጂ፣ ህንድን ከዳር እስከ ዳር ሀዲድ ዘርግቶባታል:: ገና ለብዙ ዘመን እዚህ እኖራለሁ ብሏል:: ማህትማ ጋንድሂ ይመጣል ብሎ አስቦ አያውቅ:: አለልህ ጋንድሂ፣ ገና ሳትቀናቀነው የሚደርስብህ!

በእንግሊዝ ባቡር እየተዘዋወረ አገሩን ከተዋወቃት በኋላ በ1917 (በፈረንጅ) አንድ የቡሀር (ክፍለ ሀገር) ገበሬ የቻምፓራን አካባቢ እንዲጉበኝና አምራች ገበሬዎችን አሰቃቂ ድህነት እንዲያይላቸው ጋበዘው:: ኢንዲጎ በጣም ደማቅ ሰማያዊ ቀለም ይሰራበታል:: ይህ ኢንዲጎ በአውሮፓ ጨርቃ ጨርቅ ባለፋብሪካዎች ዘንድ በጣም ተፈላጊ ስለሆነ ገበሬዎቹ እሱን ብቻ እንዲዘሩ በህግ ይገደዳሉ:: የሚከፈላቸውም በጣም ትንሽ ስለሆነ ድህነቱ አድቅቋቸዋል:: የፈለጉትን እህል ቢዘሩ ግን በመጠኑም ቢሆን ያልፍላቸው ነበር::

ጋንድሂ ይህን ጉዳይ ሲከታተል ክፍለ - ሀገሩን ለቆ እንዲወጣ ትእዛዝ ደረሰው::: እምቢኝ አለ፣ ፍርድ ቤት አቀረቡት:: ወንጀሉን አመነ::

እዚህ ላይ አገረ ገገርው ጣልቃ ገባና ይህን የኢንዲጎ ገበሬዎችን ሁኔታ የሚያጠና ኮሚቴ ተቋቋመ:: አንደኛው የኮሚቴው አባል፣ ማህትማ ጋንድሂ ራሱ:: ይህ ኮሚቴ ባቀረበው ሪፖርት ምክንያት ያ የግፍ ህግ ተሻረ፣ ይህም በምድረ ህንድ የመጀመሪያው የጋንድሂ ድል ነበር::

በ1918 ሎርድ ቼልምስፎርድ የህንድ ባለሙሉ ስልጣን አገረ ገዥ ጋንድሂን ለጦር ምክር ጋበዘው::: ጋንድሂም እንዲህ አለ «በቻምፓራን ለዓመታት ስር ሰዶ የነበረውን ኢፍትሀዊ ሁኔታ በመቃወሜ በእንግሊዝ ግዛት የሕግን ሉአላዊነት አስመስክሬያለሁ» ከእንግሊዝ ጐን ሆነው የሚዋጉ የህንድ ወታደሮችን ይመለምል ገባ:: መመሪያችን «አሂምሳ» ቢሆንም የሰው ልጆች ነንና በሁኔታዎች ተገደን ጦርነት ልንዋጋ እንችላለን::

በ1919 «የሮውላንድ ሕጎች» ታወጁ::: በመንግስት ላይ ያሴራሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች ያለፍርድ ይታሰራሉ ይላል:: ጋንድሂ ህዝቡን የሚመጣው እሁድ «ስራ እናቆማለን» ሲል ጋበዘ:: ወደ ዴልሂ ጉዞ ላይ እንዳለ ታሰረ:: እንግዲህ በአለም ትልቁ
ህዝብ ትልቅ ረብሻ ፈጠረ - አሂምሳ ገደል ገባች! ... የማበለው ነው:: «ሂማላያን

የሚያክል ስህተት ሰራሁ» አለ ጋንድሂ፡፡ ስህተቱን በይፋ ማመን የጋንዲ አንዱ ጠባይ ነው፡፡ ለጊዜው ሲቪል እምቢተኝነትን አቋርጠናል ሲል አስታወቀ፡፡ በዚያው ወራት አምሪትሳር ከተማ ውስጥ አስር ሺ ሰዎች በተሰበሰቡበት በመትረየስ ተረፈረፉ፡፡

ወታደራዊ ህግ (Martial Law) ታወጀ፡፡ ወይም የአስቸኳይ (ማለትም የአስቦ) ጊዜ አዋጅ... ጋንድሂ ሁለት ሳምንታዊ ጋዜጣዎች ያሳትም ጀመር፡፡ አንዱ በእንግሊዝኛ አንዱ በጉጂራቱ ቋንቋ፡፡ ዓላማው - ሰላማዊነትንና ፍርሀት አልባነትን ለማስተማር፡፡ የዘለቄታ አላማው ግለሰቡ ለሙብቶቹ መሟገትና ማስከበር የሚችልበት ኅብረተሰብ መፍጠር ሊኖሩት የሚገባና የሚያኮራ ህይወት የሰራተኛው የገበሬው ኑሮ ነው ይላል ጋንድሂ፡፡ በሌላ ቋንቋ «ብላ በሀፊ ገዕክ» ይላል፡፡

በ1921 ማህትማ ጋንድሂ ልብሱን ትቶ ግልድም ብቻ መልበስ አመጣ፡፡ ሀፍረተ ስጋውን ለመሸፈን ያህል ብቻ ሳይሆን፣ ለህዝቡ አርአያ ለመሆን ጭምር ነበር ይህን ማድረጉ፡፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሠዎች አሮጌ ልብሳቸውን ሲጥሉ፣ ሌላ የተሟላ ልብስ ለመተካት ድህነታቸው አያስችላቸውም አለ ማህትማ ጋንድሂ፤ ስለዚህ ግልድም ይበቃኛል ይበሉ፡፡

ጋንድሂ በንግግርም በፅሁፍም የእንግሊዝ አገዛዝን ያወግዝ ነበር፡፡ «ሰይጣናዊ ስርዐት» ይለዋል፡፡ «ሰላማዊ እምቢተኝነት (Non-cooperation) በህይማኖታዊ እና በግብረገባዊ እንቅስቃሴ መሆኑ እየታወቀም፤ ዓላማው ይህንን መንግስት ወደዚያ መገርሰስ ነው፡፡ ፍርሀት አልባነት ይሉሀል ይሄ ነው! የኢየሱስን አያስታውስህም?

ኢየሱስ ብትል፣ ጋንድሂጂ (ባገራቸው የመውደድና የማክበር ቁልምጫ ነው) ወደ ኋላ ዘመናቸው በባቡር እየተጓዙ እያለ አንድ ድፍን ጫማ ያደረገ ጉረምሳ ከፊታቸው በኩል ቆሞ እንደኳስ ቢያጎናቸው የላይኛ የፊት ጥርሶቻቸው ረገፉ፡፡ ጋንድሂጂም ደማቸውን እየተፉ «አግርህን ተጐዳህ ልጄ?» ብለው በሀዘኔታ ጠየቁት፡፡ ትዕግስት ይሉሀል ይሄ ነው፡፡ ጠላትህን መውደድሳ!? ኢየሱስ ብትል ጊዜ ነው፡፡

በ1892 ማህትማ ጋንድሂ በጉጅራት ክፍለ ሀገር ሰፊ የህዝባዊ እምቢተኛ ነት ዘመቻ ለመምራት ወሰነ፡፡ ከንግዲህ ወዲያ ለዚህ መንግስት ግብር አንከፍልም፡፡

ምን ዋጋ አለው? ኡታር ፕራዴሽ ክፍለ ሀገር እምትገኝ ትንሽ ከተማ ውስጥ የጋንድሂ የትግል ባላጋራዎች ሕዝቡን ቀስቅሰው ገፋፍተው ፖሊሶችን በድንጋይና በዱላ እንዲወርዱባቸው አደረጉ፡፡ አሁንም አሂምሳ ገደል ገባች! ቢጋንዲሂ ስህተት ሳይሆን በጠላቶቹ ብልሀት፡፡

ማሀትማ አውጆት የነበረውን የእምቢተኛነት ዘመቻ ስረዙ:: ለአምስት ቀን ሱባኤ ገባ - ማለትም ከውሀ በስተቀር ሌላ ነገር ሳይቀምስ ለዚያ ፖሊሶች ላይ ለተወሰደው ጥቃት ንስሀ ገባ::

ማሀትማ ከሱባኤያቸው ሲወጡ ህዝብን ለአመፅ በመቀስቀስ ክስ ተይዘው ለፍርድ ቀረቡ:: እምነት ክህደት ሲጠየቁም እንዲህ የሚል መልስ ሰጡ:: «እኔ እዚህ የቀረብኩት ለህግ ወንጀል የሆነ ለኔ ግን ከፍተኛ ተግባር የሆነ ድርጊት በመፈፀሜ ስጣስኩት ህግ ከሁሉ ከፍተኛ የሆነውን ቅጣት ለመቀበል ነው::»

የስድስት ዓመት እስራት ተፈረደባቸው:: ሁለት አመት ከታሰሩ በኋላ ትርፍ አንጀት አመማቸው:: ቀዶ ጥገና ወይም ኦፐሬሽን ተደረገላቸውና ዳኑ:: የተቀረው አራት ዓመት እስራት ቀረላቸውና ነፃ ተለቀቁ:: ትግሉን ይቀጥሉ ዘንድ::

ማን ለቀቃቸው? (በተለይ ለወጣት ደራሲያን በቅንፍና በድርብ ቅንፍ:: ከፈጣሪ እኩል ደራሲ የለም:: ፈጣሪ አሸናፊውን ጀግና ጋንድሂን ሲፈጥር እኩያውን ተፋላሚ ካልፈጠረ፤ ፍልሚያው ለተመልካቹ ወይ ለሰሚው አይጥምም:: ስለዚህ እኛ በታሪክ የኋሊት አይተን ስናወራላችሁ የንግስት ቪክቶሪያ የእንግሊዝዋ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ የሆነው የህንድ አገረ ገዥ - (ጨቋኝ ስለነበረ እንጥላው እንጂ) ከጋንድሂ ጋር የነበረው ግንኙነት ግን ግጭት ቢሆንም የእኩያሞች ግጭት ነበር:: ሸፍጥ የለም:: ትግል ብቻ:: ዳኛም አያስፈልገንም:: የትግል ደንቦችና ህግጋት በቂ ናቸው:: ከነሱ አንወጣም:: ምክንያቱም እኛ እንግሊዞች እሩብ አለምን የምንገዛ፤ ባህር ውቅያኖስ በቁጥጥራችን ስር የሆነ (የባህር ጦር ማለታችን ነው) የጋንድሂን ትግል እኮ ገና በእንጭጩ ልንቀጨው እንችል ነበር:: ብንፈልግ ገና ደቡብ አፍሪካ ለህንድ ዘር መብት ሲታገል:: ብንፈልግም ገና ስለ ኢንዲጎ በግዴታ አምራች ገበሬዎች መሟገት ሲጀምር አፍነን ወይ ረሽነን ወይ በስቅላት ቀጥተን መገላገል ባላቃተን:: ግና እኛ እንግሊዞች፤ የዘረጋነው ያስፈነነው ሕግ ከሚጣስ ሩብ አለም ያህል ዝርግ መንግስታችን መፍረስ ቢጀምር እንመርጣለን:: እኛም የበኩላችን ታላቅነት ሳይኖረን አይቀርም:: ስመ ጥሩው ባላጋራችን ጋንድሂ ይመስክር:-

«በእንግሊዝ ግዛት የህግን ሉአላዊነት አስመስክሬያለሁ::»... ይህ ሁሉ የሀይማኖትና የግብረገብ ትግል ሲካሄድ ሳለ በ1889 የተወለደው መልከ ቀናው ጀዋሀርላል ኔህሩ የፖለቲካውን ትግል ይመራ ነበር:: እንዲያውም ትግሉን ከጀመሩት አንዱ የጃዋሀርላል አባት ሞቲላል ኔህሩ ነበር::

ማለትም ልጁን ሆን ብሎ ለትግል ህይወት ሲያዘጋጀው ወደ ኢንግላንድ ላከው:: ጃዋሀርላል ኔህሩ ትምህርቱን ሀረው በተባለው እጅግ ዝነኛ ትምህርት ቤት ካጠናቀቀ በኋላ ከኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የህግ ድግሪውን ተቀብሎ ሲያበቃ በ1912 ወደ ህንድ ተመለሰ:: እንደ ጋንድሂ:: ወይዘሮ ኢንግላንድ ስለ ጋንድሂ

እና ስለኔህሩ ሲያወሩ እንዲህ ሳይሉ አይቀሩም፡- «እጁ አመድ አፋሽ ነው እባኩትን:: እስቲ እነዚህን ሁለቱን ከልጆቼ ሳልለይ ህግን ያህል እውቀት ካስቀሰምኳቸው በኋላ እንደዚያ በኔ ላይ ይዙሩብኝ? ባዳን ከማሳደግ ውሻን ማሳደግ ይሻላል:: ሆ! ደም እንዴት እንዴት አድርገው ተጋገዙብኝ! ዋ!»

ጃዋህርላል የብራህሚን ዘላቂ መደብ አባል ሲሆን ቤተሰቡ ምሁራንና ባለፀጋዎች ነበሩ:: ታሪክን እናስዘልላትና፣ ኔህሩ የነፃይቱ ህንድ የመጀመሪያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነ:: የኔህሩ ልጅ የሆነችው ሚስስ ኢንዲራ ጋንድሂ ጠቅላይ ሚኒስትር እያለች በተቃዋሚዎች በጥይት ተገደለች:: የሷ ልጅ የሆነው ራጂቭ ጋንድሂም ጠቅላይ ሚኒስትር እያለ በተቃዋሚዎች በጥይት ተገደለ:: ማህትማ ጋንድሂ ራሱም በተቃዋሚዎች በጥይት ነው የተገደለው:: እቺ አሂምሳ እንዴት እንዴት ያረጋታል!?

በ1918 እነ ኔህሩ የመላው ህንድ ኮንግሬስ ፓርቲን መሰረቱ:: ከጥቂት ዓመታት በስተቀር እስከ ዛሬ ህንድን የሚያስተዳድራት ይኸው ኮንግሬስ ፓርቲ ነው::

ስለ ጋንድሂ ስናነብ ቀኝ እጁ ኔህሩ መሆኑን እያስታወስን::

በ1924 ጋንድሂ የመላው ህንድ የፈታዮች ማህበርን መሰረተ:: ለሚቀጥሉት አራት አመታት ስራው በህንድ እየተዘዋወረ የፈታዮች ማህበራትን ማቋቋምና ስለ እምነቱ ማስተማር ሆነ::

በ1929 ኔህሩ እና ኮንግሬስ ህንድ ሙሉ ነፃነት ነው የምትሻው እንጂ ዶሚኒየን (ከፊል ወይም በአብዛኛው ነፃ) መሆኑን አትቀበለውም ብለው የፖለቲካ ትግል አቋማቸውን በይፋ አሳወቁ::

ማህትማ ጋንድሂ በተለይ ድሀውን ህዝብ የሚጫነውን የጨው ግብር አንከፍልም ብሎ የኅላማዊ እምቢተኝነት ዘመቻ አወጀ:: ስለዚህ ዘመቻ ሪፖርተራችን ከኒውዴልሂ የላከልንን ዘገባ ለሚቀጥለው እናቀርባለን:: እስከዚያው ናማስቴ!

## ሚያዝያ 1፣ 1987

ናማስቴ! ማህትማ ጋንድሂ የጨው ግብርን እምቢ ለማለት ተነሳ:: ከሰባ ሰምንት ተከታዮች ጋር ከአህመዳባድ ከተማ ተነስተው ሰባ ስምንት ማይል ርቀት በእግር ሄደው ጨው እንደልብ የሚዛቅበት ባህር ዳር ደረሱ::


ከዚያ ማህትማው ገላቸውን ታጠቡና ሲወጡ ጉንበስ ብለው አንድ እፍኝ የሚያክል ጨው አነሱ::

ተው እንጂ! ጨው መዛቅና መሸጥ መብቱ የእንግሊዝ መንግስት ብቻ ነው ከ፣ ሞኖፖሊ::

እሱን ሞኖፖሊ ልንቃወም አይደለም እንዴ ያህን ሁሉ መንገድ የመጣነው?

ደምኮ በቀርቡ ድሀውን ህዝብ ሲበዛ የሚጫነው የጨው ግብር ተጨምሯል። ይልቅ ቀጥል! ከማህትማው ጋር አብረው የመጡትም የፈለጉትንና የቻሉትን ያህል ጨው እየዛቁ ወሰዱ። ማህትማው ጨዋቸውን ይዘው ወደ ሚያድሩበት ገቡ። መላው የአህመዳባድ ልጅ እንደ አንድ ተነስቶ የማህትማውን አርአያ ተከተለ። ጨው እየተሸከመ ወደየቤቱ ገባ።

እስርልኝ! አለ እንግሊዝ። ህንድ እስራት በእስራት ሆነች። ጋንድሂ ራሱም ታሰረ። ከስምንት ወር በኋላ ነፃ ሲለቀቅ ታዲያ ለግል መጠቀሚያ ከሆነ፣ ማለት ለንግድ ካልሆነ - እየሄዱ ጨው ዝቆ መውሰድ የማንም ሕንዳዊ ዜጋ መብት መሆኑ ተደነገገ። ሌላ ድል አትሉኝም? ያውም በተለይ ድል ለድሀው ህዝብ፡ ከማህትማው ሌላ በመላው ሕንድ አንድ መቶ ሺ የጨው እስረኞች ተፈቱ። ሰላማዊ እምቢተኝነት፣ ፍርሀት አልባነት መልካም ውጤት አስገኙ።



ያውም አንድ ሰው ሳይሞትበን፤ አንዲት ጠብታ ደማቸውን ሳናፈስባቸው ተደርጎ አይታወቅም።

በ1931 ጋንድሂ ኮንግረስን ወክለው ስለ ነፃነት ጉዳይ ሊደራደር ወደ ለንደን ተጓዘ። ውይይቶቹ ታዲያ ስለ አናሳ ብሄሮች ጉዳይ እየሆኑ ሄዱ። ጋንድሂም የመጣሁት ዋነኛ ጉዳይ የስልጣን ርክክብ ነው፤ እንዲህ ስል ደሞ ኮንግሬስ የህንድን ህዝብ ከመቶ ሰማንያ አምስቱን እንደሚወክል ላስታውሳችሁ ግድ ይሆንብኛል አላቸው።

ከስብሰባዎቹ በኋላ ጋንድሂ የእንግሊዝ የጨርቃ ጨርቅ አምራች ከተማዎችን ጎብኝቱ፣ የሱ የፈታዮች ማህበር የስራ ውጤት ወደ ህንድ ይላክ የነበረው ጨርቃ ጨርቅ በጣም ስለቀነሰ ፋብሪካዎቹ ሠራተኞችን በማባረራቸው ስራ አጥነት በጣም ጨምሯል። እንዲያም ሆኖ ግን ጋንድሂ የህንድን ፈታዮችና ሌሎችም ድሆች የባሰ ሁኔታ በቀጥታ ስለገለፀላቸው ነገሩ ገብቷቸው በወዳጅነት እየተቀበሉ ሸኝተውታል።

አንዱ ከተማ ውስጥ ታድያ ጋንድሂ ገለፃ ሲያደርግ አንዱ ጋዜጠኛ «ባለፈው ሳምንት ለንደን የተናገርከው ግን እንዲህ የሚል አልነበረም» አለው። ሊያሳፍረው ወይም ሊያፋጥጠው መሞከሩ ነበር። ተራ የፖለቲካ ሰው መስሎት። ጋንድሂ ታድያ ፈገግ አለና፣ «ከሳምንት ወዲህ ያኔ ያላወቅኩትን አሁን ለማወቅ

ችያለሁ።» ሁቱን ፍርጥ! ማህተማ ጋንድሂ ወደ አገሩ እንደተመለሰ ሲያይ ሁኔታዎች ምንም አላማሩትም። እነ ጃዋሀርላል ኔህሩ እስር ቤት ናቸው። ኮንግረስ የህዝብ ሰላማዊ እምቢተኝነት ዘመቻ አውጇል። በ1932 እነ ጋንድሂ ታሰሩ። እስር ላይ እያሉ የወረዳዎች የህዝብ ወኪሎች ምርጫ ሊደረግ ሆነ። መራጮቹ ግን ባለስልጣናት በሁለት ከፍለዋቸዋል። በዚህ በኩል ሰው ነን ባዮቹ ሶስት የህንድ ዘላቂ መደቦች - ብራህሚን፣ ክሻትርያ፣ ቫይስያ። በዚያ በኩል ደግሞ እነዚህ ሶስቱ ወግነው እሱን ተፀይፈው ቆሻሻውን ሥራ ብቻ እየፈቀዱለት አቆሸሸው ሲያበቁ ዘወር ብለው ሰው አይደለህም! ጨርቃችንን እንኳ ብትነካ ታቆሽሸናለህ፤ (ምናልባትም ታረክሰናለህ ይሉት ይሆን?) የሚሉት ታችኛ ዘላቂ መደብ ሹድራ። ሶስቱ መደብ ዘላለም ሊረግጠው ተነስቶ ነበር፣ ጋንድሂጂ ደረሱለት እንጂ! አብርሃም ሊንከን ላገሬ ባርያ መደብ የደረሰለትን ያህል...

አብርሃም ሊንከን ብትሉ፤ እነዚህን ሁለቱን የነፃነት አዋላጆች ሳነፃፅርላችሁ፤ ሚወለደውማ ህዝቡ ነው። የሳት ፈታውራሪ የሆነውን ሊንከንን ለማንኳሰስ ሳይሆን ባለፈው ማህቫራን ጠርተነው የጋንድሂን መንፈሳዊ ጐን እንዳበራልን፤ አሁን ደሞ ሊንከን ነፃ አውጪውን ጠርቼው ጋንድሂን በተራውና በበኩሉ እንዲያበራልኝ ብዬ ነው።

ሊንከን ከጋንድሂ ዘመን ቀድሞ ደቡብ አሜሪካን ጥጥና ትምባሆ ለነጮቹ ጌቶቻቸው ያመርቱላቸው የነበሩትን ባሮች በፕሬዝዳንት ሕጋዊ መብቱ በብሩህ ህሊናው ተመርቶ የባሮችን ነፃነት አወጀ። በቃ! እንግዲህ ለባሪያ ነፃነት በዚያች ፕሬዚዳንት ሊንከን ባወጁት ሀገር ቢዘገይ ቢጎተት ቢደናቀፍ እንጂ መምጣቱ የማይቀር ሆነ በታሪክ አይን ጊዜን የኋሊት ስናነበው። ዛሬ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የጥቁሩ የማርቲን ሉተር ኪንግ ቀን ከጆርጅ ዋሽንግተንና ከአብርሃም ሊንከን እኩል ብሄራዊ በአል ሆኖ በየአመቱ ተከብሮ ይውላል። ቀስ በቀስ ገና ይቀጥላል፣ ይጠራቀማል የነሊንከን ቅርስ።

የገዛ ታሪኬን ቀደምኩት እንጂ፤ እንደዚሁም ጋንድሂጂ ለዘመናት ሲረገጥ የኖረውን ሹደራ ዘላቂ መደብ ከሶስቱ ንፁህ ነን ባይ መደቦች እኩል ንፁህ ነው! እንዲያውም ባይበልጥ! ብለው አውጀው ለጊዜው በሀሳብ በእምነት ደረጃ ብቻ እንኳን ቢሆን፣ ፈጠነም ዘገየ ግን መከረኛው ሹድራ መደብ ወደ እኩልነት የማይታጠፍ መንገዱን አስይዘውታል ጋንድሂጂ።

ሊንከንና ጋንድሂ ነፃ አውጭነታቸውና ለሰው ልጅ ያላቸው ፍቅር ሲመሳሰልብን፣ ተተክለው ነበረ ብንል የነቀሏዋቸው፣ ታንፀው ነበረ ብንል የፈነቀሉዋቸው አስከፊ ስርዓቶች ዓይነታቸው ይለያያል። ባርያ ይሸጣል፣ ይጫል፣ ይታዘዛል እንጂ፣ በይሉኝታ እንጠየፈዋለን፤ ጨርቃችንን አትንካም አንልም። እኛ ባሪያ አሳዳሪዎቹ እንዲያውም ሚስት ከሲለን ወይ ከታመመችብን

ከሞተችብን ወይ ከተጨማለቀችብን! ጭለማ ለብሰን ከሁሉ አረዳ ዓርቻችን የምታምረውን አቅፈን እናመሻለን:: ልጅም ይወለዳል:: ለይሉኝታ ስንል በደፋ ባንቀበለውም እናቲቱ እንድታሳድገው ልናስችላት እንችላለን:: ያውም ምንም ሳይጐድልበት:: አንድ ፍሬያችን ጥሞናልና ያንኑ ጭለማችንን ለብሰን አንድ ሁለት ሦስት ልጆች ሁሉ መጨመር እንችላለን:: ስለዚህ የባሪያ ሥርዓት ሲያስትም ጥቅማችን ተነካ እንጂ ሰውነታችን ወይም እኛ የሰው ክብራችን የምንለው አልተነካብንም::

ሕንዶቹ ሹድራም ያው እኩያችሁ ነው ሲባሉ ግን ብዙዎቹ በተለይም ወግ አጥባቂዎቹ የሰው ክብራቸው እንደተዋረደ ይቆጥሩታል:: እንዲያም ሆኖ ግን ... ባለስልጣኖቹ ሰው ነን ባዩን ሕንድና አበሰኛውን ሹድራ እንደ ሁለት ሕዝብ አድርገው ምርጫ ሊያካሂዱ መሆኑን ሲሰሙ ማህትማው ከእሥር ቤት መልእክት ላኩ «አንድ ህዝብ አንድ ምርጫ ካልሆነ እስከ ሞት ድረስ እፆማለሁ» ማህትማው ያማቸውን የጀመሩበት ቀን በመላው ሕንድ የፆምና የፀሎት ቀን ሆኖ ተከብሮ ዋለ:: ብዙ ቤተ መቅደሶችም በራቸውን ለሹድራዎቹ ክፍት አድርገውላቸው ዋሉ:: (ይህ ሁሉ እንግዲህ አንድ ኮሳሳ ባለ መነፅር ባለ ግልድም ሽማግሌ መፆም ስለጀመረ ነው:: እና ሰው ሁሉ እኩል ነው ስንል በህግ ፊት ማለታችን ነው እንጂ ማህትማ ጋንድሂ እና ሚስተር ፓቴል ወይም ሚስተር ሲንግ እኩል ወይም እኩያ ናቸው ማለታችን አይደለም::)

ማህትማ አምስት ቀን እንደ ፆሙ ባለስልጣኖች ህዝቡ ሳይከፋፈል እንደ አንድ አገር ዜጋ እኩል እንዲመርጥ ተስማሙ:: (ባለስልጣናቱም እንግሊዝ ሳይሆኑ እነ አጅሬ ቢሆኑ ኖሮ ግን «እሞታለሁ? ለምን ክንችር አይልም? ኧረ ገመድ ስጡት ይታነቅ!» ይሉ ነበር::)

ከዚህ በኋላ ማህትማ ጋንድሂ «እኔም ሹድራ ነኝ» አሉ:: የሹድራዎቹን ስም ለውጠው «ሀሪጃን» አሉዋቸው:: ትርጉሙም «የእግዚአብሄር ልጆች» ማለት ነው:: «እግዚአብሄር አብልጦ የሚወደው ከሁሉ የተናቁትን ስዎች ነውና» አሉ ማህትማው:: በ1933 «ሀሪጃን» የሚል ሳምንታዊ መፅሔት ያወጡ ጀመረ:: መፅሄቱ ስለ ሀሪጃኖች የሚያስተምሩበት ሲሆን እስከ 1942 «ሀሪጃን» መፅሄት በአስር የሕንድ ቋንቋዎች እየታተመ ነበር::

ማህትማው ለሀሪጀኖች የሚውል ገንዘብ መዋጮ ፍለጋ አገሪቱን ስአስር ወራት ተመላለሱበት:: ስምንት መቶ ሺ ሩፒ ሰበሰቡ - አብዛኛው በነሐስ ሳንቲሞች (ማለትም ድሆዎች ያዋጡት) ጥቂት ደሞ በሴቶች ወርቃ ወርቅ::

በ1932 ጋንድሂጂ ከኮንግሬስ ተሰናበቱ:: ከእንግዲህ ስራቸው በየመንደሮች እየዞሩ ማስተማርና እላቸው አዲስ የመሰረቱትን የመላው ህንድ የመንደር ኢንዱስትሪዎች ማኅበራትን መምራት ሆነ:: የልብስ መፍተል፣ መሽመንና

ለጊዜያ ማቅረብ ስራን በአምስት ሺ መንደሮች አቋቋሙ። ያለ የጋንዲሂጂ ተጨባጭ ውጤት የሚያስገኝ ስራ ሕዝቡን እጅግ አስደስቶ ስለቶየ ምርጫ ሲመጣ ኮንግሬስ ከአስራ አንዱ ክፍለ አገሮች ዘጠኙ ውስጥ ተመረጠ።

የጋንዲሂጂ ገድል በድራማ የተሞላ ሲሆን፤ እኛ ግን ለተምሳሌ ያህል የቀነጨብንላችሁ እዚሁ ይብቃና ለመሰናበቻ ድርብ ተልእኮዎቻቸውን እናስታውሳችሁ።

አንድ/ ህንድን አራት መቶ አመት ተሸክማው ከኖረችው የእንግሊዝ ግዛት ነፃ ማውጣት፤


ሁለት/ ሀሪጃኖቹን ለሺዎች ዓመታት ሲረግጧቸው ከኖሩት ከሦስቱ ዘላቂ መደቦች ጭቆና ነፃ ማውጣት፤

የጭለማ ሀይላት ብርሀኑን ሲያዩ ካላጠፉት አይሆንላቸውምና፤ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ወጣት በአክብሮት እጅ እየነሳ ማህተማ ጋንዲሂን ተጠጋና በሽጉጥ አሰናበታቸው። ናማስቴ!

ሚያዝያ 8፤ 1987

# ፬ 4 ፬

# አብርሃም ሊንከን
# *Abraham Lincoln*



የዩናይትድ ስቴትስ አስራ ስድስተኛውና ታላቁ ተወዳጅ ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን የማንም ቤተክርስቲያን አባል ሆኖ አያውቅም፡፡ ከዚህ ጋር ግን እውነተኛ ክርስቲያን እንደ ነበረ ስራው ይመሰክራል፡፡ ሊንከን የአሜሪካውያንን ጥሩ እና ጠንካራ ጎን ይወክላል፡፡ አንድ አሜሪካዊ የልብ ፍላጎት፣ ታታሪነት፣ የወኔ ሰናት እና የማሰቢያ ጭንቅላቱ ካለው ከባዶ ተነስቶ ፕሬዚዳንት ሊሆን ይችላል የሚለው የአሜሪካኖች እምነት በሊንከን የህይወት ታሪክ ሲታይ እውነት ነው ያሰኛል፡፡ ለጤነኛው አሜሪካዊ አብርሃም ሊንከን አርአያ ነው፡፡ ናሙና ነው፡፡

ሊንከን ተወለደ፡፡ ያደገው በድህነት ውስጥ ነበር፡፡ የተማረበት ጊዜ ተደምሮ አንድ አመት እንኳን አይሞላም፡፡ ወጣቱ (በጣም ረዥሙ) ሊንከን በሚኖርበት አካባቢ ዙሪያውን የአንድ ቀን መንገድ ርቀት እየሄደ መፅሀፍ እየተዋሰ ነበር የተማረው፡፡ በዚህ ብቸኛ ጥረት ጠበቃ ለመሆን በቃ፡፡ ከጥብቅናው ተነስቶ ቀስ በቀስ ወደ ፖለቲካው ዓለም ገባ፡፡ ከቀልድና ከሳቅ ጋር፡፡

«እግዜር ድሆችን ይወዳቸዋል:: ለዚህ ነው አብዝቶ የሰራቸው» በጥብቅናው ዘመን አንድ ቀን ቢሮው ተዝናንቶ አንድ እግሩን ጠረጴዛው ላይ ዘርግቶ ጋዜጣ ሲያነብ ጓደኛው ገባና በጣም ተገርሞ እንዲህ አለ «ኧረ በስመ አብ! እግርህ እንዴት ረዥም ነው ባክህ! እኔ ከተፈጠርኩ እንደዚህ የተመዘዘ ረዥም ቀልጥም አይቼ አላውቅም::»

«ካልክስ ይኸውልህ ሌላ ከሱ እኩል ረዥም ቀልጥም» አለና ሊንከን ሌላ እግሩንም ጠረጴዛው ላይ ዘረጋው::

ሊንከን ገና የአስራ ሰባት አመት ጉረምሳ እያለ አካባቢውን የሚያውኩ ሶስት ወንድማማቾች ተነሱ:: እየዞሩ ሰው ይደበድባሉ «ያስገብራሉ»:: አገር ተመረረ:: አንድ ቀን ወደ አመሻሽ ላይ አብርሃም ሊንከን ብቻውን ወደነዚህ ወንድማማቾች ቤት መጣና «ባለጌ ስለሆናችሁ ስነስርአት ላስተምራችሁ መጥቻለሁ» አላቸው::

«እንዴት አድርገህ ባክህን» አሉት::

«እንደዚህ ነዋ!» አለና በቡጢ በጥፊ በክርን በእርግጫ አጣደፋቸው፤ በቃን ተወን አይለምደንም አሉት::

እነዚህ ወንድማማቾች አገር መበጥበጡን ርግፍ አርገው ተውት:: ይህ ብቻም አይደለም፣ የሊንከን የቅርብ ጓደኞች ሆኑ:: እስከ እለተ ሞቱ ድረስ የልብ ጓደኞቹ ሆነው ኖሩ::

ይቺ የሊንከን ጀብዱ ወደ ፊት ፕሬዚዳንት ሲሆን በአገር ደረጃ ለሚፈፀመው የነፃ አውጭነት ገድል እንደትንቢት ወይም እንደ ቅምሻ ነበረች:: የሊንከን ጀብድም ገድሉም በቀልድ የታጀበ በሳቅ ያጌጠ ነበር::

* * *

እንደ ካንጋሮ ወይ እንደ ጥንቸል፤ ወይ እንደቁንጫ፤ እየነጠርን እየዘለልን በሊንከን እድሜ ዘመን እንመላለስና፣ ያ ዘጠኝ መቶ ሺ ሰው ያለቀበት ጦርነት ተፋፍሞ ነበር:: የሊንከን ዋና ጀነራል የነበረው ማክሌላን ግን እንዲዋጋ ትዕዛዝ ሲደርሰው እንደ መዋጋት መሸሽ እያበዛ አስቸገረ:: ስለዚህ ሊንከን ከስራው ሊያሰናብተው እንዲህ ብሎ ፃፈለት:: «እንደው ለምናልባቱ አንድ ቀን ለመዋጋት የፈለግኩ እንደሆነ ሰራዊት ስለሌለኝ ሰራዊትህን እንድታውሰኝ::» ሊንከን ከጥብቅናው ወደ ፖለቲካው መድረክ በተሻገረበት በዚህ ጊዜ በኖረባቸው አካባቢዎች የታወቀ ነበር እንጂ በሀገር ደረጃ ስሙን ገና ማንም አያውቀውም::

ለፌዶራል (ሀገር-አቀፍ) የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ወንበር ከሊንከን ጋር ሊወዳደር የተነሳው ዳግላስ ግን በመላው አገር ዝናው ተዘርግቷል:: ሊንከን ዳግላስን በሰባት የተለያዩ ከተሞች ስለ ፖለቲካዊ አቋማችን እንሟገት ይዋጣልን አለው:: ዳግላስ እሺ ይዋጣልን አለ:: ሰባቱም ሙግቶች በጋዜጠኞች ዘገባ በመላው አሜሪካ ተደመጡ:: ዳግላስ አሸነፈና ሴኔት (Senate) ገባ:: ሊንከን

በዚሁም የዳግላስን ዝና ተመርኩዞ በመላው አሜሪካ ስሙን ተከለ:: ለሚቀጥለው የፖለቲካዊ ስትራቴጂ እርምጃ ዝግጁ ሆነ::

አንዱ ሙግታቸው ውስጥ ታዲያ ዳግላስ ሊንከንን «ይሄ ባለ ሁለት ፊት ሰውዬ!» ብሎ ሰደበው:: እንግሊዝኛው አባባል «ይሄ በሁለት ቢላዋ በሊታ ሰውዬ!» የምንለውን ሀሳብ ያስተላልፋል:: አብርሃም ሊንከን ደግሞ በጣም ተወዳጅ ይሁን እንጂ በጣም አስቀያሚ ነው ፊቱ:: እና ለዳግላስ ስድብ እንዲህ ሲል መለሰ:: «ክቡራንና ክቡራት! ባለ ሁለት ፊት ተብዬ ስስደብ ሰምታችኋል:: እስቲ አስቡት:: ሁለት ፊት ቢኖረኝ ይህን ፊት ለህዝብ አሳይ ነበር'ንዴ?»

በዚህን ጊዜ አሜሪካን ለመምራት የሚወዳደሩት ዴሞክራት እና ሪፐብሊካን የተባሉት ፓርቲዎች ናቸው:: ከከባድና እጅግ ሞቅ ያለ ህዝብ በተመሰጠ የሳበ ውድድር በኋላ ሊንከን የሪፐብሊካን ፓርቲ መሪ ሆኖ ተመረጠ:: በሚቀጥለው ስትራቴጂክ እርምጃ ሊንከን አስራ ስድስተኛው ፕሬዚዳንት ሆኖ ተመረጠ:: እና ለሪፐብሊካን ፓርቲ መሪነት ሲታገል ዋና ባላንጣዎች ሆነው ተወዳድረውት የነበሩት ጥይት ሰዎች መንግስት ሲቋቋም ቁልፍ ቁልፍ (ማለትም ዋና ዋና) የሆኑትን የስልጣን ወንበሮች ሰጣቸው:: እነሱም ከልባቸው አገለገሉት (በቃን እስኪሉ የደበደባቸው ሰስት ወንድማማቾች ተለውጠው የልብ ጓደኞቹ የሆኑት ትዝ ይሉናል)::

ሊንከን በፕሬዝዳንትነት በሚወዳደርበት ወቅት ፖለቲካዊ አቋሙን ለመራጩ ህዝብ ሲገልፅ እንዲህ ብሎ ነበር:: ኢየሱስን እየጠቀሰ «እርስ በርሱ የተከፋፈለ ቤት ሊቆም አይችልም፤ አገራችንም ተከፋፍላ መቆም አትችልም፤ ወይም በሙሉ የባርነት አገር መሆን አለባት::»

ሊንከን ተልእኮው በቅደም ተከተል እንዲህ ይታየዋል:: በመጀመሪያ ደረጃ በመናጋት ላይ ያለውን የአገሪቱን አንድነት መጠበቅና ማፅናት:: በሁለተኛ ደረጃ ባርያዎችን ነፃ ማውጣት:: የሀገራችንን ህገ መንግስት እስካልጣስን ድረስ ሁለቱንም የተቀደሱ ተግባሮች እኩል እያራመድን ከዳር ማድረስ::

በነሱ በኤፕሪል 12/1861 ትልቁ የአሜሪካ እርስ በርስ ጦርነት ተጀመረ:: ሰሜኖቹ ድል አድርገው አንድ ክፍለ ሀገር በያዙ ቁጥር ሊንከን የጦር ሀይሎቹ ዋና አዛዥ ነውና በዚህ ስልጣኑ «ለጦርነቱ አስፈላጊ ሂደት የምንወስደውን እርምጃ» ይልና በጠላት ስር ባርያ የነበሩ ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ ነፃ ናቸው ብሎ ያውጃል::

እንዲህ እያለ ቀጠለና ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን በ1863 «የነፃነት አዋጅ» ፈረመ! አወጀ:: ከዚያ በኋላ ባገር ሰዎች (The Emancipator) «ነፃ አውጪው» ተባለ! ከዚያ ሲቀጥል በጀንዋሪ 1/1863 ነፃ አውጪው ከእንግዲህ ጥቁሮች የዩናይትድ ስቴትስ የጦር ሀይሎች ሙሉ አባል ሆነው ከነጮች እኩል

ለሀገራቸው ደማቸውን ማፍሰስ መብታቸው ነው ብሎ አወጀ:: ከሰው እኩል ሰው አደረጋቸው::

ከዚህ አዋጅ ተነስተን አንድ መቶ ሃያ ሰባት አመት ስንቆጥር በፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ዘመን በ1990 የኢራቁ ፈላጭ ቆራጭ ኩዌትን ወረረ:: የአሜሪካ ሰራዊት የሳዳምን ጦር ከኩዌት ለማስወጣት ዘመተ:: የሳዳምን አገር ልክ እስኪገባ ድረስ ደበደቡት:: አቅሙን የማያውቅ መሪ አይላክብን! ሳዳም ሁሉን ጥራዋን ሸጉባ ወደ አገርዋ ተመለሰች:: የአሜሪካው የጦር ሀይል የበላይ አዛዥና «የምድረ በዳ ማዕበል» የተባለው ዝነኛ ውጊያ ድል አድራጊ ጥቁር ጀነራል ኮሊን ፖውል ለፕሬዚዳንትነት ቢወዳደር የመመረጥ እድሉ ከፍተኛ ነበር ይባላል:: ለምን አልተወዳደረም ይሆን? መቼ በቃኝ እንደሚባል ጥበኑ ተገልፆለት ይሆን?

ስለሊንከን ስንጥፍ ቆይተን እንዴት ያለቀልድ ያለ ሳቅ ልንደመድም እንችላለን? ሰውየው ስለ አስቀያሚ መልኩ ብዙ ጊዜ ይቀልድ ነበር:: በሚዝናናበት ሰዓት ሴንጢ አወጣ::

«ምን የሚያክለው ግድንግድ ሴንጢ ነው ባክህ» ይላል አንዱ ጓደኛው «ከየት አመጣኸው?»

«ተሸልሜ ነው»

«ማ ሸለመህ በል?»

«አንድ ቀን መንገድ ላይ አንድ በጣም በጣም አስቀያሚ ከኔ የባሰ መልክ ጥፉ ሰውዬ አቆመኝና «ሚስተር ሊንከን! ከኔ የባሰ አስቀያሚ እስኪያጋጥመኝ ስፈልግ ስፈልግ ብዙ አመት ሆነኝ:: ይኸው አሁን አገኘሁህ:: እንካ ይህን ሰንጢ ሸልሜሀለሁ:: ካንተ የባሰ መልክ ጥፉ ስታገኝ ተራህን ይህን ሴንጢ ሸልመው» ብሎ ሰጠኝ:: እኔም ተራዬን ከኔ ያባሰ መልክ ጥፉ ፍለጋ ላይ ነኝ እላችኋለሁ:: እኔና ይሄ ሴንጢ ለብዙ ረዥም ዓመታት አብረን ኖረናል አንዳችን እስክንሞት መለያየታችንን እንጃ!»

መስከረም 4፣ 1990

# 5

# ጋሊሊዮ፣ ማርቲን ሉተርና ጆርዳና ብሩና

# *Galileo, Martin Luther & Giordano Bruno*



ማርቲን ሉተር



ጋሊሊዮ

ማርቲን ሉተርና ጆርዳኖ ብሩኖ ሁለቱም መነኩሴዎች ነበሩ:: አንዱ ኢንኩዊዚሽን (የካቶሊክ ሃይማኖት ጠባቂ ፍርድ) አመለጠ፣ ሌላው ተፈርዶበት ባደባባይ በእሳት ተቃጥሎ ሞተ:: የአዲሱ ሳይንስ ነብያትና ሀዋርያት ሰማዕታት በርካታ ሲሆኑ፣ ከዚህ ርቀት እጅግ ጉልተው የሚታዩን እነዚህ ሁለቱ መነኩሴዎች እና ጋሊሊዮ ጋሊለይ ናቸው:: Galileo Galilei (1564-1642) መነኩሴ አልነበረም:: ስለ ሃይማኖትም ያን ያህል የሚጨነቅ አልነበረም:: የሱ ሀሳብ የሚሽከረከረው በሳይንስ ዙሪያ ነበር:: እድሜ ለነ ጋሊሊዮ ዘመናችን የሳይንስ ዘመን ሆነ:: ሳይንስን ከፈጠሩት ከነጋሊሊዮ ጋር እግረ መንገዳችንን ወደፊት!

እግዚአብሄርም አለ «እነሆ ሳይንስ ምንም ሀይል ሊያጨናግፈው ወይም ሊገታው በማይችል እመርታ የሚያድግበት ጊዜ ደረሰ» ይህም ይሆን ዘንድ ጋሊሊዮ ተወለደ::

እኛ ንፁህ የዋህ ሰው ስናይ «እግዜር እጁን ታጥቦ የፈጠረው» እንላለን:: ጋሊሊዮን ስናስብ ደሞ «እግዜር ሳይንስን እያሰበ የፈጠረው» እንበል እንጂ:: ምክንያቱም እግዜር ለገዛ ምክንያቱ ጋሊሊዮ ውስጥ አንድ ተራ ሳይንቲስት

ሳያዘዝን ወደር የሌላቸውን ሳይንቲስቶች አበቀለ።

ያ እግዜር የፈጠረው ጋሊሊዮ በተራው ሶስት የተለያዩ ሳይንሶችን ፈጠረ ይባላል። ማቴማቲክስ፣ አስትሮኖሚ እና ፊዚክስ። ሰው ያቅዳል እግዜር ይፈፅማል እንዲሉ፣ ጋሊሊዮ ህክምና ለመማር ነበር ፒዛ ዩኒቨርስቲ የተመዘገበው። እግረ መንገዱን ማቴማቲክስ ሲያጋጥመው ጊዜ ህክምናውን ትቶ ወደ ማቴማቲክስ ዞረ። በኋላም እዚያው ዩኒቨርስቲ የማቴማቲክስ ፕሮፌሰር (መምህር) ሆነ። ቀጥሎም በፓድዋ ዩኒቨርስቲ የማቴማቲክስ መምህር ሆነ። እኛ የማቴማቲክስ እውቀት ስለሌለን ኢንሳይክሎፒድያ ውስጥ ያነበብነውን በማመን የጋሊሊዮ አስተዋፅኦ ባይሸኝት ኖሮ የማቴ ማቲክስ ሳይንስ እዚህ ደርሳ እነ አልበርት አይንስታይንን ባላፈራች ነበር እንላችኋለን።

(ይሄ እንግዲህ የወሬ ወሬ መሆኑ ነው።)

ከጋሊሊዮ ጋር ወደ አስትሮኖሚ ስንገባ በዚያን ጊዜ ሆላንድ ውስጥ ቴሌስኮፕ ተፈጠረ። ሩቅ ያለውን ተራራ ይሁን ወይ ኮከብ ወይ ሌላ አካል አይተን ብቻውን ከሚያየው ሶስት ጊዜ የበለጠ አጉልቶ የሚያሳይ መሳሪያ ነበር። ጋሊሊዮ ሀሳቡን ተበድሮ ወሰደና ሰላሳ ሁለት ጊዜ የበለጠ አጉልቶ ወይም አሳድጉ የሚያሳይ ቴሌስኮፕ ሰራ። እና በዚህ በቴሌስኮፕ ሰማይቱን ያስስ ገባ።

እና ምን አስተዋለ? ጉድ ፈላ! ለካ እውነቱ ሲታይ ፀሐይ መሬትን አትዞራትም፣ መሬት ናት ፀሀይን የምትዞር! ሳይንቲስት ነውና ግኝቱን ለሌሎች አሳወቀ - ልክ ይሁን አይሁን ሌሎች ሳይንቲስቶች አይተው እንዲመሰክሩለት ወይም ተሳስቶ ከሆነ እንዲያርሙት። ምክንያቱም ሳይንስ እንደ ሀይማኖት አንድ ጊዜ የተደነገገ ቋሚ እምነት ሳይሆን፣ ማንኛውም ሳይንቲስት መቼም ቢሆን ባዲስ አይን ሲመረምረውና ሲያሻሽለው አንዳንድን ነጥብ ሲጨምርበት ወይም ሲቀንስበት ይችላል። ሀሳቦቹን ለሌሎች ሳይንቲስቶች ይፋ ካደረገ በኋላ፣ እነሱ ደሞ ተራቸውን የሱን ግኝት በራሳቸው አዲስ አይን አይተው ወይ ትክክል ሆኖ ያገኙትና ድጋፋቸውን ይገልፃሉ፣ ወይም እርማት ያካሂዳሉ። በሳይንስ ውስጥ ለዘወትር ጥያቄና ምርመራ ያልተጋለጠ ቋሚ ሀቅ የሚባል ነገር የለም።

ወደ ጋሊሊዮ ስንመለስ፣ እሱ ጉድ እንዳፈላ በሱ ላይ ጉድ ፈላበት። ምሁራንም ሃይማኖታውያንም ተነሱበት። አሁንም አሪስቶትል ሊመጣ ነው። ምሁራኑ «አሪስቶትል በሰማይት ለውጥ ሊኖር አይችልም ብሏል» አሉ። ጋሊሊዮ ወይም ራሱ ተሳስቷል ወይም ለገዛ ምክንያቱ የፈጠረው ውሸት ነው። አሪስቶትል ራሱ በግልፅ የፃፈውን ሀቅ እያያችሁት እየተፃረረ!

ሃይማኖታውያን ደሞ መፅሀፍ ቅዱሳቸውን ገለጡና ሰማዩቱ አይለዋወጡም ጋሊሊዮን ሰይጣን አሳስቶታል አሉ። መሬትና ሌሎቹ ፕላኔቶች በፀሀይ ዙሪያ ይሽከረከራሉ የየራሳቸውን ርቀት እንደጠበቁ። ተባለ እንዴ? ጋሊሊዮ ከጳጳሱ

ትእዛዝ የረሰው፡፡ «ያዘን ማንት የምትለውን ፈጣጣ ጠቅት በይፋ እንድትክደውና ሰይጣን አስቶኝ ነው ብለህ ንስሀ እንድትገባ ይሁን፡፡»

በ1633 ጋሊሊዮ ኢንኩዊዚሽን ችሎት ፊት እንዲቀርብ ወደ ሮማ ተወሰደ፡፡ «የስፉት ስህተቶቼን ከጃቸዋለሁ እረግሜያቸዋለሁ ጠልቻቸዋለሁ!» ብሎ በይፋ ንስሀ ገባላቸው፡፡ በእሳት መቃጠል ቀረለትና ወደ እድሜ ልክ እስራት ተሻሸለለት፡፡ ጳጳስ ኧርባን ስምንተኛ ገና ጳጳስ ሳይሆን በፊት ጀምሮ ለጋሊሊዮ የወዳጅነት አስተያየት ስለነበራቸው፤ እድሜ ይፍታህ እስራቱን አሻሻሉለት፡፡ ከቤቱ እንዳይወጣ የቤት እስረኛ ሆኖ እንዲኖር ተወሰነለት፡፡

በ1637 አይኑ እስኪታወር ድረስ ጋሊሊዮ በድሮው የሳይንቲስት ስራው ቀጠለበት፡፡ ማቴማቲክስ - አስትሮኖሚ - ፊዚክስ፡፡

ከአስትሮኖሚ ወደ ማቴማቲክስ - ፊዚክስ ምርምር ሳንወጣ፣ ጋሊሊዮ በግንባር ቀደምነት እና ለመጀመሪያ በእንቅስቃሴ እና በስበት (Gravitation and Motion) ላይ ብዙ ሳይንሳዊ ምርምርና ጥናት አካሄደ፡፡

ሳይንቲስት ነውና ለሳይንቲስቶቹ በይፋ ካሳወቀው ብዙ ነጥብ መካከል አንዷ አሪስቶትል የሚለው ልክ እንዳልሆነ የምታሳይ ሆነች፡፡ አሪስቶትል ምድራዊ የሀቅ ብርሃናቸው እና በተለይም የእንጀራቸው ምጣድ ስለሆነ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮችም በበኩላቸው በጋሊሊዮ ላይ ተነሱበት፡፡

ያን ጊዜ እጅግ የተማሩ በጣም አዋቂዎች የሚባሉት ጀዝዊት የተባለው የምንኩስና ስርዓት አባላት ደሞ «ጋሊሊዮ በነባሩ የማስተማር ስርአታችን ላይ የሚያደርሰው አፍራሽ ተፅእኖ ማርቲን ሉተር እና ካልቪን ተዳምረው ከሚያደርሱት ጉዳት ይብሳል» ብለው ከሰሱት፡፡ (John Calvin 1509-1564) ፈረንሳዊ ሲሆን ከሉተር ቀጥሎ ካልቪን የፕሮቴስታንቱ እንቅስቃሴ ዋና መሪ ነበር፡፡

የሳይንስ ዋና መሳሪያ ወይም ዘዴ የሆነውን «በሙከራ ማየትና ማሳየት» የጀመረው ወይም የፈጠረው ጋሊሊዮ ነው፡፡ እና በሀሳብ የምንደርስበትን እርግጠኛ ነት ነገ ያው ሀሳባችን ሲመረምረው ስህተት ሆኖ ሊያገኘው ይችላል፡፡

ስለዚህ ሀሳባችን የደረስበትን በአይናችን በእጃችን በሚታዩ በሚዳሰሱ ነገሮች ሞክረነው ልክ ሆኖ ስናገኘው ያን ጊዜ ነው ሳይንሳዊ ሀቅ ላይ ልንደርስ የምንችለው፡፡ በእንግሊዝኛ (the experimental method) ይሉታል..... አንዳንድ ሰዎች «ጆርዳኖ ብሩኖ ለሀቅ እሞታለሁ ብሎ በእሳት ተቃጠለ፡፡ ጋሊሊዮ ግን ያገኛትን ሀቅ ሳያንገራግር ወዲያው ካዳት፡፡ ምን ነካው?» ይላሉ፡፡

ምንም አልነካው እንደሆነስ? ሳይንቲስት ቢሆንም ሰው ነውና ከመሞት መሰንበት ይሻላል ብሎ ወስኖ ቢሆንስ?

ደግሞ ፀሀይ በምድር ዙሪያ ዞረች ወይስ ምድር በፀሀይ ዙሪያ ዞረች? እና ጋሊሊዮ ይህን አለ? ወይስ ያንን አለ? ይኼ ለጋሊሊዮ ለራሱ ምኑ ነው? የሉ

ጉዳይ የሰዎችን መጨዋወቻ መጋደል ለነሱ ትቶላቸው እሱ ተለምሯቱ
ወደማያልቀው ወደ ሳይንስ ጥናትና ምርምር መመለስ ሆነ።
ይኼ ሰውዬ ብዙ የሰይጣን ስራ የሚጠብቃቸው ሰስት ታላላቅ ሳይንቲስቶች
እውነቱ ስላሉ ለተራ ትርኪምርኪ ጂኒጀንካ ጊዜም ፍላጎትም አይኖረውም።

ሰኔ 22፣ 1989

## ሳይንስ

ከተለያዩ አንባቢያን ደጋግሞ የደረሰን አስተያየት እንዲህ ይላል- ‹እኮ ምንድ ነው እሁድ ነጋ ለንበት ጠባ ባህል ታሪክ ስነ-ፅሁፍ? ዘመኑ የሳይንስ ነው:: ስለ ሳይንስ ትንሽ ንኳ አትጥፉልንም እንዴ?’

መልካም ነው፣ ስለ ሳይንስ እንፃፍላችሁ:: ግን እኛ ሳይንቲስት ባለመሆናችን ስለ ሳይንስ ስንፅፍ ስለ ሰው መሆኑ አይቀርም:: ዘመኑ የሳይንስ ነው:: የሳይንስን ጥበብ ለሰው ጥቅም በስራ ላይ የሚያውለው የእውቀት ዘርፍ አንዱ ቴክኖሎጂ ይባላል:: ሳይንስና ቴክኖሎጂ ባይኖር ኖሮ ይኸ የምንኖርበት ዓለም ሌላ ይሆን ነበር::

አይሮፕላን፣ ሞተር፣ መርከብ፣ ባቡር፣ መኪና የለም ነበር:: ቴሌግራም፣ ቴሌፎን፣ ቴሌቪዥን፣ ሲኒማ አይኖርም ነበር:: ኤሌክትሪሲቲ ለብርሃን ይሁን ምግብ ለማብሰያ ለማቀዝቀዣ ወይም እስረኛ ቶርች ለማድረጊያ አይሆንም ነበር:: የቧምቧ ውሀም የለም:: ባጭሩ ብንናገር የከተማ ኑሮ ባሁኑ ዘመን እንደምናውቀውና እንደምንኖረው አይሆንም ነበር:: አልቤን ጠመንጃ የለ፤ መውዜር ሽጉጥ የለ፣ ካላሽኒኮቭ የለ፣ መድፍ የለ፣ ተራ ቦምብ የለ፣ ሃይድሮጅን ቦምብ የለ:: ግፋ ቢል እየሸለሉ እየፎከሩ ጦር መወርወር እና ወንጭፍ ማወናጨፍ ነበረ እንደነዳዊትና እንደነጎልያድ:: ያውም ፀሀይ ስታሽቆለቁል ውጊያው ይቆማል::

ሳይንስ ባይኖር ጠፈር ህዋ መምጠቅ የለ፤ በሮኬት መምጠቅ የለ፤ ወደ ጨረቃ ደርሶ መመለስ የለ:: ሰማያቱን በቴሌስኮፕ ማሰስ የለ፤ ለዓይን የማይታዩ ፍጡራንን በማይክሮስኮፕ አጉልቶ ማየት የለ፤ መርፌ ተወግቶ መዳን የለ፤ ቀዶ ጥገና ህክምና የለ፤ መድኃኒት ቤት ሔዶ ኪኒን መውሰድ የለ:: ሳይንስ ከሌለ ያሁኑ ዓለማችን የለም...

በምናባችን በሀሳባችን እንደ ዘመዶቻችን እንደቁንጫ ወይም እንደ ካንጋሩ ወደየአቀጣጫው እንዝለልና ሳይንስ ባይኖር ኮልፌ ገበያም የለ፣ ታይዋንም የለ፣ ሰልቫጅም የለ::

ምንድነው ያለው በዚያ ሳይንስ በሌለበት ዘመን? ምናልባት አንድ ለማንያ ያህል አባላት ያሉት ማህበረሰብ:: ሁላችንም ግል ለግል እንተዋወቃለን:: አደጋውንም መልካም እድሉንም እኩል ነው የምንካፈለው:: ዋናው አለቃ

የጉላውን እባላት አንድ በአንድ በግል ያውቃችዋል!

የአገራችን የአድማስ ስፋት የአንድ ቀን መንገድ ነው። ከዚያ ወዲያ ያለውን አገር አናውቀውም። እንደኛ ያሉ ጉሳዎች ይኖሩበት ይሆናል።

አሁንም ዘመናት እንዝለልና ሰው ሰውነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉሳ ጉሳን እየጠቀለለ፣ ነገድ ነገድን እየጠቀለለ ይሄድ ይሄድና የት ይደረሳል? አለቅየው እንደቀድሞው ህዝቡ ግን ሃያ ሰላሳ ሚሊዮን ይሆናል። ዘመን ተለወጠ። አለቅየው ህዝቡን የሚመራው ከሩቅና በቁጥር በስታቲስቲክስ እንዲሁም ልዩ ልዩ የባለሙያ ኮሚቴዎች በሚያወጡለት በዓመታዊና አስር ዓመታዊ ብሔራዊ እቅዶች ይሆናል። እሱ የሚመራው ህዘብን እንጂ ግለሰቦችን አይደለም። ግለሰቦችን የት ያውቃቸውና? ከዚህ የሚቀጥለው የሳይንስ ታሪካችን ሲዘረጋ የሰው ልጅ እዚህ ከሩቅና በሚልዮናት አንድ መሪ የሚያንቀሳቀስበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ሰስቱ ዋና ገፀ ባህሪዎቻችን ማርቲን ሉተር፣ ጆርዳኖ ብሩኖ እና ጋሊሊዮ ጋሊሰይ ናቸው። በየበኩላቸው የሚሊዮናት መሪዎች ናቸው።

<u>ሁለት</u>

## ማርቲን ሉተር (Martin Luther)

(1483 - 1546) ምዕራባዊውን ዓለም ከቀረፁት ታላላቅ ሰዎች አንዱ ነው። በጣም ከልቡ ክርስቲያን ነው እጣው እድሉ ሆኖበት የአውሮፓ ክርስትናን ለሁለት ሰነጠቃት እንጂ። ሰሜኑ ፕሮቴስታንት ደቡበ ካቶሊክ ሆነ።

ሉተር በ1505 የሕግ ትምህርት ጀመረ። አንድ ቀን በጣም ሀይለኛ የሆነ አውሎ ነፋስ ተነስቶ ማርቲን ሉተር ከመሞት ለትንሽ አመለጠ። ይህ ገጠመኝ ከሞተ ያተረፈውን እግዚአብሄርን ለማገልገል ሲል እንዲመነኩስ አስወሰነው።

በ1507 የአውጉስጢኖሳዊያን ባህታዊያን (Augustinian Hermits) አባል ሆኖ መነኰሰ። በ1511 የስነ ሃይማኖት (ቲዮሉጂ) ዶክተር ሆኖ ተመረቀ የብሉይና ሃዲስ መፅሀፍት መምህር ሆኖ ተሾመ።

በ1510 ይህ ሃይማኖታዊ መነኩሴ ለስራ ጉዳይ ወደሮማ ተላከ። እዚያ ጉድ አየ! የሮማው ጳጳስና የከበሩት የክርስትና ቁንጮዎችና መሪዎች ኃላፊነታቸውን ወድያ ጥለው በሃይማኖት ንግድን እንደ ዋና ተግባራቸው ይዘውታል። ማርቲን ሉተር በዚህ የክርስትና መሪዎች መበላሸት ሲቆጭ ሲመረር ሲያስብ ሲፀልይ ሰባት ዓመት ካሳለፈ በኋላ በ1517 ቪተንበርግ (Wittenburg) ከተማ ቤተክርስቲያን በር ላይ ዘጠና አምስት አንቀፆች (Ninety - Five Theses) የሚል የተፃፈበት ረዥም ወረቀት ለጠፈ። ሰው ሁሉ እንዲያነበው። የቤተክርስቲያኒቱን ዘጠና አምስት ግድፈቶች ወይም ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች ይዘረዝራል ወረቀቱ። የቪተንበርግ ሰዎች እነዚህን ዘጠና አምስት ግድፈቶች እየገለበጡ በመላው አውሮፓ - በተለይም በሰሜን አውሮፓ - አደረሱዋቸው።

ያነበቡዋቸው ሁሉ እውነት ሆነው ስላገኙዋቸው የፕሮቴስታንት ንቅናቄ ተጀመረ::

የአውሮፓ ነገስታት ሁሉ የሚታዘዙት የሮማው ጳጳስ ለሳክሰኒ ንጉስ ለፍሬደሪክ ሶስተኛ ማርቲን ሉተርን ለፍርድ ወደ ሮማ ይልከለት ዘንድ አዘዘው:: ንጉስ ፍሬደሪክ እምቢ አለ:: ጳጳሱ ለማርቲን ሉተር ላከበት «ንስሀ ለመግባትና የለጠፍካቸውን ዘጠና አምስት ነጥቦች ከደህ ተሳስቼ ነው ብለህ ለመናዘዝ ስልሳ ቀን ተሰጥቶሀል» ማርቲን ሉተር አሻፈረኝ አለ:: በ1521 ጳጳሱ ማርቲን ሉተርን አውግዞ ከክርስቲያን መዝገብ ሰረዘው:: ዉጉዝ ከመአርዮስ እንደምንለው::

ማርቲን ሉተር ለህይወቱ ስለፈራ ሸሽቶ አንድ ቤት ውስጥ ተሸሸገ ለስምንት ወር ኖረ:: በዚህ በስምንት ወር ውስጥ መፅሀፍ ቅዱስን ለህዝቡ ከማይገባቸው ከላቲን ቋንቋ አንብበው ሊረዱት ወደሚችሉት ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ ተረጎመው:: ተተረጎመ፣ ታተመ፣ ተሰራጨ፣ ተነበበ::

ማርቲን ሉተር አዲስ ሀይማኖት መሰረተ:: መመልከስ የለም አለ:: ወንድና ሴት አርጎ የፈጠረን ብዙ ተባዙ ብሎ ነው እንጂ መንኩሱ ገዳም ግቡ ብሎ አይደለም:: መነኩሴ የነበረው ማርቲን ሉተር ራሱ አንዲቷን መነኩሲት የነበረች ሴት አገባና ስድስት ልጆች ወልደው አሳደጉ:: የካቶሊክ ቄሶች ድንግላውያን ናቸው፣ ማርቲን ሉተር ግን ቄሶችም ሰው ናቸው አግብተው መውለድ ማሳደግ ይገባቸዋል አለ::

እኛ መፅሀፍ ቅዱስን በቀጥታ ስናነበው የእግዚአብሔርን ቃል እንሰማለን፡ ከቃሉ ጋር በቀጥታ በእምነትና በፀሎት እንገናኛለን እንጂ አማላጆች አስተርጓሚም አያሻንም፣ ንስሀ የምንገባውም በቀጥታ ለእግዚአብሄር እንጂ ለቄስ አይደለም::

ሳይንስ ባይኖር የዓለም ጦርነት የለም:: የሙሶሎኒ ቡፋም የለ:: የፋሽስት ወረራም የለ:: የአርበኞች ተጋድሎም የለ::

ሳይንስ ባይኖር ማርቲን ሉተር መፅሀፍ ቅዱስን ወደ ጀርመንኛ ተርጉሞ ባላሳተመው ነበር:: ፕሮቴስታንት ሃይማኖትም ባልተወለደ ነበር:: ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም ለሁለት ባልተሰነጠቀች ነበር::

የሰው ልጅ ገና ጧት ከእንቅልፉ ሲነቃ ጀምሮ በሳይንስ እውቀት ውጤቶች የተከበበ መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል:: አንሶላው፣ ብርድ ልብሱ፣ አልጋው፣ ፍራሹ - እነዚህ ወይ በፋብሪካ ተሰርተዋል ወይ በመኪና ተጭነው መጥተዋል፡ በቀጥታ ይሁን ወይም በተዘዋዋሪ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እጅ አለበት::

ለቁርስ የሚቀርብልን ሹካ ማንኪያ ቢላ ሳህን ዳቦ ሻይ ቡና ወተት እንጀራ እንቁላል ወዘተ:: እነዚህ ወይ በፋብሪካ ተሰርተዋል ወይ በመኪና በአሮፕላን ተጭነው መጥተዋል:: ሳይንስና ቴክኖሎጂ::

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ከበውናል፣ ይንከባከቡናል:: ሳይንስ እ

ዛሬው መላው አለም የሚያምነውና የሚከተለው አለማዊ ሀይማኖት ሳይሆን በአዲስነቱ በልጅነቱ ዘመን እንደማንኛውም ሀይማኖት ነብያቱና ሀዋርያቱ ተንከራትተውለታል:: ተሰቃይተውለታል:: ተሰውተውለታል::

ከነዚህ የሳይንስ ነቢያትና ሀዋርያት አንዱ ጆርዳኖ ብሩኖ ይባላል:: Giordano Bruno (1548-1600) የኖረበት ዘመን (late renaissance) የኋለኛው ዳግማዊ ልደት ይባላል:: ጥንታዊው የግሪክና የሮማ ብርሀን ጨልሞ ብዙ ዘመን ካለፈ በኋላ የእውቀት ብርሀን እንደገና የነጋለት ዘመን ነው:: እጅግ ደማቅ የሆኑት ብርሀናት አንዱ የሆነው ጆርዳኖ ብሩኖ የቅዱስ ዶሚኒክ ገዳም መነኩሴ ነበረ:: (ማርቲን ሉተር መነኩሴ ነበር)

ይህ ጆርዳኖ ብሩኖ ለሚያምንበት እውነት ሁልጊዜ በይፋ የሚመሰክር ሀቀኛ ግትር ሰው ነበር:: ያ በሄደበት የሚሰፍፈው እውነት ደግሞ ሲበዛ ወግ አጥባቂ የነበሩትን የሀይማኖት መሪዎች የሚያስቆጣ በመሆኑ ጆርዳኖ ብሩኖ ከአንዱ አውሮፓዊ ከተማ ወደ ሌላው እየሸሸ ብዙዎቹን አዳረሰ::

በ1576 መናፍቅ ነው ተብሎ ስለተጠረጠረ እና ነፃነቱም ህይወቱም ለአደጋ ስለተጋለጡ ናፖሊ ከተማን ለቆ ወደ ሮማ ሸሸ:: እዚያም የራሱን እውነት እያስተማረ ለሁለት አመት ባለስልጣናቱን ሰላም ከነሳቸው በኋላ ትዕግስታቸው ማለቁን ሲያውቅ በ1578 ወደ ጀኔቫ ሸሸ:: እዚያም ደርሶ ሀቁ ስላስገደደው የቅዱስ ዶሚኒክ ገዳም የመነኩሴ ልብሱን አውልቆ ወድያ ጣለውና የማተሚያ ቤት አናባቢ (ፕሩፍ ሪደር) ሆኖ ተቀጠረ:: ፕሩፍ ሪደር ጆርዳኖ ብሩኖ የታየውን ሀቅ በይፋ የማወጅ ባህሪዩን ስለ ቀጠለበት የሀይማኖት መሪዎቹን ትእግስት አስጨርሶ በ1581 ወደ ፓሪስ ለመሸሽ ተገደደ::

በዚህን ጊዜ አውሮፓውያን ምሁራን ሁሉ የጆርዳኖ ብሩኖን ሀቆች በሰላ ጆሮ እያዳመጡዋቸው ነው:: ከነዚህም አንዱ የፈረንሳዩ ንጉስ ሄንሪ ሳልሳዊ ጆርዳኖ ብሩኖን ፓሪስ እስካለ ድረስ አስተናገደው::

ጆርዳኖ ብሩኖ በሄደበት ሁቆቹን ማወጁን አልተው አለ፤ ሲቃን ቀሳውስቱም በቅጣት ዝም ለማሰኘት መሞከራቸውን ቀጠሉበት:: በ1583 ወዳጁ ንጉስ ሄንሪ ላከውና ኦክስፎርድንና ለንደንን በመምህርነት ጐበኘ::

«እነኚህ የኛ ሰማያትና ምድራችን ብቻ አይደሉም ያሉት:: ለዘለአለም ስንቆጥር ብንኖር ቆጥረን የማንጨርሳቸው አለማትና ሰማያት አሉ» ይላል ጆርዳኖ ብሩኖ:: ምነው አይቆጡ ቀሳውስቱ፤ ዝም ሊያሰኙትስ ምነው አይሞክሩ፤ እንደ ቀበሮ እያመለጣቸው ከከተማ ከተማ እየዞረ እያስተማረ ጉዳናቸውን የሚወጋ እሾህ ሆነባቸው::

በ1586 ጆርዳኖ ብሩኖ በአሪስቶትል ሀሳቦች ላይ ተቃውሞ ሰንዝረሀል ተብሎ እስራትና የመሳሰሉ አደጋ ሊደርስበት ሲሆን ጊዜ ፈረንሳይ አገርን ለቆ መሸሸግ ግድ ሆነበት:: እዩልኝ እንግዲህ፤ ይህ የሚደረገው በ1586 አመተ

ምህሬት በክርስቲያን አገር ነው:: አሪስቶትል ግን በአምስተኛው መቶ አመት ከክርስቶስ በፊት በአቴንስ ከተማ የኖረ የፍልስፍና አስተማሪ ነው:: በሁለቱ መካከል የሁለት ሺ አንድ መቶ አመት ርቀት አለ:: የክርስትና ቄሶች ምን ሲያገባቸው የጣኦት አምላኩ ህዝብን ፈላስፋ እንዲህ ተቆረቆሩለት? የእንጀራ ጉዳይ ሆኖባቸው ነው:: በታሪክ ሂደት የመጣ አሪስቶትል በአውሮፓ ዩኒቨርስቲዎች በሙሉ የሚቆጠረው የሳይንስና የፍልስፍና ምንጭ ተደርጉ ነው:: ከእግዜር በታች የእውቀትና የሳይንስ የፍልስፍና አምላክ አሪስቶትል ነው ለማለት ምንም አይቀራቸውም ነበር::

ያ በጥባጭ ጆርዳኖ ብሩኖ ደሞ አሪስቶትልን በሳይንቲስት መነፅር አንብቦ ተንተነው እና አንዳንዶቹን የአሪስቶትል ነጥቦች ወይም ሀሳቦች ብትንትናቸውን አወጣቸው:: ቆይማ ቀኑን ይጠብቅ! የሚገባውን ቅጣት ያገኛል::

ከከተማ ከተማ እየነጠረ የቼኮዝላቫኪያ ዋና ከተማ ፕራግ (Prague) ደረሰ:: እዚያ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ጆርዳኖ ብሩኖን ከክርስቲያን መዝገብ ሰረዘችው:: በኛ ውጉዝ ከመ አርዮስ እንደሚባለው አይነት::

በ1591 አንድ የጣሊያን መኳንንት ጆርዳኖ ብሩኖን ና ከኔ ጋር ትኖራለህ ብሎ ወደ ቬኑስ ከተማ ጋበዘው:: በ1593 ይኸው መኳንንት ወደ ኢንኩዊዚሽን Inquisition ባለስልጣናት ሄዶ ጆርዳኖ ብሩኖን እስከ ሞት ቅጣት የሚያደርስ መረጃ አቀረበላቸው:: ጆርዳኖ ብሩኖ ታሰረና ለፍርድ ሮማ ወደ አለው ኢንኩዊዚሽን ፍርድ ቤት ተወሰደ:: እዚያ ተፈረደበትና ሰባት አመት በእስር ቤት ማቀቀ::

ስለዚህ ስለ ኢንኩዊዚሽን አጭር ገለፃ ያስፈልጋል:: መነኩሴው ማርቲን ሉተር የአውሮፓን ክርስትና ለሁለት ሲገምሱት ጊዜ ካቶሊካዊው ግማሽ ሲበዛ ተደናገጠ:: እቺው የቀረችው ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በየስርቻው የማርቲን ሉተር ብጤዎች መናፍቃን እንዳታበቅል ፈሩ:: ቀሳውስቱና ምሁራኑ እነዚህን መናፍቃን እንደ አረም እየመነጠሩ ማቃጠል የክርስቲያን ተግባር ነው ተባለ::

ጳጳሳዊው ኢንኩዊዚሽን በጳጳስ ግሬጎሪ ዘጠነኛ ተቋቋመ:: አሰራሩም እንዲህ ነበር:: የኢንኩዊዚሽን መርማሪዎች በአንድ አካባቢ ይደርሳሉ:: የአካባቢው ኗሪዎች ልክውባቸው ወይም መርማሪዎቹ ፕሮግራማቸው ወደዚህ አካባቢ እንዲመጡ አድርጉአቸው ሊሆን ይችላል::

መርማሪዎቹ መጥተው ችሎት እንደተቀመጡ እገሌ መናፍቅ ነው የሚል ወሬ የቀርባሉ:: ወሬ አቀባዮቹ ሁለት ከሆኑ ወሬያቸው እገሌ በተባለው ግለሰብ ላይ ክስ ለመስረት በቂ ነው:: በዚያውም አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ወሬ ያቀበሉበት ሁለት ሰዎች ማን እንደሆኑ ተከሳሹ አያውቅም::

ተከሳሹ ጥፋቱን እስካላመነ ድረስ ሊፈረድበት አይችልም:: ስለዚህ፣ እስኪያምን ድረስ ይገረፋል:: ልክ ባሁኑ ዘመን ቶርች እንደምንለው በውሸት

ተሰኑኑ ቢሆንም ከስቃዩ ለመገላገል ሲል ያላጠፋውን ጥፋት ያምናል። እንደ ጥፋቱ ክብደት ታይቶ ወይ የዓመታት እስራት ወይ እድሜ ይፍታህ እስራት ወይም ሞት በእሳት ይፈረድበታል።

ቤተክርስቲያን ሕግዋ ሰው መግደል ስለሚከለክል የፈረዱበትን እንጊን በስነስርዓት ሬግመውት ለህዝብ እሣት ዳርገውት ሲያበቁ እንደ ዳመራ በእሣት ይቃጠል ዘንድ ለመንግስት ያስረክቡታል። ሕዝብ በተሰበሰበበት በአደባባይ ተከሳሽ ይቃጠላል።

ተከሳሽ ከፈለገ መውጫ ተመቻችቶለታል ይናዘዛል። ልክ ነው አጥፍቻለሁ፤ ሰይጣን አሳስቶኝ ነው እንጂ እኔ ግን ከእንግዲህ አይለመደኝም፤ ወደ እውነተኛ ካቶሊካዊ እምነት ተመልሻለሁ ይላል። ንስሐውን ይቀበሉና ይህን ያህል ገንዘብ ለድሆች መፅውት ብለው ይምሩታል።

አሁን ወደ ጀግናው ወደ ጆርዳኖ ብሩኖ። መርማሪዎች በጣም የፈለጉት ጥፋት አጥፍቻለሁ ብሎ ንስሐ ገብቶ ምህረት እንዲያገኝ ነበር። እሱ ግን በሀቂ የመጣ ወይ ፍንክች አለ። የሰባት ዓመት ሙሉ እስራት ውሳኔውን ሊያስቀይረው አልቻለም። ቀሳውስቱና ሊቃነ ቀሳውስቱ ለመጨረሻ ጊዜ ትዕግስታቸው አለቀ። መርማሪው ኢንኩዊዚሽን ሞት ፈረደበት። አሁንም ተው ምህረት ይሻልሀል ተባለ።

ጆርዳኖ ብሩኖ ግን ሀቅ ሀቅ ነው ለሀቂ እሞታለሁ አለ። በፌብሩዋሪ 17 ቀን 1600 ዓመተ ምህረት ጆርዳኖ ብሩኖ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ በእሣት ተቃጥሎ ሞተ። አድናቂዎቹን አማኞቹን እና መሰሎቹን የሚያኮራ አኗኗርና አሟሟት ነበር።

ሰኔ፣ 15 1989

## ❧ 6 ☙

# ኤድጋር አላን ፖ
# *Edgar Allan Poe*



እውስጣችን ሁሌ የሚኖረው ኤድጋር አላን. ፖ. (Edgar Allan Poe) በ1809 በቦስተን ከተማ በማሳቹሴትስ ስቴት ተወለደ:: አሺ እዚህ አገራችን ላልታወቀ ምክንያት ማንም ጋዜጣ መፅሔት ወይም የመቃብር ድንጋይ (እብነበረድ!) የሚለውን እንበል:: የባህል ትሁት መንጋዊ ተከታይ እንሁንና ይኸው እንንገራችሁ:: በዚያ ጊዜና ስፍራ ኤድጋር አላን ፖ የተወለደው ካባቱና ከናቱ ነበር:: ሌላ ከማ ሊሆን ኖሯል?

ይሄ ሰውዬ እንደ ሌሎቻችን ካባትና ከናቱ ተወለደ'ንጂ የኖረው ኑሮ እና የሰራው ስራ ግን ሌላ ነበር:: ሌላ ሌላ! ልዩ ሌላ የሚያደርጉትን ነጥቦች እስቲ ጆብዱ ወይም ገድል ያልነበሩ ይመስል በተራ ፊደላት በስድ ንባብ እንጣፋቸው::

ሀ/ ኤድጋር አላን ፖ ከማናቸውም አሜሪካዊ ደራሲ የበለጠ በውጭ አገር የታወቀና የተወደደ ነው:: ለስራዎቹ የተከፈለው ገንዘብ ግን እቺን እምቢ የማንላት ሆድ ለማስታገስ ያህል እንኳ በቅቶት አያውቅም:: ሰውየው እጦት የሚሉት የዘመናችን ቺስታነት እጅግ ተወዳጅ ልጁ ነበር - ለአንድ ዓመት ያህል እንኳ ተለይታው አታውቅም:: እሱ የአለም ስነፅሁፍ ሀብት ቢሆን እጦት ግዱ ነው? ስትወደውስ?! ፖ አጫጭር ልቦለዶቹም ግጥሞቹም እያንዳንዳቸው ጥልቀት

የእሱ ጥበብ ናቸው፡፡ የነገ የቀላት ጠቢብ ወይም የቀላት ምትሀተኛ መሆኑን ቀድመው በማንበብ የተረዱለትና የመሰከሩለት ግን አሜሪካውያን ሳይሆኑ እንዱ ፈረንሳዊ እንዱ እንግሊዛዊ ናቸው፡፡ በድሌር (Beaudelaire) የዘመናዊው ፈረንሳዊና ስነግጥም ፈር ቀዳጅና ወደር የሌለው ባለቅኔ ነው፡፡ የኤድጋር ፖ ስራዎችን በድሌር እንዳነበባቸው ወዲያው ተደንቆባቸውና የኤድጋር ፖ መንፈስ ስለደረሰበት ይበል በሚያሰኝ ፈረንሳይኛ ተረጎማቸው፡፡

ከዚያም ገዜ ወዲህ ፈረንሳዮች ለኤድጋር ፖ ዘላቂ ፍቅር አደረባቸው፡፡ ዛሬም ኤድጋር ፖ ፈረንሳዮች ከሚያነቡዋቸው አንቱ ደራሲያን አንዱ ነው፡፡ አሜሪካኖች እየረሱት የነበረውን ደራሲያቸውን እድሜ ለበድሌር ከፈረንሳይ አገር «አስመጡት» እና መልሰው የራሳቸው አደረጉት፡፡ «ነብይ በአገሩ አይከበርም» አላለም ሰውየው? በእጅ የያዙት ወርቅ የመዳብ ያህል ነው አላሉም አበው፣ እመው?

አርቲስትን አገር ወይም ቋንቋ አይወስነውም፡፡ ወፍን ቀበሌስ ይሁን፣ ወንዝስ ይሁን፣ አገርስ ይሁን ይወስናታል? ኧረ ከቶ!

ኮናን ዶይል የፈጠረውና በአለም ደረጃ ከማንም የግል ዲቴክቲቭ (የወንጀል መርማሪ) ቀድሞና ሁልጊዜም ጎልቶ ደምቆ የሚታየው ሸርሎክ ሆምዝ Sherlock Holmes እንዲያም ሆኖ ግን በአለም የመጀመሪያውን የዲቴክቲቭ አጭር ልቦለድ የጻፈው ኤድጋር አለን ፖ ነው፡፡ ኮናን ዶይል ራሱ እንዲህ ሲል መስክሯል «እኔ የዲቴክቲቭ ልቦለድ መፃፍ የተማርኩት ከኤድጋር አለን ፖ ነው፡፡»

The Murders in the Rue Morgue «የነብስ ግድያዎች በሞርግ ጎዳና» የተባለውን የፖ አጭር ልቦለድ ስናስብ ልክ እንዲያው ቁርጥ «ኮናን ዶይል የጻፈው ይመስላል፡፡ ብቻ ዲቴክቲቩ እና ጓደኛው ፓሪስ የሚኖሩ ፈረንሳዮች ናቸው፡፡ እንጂ ከስማቸው በስተቀር ያው ሸርሎክ ሆምዝ እና ጓደኛው ዋትሰን ናቸው፡፡

ከዚያ በኋላ እኮ ስንትና ስንት የዲቴክቲቭ ልቦለድ ወይም ተውኔት (ትያትር) ወይም ፊልም ተተርጓል፡፡ ያ ሁሉ የተንገረገረው የወይን ዘለላ የበቀለው ኤድጋር አለን ፖ ከዘራት ብቸኛ አጭር ልቦለድ ነው፡፡ ምን ታረገዋለህ? እንደ ምድር አሸዋ ወይም እንደ ሰማይ ኮከብ ዘርህን አበዛዋለሁ የተባለው አብርሃምምኮ ከአብራኩ አንድ ልጅ ብቻ ነው የወለደው፡፡ ልክ እንዲሁ ለኤድጋር አለን ፖም አንድ ልጁ መፅሀፍ ነው፡፡ የልጁም ስም «የነብስ ግድያዎች በሞርግ ጎዳና» ይባላል፡፡

ለ/ የኤድጋር አለን ፖ አጦት የገንዘብና የምቾት ብቻ አልነበረም፡፡ አባቱና እናቱ በምስራቅ ዩናይትድ ስቴትስ ከከተማ ከተማ ከሆቴል ሆቴል እየተዘዋወሩ መድረክ ላይ ትያትር የሚጫወቱ ተዋንያን ነበሩ፡፡

አንድ ቀን ኤድጋር ገና የዘጠኝ ወር ህፃን እያለ አባቱ ከቤት እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ። የት ሄደ? ምን አገኘው? አይታወቅም። ሚስዝ ፖ ሁለት ህፃናትና አንድ ሽል በማህፀንዋ ተሸክማ ቀረች። እቺ የፈረደባት እናትም ኤድጋር ገና የሁለት ዓመት ጨቅላ እያለ ሞተች።

ጆን አለን የተባለ ሰውዬ ኤድጋርን ሊያሳድገው ወሰደው። ያሳድገው እንጂ ፍቅር ግን አልሰጠውም፤ ሚስዝ አለን ነበር እንደ እናት ያፈቀሩት። መሀን ስለነበሩ ኤድጋርን ልጃቸው አደረጉት። ጉረምሳው ኤድጋር አላን ዩኒቨርሲቲ ገባ። እዚያ መጠጣትና ቁማር መጫወት አዘወተረ። ኤድጋር ብዙ የቁማር እዳ ተጠራቀመበት። የከተማው ባለሱቆች ሚስተር አለን ሀብታም ስለሆነ የልጁን እዳ ይከፍላል በማለት የሚያስፈልውን ሁሉ ለኤድጋር በዱቤ ይሰጡት ነበር። እዳ በእዳ!

ሐ/ ሚስተር አለን እዳ የከፈለው ከነጋዴዎቹ የወሰደውን ዱቤ ብቻ ነው። ስዚያውም የራሱን የሀብታም ክብር ስመጠበቅ ሲል ነው። ከዚያ በኋላ ኤድጋር አላን ፖ በአስራ ስምንት ዓመት ልጅነቱ ብቻውን ቀረ። ጠጪ ሆነ። ጭልጥ ብሎ እስኪሰክር ይጠጣል። ሰዎች ስለሱ ሲያወሩ ወሬያቸው እንዲሞቅላቸው ስለጠጪነቱ ደጋግመው ያወሩ ገቡ። ቀስ በቀስም ሁል ጊዜ በየእለቱ ይሰክራል የሚል ግማሽ ተረት ስሙን ከበበው እንጂ እሱስ ሲነሳበት ስወራት ያህል መጠጥን እርግፍ አርጎ ይተዋል። ያን ጊዜ ነው እንደ ምትሀት የማይታመነውን የሚያሳምኑን ልባለዶቹንና ግጥሞችን የሚፅፋቸው። የታተሙት ግን በመፅሄቶች እንጂ ተሰብስበው በመፅሀፍ ቅፅ ስላልሆነ እየተረሱ ሄዱ። ቦድሌር ምስጋና ይግባው ነጥረው ከፍራንስ መጥተው ሲያበቁ እንደገና የአሜሪካውያን ቋሚ ዘላቂ ሀብት ሆኑ።

መ/ ስራዎቹ በመፅሄቶች ሲታተሙ ግን የመፅሄቶቹ አዘጋጅ ማን ነበር? ኤድጋር አላን ፖ ራሱ ነዋ! እዚህ ላይ ትረካችንን በቅደም ተከተል እንሂደው።

በታሪካዊ ማስተካከያ እንጀምር። በዚያን ዘመን በነበረው ግማሽ ኋላቀር የአሜሪካን ኢኮኖሚያዊ አቅም አንድ ደራሲ ሊፅፍ የሚችለው ሁለት አስፈላጊ ሁኔታዎች ሲሟሉለት ብቻ ነበር። አንደኛ ለእንጀራ ደሞዝ የሚሰራው ከድርሰት ጋር የማይገናኝ ስራ ግን በቂ ለመኖር የሚያስችለው እና የስራ ሰዓቶቹ ጥቂት ወይም የሙሉ ቀን ስራን ግማሽ የሚሆኑ። በተቀሩት ሰዓቶች ስለሆነ እና ስለ ቺስታነት ሳይጨነቅ ፈጠራውን ማካሄድ እንዲችል።

በዚህ አገር አቀፍ ሁኔታ ውስጥ ነበር ኤድጋር አላን ፖ እፅፋለሁም በፖ [illegible] ስራዎቼም እንጀራዬን አገኛለሁ ብሎ የተነሳው። ተሞክሮ የማያውቅ አልፎ አልፎ ግን የኤድጋር ተፈጥሮው ተሞክሮ ባያውቅም አንተ ትችለዋለህ የሚለው ይመስላል።

በየወሩ ወይም በየሁለት ወሩ የሚታተሙ መፅሄቶች ናቸው ያሉት።

እና ኤድጋር አላን ፖ ለአራት የተለያዩ መፅሄቶች አዘጋጅ ሆኖ ሰርቷል። አራቱም በሱ አዘጋጅነት ጊዜ ጥራታቸው ስለጨመረ የአንባቢያን ብዛትም እጅጉን ጨመረ።

ይሄ ቺስታኑትን የሚያውቋት አንባብያን ታቦት ሊቀርፁለት የሚገባው ሰውዬ ምንም ሳያልፍለት አለፈ። እዚች ምድር ላይ አርባ ዓመት ተንከራተተ።
... «ሺ ከመናገር አንድ ማሳየት» ይባላል በቻይና።

መስከረም 18፣ 1990

# ፀ 7 ☙

# ኮናን ዶይል
# *Conan Doyle*



(በአስራ ዘጠነኛው ምእት) በለንደን ከተማ አርተር ኮናን ዶይል /Arthur Conan Doyle/ የተባለ ደራሲ እና እሱ የፈጠረው ገፀ ባህሪ እጅግ ሲበዛ ተወዳጅ ሆኑ:: ደራሲው ኮናን ዶይል ግን በበኩሉ ገፀባህሪዩን ሸርሎክ ሆምዝን ስራ አስፈታኝ ብሎ ጥምድ አርጎ ያዘው:: የመጀመሪያ ፈጠራው፣ እንደሚሉትም የበኩር ልጁ ነውኮ:: **እንዲያውም** ሊገድለው ከትልቅ ገደል ላይ የመቀመቅን ያህል የሚያስፈራ **ርቀት ወርውሮታል**:: ግና ሸርሎክ ሆምዝን መግደል መች እንዲህ **ቀላል** ነው? እስቲ ወደ አጀማመራቸው ልውሰዳችሁ...

ኮናን ዶይል የህክምና ዲግሪውን ተቀብሎ ክሊኒክ እንደከፈተ ወራት፣ ገና ጀማሪ በመሆኑ በሽተኛ የሚመጣለት በጣም አልፎ አልፎ ብቻ ስለነበረ ጊዜ ለማሳለፍ ሲል ጥቂት አጫጭር ልቦለዶች ፃፈ:: የሁሉም ገፀ ባህሪያቱ ሁለት አብረው የሚኖሩ ጓደኛሞች ናቸው:: ዋናው ገፀ ባህሪ በግሉ ተነሳስቶ የለንደንን ወንጀለኞች ሊዋጋ የጀመረ እልኸኛ ቆፍጣና ነው (Sherlock Holmes) ሸርሎክ ሆምዝ የተባለ:: ሁለተኛው ገፀ ባህሪ እንደ ፈጣሪው እንደ ኮናን ዶይል ሀኪም የሆነ /Watson/ **ዋ**ትሰን የተባለ ነው:: ታሪኮቹን ሁሉ የሚነግረን እሱ ነው::

ደራሲው ኮናን ዶይል ዩኒቨርሲቲ በሚማርበት ዘመን እጅግ በጣም የሚያደንቃቸው የኬሚስትሪ ፕሮፌሰሩ ነበሩ:: የሎጂክ (ተጠየቅ) አጠቃቀማቸው

ሁል ጊዜ ይገርመዋል። ገፀባህሪዬ ሸርሎክ ሆምዝ እንዲህ ስሙንና መልኩን ለውጦ ነው እንጂ የፕሮፌሰሩን የምላጭ አንጉላቸውን ግን እንዳለቱ ወርሷታል።...

... በነገራችን ላይ፤ ልቦለድ ውስጥ የሚያጋጥሙን ገፀባህሪያት አንዳንዶቹ የፈጠራ ሳይሆኑ ስምና መልካቸውን የለወጡ ደራሲው ቀደም ሲል አብሮ የሚያውቃቸው የእውነት ሰዎች ናቸው። ደራሲው የዝጊርን ድርሰት እንዘ ለኛ በፅሁፍ አቀረበልን እንደማለት።...

...(The Strand) ዘ ስትራንድ የሚባል የለንደን ወርሀዊ መፅሔት ነበረ። አሜቹር ልቦለዶችን ያስተናግዳል። የሸርሎክ ሆምዝን ታሪኮች አከታትሎ በየወሩ ሲያቀርብ ጊዜ አንባቢዎች ሸርሎክ ሆምዝን በጣም ከመውደዳቸው የተነሳ መፅሔቱ በሚሸጥባቸው መደብሮች ሳያመልጣቸው ልሻማ በሚል ረዥም ሰልፎች ላይ ቆመው መጠበቅ አመጡ። በአንድ አመት የወጡት ታሪኮች አንድ መድብል (ስብስብ) ሆነው ታተሙ። የሸርሎክ ሆምዝ ዝና በእንግሊዝኛ ተናጋሪው አለም ተናኘ ሰፈነ።

ኮናን ዶይል ደሄ ሸርሎክ ሆምዝ በቃኝ ከእንግዲህ ቁምነገር ያላቸው መፅሀፍት ነው ልደርስ የምፈልገው ብሎ ወሰነ። ዳሩ ምን ይሆናል የስትራንድ መፅሄት አዘጋጅ ክሊኒኩ ድረስ መጣና አባክህን እንዳለፈው ለሚቀጥለው ዓመት በየወሩ አንድ የሸርሎክ ሆምዝ ታሪክ ፃፍልን አለው። ኮናን ዶይል ሰውን ማስቀየም የማይወድ ሲበዛ ጨዋ የሆነ እንግሊዛዊ ጀንትልማን ስለነበረ አዘጋጁን እምቢ ሊለው አልፈለገም። እምቢታው ከአዘጋጁ ይምጣ ብሎ በማሰብ ሃያ አምስት ፓውንድ ትከፍሉኛላችሁን?

አዘጋጁ ለሰከንድ እንኳ ሳያመነታ እንከፍልሀለን አለው። ኮናን ዶይል ቃሉን ማጠፍ የማይሆንለት እውነተኛ ጀንትልማን ስለነበረ እንግሊዞች ለሁለተኛ ዓመት በየወሩ አንድ የሸርሎክ ሆምዝን የጭንቅላትም የጡንቻም የተኩስም ጀብዱ ከመከመ ተሰልፈው አየገዙ። እነዚህ አስራ ሁለቱም በአንድ መፅሀፍ ታትመው ተሰራጩ።...

... ሸርሎክ ሆምዝ ረቫፍም ነው። ቀጠን ዘለግ ያለው ሰውነቱ ያምርበታል። አንድ ቀን አንድ የገደል ቅራፊ የሚያክል አስፈሪ የሆነ ሰውዬ እቤታቸው ድረስ ይመጣና ፊቱ በንዴት ቀልቶ «የትኛችሁ ናችሁ ሸርሎክ ሆምዝ? አንተ ነህ? ባል በኔ ጉዳይ ገብተህ መፈትፈቱን ከዚች ደቂቃ ጀምረህ እንድታቆም። አስጠነቅቃለሁ» ይልና በትር የሚያክለውን ከነሀስ የተሰራ የእሳት መቆስቆሻ ብድግ አድርጎ በትከሻው አኑሮ በሁለት እጆቹ ወደፊት በአንገቱ ወደ ኋላ ለመግፋት ወይም ቀ አስመስሎ መሀሉ ላይ እንደ ከዘራ አጉብጦ ወለሉ ላይ ይጥለውና «እንደዚህ ብረት ነው እማጣምምህ!» ብሎ ወጥቶ ይሄዳል። እቤት የጡንቻ ያለ

ሸርሎክ ሆምዝ ይነሳና «እስቲ የጉበጠውን እናቅናው» እያለ እንደዚሮ

ሰጡዩ አድርጉ በእጆቹና በአንገቱ ተቃራኒ ግፊት ያቃናዋል:: ከማንኛው ማትና ቱ እጅግ የበለጠ ጡንቻ ይጠይቃል::

ሸርሎክ ሆምዝ ወንጀልን ለመዋጋት ታጥቆ የተነሳ በመሆኑ (ቦክሰር ነው፤ ሆም በዱላ ምክቶሽ ማንም አይችለውም፤ ቢያስፈልግ በሻምላም ይፋለማል።

አንዳንድ ቸኦ ሰሞን በለንደን በቂ አስቸጋሪ ወንጀል ካልተፈፀመ ቢልቾት ይለውና ሽጉጡን መዝዞ እዚያኛው ግድግዳ ላይ ደጋግሞ እየተኮሰ VR (ቪአር) ይለፋል:: Victoria Regina ማለት ነው:: ንግስተ ቪክቶሪያ:: ሚስተር ሆምዝ የጁዶ ጥበብ ማስተር ወይም ሊቅ ነው:: ጁዶ ለትጋጠም ብዙ ጉልበት አያሻም፣ በተቃዋሚህ ጉልበት ነው የምትጠቀመው:: አለቻ ጭንቅራት! የሸርሎክ ሆምዝ ቤት አንድ ራሱን የቻለ ሙሉ የኬሚስትሪ ላቦራቶሪ አለው:: ስለ መርዝ ስለ ምናምን የሚመራመርበት ነው::

ሸርሎክ ሆምዝ ሃያ ስድስት ዓይነት የሲጃራና የትምባሆ አመድ ለይቶ ያውቃል::

ለምሳሌ አንድ ሰው እንግዳ ቤቱ ውስጥ ተገድሎ ይገኛል:: ገዳዩ ማን ይሆን? የሲጃራ መኰስተሪያው ላይ የሚገኘው አመድ ገዳይ ምን አይነት ሲጃራ ወይም ትምባሆ እንደሚያጨስ ይነግረዋል:: ሌላ አይነት የሚያጨሱትን ከጥርጣሬው ያሰናብታቸዋል::

ድንቅየው ዲቴክቲቭ አደኑን ይቀጥላል:: ወንጀሉ ከተፈፀመበት ክፍል ዶክተር ዋትሰን አጅቦት ሲወጣ ከኪሱ ተለይቷ የማታውቀውን (lens) ሌንስ ያወጣታል:: ስፋትዋ የጭልፋ ግማሽ የሚያክል የማጉሊያ መነፅር ናት፤ ለአይናችን ያነሰብንን አተልቃ የምታሳይ::

ከዋትሰን ጋር ሲወጡ በሩ ከተዘጋ በኋላ ዋትሰን ቆሞ ያስተውላል እንጂ አይንቀሳቀስም:: ሆምዝ የማተለቂያ መነፅሩን ያወጣና ከቤቱ የወጡት ሰዎች ትተዋቸው ያለፉትን ዱካዎች ያጠናቸዋል:: ጉንበስ ማለት ካልበቃው በሆዱ ይጋደማል:: መጨረሻ የወጣው ማነው? ያ ሲጃራውን በአመዱ ያወቅንበት::

አሁን ደሞ ሸርሎክ ሆምዝ የገዳዩን የጫማውን ማንም ያልረገጣት አዲስ ዱካ ያጠናል:: በዱካው ስንሄድ ሰውየው በጣም ከባድ መሆን አለበት:: ዱካይቱ በጉድጓዳነት አጠገብዋ ካሉት ቀድመዋት ከተረገጡት ዱካዎች ጠለቅ ትላለች:: ወዘተ...

... የሸርሎክ ሆምዝ ታማኝ ረዳት ጓደኛው ዶክተር ዋትሰን ሲሆን፣ ታማኝ ተጨማሪ ሀይልም አለው:: ሸርሎክ ሆምዝ የገዛ ሰፈሩን ብቻ ሳይሆን መላ ለንደንን ጠንቅቆ ያውቃታል:: የሰፈሩን የጉዳና ተዳዳሪ ልጆች እነማን እንደሆኑ ያውቃቸዋል:: ከነአለቃቸው:: አንዳንድ ጊዜ ሚስተር ሆምዝ ከቤቱ ሳይወጣ ይውላል:: እውጪ በድብቅ በየተራ ቆመው መውጫ መግቢያውን ሲጠብቁ የሚውሉት አሁን የምንጋተራቸው ወንጀለኞች ያላወቁት ምንድነው? ከጉዳና

ተዳዳሪዎቹ እንዱ ወይም ሁለቱ ማንም ሳያስተውላቸው ወደ ሚስተር ሆምዝ ቤት እየገቡ የሚልኳቸውን እየፈፀሙለት ይመለሳሉ:: ሚስተር ሆምዝ ራሱ እንደ ልቡ ሲገባ ሲወጣ እንደዋለ ይህል ነበር::— እጣው ሆኖበት ኮናን ዶይል ሸርሎክ ሆምዝን እንደ እንቅፋት ይቆጥረው ነበር:: በሱ የሚያጠፋውን ጊዜ ለሌላ ፅሁፍ ሊያውለው በወደደ:: ሳይንስ ፊክሽን (ማለትም ስለ ሳይንስ የሚያወሳ ልቦለድ) ይፅፍ ነበር:: በይበልጥ ደግሞ ኮናን ዶይል መፃፍ የሚወደውና እንዲ ህዝብም እንዲያስታውሰው ተስፋ የሚያደርገው ታሪካዊ ልቦለዶችን ነው:: እንጂ የሸርሎክ ሆምዝን ጊዜ ማሳለፊያ ጨዋታ አይደለም::

ስለዚህ አስራ ሁለተኛውና መጨረሻው ታሪክ ርእሱ «ለመጨረሻ ሲበናበት» ይባላል:: እጅግ ሲበዛ ልብ በሚሰቅል ትረካ ዶክተር ዋትሰን ውድ ጓደኛው ሸርሎክ ሆምዝን ፕሮፌሰር ሞሪያርቲ የሚባሉ፣ እሱ ራሱ «የወንጀለኞች ናፓሊዮን» የሚላቸው ሰውዬ ከመቀመቅ አፋፍ ላይ ወርውረው ሲገድሉት ያረዳናል::

በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አንባቢያን ለኮናን ዶይል ስለ ሸርሎክ ሆምዝ መሞት የሀዘን፣ ቅሬታ፣ የንዴት፣ የነቀፌታ፣ የስድብ ደብዳቤዎችን ላኩለት:: እሱ ግን «እፎይ! ግልግል!» አለና ለሚከተሉት አስራ አንድ አመታት ከሸርሎክ ሆምዝ ተለይቶ ኖረ:: ሸርሎክ ሆምዝ በነሱ አቆጣጠር በ1893 ሞተ:: በ1899 «የቦር ጦርነት» የሚባለው በደቡብ አፍሪካ ተነሳ:: እንግሊዝና የደች (የሆላንድ) ዝርያ የሆኑት ደቡብ አፍሪካዊያን ሶስት ዓመት ሙሉ ተጨራረሱ:: እንግሊዝ ድል አደረገች:: ከልቡ አገር ወዳድ የሆነው ኮናን ዶይል ለእንግሊዝ አቋም የሚሞግቱላት ሁለት መለስተኛ መፅሃፍትን አሳተመ:: የእንግሊዝ መንግስት በ1902 ሰር አርተር ብሎ ጥንታዊውን የእንግሊዝ ጀግና ጦረኛ ማእረግ ሸለመው::

በ1904 የሰር አርተር ውድ ባለቤት ሸርሎክ ሆምዝን እንዲያስነሳላቸው በራሷም በአንባቢዎቹም ስም ተማፀነችው:: ምን መማፀን ብቻ? ተአማኒ በሆነ ዘዴ የሚያስነሳበትን ሀሳብ ሰጠችው:: The Return of Sherlock Holmes (ሸርሎክ ሆምዝ ሲመለስ) በሚል ርእስ ነበር የመጀመሪያው ስብስብ የታተመው::

ኮናን ዶይል ራሱ ስለ ሸርሎክ ሆምዝ አራት ልቦለዶችና ስልሳ አምስት አጫጭር ታሪኮች ፅፏል:: ሸርሎክ ሆምዝ እንደ ዛር ያደረባቸው ብዙ ሌሎች ደራሲያን ደሞ በየበኩላቸው ልቦለዶችን አጫጭር ልቦለዶችን፣ ትያትሮችን እና ፊልሞችን ፅፈዋልም ሰርተዋልም:: ምን ጊዜም ሸርሎክ ሆምዝና ዶክተር ዋትሰን ወንጀለኞችን እናወድማለን!

በነገራችን ላይ ሸርሎክ ሆምዝ ለሀገሪቱ ለሰራላት ብዙ ውለታ የእንግሊዝ መንግስት ሰር ሸርሎክ ብሎ ጥንታዊውን የእንግሊዝ ጦረኛ ማእረግ ሊሸልመው ፈልጎ ነበር:: ሸርሎክ ሆምዝ ግን ሽልማቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ:: ስሚ ይበቃኛል አለ::

# ꧁ 8 ꧂

# ዮሀን ቮልፍጋንግ ፎን ገተ

# *Johann Wolfgang von Goethe*

## (ጀርመናዊው ደራሲ ፈላስፋ ሳይንቲስት...)

## *(The German author, philosopher & scientist)*



ሙያ - ገጣሚ፣ እና ልቦለድ ደራሲ፣ እና ፀሀፊ - ተውኔት፣ እና ሳይንቲስት እና ፈላስፋ፣ እና የሙዚቃ ሰው፣ እና ሀገር አስተዳዳሪ (አንድ ሙያ አይደለም እዝጌር የሰጠው ሰባት ሙያ ነው) እንዲህ አይነት ብዙ ፀጋ ተጠቃልሎ የተሰጣቸው ሰዎች በጣም፣ በጣም ጥቂት ናቸው:: «እናንተ የምድር ጨው ናችሁና» እንደተባለላቸው አይነት::

አገር:- ቀደም ሲል ጀርመን ሲቀጥል አውሮፓ አሁን መላው ዓለም እናስታውሳችሁና፣ እንግሊዞች «የናንተ የስነፅሁፍ ጉልላት ወይ ቁንጮ ማነው» ቢሉዋቸው «ጆን ሚልተን ነው» አሉ::

«እንዴ ሼክስፒርስ?»

«እሱማ የአለም ነው::»

የዘመዶቻቸው ከመሆን አልፈው፣ ያገራቸው ከመሆን አልፈው፣ ተርፈው የመላው አለም ሀብት ከሆኑት ጥቂቶች አንዱ ገተ ነው:: አጋጣሚው ሌላ ሆኖ ሰዎች ጀርመኖችን «የናንተ የስነፅሁፋችሁ እንቁ ወይም አልማዝ ማነው?»

ቢሉዋቸው ኖሮ (Friedrich Schiller) ፍሪድሪክ ሺለር ነው ይሉ ነበር።

«እስኪ! ዮሀን ቮልፍጋንግ ገተ የት ሄዶ ነው?» ቢሉዋቸው

«እሱማ የዓለም ነው!» ባሉ ባማረባቸው ነበር።...

... ገተ በአስራ ስድስት ዓመቱ ላይፕዚግ (Leipzig) ዩኒቨርስቲ ገባ። በ1771 የህግ ድግሪውን ተቀበለና አራት ዓመት በጥብቅና ሰራ። የግጥሞችና ልቦለዶቹ እና በተለይም (Faust) ፎስት የተባለው በድንቅ ግጥም የተፃፈ ድራማው ገተን ፈር እንደቀደደና አገር እንዳቀና ያስቆጥሩታል። (Romanticism) ሮማንቲሲዝም የሚባለውን የስነፅሁፍ ዘርፍ ከመሰረቱትና መልክ ካስያዙት ጠቢባን አንደኛውና ዋነኛው ገተ ነው።

ከጥብቅናው ዓለም ወደ ፖለቲካው ዓለም ተሻገረ። ለአስር አመታት ከዋነኞቹ የአገሪቱ የፖለቲካ መሪዎችና አስተዳዳሪዎች አንዱ ሆኖ አገለገለ። ሻርሎት ፎንስታይን (Charlotte Vonstein) ለተባሉ ለሰባት ዓመት የሚበልጡት ባለትዳር ሴትዮ ግጥሞች ፃፈላቸው። እነዚህ ግጥሞች የሀገሩን አንባቢያን ልብ ጠልቀው አስደሰቱት። ከ1786 እስከ 88 ሁለቱን አመት በጣሊያን አገር እየተዘዋወረ አሳለፈ። ኢጣልያ የገተን አይን ከፈተችለት። አርቲስት ነው ለካ! ሙሉ ልቡን ወደ ስነ ፅሁፍ አዞረ። ከ1794 እስከ 1805 ዮሀን ቮልፍጋንግ ገተ እና ፍሪድሪክ ሺለር እየተባበሩ እየተረባረቡ ሲበዛ የተዋጣላቸው ግጥሞችን አበረከቱ። እቺ አስራ አንድ አመታት የጀርመንኛ ስነፅሁፍ ቁንጮ ሆና ትታያለች።

ገተ በበኩሉ ካለፍኩ በኋላ ትውልድ ቢያስታውሰኝ ለባዮሎጂ (ለስነ ህይወት) ሳይንስ ባበረከትኩለት አስተዋፅኦ ይሆናል ብሎ ያምን ነበር። ታሪክ እና አለም ግን የሚያስታውሱት በተለይና በይበልጥ ፎስት በተባለው ስነግጥማዊ ድራማው ሆነ።...

(...Robert Frost) ሮበርት ፍሮስት በሀያኛው ምእት አሜሪካውያን አብዝተው የሚወዱት ገጣሚ ነበር። የጨለማ ሀያላት ወገኖች በግማሽ መንገድ የቀጩትና ከታላላቆቹ ፕሬዚዳንቶች አንዱ የነበረውን ጆን ኤፍ ኬኔዲ ህዝቡ ለአራት ዓመት ምራን ብሎ መርጦት የምረቃ ስነስርአቱ ሲፈፀም የተነበበው የይቅናን የመልካም አራት አመት ይሁንልን ግጥም ኬኔዲ የራሱ የልቤ የሚለውን ገጣሚ ከማክበር ጋር እባክዎትን የፈለጉትን ግጥም ያንብቡልን ሲል ጋበዘው።

ደስታውን አልችለውም የሚሰማኝ ክብርም ያን ያህል ነው ብሎ አነበበ። (እንግሊዝኛ ሌላ አማርኛ ሌላ!)

ሮበርት ፍሮስት ከፃፏቸው አጫጭር ግጥሞች አንዷ ወደ ታላቋ ግጥም ፍሮስት ትወስደናለች እንደ ድልድይ። ሃሳቧ ጭብጧ እነሆ።

ርእስ «ያልሄድነው መንገድ» (አብዛኛዎቹ የፍሮስት ግጥሞች ገጠርኛ አገር ቤትኛ ናቸው) ለአንድ ሁለት ሰዓት ሽርሽር በፈረስ ወጣሁና በልቤ ያንን

እፊቱ ያለውን የደስ ደስ የተሳለለውን ጫካ ተመለከትኩት::

እዚህ ውብ የውበት ጫካ ደርሰን መንገዳችንን በጥግታ ስንሄድ እዚህ መንገድ ይመስል የነበረው ባላ መሰለ:: መንገዳችን ተገንጠለ በሆትኛው እንሂድ? በመረጥነው መሄድ እንችላለን:: እሱማ አንዱን መንገድ መሄዳችን የማይቀር ነው:: ቅሬታ እየደበተን ነው እንጂ የምንሄደው:: የኛው ያልሄድነው ባላ መንገድ ስለቀረብን እየናፈቅን::

እቺ ሃሳብ ጉተ የተባለ ሌላ ሰው በሌላ ዘመን የኖረ እንደጻፉት Faust ፎስት ትራጀዲ ትሆናለች:: ዶክተር የሀን ፎስት አሁን ጥርጥስ ብለው ሸምግለዋል:: አመሻሽ ላይ ሰውነታቸውን ለማፍታታት በእግር ተዘዋውረው ወደ ቤታቸው እየተመለሱ ነው:: አንድ ግዳቢ ደጋግሞ ወለል ብሎ ይታያቸዋል:: በዚህ በኩል ጥበብንና ምትሀትን በትጋት ሲመረምሩ ሲያጠኑ ዓመታቱ ሄዱ፤ አለፉ፤ በዚህ በኩል የቅመማ ላቦራቶሪያቸው ውስጥ ከብዙ ክልባሎችና ጠርሙሶችና አሲዶችና ምናምኖች ጋር በማበርና በመተባበር ያችን ስውር ችሎታ ሲፈልጉ ዓመታቱ በረሩ፤ ከነፉ፤ ያቺ የሚፈልጓት ችሎታም ማግኛውም ነሳ! ወይ ኒኬል፣ ወይ ብረት፣ ወይ ማግኛውም ማእድን የሚፈልጉት ሲሆን ድግምቱን እየደገሙ «የፈላስፋ ጠጠር» የምንላትን ብናስነካው ያ ማእድን ወድያው ወርቅ ይሆናል:: እንደገና በዚህ በኩል ዶክተር ፎስት የህይወትን ኤሊክሲር (elixir) ፍለጋ ብዙ ጥረት ሲያደርጉ አመታቱ ተፈተለኩ:: የህይወት ኤሊክሲር እንደ ገነት ውሀ አይነት ናት:: እርጅተን ጨርጭሰን ጨርሰን አንድ ሁመስ ሲቀረን የህይወት ኤሊክሲርን ስንጠጣት ወዲያውኑ ወጣት ነው ምንሆነው:: ወጣት የነበር ጣት!

ደጋግሞ ይታያቸዋል ታዲያ:: ለካ ወጣትነታቸውን ጉርምስናቸውን ጎልማሳነታቸውን እርጅናቸውን ሳይቀር ምንም እንደሰው ሳይኖሩበት በከንቱ ኖሯል ያሳለፉት:: ሄደች በቃ አለፈች ያች እንዲትዩ ህይወታቸው ምንም ሳይኖሩባት፣ ብቻ ከንቱ ቅዥት ሲያሳድዱባት አለፋች::

ለዓይን እየያዘ ከሄደ ቆይቷል:: ዶክተር ፎስት አጠገባቸው አንድ ቡችላ አዩ፤ ጥቁር ጠጉራም ደስ የሚል:: የተደሰቱ ይመስላል! ጭራቱን እየወዘወዘ ተከትሏቸው ወደቤታቸው ገባ:: ብዙም ሳይቆይ ቡችላየው ወደ ሰው ተለወጠ:: «ሰው እንኳን አይደለሁም ዶክተር» አላቸው «ሜፊስቶፊሊስ Mephistopheles እባላለሁ:: ከሳጥናኤል በታች የፅልመት ሀይላት ባለስልጣን ነኝ:: ለእም ልርዳዎ የሚበጅ ሀሳብ ይዤ ነው የመጣሁት:: ይሰሙኛል?»

«እሰማለሁ»

«እኔ ያን ሁሉ በከንቱ አለሳ ዳበሳ ፍለጋ ያሳለፉትን ዘመንዎን ልመልስልዎትና እፍላ ጉረምስ ላድርግዎት:: ከዚያ ህይወትዎን እንደፈለጉ

ይኖሯታል::»

«ለምን በድጋሚ ልኖራት?»

«እንደፈለግኩ?»

«እንደፈለጉ»

«ከዚያስ?»

«ከዚያማ ህይወትዎን እንደልብዎ ከኖሯት፣ በኋላ አርጅተው ጫርጭሰው ሲሞቱ ነብስዎን እኔ እወስዳታሁ::»

«ነብሴን በህይወት ልለውጣት?»

«ማለት ነው»

«ይሁና እንግዲህ»

«እኔ ዮሀን ፎስት ከሜፊስቶፊሊስ ጋር ነብሴን በህይወት ተለዋውጫለሁ::» እንዲህ ከተፃፈ በኋላ ዶክተሩ በቀለም ሳይሆን በደማቸው ፈረሙት:: እንዲህ ነው የሚጀምረው የገተ ትያትር::...

ሐምሌ 14፣ 1988

# 9

# ቼሆቭ

# Chekhou



ፓቭሎቪች ቼሆቭ:: 1860 - 1904 በነሱ አቆጣጠር::
ስም - አንቶን ፓቭሎቪች ቼሆቭ:: ስሱ ለቼሆቭ ታጥርበት
የእድሜ ዕዋው መጠን - አርባ አራት አመት ብቻ:: በስራው
ይሆናል እንጂ እኛ አንባቢያን ደራሲያችንን በእድሜው አንለካውም:: በፈለገችው
እንጂ! የስነፅሁፍ አድባር ደሞ በፈለገችው እድሜህ ትጠራህና የምታሰናብታቸው
እድሜህ ታሰናብትሀለች:: አንድ ኑበስ ያለው ፅሁፍ አስጥፋ
እንኳን እሱ:: የኛን ቼሆቭስ?

ኢንሳይክሎፒዲያው እንዲህ ይላል:: ቼሆቭ የዚህን ክፍለ ዘመን የቲያትር
አፃፃፍ ረዥም እርምጃ ለመዝለል ካስቻሉት አንዱ ነው:: ከዚህም ጋር ከ1888-
1904 የታተሙት ስድሳ አጫጭር ልባለዶች ለልቦለዱ መስክ ተመሳሳይ
አስተዋፅኦ አድርገዋል:: በሌላ አባባል አንቶን ቼሆቭ ለልቦለድም ለትያትርም
ከጥቂቶቹ ፈር ቀዳጆች አንዱ ነው::

ቼሆቭ በህይወት እያለ በመላው ሩሲያ የታወቀና እጅግ በጣም የተወደደ
ደራሲ ሆነ:: ለውጭው አለም የተዳረሰው ግን ከ1920ዎቹ በኋላ ነበር:: ዛሬ
የቼሆቭ ስራዎች የአለም ታላላቅ በሆኑት ወይም ብዙ ተናጋሪ ባለባቸው ቋንቋዎች
ሁሉ ተተርጉመው በየጥቂቱ አመት በአዲስ እየታተሙ በብዛት በመነበብ ላይ
ይገኛሉ:: ድራማዎቹም እንደዚሁ በመላው አለም በመታየትና በመደነቅ ላይ
ናቸው:: ቼሆቭ ወጣት ደራሲ ሳለ እንጋፋ ደራሲው እና በኋላ ወዳጁ የነበረው

ሊዮ ቶልስቶይ በዚያን ዘመን የመሰከረለት አሁንም እውነት ነው - «የእንስሳትን ሩስያውያን ልብ ብቻ አይደለም ቼሆቭ የሚገባው! በሰው ልጆች ሁሉ ልብ ሰተት ብሎ ይገባል።»

ቼሆቭን ስናስብ ልባችን የቼሆቭ ልብ ይሆንና ገፀባህሪያቱ ያላቸውን ለሰው ልጅ ያለን ፍቅርና እዘኔታ ሆዳችን ውስጥ ይተራመሳል። ወጣቶቹ ውቦች ገፀባህሪያት ወይ በስራ ወይ በፍቅር ተጠምደዋል በህይወት እርግጥ ላይ ምን ዋጋ አለው? ፍቅሩም ሆነ ስራው ምን ውብ ቢሆን ደስታ አያገኙበትም።

ደስታ ወጣቶች ሆነው ሲያዩዋት በውኑ የሌሉ አብረቅራቂ ቀለማትን ለብሳ የምትጠራቸው ናት - ጥሪዋን አክብረው ሲሄዱ ግን ለካ እሷ አይደለችም የጠራቻቸው አብረቅራቂ አልባሳትዋ እንጂ።

በእድሜ የገፉት ደሞ ደስታን የሚያዩዋት በጊዜ ወደ ኋላ ዞረው በትላንት መስኮት እያማተሩ ነውና በአማርኛ እንደሚባለው «እድሜ አተላ!» እሳት አመድ ወለደ! ብርሀን መስላ ትታያቸዋለች ያቺ ጥንት የተብለጨለጨችና የጠራቻቸው ደስታ የሚሏት ቢይዟት እንኳ ሙልጭ ብላ የምታመልጥ እንደ ቀስተ ደመና ብቻ ከሩቅ የምታምረን የምትጠራን። ጊዜ እያለፈንና እያሳለፈን መሆኑ ሁሌ እንደታወቀን ነው። አልፎ አልፎ እንዳጋጣሚ ወይም በዘፈቀደ የህይወትን ትርጉም ለማወቅ መጣር መፍጨረጨርማ የት ይቀራል? ህይወት የማውቅን መንገድ ብንሄደው ለካ እውቀት ዘንድ አያደርስም፡፡ ምናልባት አለች ይሆን'ንጂ ግን እቺ የምንፈልጋት የህይወት ትርጉም? አቤት ሲንዙት ሲያሳዝን ይቺ የህይወት ጉዳና ልጆችዬ! አልቅሱ አልቅሱ ይላል። እኛ በረባውም ባልረባውም ጉዳይ ተወጥረን ስንውተረተር ከለቅሶው ፋታ አናገኝለትም እንጂ... ግድ የላችሁም ጉደሎ ሳትሆን አትቀርም ነገርየዋ ህይወት የምንላት። ሁሌ ፍለጋ ንጂ ማግኘት አይዋጣላት። ፍቅር ፍለጋ'ንኳ ሄደው ስናያቸው ሦስት ሴቶችና ሦስት ወንዶች ሆነው - አንዱ ሁለተኛዋን ያፈቅራል። እሷ ግን አምስተኛውን ነው የምታፈቅረው። እሱ ግን ስድስተኛዋን ነው የሚያፈቅራት። እሷ ግን አንደኛውን ነው የምታፈቅረው። ወይ ግሩም! አፍቅረን አፍቅረን ዞረን ዞረን ፍቅራችንን ሁላችንም ያልተፈቀረ አፍቃሪ ሆነን ቀረን! አይ ኑሮ! ይሄም ተኖረ ይባላል።...

እንዲያውም ሆኖ ግን እዝጊሐር ጨክኖ አይጨክን'ምና አንቶን ፓቭሎቪች ቼሆቭ የዕለት ተዕለት ኑሮውን ሲኖራት ሳለ ብዙ ብዙ ሳቅ እየሳቀም ነበረ የሚኖር ቼሆቭ የገፉቸው ነው የሚመስሉት። ስናነባቸው በሳቅ መንከትከት ነው። በመድረክ ብናያቸው ደሞ በሳቅ መንከትከት! እንባችን እየፈሰሰ።

አንቶን ቼሆቭ በ1884 የህክምና ዲግሪውን ከሞስኮ ዩኒቨርስቲ ተቀበለ። ህክምና የሚሰራበት ሁልጊዜ ሳይሆን አልፎ አልፎ ነበር። ይልቁንም ከህክምና

ልምድ ያገኘውን እውቀት ለስነ ፅሁፍ ስራው ያውለው ነበር::

በ1880ዎቹ ቼሆቭ እየፃፈ እያከመ ሞስኮ ውስጥ ኖረ:: በ1890 ከሞስኮ ወደ ምስራቅ 2400 ኪሎ ሜትር ርቃ ከጃፓን በስተሰሜን በምትገኘው ሳካሌን ደሴት ላይ የነበረውን የእስራት መንደር ሄዶ ከጎበኘ በኋላ ስለ እስረኞቹ ኑሮ ሁኔታ የሚዘግብ መፅሀፍ አሳተመ:: ከዚያ በኋላ ከሞስኮ በስተ ደቡብ በምትገኝ ሜሊኮቭ በምትባል መንደር የሀኪምም የገበሬም የደራሲም ኑሮውን ተያያዘው::

በ1897 በሳምባ በሽታ ምክንያት ሙቀት ፍለጋ ወደ ደቡብ ለመሰደድ ስለተገደደ ያልታ ከተማ መኖር ጀመረ::...

... በ1896 The Seagull «የባህር ወፊቱ» የተባለው ድራማው ለሴንት ፒተርስበርግ ከተማ ታየ:: ማለት ሲታይ ተሞከረ:: ያልተለመደ አዲስ አይነት ተውኔት ስለነበረ ተመልካች አልፈቀደውም:: ፉርሽ!

በ1898 የኮንስታንቲን ስታኒስላቭስኪ ሞስኮ አርት ትያትር «የባህር ወፊቱን» አሳየ:: ለካ ድንቅ ተውኔት ኖሯል! ከዚያማ ተውኔቶች ተከታተሉ:: ቼሆቭ የደረሳቸውና ስታኒስላቭስኪ ያዘጋጃቸው የሞስኮ አርት ቲያትር ተዋንያን እየተጫወቱዋቸው የሩሲያ ህዝብ ተምበሸበሸ::

Uncle Vanya «አጎቴ ቫንያ» The Three Sisters «ሦስቱ እህትማማች» The Cherry Orchard «የቼሪ አታክልት» በተለይ እንደ ታላላቅ ተውኔቶች የሚጠቀሱ ሲሆን እነዚህን የመጨረሻዎቹን ሁለት ቼሆቭ የደረሳቸው በተለይ የሞስኮ አርት ተዋንያን እንዲጫወቱዋቸው ሆን ብሎ አስቦበት ነው:: በ1901 ቼሆቭና ኦልጋ ክኒፐር የተባለች የሞስኮ አርት ትያትር ተዋናይት ተጋቡ:: የተቀረውን በዝምታ እንለፈው::

ሐምሌ 7፣ 1988

# ም 10 ራ

# ጀግናው በላይ ዘለቀ

ፊታውራሪ ተሻለ ዓለሙ የሰባ አራት ዓመት አዛውንት ናቸው። «እኛ በላይ ዘለቀ የወንድማማች ልጆች ነን» አሉኝ። «በዕድሜ አራት አመት እበልጠዋለሁ።» እንግዲህ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ይሄን ጊዜ ሰባ ዓመታቸው ነበር ማለት ነው። የተወለዱት በ1902 ዓ.ም. ነው ማለት ነው።

ፊታውራሪ ተሰማ ላቀው ስድሳ ሰባት ዓመታቸው ነው። «የበላይ ዘለቀ የአባቱ ትንሽ ወንድም ነኝ» አሉኝ። ፊታውራሪ ቀለመወርቅ መዝገቤ ስድሳ ሁለት ዓመታቸው ነው። የደጃዝማች በላይ ዘለቀ ዋና ፀሐፊ ነበሩ። የሚከተለውን ታሪክ የነገሩኝ እነዚህ ሦስት አዛውንት ናቸው።

## በላይ ዘለቀና ወንድሞቹ

ዘለቀ ላቀው (የበላይ ዘለቀ አባት) የልጅ ኢያሱ አንጋች ነበሩ። ልጅ ኢያሱ ሲገለበጡ፣ ዘለቀ ላቀው ወደ ሚስታቸው አገር ወደ ጫቀታ ሄደው ልጆቻቸውን ይዘው ወደ አገራቸው ወደ ለምጨን (ቢቸና ወረዳ) ተሻገሩ። (ቢቸና ጎጃም ውስጥ ጫቀታ ወሎ ውስጥ፣ ከዓባይ ወንዝ ማዶ ለማዶ ናቸው። ይገበያያሉም፣ ይጋባሉም።)

በ1916 ዓ.ም. ማለት በላይ ዘለቀ የአስራ አራት ዓመት ልጅ ሳለ፣ ፊታውራሪ እምቢ አለ የተባለ የራስ ኀይሉ ሌባ አዳኝ (ፀጥታ አስከባሪ) ዘለቀ ላቀውን ከበባቸው። ዘለቀ ላቀው እጄን አልሰጥም ስላሉ ተኩስ ተከፈተ። ዘለቀ ላቀውና አብረዋቸው የነበረ ዓለሙ መርሻ የተባሉ ወንድማቸው ከአስር ሰው በላይ ገድለው፣ ብዙ ሰው አቆሰሉ።

«እኛ ልጆች ተኩሱ ካባራ በኋላ ተየጫካው ስንመለስ ሁለቱም ሞተዋል። የዘለቀ ላቀው ሬሳ እቤቱ በራፍ ላይ ተሰቅሏል» አሉ ፊታውራሪ ተሻለ ዓለሙ። እንግዲህ በላይ ዘለቀና ተሻለ አለሙ እኩል አባቶቻቸውን አጡ፣ አብረው የሀዘንን ፅዋ ቀመሱ፣ እኩል በቀልን እያሰላሰሉ አደጉ፣ በኋላም አብረው ጠላትን ተ ፆጉ።

ዘለቀ ላቀው ሲሞቱ ልጆቻቸው ወደ እናታቸው አገር ወደ ጫቀታ ተመለሱ። በላይ ዘለቀ የአባቱን ደም ለመመለስ ተኩስ እየተማረ አደገ። አደገና የአባቱን «ናስ ማሰር» (ባለ ነሀስ ማሰሪያ) ውጅግራ ጠመንጃ ይዞ፣ ወደ አባቱ አገር ወደ ለምጨን (ቢቸና) ተሻገረ።

አባቶቻቸው የተገደሉባቸው ጉሬምሶች ዳኛነት እንዳይሹ ዳኛው ራስ ኃይሉ ሆኑባቸው፣ የቀረቻቸው ምርጫ በቀል ሆነ፡፡

መሳሪያ እየገዙ እየተዘጋጁ ለምጨኔን ቀንጦ ማርያም እያረሱ፣ ቀን ይጠብቁ ይመሩ፡፡ ... እንዲህ ሲል ጥልያን መጣ... በ28 ሚያዝያ (በሚያዝያ ወር 19/28 ዓ.ም.) ለቀኛዝማች መሸሻ ጥልያን መሳሪያ በአየር አወረደላቸው፡፡ (ለጥልያን ያሉ) ካለው ስበካ ያዙ፡፡ በረንታ ወረዳ (ቢቸና አውራጃ) ደረሱ፡፡ የዱህ ከተማ ያቋረጡ ሕዝቡን መሳሪያ እየነጠቁት (ጥልያንን እንዳይወጋ) ጥልያን ደግ መንግስት ነውና እንገዛለን እያሉ ይሰብካሉ (እንዲሾማቸው)፡፡

«ልጅ በላይ ዘለቀ ግን እዋጋለሁ፣ እንዋጋ እያለ እኛን ወንድሞቹን አነሳሳን» አሉ ፊታውራሪ ተሻለ ዓለሙ «ቀሰቀሰን ከሰላሳ እስከ ሀምሳ የምንደርስ ያንድ አያት ልጆች... የገልገል ቂልጡ ልጆች... ታጥቀን ተነሳን፡፡ ከቀኛዝማች በላይ መሸሻ ሰዎች መሳሪያ እየነጠቅን በረሀ ገባን፡፡»

«ጦር ሲያሳድደን... ስንሸሽ... ቤት ሲያቃጥልብን... ከኋላው ወይም ከጐኑ በድንገት እየመታነው መሳሪያ ነጥቀን ስናመልጥ... እንዲህ ስንል አንድ ቀን የማናልፈው ጉዳይ መጣ፡፡ ግንባር መግጠም ግድ ሆነ፡፡ ጠላት መሸሻ አሳጣና፡፡»

«የዛሬን ጦር ማን ይምራው?» አለን ልጅ በላይ፡፡

«አንተን መርጠናል... እስከ መጨረሻው» አልነው፡፡

«ሁላችሁም ወንድማማች ናችሁ፡፡» አልኩዋቸው ፊታውራሪ ተሻለን «በላይ ዘለቀን እርስዎ እንኳን በአራት ዓመት እበልጠዋለሁ ብለዋል፡፡ እንግዲያው በምን ነው አለቃችሁ እንዲሆን የመረጣችሁት?»

«እንዴ! በደግነቱ፣ በጀግንነቱ! ጠባየ መልካም በመሆኑ! እኔ ይቅርብኝ ብሎ ለሌላው ስለሚያዝን!» (ያን ጊዜ፣ 1928 ዓ.ም. ልጅ በላይ ሦስት ወልደዋል፡፡ ልጅ ተሻለ ግን ገና በታህሳስ ነው ያገቡ፡፡)

ወይዘሮ ድንቅነሽ ኃይሉ (የራስ ኃይሉ ልጅ) ጥልያን ሾምዋቸው የለም ጨጌ ጉልተ ገዥ ሆነው ሄዱ፡፡ ሕዝቡን መሳሪያ አግባ ብለው አሰባሰቡ፡፡ በላይ ዘለቀና ወንድሞቹ በድንገት ገብተው መሳሪያዎቹን ነጥቀው ሴትየዋን ሳይጉዱ፣ ሳያጎሳቁሉ ወደ መጡበት መልሰው ላኩዋቸው፡፡ የነጠቁዋቸውን መሳሪያ ሰላሳ አምስት ያህል ጠመንጃ ዋሻ ደበቁት፡፡ ለራሳቸው በቂ መሳሪያ ይዘዋል!

ከዚህ በኋላ፣ የደብረ ማርቆስን ጥልያን እያዘዘ፣ በላይ ዘለቀን ያሳድነው ጀመር፡፡ ከ28 ዓ.ም. ሚያዝያ እስከ 29 ግንቦት ድረስ ሁኔታው ተመሳሳይና ተደጋጋሚ ነበር፡፡ ጦር ይመጣል... ያስሳል... እነ በላይ ዘለቀ ይሸሻሉ... ዘኋላ ... መሣሪያ ነጥቀው... እልም! መሳሪያ

ቤቶች በሙሉ ተቃጠሉ:: ከብቱም ተዘረፈ:: ጠላት ሰምጨንን ሦስት ጊዜ ነው ያቃጠለ::

«እስከ 29 ታኅሳስ ድረስ አሰሳው የሚካሄደው በባንዳ ነበር» በታኅሣሥ ፬ ቀን 1929 ግብጣን ደበቡ የተባለ ጥልያን ቢቸና ገባ ቢሉን፣ ከዱማ ገስግሰን ቢቸና አደጋ ልንጥል ስንል፣ ካህናት ፅላት ይዘው ስእል መስቀል ይዘው፣ «አገሩንና ታቦቱን ያቃጥልብናልና አትውጉት:: እሱን እኛ ተመለስ እንለዋለን» ብለው መለሱን:: ግብጣን ደበቡም በላይ ዘለቀ መጣብህ ቢሉት ወደ ማርቆስ ተመለሰ::»

በየካቲት 29 ጥልያን አገሩን አስነስቶ ወረረን:: ከየአውራጃው ግብጣን ደዘኑ አስከተተ:: ጦሩ ሲመጣባቸው እነ በላይ ዘለቀ ሸሹ:: አጥቂቸው ሲመለሱ እያደፈጡ፣ በጉን አደጋ እየጣሉ፣ ብዙ መሳሪያ ነጠቁት::

«የማንበት እርገት ዕለት... በ29 ነበር የዋለ... ጥልያን ራሱ መጣ::» የበላይ ዘለቀን ዘመዶች ከሰምጨን ሰብስበው፣ እየደበደቡ ወደ አርበኞቹ እንዲመሩዋቸው አስገደዱዋቸው::

«ጦሩ ሲመጣ አሳለፍነው:: ከጉን አደጋ ጣልንበት:: በላይ ዘለቀ አንዱን ትሊንቲ ገደለው፣ ኮሬኔሉን አቆሰለው:: ብዙ ባንዳዎችም ሞቱ::»

ታስሮ እየተደበደበ ሲመራ የነበረው አባቴ፣ ቢያዝን ዱብዳ የተባለው የበላይ ዘለቀ ዘመድም ቆሰለ::

በሰኔ 29 (1929) ጠላት በቅምቢት፣ በደጀን፣ በገበያ፣ በሸበል፣ በበረንታ የነበረውን «ደንበኛ» በሙሉ አስከተተ:: (ደምበኛ የሚባለው «የመንግስት» የደምብ ብረት የያዘ ነፍጠኛ ነው) ቀኛዝማች ስማ ነገዎ አዝማች ሆኖ፣ ይህን ሁሉ አስከትቶ አባይ ወረደና አባራ ጊወርጊስ ሰፈረ:: ሀሳቡ እነ በላይ ዘለቀ ወደ ጫቀታ እንዳይሻገሩ በር በሩን ለመዝጋት ነበር::

«እንውጋው» አለ በላይ ዘለቀ

«ጦሩ በጣም ብዙ ነው አንችለውም» አሉት ሌሎቹ

«ግድ የለም:: ጦሩ በየመንደሩ ይመራል:: አዝማቹ ላይ አደጋ እንጣልበት::»

እነ በላይ ዘለቀ፣ ቀኛዝማች ለማ ነገዎ ያደረበትን በለሊት ከበቡት:: ሲነጋ ለማ ነገዎን ከነወንድሞቹ ደመሰሱት:: ጦሩ በሙሉ እጁን ሰጠ:: መሳሪያውኝ በቅሎውን አስረከበ:: ድል አድራጊዎቹ መሳሪያውን ዋሻ ውስጥ ደበቁት፣ በቅሎዎቹን ወደ ጫቀታ ልከው በጥይት ለወጡዋቸው:: «ይኸ የሆነው ሰኔ 10 ነበር:: ሰኔ 12 በአሮፕላን ይደበድበን ጀመር:: በረንታ ጉይ ጊወርጊስ ላይ 11 ሰው ሞተብን:: እኛም ተመልሰን ወደ በረሀችን ሸሸን::»

ፊታውራሪ ደልማ ሞገስ የጣሊያን የጦር እንደራሴ ሆኖ ከማርቆስ ተልኮ

በሙ:: ድል ነሱት:: … ሀገባ ዘበባቸው:: ውዋተው

ብዙ ሰው ሞተበት፣ እሱ ግን አመለጠ::

እነ በላይ ዘለቀ ስድሳ ያህል ምንሽርና አልቤን ማረኩ:: ምንሽርና አልቤን ሲያገኙ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር:: እስካሁን ግን ሲዋጉ በናስማስር፣ ውጅግራ፣ በለበን ብቻ ነበር::

«ድፍን ሐምሌን ተከበብን:: ለምጨን አንድ ዋሻ ገብተን ተደበቅን:: አንድ ጊዜማን ጊዜ የጉይ ጊወርጊስንና ያካባቢውን ሕዝብ ጉይ ላይ ሰብስቦ፣ በላይ ዘለቀን ካላመጣችሁ ብሎ በመትረየስ ፈጃቸው::» በላይ ዘለቀ የተኩሱ እለት ሞቶ ተቀብሯል ተብሎ ለጥልያኖች ተነገራቸው:: ሰው ሰደው መቃብሩን ሲያስመረምሩት ሴት ሆና ተገኘች::

አንዱ አሳባቂ በላይ ዘለቀ ወደ እነብሴ አውራጃ ነው የሄደው ብሎ ለጥልያኖች ጠቆማቸው:: የጥልያን ጦር ወደ እነብሴ ዘመተ:: የእነብሴና የጉንቻ ሕዝብ ገጠመውና ጨረሰው:: አንድ ጥልያን ብቻ አመለጠ::

## በላይ ዘለቀና አገሬው

እስከ ነሐሴ 1929 ድረስ የበላይ ዘለቀ ተከታዮች ከሰላሳ እስከ ሀምሳ የሚደርሱት ወንድሞቹ ብቻ ነበሩ::

«ነሐሴ ጊወርጊስ በላይ ዘለቀ በረንታ ላይ አዋጅ አስነገረ:: እኛን ምሰሉ፣ እርዱን:: አለዚያ ግን ይህ የጦር ሜዳ ነውና፣ እንዳትጐዱ ሂዱ ልቀቁ::»

«እናርጅ እናውጋ (የደብረወርቅ ወረዳ) በረንታና ሸበል፣ ጉበያ (ደጀን አጠገብ) እነማይ (ቢቸና አውራጃ)... ይኸ ሁሉ አመነ፣ ተባበረን::

«ከህዳር ማርያም (1930) እስከ መጋቢት ውድማትን፣ አዋባልን፣ ቅምቧትን፣ ሊበንን፣ ባስን፣ አነድድን ደጀንን... እነዚህን ያዝን::»

«በየካቲት ትሊንቲ ከጫቀታ ዘመተብን ዓባይ ደረሰ:: አገድነው:: ብዙ ውጊያ ተደረገ:: ሰማንያ ብረት (ከነሰው) ማረክን፤ መለስነው:: ወደ ደጀን ተመለስን::»

«ከሸዋ ሲዘምትብን ዓባይ ላይ አገድነው:: ወር ካስራምስት ቀን ተዋጋነው:: ሦስት መኪናዎች ሰበርን፣ ውስጣቸው የነበሩ ጥልያኖች ሞቱ::

«ጥልያን ኃይሉን አጠናክሮ በደጀን በኩል ከሸዋ መጣብን:: አስራ ሁለት ዘጠሰኔ በጀኔራል ማሊን አዝማችነት መጣ::

«መጋቢት 19 ቀን (1930) ውጊያው ማለዳ የጀመረ በአስራ አንድ ተኩል ላበቃ:: መትረየስና መድፍ ከታች፣ ፈረሰኛ በሻምላ (በጉራዴ)» ተጨምሮበት፤ ከላይ አሮብላ:: ወንድሞቻችን አለቁ:: የጦሩ አዝማች የነበረው የበላይ ዘለቀ

ወንድም ደጀዝማች ታደሰ ላቀው ወደቀ። ተሰማ ላቀው ቆስሎ አመለጠ። ሦስቱ ሙቶ ያህል አለቅን። የተቀረነውን ጨለማ ገላገለን።

«ጠላት ጥሰን ማርቆስ ገባ። እኛ ወደ በረሀችን ገባን::»

«ሚያዝያ 4 (1930)፣ እበረሀችን አፋፍ ላይ እንደሰፈርን ጠላት ባራት ረድፍ ቢቸና ገባ። ሚያዝያ 6 ጦሩን ባራት ማሰዘን አቀነባብሮ በረሀችንን በሙሉ ከበበው። በመካከሉ ደሞ በግምባር እልፍ አእላፋት ጦር ይዞ ተሰለፈ።»

«ባሰው ሀይላችን ገጠምነው::»

«ሊያፍነን ሞከረ በብዛቱ::»

«የቆላ ጫካ ነው... እሳት ለቀቅንበት»

«ይገርማል 'ኮ የቀን ነገር! ነፋሱ እሳቱን እያንቦገቦገ ወደነሱ ወሰደው። ብዙዎችን እሳት በላቸው፣ ብዙዎች አመለጡ::» የበላይ ዘለቀ ሚስት ወይዘሮ ሸከሚቱ አለማየሁ፣ በመትረየስ ሞቱ (እንደ ወንድ ለብሰው ነበር::) ልጅ የሻሸወርቅ በላይ ተማረከች። የናትየዋ እናትም ተማረኩ::

«ከዚህ በኋላ አባይን ተሻግረን ጫቀታ ገባን:: ያጌ ከተማ ግዛው ሰብሴ ፊታ ውራሪና ቀኛዝማች እያሉ ልጅ በላይ ሾመው... ተመለስን ወደ ሰምጪን በረሀችን ገባን::»

«ክረምቱን ከረምን::» (ያን ጊዜ ወንዞች ስለሚሞሉ እነ በላይ ዘለቀም ያርሳሉ ጥልያንም በየካምቦው ይከርማል::)

በህዳር 27/1931 ጥልያን የዴንሳ አማኑኤልን ክልክል ሸምበቆ ሊቆርጥ (ሰፈር ሊሰራበት) ይመጣል ማለትን ሰማን አርበኞቹ:: ደፈጣ አድረገው መሸገው አደሩ:: ማለዳ ሲመጣ ገጠሙት::

«ብዙ ባንዳ ገደልን፤ ብዙ መሣሪያ ማረክን፣ ጥሊያኑ ግን አመለጠ::»

በሦስተኛው ቀኑ ሰምጬን ዋዳዳ በሚባል ቀበሌ፣ ኮሬኔል አጉሬኔ አውጉስቶ የተባለ ጥልያን ሁለት መድፍ ጠምዶ ገጠማቸው:: ከሁለቱም በኩል ብዙ ሰው አለቀ:: ሰቀላ ገብርኤልን አቃጠለ። በዘጠኝ ሰዓት ኮሬኔሉ ድል ሆኖ ወደ ካምቦ ተመለሰ::

«ይኸ ሁሉ ሲሆን፤ ሰምጬን ውስጥ ፈላው በሚባል ቦታ ላይ ከትመን ከዚያ እየወጣን ነው ጦርነት የምናደርግ:: ፈላው ነበር ዋናው ምሽጋችን። ከ30 እስከ 33 ዓ.ም. ድል ሆነን አናውቅም::»

ሰኔ 1931 እነ በላይ ዘለቀ ወደ ማርቆስ ልንዘምት ነው ክተት ብለው አወጁ:: ጦሩ ከተተ:: መነሻቸውን ወደ ደብረማርቆስ አስመሰለው፣ ሰሊት አባይን ተሻግረው ወደ ጫቀታ ገቡ:: ሲነጋ ደጋው ደርሰዋል::

«ጎይሉ ሮባ የተባለ የጥልያን እንደራሴ ያጌ ላይ ገጠመን:: ተሸንፎ ሸሸ

ከረምቱን አርበኞቹ በምሽጋቸው ከረሙ። ታኅሳስ 1933። አርበኞች የቢቸናውን ካምቦ (ምሽግ) ለመክበብ ሲዘጋጁ ራስ ኃይሉ በላይ ዘለቀን መጥተው ሳነጋግርህ ብለው ላኩበት። «እሺ! ግን ከጠላት ጋር የነበረ ባንዳ እንዳይከተልዎ፣ ፎቶ አንሺም እንዳይመጣ» ብሉ ላከባቸው። ሰቀላ ገብርኤል ድረስ መጥተው አነጋገሩት።

«ከተዋጋችሁ አገሩም ይጠፋል፤ ጥልያንም እኔን ላያምነኝ ነው። ካልተጋሽው ግን ራሱ አገሩን ይለቃል።»

«እሺ ይሁን»

«ጃንሆይም መጥተዋል» አሉት።

«እንግዲያው እሱንም አፍነን እናስቀረው። እሱስ ይዞት የመጣው እንግሊዝ ያው ነጭ አይደለም?» አላቸው።

«አይሆንም» አሉት።

ተቀየሙ። ግን መውጋቱን ተው።

«ነጭ እዚህ ግድም እንዳላይ» አላቸው ራስ ኃይሉን፤ «እርስዎም እንዳልደፍርዎት ቶሎ ይዘውልኝ ይውጡ።»

ሌሊቱን ተነስተው ሄዱ። ጥልያንም ቢቸናን ለቆ ሄደ።

(ራስ ኃይሉ ደብረወርቅ ሲደርሱ ራስ ተመስገን ፈንታ ወግቶ ጓዛቸውን ብዙ ጠገራም አገኘ። እሳቸው ግን አመለጡ።)

## በላይ ዘለቀና ምቀኞቹ

መጋቢት 1933 ዓ.ም. ከበደ ተሰማ (ደጃዝማች) ወደ አገራቸው ለመመለስ መንገድ ላይ ከነበሩት ንጉስ ተልከው መጡ። ከሳቸው ጋር የነበረው ጀነራል ሳንፎርድ በላይ ዘለቀን ለመጨበጥ እጁን ሲዘረጋ በላይ ዘለቀ «ለፈረንጅ እጄን አልሰጥም» ብለው ሳንፎርድን አግባቡት።

በኋላ ልጅ መርድ መንገሻና እንግሊዞች ወደ ደጀን መጡ። ወደ በላይ ዘለቀ ላኩባቸው። ሄዱ። «የደጀንን ምሽግ ለመስበር ተባበሩን» ተባለ።

«መድፍ ይዛችኋል? ኤሮብላ ይዛችኋል?» አላቸው በላይ ዘለቀ።

«አልያዝንም ግን መክበብ ይበቃል» አሉት።

«አይበቃም» አላቸው። «ከዚህ በፊት ወር ካስራ አምስት ቀን ሙከረን ብዙ ወንድሞቼ አልቀዋል። መድፍና ኤሮብላ አምጡና ምቱት ለሌ... ለኛ ተውልን። አለዚያ ግን እኔ ወንድሞቼን በከንቱ አላስፈጅም።»

ሳይስማሙ ተለያዩ።

ንጉሱ ደብረ ማርቆስ ሲገቡ አርባ አራት ሺህ የበላይ ዘለቀ ሠራዊት በፊታቸው በሰልፍ አለፈ። ያውም ባንድ ቀን ጥሪ የደረሰው ነው እንጂ ሠራዊቱ

በሙሉ አይደለም።

በላይ ዘለቀ እንግዲህ በሰላም አርፌ እኖራለሁ ብሎ ንጉሡን «አገሬንም ሠራዊቴንም ይረከቡኝ» አላቸው።

«የሰላም ጊዜ ስራ አለ፤ አገርን ማስተዳደር አለ» አሉት።

«እኔ ተራ ሰው ነኝ፤ ሀረግ የሚቆጥሩት ሰዎች አያሰሩኝም። ከርስዎ ጋር ይጣሉኛል» አላቸው።

«እኛ የማንንም ወሬ አንሰማም። እንደ አባትህ ቁጠረን፤ እነዚህ ልጆቻችንም ወንድሞችህ ናቸው።...»

ከዚህ ወዲያ ያለው የበላይ ዘለቀ ታሪክ እጅግ የሚያሳዝንና እጅግ የሚያሳፍር ስለሆነ በጣም አሳጥረዋለሁ። ከአንድ በኩል የሰማሁት ስለሆነም የሰዎችን ስም አልጠራም። ታሪክ ፀሐፊዎች ተመራምረው አጣርተው ሊሰሩት ይገባል።

ንጉሡ ሹም ሽር አደረጉ። በላይ ዘለቀ ከወንድሞቹ ጋር ሆኖ በኋላም ከአገሬው ጋር ሆኖ ጠላትን ተዋግቶ ነፃ ያወጣው ጠቅላይ ግዛት ለራስ ኃይሉ ተሰጠ።

በላይ ዘለቀ ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ ደጃዝማች ተባሉ፤ የቢቸና አውራጃ ገዥ ሆኖ ተሾመ።

የቢቸና አውራጃ ገዥ ሆኖም ሊሠራ አልቻለም። ከደብረ ማርቆስ ትዕዛዝ እየመጣ ወረዳዎቹ ሁሉ ቀድሞ ባንዳ የነበሩ ሰዎች ተሾመባቸው። ብስጭት በዛበት በላይ ዘለቀ።

«ሊወጋን ነው... እምቢ አለ...» እያሉ ማስወራት ጀመሩ።

በቱ ካስወሩ በኋላ፤ ከራያና አዘቦ ጦር አስዘመቱበት።

(ጉጃሚማ በላይ ዘለቀን ወይ ይወደዋል ወይ ይፈራዋል።)

በላይ ዘለቀና ወንድሞቹ ከጥቂት ታማኝ ተከታዮቹ ጋር ሆነው ወደ ሳማ አምባ ሸሹ። በላይ ዘለቀ ሸፈተ ተባለ።

ሳማ አምባ ያለ ሁለት በር የላትም ሁለቱንም በር ይዘው ሃያ አምስት ቀን ሌትና ቀን ተዋጉ።

«ምረነዋል ልቀቁት ይምጣ» የሚል መልዕክት ከንጉሱ መጣ።

ከሳማ አምባ ከወረዱ በኋላ ተከበቡና መሣሪያቸውን ተነጥቀው እንደ እስረኞች ወደ አዲስ አበባ ተወሰዱ።

በላይ ዘለቀ ሞት ተፈረደበት። ንጉሡ «ምህረት» አደረጉለትና ቅጣቱ ወደ እስራት ተለወጠለት።

መስከረም 1936 ዓ.ም. በላይ ዘለቀና ወንድሞቹ በያገሩ ተበትነው ታሰሩ።

በላይ ዘለቀና ወንድሙ እጅጉ ዘለቀ ወሊሶ በበቀለ ወያ ጠባቂነት ታሰሩ።

የበላይ ዘለቀ ምቀኞች አሁንም አላረፋለትም። በላይ ዘለቀ ከዳ፣ አመለጠ፣ ጠፋ እየተባለ ይወራ ጀመረ። በቀለ ወያ ተያዘና «ምን ቢሰጥህ ነው የለቀቅከው» ተባለ። «ኧረ አልለቀቅኩትም» አለ።

በላይ ዘለቀንና እጅጉ ዘለቀን ወደ አዲስ አባ አመጡዋቸውና ከአንድ ሌላ ሰው ጋር አሰሩዋቸው። ያ ሰው እናምልጥ እያለ እነ በሰይ ዘለቀን ይጉተጉታቸው ጀመር።

አንድ ቀን «ጠባቂዎቻችንን የኛ ወዳጆች ገዝተዋቸዋልና እናምልጥ። በገዳይ ያለ ስፍራ እነእገሌ መኪና ይዘው እየጠበቁን ናቸው» አለ።

«ወንድሞቼ በየቦታው ተበታትነው ታስረው እኔ ማምለጥ ምን ያረግልኛል?» አለ በላይ ዘለቀ።

«ፈራህ እንዴ በላይ ዘለቀ?» አለው።

«እኔ የዘለቀ ልጅ!»

በላይ ዘለቀ ወንድሙን ላከው መኪናው እተባለበት ስፍራ መኖሩን ለማረጋገጥ። ወንድምየው በተባለበት ስፍራ መኪና አየ። እስረኞቹና ጠባቂዎቻቸው አብረው አመለጡ።

እመኪናው ቦታ ሲደረሱ መኪናው የለም። እንግሊዝም የለም።

ጠባቂዎቻቸው ከዚያ ሮጠው አጠገባቸው ከነበረው ጫካ ገቡና ደጋግመው ተኮሱ። ምልክት ነው።

በላይ ዘለቀ እጠላቶቹ ወጥመድ ውስጥ መግባቱን አወቀ።

በላይ ዘለቀና እጅጉ ዘለቀ ከዚያ ሮጠው አመለጡ።

ሰላሌ ደርሰው በቅሎ ለመከራየት ሲነጋገሩ ተከበቡ።

በላይ ዘለቀ በጦር ፍርድ ቤት ሞት ተፈረደበት። ንጉሱ ፍርዱን አፀደቁት።

ጥር 1937። በላይ ዘለቀ በስቅላት ሞተ። እድሜው ሰላሳ አምስት ዓመት ነበር።

ጥልያን በመድፍ፣ በመትረየስ፣ በአውሮፕላን ሊገድለው ያልቻለውን ጀግና፣ በቅናት የተነሳሱ ምቀኞች የሸረቡት ገመድ ገደለው። ፊታውራሪ ተሻለ ዓለሙ ሰላሳ አመት ታስረው በለውጡ ተፈቱ።

በላይ ዘለቀ ፎቶ ተነስቶ አያውቅም። መልኩን ፊታውራሪ ተሻለ ዓለሙ እንዲህ ብለው ይገልፁታል።

«አፍንጫው ሰተት ብሎ ወርዶ ቅጠሉ ነፋ ነፋ ይላል። ከንፈሩ ከበድ ይላል። ጠጉሩ ከርከም ጉፈሬ፣ ፂሙ ሙሉ ለስላሳ ረዥም፣ ጣቱ መልካም ወተት የተነከረ ነው የሚመስለው ጣቱ። እግረ ቀጭን።»

በላይ ዘለቀ ደጃዝማቾች ተብሎ ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ማርቆስ እንደተመለሰ ከባለሟሎቹ ጋር ለመገናኘት ወደ «ጠቅላይ ግዛቱ» ጽሕፈት ቤት ሄደ። ዘበኞቹም አጋፋሪውም ሲያዩት ጊዜ ሽሽታቸውን ለቀቁ። ስሙና ግርማው ያን ያህል የሚያስፈራ ነበር።

ከጽሕፈት ቤቱ ወጥቶ ወደ ሚያርፍበት ቤት ሲገባ፣ ወሬው ከተማውን ከመቼው እንደዳረሰው አይታወቅም፣ ማርቆስ ያለ ሰው ሁሉ እንጀራውን፣ ወጡን፣ ጠላውን፣ ጠጁን አረቄውን እየያዘ መጣ። በላይ ዘለቀን ሕዝቡ ሲወደው ያን ያህል ነበር። ምግብና መጠጡ ከመብዛቱ የተነሳ፣ ሰዎች ወደ ውጭ ተላኩና፣ አላፊ አግዳሚውን «የራበህ ስንቅ የሌለህ፣ ና ብላ! በበላይ አምላክ ና ግባ» እያሉ ጋበዙት።

በበላይ ዘለቀ ሰራዊት ውስጥ መሪና ተከታይ፣ አለቃና ጭፍራ ያለው በውጊያ ሰዓት ነው እንጂ በምግብ ሰዓት ሁሉም እኩል ነው። ለሰራዊቱ የማይበቃ ምግብ ከሌለ፣ ያለው ተቆራርሶ ለሁሉም እኩል ይደርሰዋል።

በላይ ዘለቀ መሰብ ሲቀርብለት «ሁሉም በልቷል?» ይላል።

«አይ! ዛሬ እጥረት አለ» ካሉት

«እንግዲያ መልሱ። እኔ አልበላም» ይልና ጦሙን ያድራል።

(አንዳንድ ጊዜ ሁሉም ባይበላም ውሸታቸውን ሁሉም በልቷል ይሉና ያበሉታል።)

«አንድ ጊዜ፣ ሁለት ቀን ጦም አድረን፣ በላይ ዘለቀ ዛሬ ሦስት ድርብ (ሁለት ቁና) ሽምብራ ላመጣልኝ ጠመንጃ እሰጠዋለሁ አለ። አንድ ገበሬ ሽምብራውን አመጣ፤ ጠመንጃውን ወሰደ። ሽምብራውን በልተን አደርን።»

በላይ ዘለቀ የገንዘብ ፍቅር የለበትም። እንዲያውም ብር በእጁ አያድርም። «ራሴ ጌታ አታርጉብኝ... ይቀጠቅጠኛል» ይላል።

ያቃዠኛል ማለቱ ነው በጐጃምኛ።

ንጉሡ ደብረ ማርቆስ የመጡ ጊዜ አስራ ሁለት ሺ ብር ሰጥተውት ሄዱ። በላይ ዘለቀ ከማርቆስ ወደ ቢቸና ሲጓዝ፣ አንዱ መጥቶ «ቤቴ ተቃጠለ» ገንዘብ ሲሰጠው፤ ሌላው መጥቶ «ከብቴ ተዘረፈ» ሲል ገንዘብ ሲሰጠው እንዲህ ሲል፤ ገና ቢቸና ሳይገባ አስራ ሁለት ሺ ብር አለቀ።

«ጊዮርጊስ ያውቃል» ይላል በላይ ዘለቀ። በጊዮርጊስ በጣም ያምናል። ፍልሰታ ሲሆን ሁል ጊዜ ሱባኤ ይገባል። «እኔ የዘለቀ ልጅ!» ይላል ሲቆጣ። «ሞድር በሰማይ የሚያስጉዘው! በላይነህ የወንዶች ቁና!» ይላል ሲፎክር።

በላይ ዘለቀ ተኩሶ አይስትም። ፍጥነቱ ደሞ ሲደግና ሲተኩስ እኩል ነው። ውጊያ ሲጀመር ሲል «እኔ ሳልተኩስ እንዳትተኩሱ» ብሎ ያዛል። አንዳንድ ጊዜ በውጊያ ሰዓት፤ «እርስዎ እዚህ ይቆዩን» ሲሉት «ምን?» ይላል ቁጣ

እየጀመረው። «እርስዎ ከወደቁ መሪ የለንም» ሲሉት፣ «ወይድ፣ እኔ እርን ነፍጠኛ ነኝ» ይልና ግንባር ይጋፈጣል።

በላይ ዘለቀ ራሱ ሲዋጋ፣ «ገምባው» የተባለው ጥሩምባው ይነፋል። «ገምባው» ባንዳን ያስበረግጋል፣ ጥልያን ይብረከረካል።

በላይ ዘለቀ የዘመኑን አስተሳሰብ በማወቁ፣ ሕዝቡን ለማስተባበር «ትልቅ ሰው» ማስፈለጉን በመገንዘቡ፣ እሱ ራሱ ግን ተራ ሰው በመሆኑ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ሀረግ ለሆኑት ለልጅ ኃይሉ በለው ደብዳቤ ፃፈላቸው።

የደብዳቤው ሀሳብ በአጭሩ፣ «ሕዝቡን ለማስተባበር እርስዎ የበላይ ሆነው እኔን የጉበዝ አለቃ ይሹሙኝና ጠላትን እንቋቋመው። እኔው እዋጋለሁ። እርስዎ ወደ ጦር ግንባር መድረስ አይኖርብዎትም» የሚል ነበር። ደጋግሞ ደብዳቤ ፃፈላቸው። ገፀ በረከትም ላከላቸው፣... ጠመንጃ፣ ሽጉጥ፣ ዝናር ከነጥይቱ፣ ሦስት መቶ ብር፣ እና ካባ።

ልጅ ኃይሉ በለው ለደብዳቤዎቹ አንድም መልስ ሳይሰጡ፣ አንድ ቀን አንድ የትእዛዝ ደብዳቤ ላኩበት፣ «ደብረ ወርቆች ገበያችንን ያለ አግባብ ቀረጡብን ብለዋልና ከእንግዲህ ቆቅ የሰገረ ወፍ የበረረ እንዳይደርስባቸው። የተወሰደባቸውም ቀረጥ እንዲመለስላቸው።»

በላይ ዘለቀ ተናደደ። አብረውት የነበሩትን፣ «ጉበዝ እግዚአብሔር የወለደው ሰው አለ?» ሲል ጠየቀ።

«እግዚአብሔር ይፈጥራል እንጂ አይወልድም» አሉት።

«ንጉሥስ?»

«ንጉሥንም እግዚአብሔር ይቀባዋል እንጂ አይወለድም። ይፈጥረዋል እንደሌላው ሰው»

«እኔንም ፈጥሮኛል። ሊቀባኝ አይችልም?»

«የሱ ኃይል ከደረበዎ የፈለጉትን ማድረግ ይችላሉ።»

«እንግዲያው ከዛሬ ጀምሮ ለማንም አልታጠቅም።»

ተመስገን ፈንታ የበላይ ዘለቀ የቅርብ ጓደኛው ነበር። አንድ ቀን ከጠላት በፊት ተመስገን ፈንታ በላይ ዘለቀን፣

«ሸዋ ሄደን ለትልቅ ሰው እንደር። እንሾማለን፣ እንሸለማለን» አለው።

«እኔ ሰው ሆኜ ለሰው አላድርም» አለ በላይ ዘለቀ።

«ባንተ ተኩስ፣ ባንተ ወኔ፣ ባንዳፍታ ትሾማለህ»

«ጀግንነት እደጃችን ድረስ ይመጣ እንደሁ ማን ያውቃል?» አለው በላይ ዘለቀ። ዓመታት አለፉ።

ሞረድ እጀ ጠባብ፣ ከሥመሩ እሚመጣ አፈ ሾሌ ሱሪና ተመሳሳይ ኮት፣

ቀንገ ድርብ ጥበብ ኩታ፣ በቅሉ እንደተጫነች፣ ጠመንጃ ከነሙሉ ዝናር ቀይቶ... በላይ ዘለቀ ይህን ሁሉ አዘጋጀና፣ ተመስገን ፈንታን ጠርቶ፣

«ያ የጌታ አዳር ሄደን እንሸለማለን ያልከው ይኸውና» ብሎ ሸለመው።

በአርበኝነት ዘመን ጓደኞቹ አልተለያዩም።

በላይ ዘለቀ መጀመሪያ «ራስ» ብሎ የሾመው ተመስገን ፈንታን ነበር።

«እኔንስ ራስ አልከኝ። አንተ ማን ልትባል ነው?» አለው ተመስገን ፈንታ።

«እኔንማ እናቴ አንደዜ በላይ ብላኛለች» አለ በላይ ዘለቀ።

የካቲት 3ኛ ዓመት ቁጥር 7 ሐምሌ 1972

# ፩ 11 ፪

# ካስትሮ

# *Castro*



አሜሪካ የጣለችባትን የኢኮኖሚ ማዕቀብ ኩባ ልትቋቋመው የቻለችው ወደ ሶቭየት ኅብረት በመጠጋት ነበር። በዓለም አቀፋዊ ኢንተርናሽናሊዝም መንፈስ ለኩባ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ቴክኒካዊ እና ወታደራዊ እርዳታ ታደርግላት ጀመር። ባጠቃላይ በዓመት እስከ ሁለት ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ እርዳታ ነበር።

(የቤይ ኦቭ ፒግስ ወረራን የኩባ ሕዝብ ካከሸፈ በኋላ ፊደል ካስትሮ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፤ «ይህን ሁሉ ጊዜ ማርክሲስት ሌኒኒስት ነበርኩ። እስከሞትም እንደምቀጥልበት ነው።»)

በ1982 (በነሱ) የኩባው የሚሳይል ፍጥጫ ተከሰተ። አንድ ቀን አሜሪካውያን በቴሌቭዥን በሬድዮና በጋዜጣ ጉዳቸውን ሰሙ። ከጠረፋቸው ዘጠና አምስት ማይል ብቻ ርቆ የሶቭዬት ሚሳይሎች ተጠምደው አሜሪካ ላይ አነጣጥረዋል።

ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ ለጦር ኃይሎቻቸው «ቀይ ተጠንቀቅ» (Red Alert) አወጁ። ማለትም በማንኛውም ደቂቃ ሶቭየት ኅብረትን ለመውጋት ተዘጋጅ ብሰው አዘዙ።

ፊታድ ላይ የነበረ ሚሊተሪ በሙሉ ከባለ አራት ኮከብ ጀነራል እስከ ተራ

መተዳደር ከሁሉ ቀድሞ በሚያደርሰው የማመላለሻ ዘዴ ወደ የኮምፖቹ ወደ አየር ኃይል ጣቢያው ወደየ መርከብ ኃይል ወደቡ ወደ የጦር መርከቡ ወደ የሰበማሪን (ባህር ውስጥ ለውስጥ እንደ ዓሣ የሚሄድና ከባህር በታች ሊሰነብት የሚችል ሰቢ.ዩ.ት ኅብረት ላይ ከባህር ተወንጭፎ ደራሽ ሚሳይል የጠመደ መርከብ) ተመለሰ። እንዲሁም እየተፋራረቁ ሃያ አራቱን ሰዓት ሙሉ ኑክሊየር ቦምብ ተጭነው ሞስኮ - ሌኒንግራድ፣ ወዘተ ላይ ለመጣልና ሲፈነዳ ከተማዎቹን እንዳልነበረ ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ ፍጥነታቸው ድምፅን የሚቀድም አውሮፕላን እየበረሩ ናቸው።

ዓለም በፍርሀት ትንፋሽዋን ዋጠች። ፕሬዚዳንት ኒኪታ ክሩስቾብ በዚች ሰዓት ታላቅ ሰው መሆናቸውን አስመሰከሩ። በሶስት ዓመት ያደነቅነውን ኬኔዲንም ለስላሳ ስድስት ዓመት ሲያስደንቀንና የጀግና ኮከብ ጠልቃ እንደማትጠልቅ በድርጊት ሲያሳየን የኖረውን ካስትሮን ሳይቀር። እሳቸው በለጡ።

እኮ ምን ጀብዱ ሰሩ?

ኬኔዲ «ትኩስ መስመር (hot line)» የሚባለውን የሳቸውንና የፕሬዚዳንት ክሩስቾብን ቢሮዎች በቀጥታ የሚያገናኘውን ቴሌፎን እየደወሉ እንዲህ ይላሉ፡፡ «ኩባ ላይ የተተከሉት ሚሳይሎች ተነቅለው አገራቸው ካልተወሰዱ ዩናይትድ ስቴትስ ኦብ አሜሪካ ላይ ጦርነት እንደከፈታችሁ ቆጥረን አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን።»

ለሁለት ቀን ነበር ወይስ ለሦስት ቀን ነበር መላው ዓለም በፍርሀት የተሸማቀቀው?

ሁለቱ ኃያላን ኑክሊየር ጦርነት ከገጠሙ እነሱ ራሳቸው ብቻ ሳይሆኑ መላው የሰው ዘር ከብዙ ሌሎች ፍጡራን ጋር ሊጠፉ ይችላሉ። እድሜ ለኒኪታ ክሩስቾብ ተርፈናል። ሚሳይሎቹ ተነቀሉ፤ መላዋ ዓለም እፎይ አለች።

ግማሽ ዓለም ለጆን ኤፍ ኬኔዲ አጨበጨበችለት። ብራቮ! ተባለ። እነዚያን ኮሚኒስቶች ልካቸውን አሳወቃቸው ተባለ። የቤይ ኦብ ፒግስን ቅሌት ከንግዲህ የኩባ ሚሳይል ፍጥጫ ቆራጥነት አስረሳው። መልከ ቀናው ቀልደኛው ኬኔዲ እጅግ ተወዳጅ ፕሬዚዳንት ሆነ። ዋና ከተማው ዋሺንግተን ዲሲ ካሜሎት ተባለች። ካሜሎት ለእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች እንደ ባህላዊ ዋና ከተማቸው ናት። እየሩሳሌም የኛ ሃይማኖታዊ ዋና ከተማ እንደሆነች አይነት። ካሜሎት የተወዳጁ የንጉስ አርተር እና የውቢቱ የንግስት ጉዌነቪር ከተማ ናት። በካሜሎት ዝነኞቹ የንጉስ አርተር የክብዋ ጠረጴዛ አርበኞች እነሰር ላንሰሎት፣ ጋላሀድ፣ ጋወይን የጦር ልብሳቸውን እንደለበሱ ሲሄዱ ሲመጡ ይታያሉ። እጅግ ቆንጆ የሆነችው ጃክዊሊን ኬኔዲ እንደ ንግስት ጉዌነቪር ትታይ ጀመር።

እነ ሊዮኒድ ብረዥኔብ በበኩላቸው ክሩስቾብ ዓለምን ከጥፋት አፋፍ ላይ በላ መለሷት አላመሰገኑዋቸውም። «የኩባ ሚሳይል ቅሌት» ብለው ሌሎችንም

ስህተቶች ደምረውባቸው ከሩስቾቭን ከስልጣን አወረዱዋቸውና ብሬዥኔብ ፣ ፕሬዝዳንትነቱን ነጠቁዋቸው። (እይ እቶ ብሮዥኔብ! ሶቭዬት ኅብረትን ያህል አገር ጠክለውህ አሜሪካን ያህል አገር ከሚወክሉ ፕሬዚዳንት ጋር መፋጠጥ የሚጥም ጨዋታ መስለህ ነው? በል ታገኛታለህ!!)

– ለሶቪዬት ኅብረት አሜሪካ ጓሮ ያለችውን ኩባን መሻረክ በጣም የሚፈለግ ሊሆን ፊደል ካስትሮ ግን የሚመች ሰው አልሆነም። «ከሁሉም ነገር በፊት የኩባ ህዝብ ጥቅም» ባይ ሆነባቸው። በሌሎቹ ወዳጆች ኮሚኒስት አገሮች ሁሉ እንደሚያደርጉት በኩባም ለማድረግ ሲፈልጉ ካስትሮ አላስደርግ እያለ አስቸገረ። ኩባ፣ በዚህ መንገድ ምራ ሲሉት፣ የኩባን ሕዝብ ፍላጐት የምናውቀው እኔና ጓዶቼ ነን እንጂ የውጭ ሰዎች አይደሉም ይላል።

እነ ካስትሮ የኩባን ሰፊ ሕዝብ እንደጠቀሙት ጠላቶቻቸው እንኳ ሊክዱ አይችሉም። ከሌላው የላቲን አሜሪካ ሰፊ ሕዝብ ኑሮ ጋር ሲተያይ የትናየት ነው። በትምህርት ደረጃ ብንሔድ የኩባ ሰፊ ሕዝብ አንደኛ ነው። በጤና ረገድ ብንሄድ የሀኪሞችና የህዝቡ ብዛት ሲነፃፀር ከሁሉ ሰፊ ሕዝብ የኩባ ሕዝብ ነው ብዙ ሀኪሞችና የጤና ባለሙያዎች ያሉት። እና ከሁሉም በላይ፣ ላቲን አሜሪካ ውስጥ (ምናልባትም በመላው ሦስተኛ ዓለም ውስጥ) ኩባውያን ብቻ ናቸው አፋቸውን ሞልተው «ቢከፋም ቢለማም አሁን አሁን ካሉት መሪዎች ሌላ አንፈልግም!» የሚሉ።

የምትቀጥለዋስ የኩባ ወዳጅና ጠበቃ አምባሳደርና መንፈሳዊ ዜጋ የሆነው የደርጋለሙ ዶክተር ተድላ በነገራችሁ! አቤት እንዴት አሪፍ አርጐ በነገራችሁ! ፊደል ካስትሮ ታድያ ለኩባ ሕዝብ ተመቸው እንጂ ለክሬምሊን ገዥዎች አልተመቻቸውም። ሊያስወግዱትና በምትኩም የሚመቻቸው ኩባዊ ሊሾሙ ወሰኑ። ኬጂቢ (ስለላ ድርጅታቸው) እቅድ አወጣና ካስትሮን ለማግለል እርምጃ ሊወ..ድ ሲል ተነቃበት። ያን ጊዜ የኩባ የሕዝብ ደህንነት የፊደል ታናሽ ወንድም በመሆኑ ሳይሆን ታጋይ ተዋጊ ነፃ አውጪ ጀግና ስለሆነ ነ"። በሶቭየት ኤምባሲ እና በልዩ ልዩ መስሪያ ቤት ኤክስፐርት አማካሪ ተብለው ተሰግስገው የነበሩትን የኬጂቢ አባላት ራውል በገዛ ሥልጣኑ በሀያ አራት ሰዓት ኩባን ለቀው እንዲወጡ አዘዛቸው። ራውል ካስትሮ በዚህ ፍጥነት ኬጂቢን በካልቾ ብሎ ካስወጣ በኋላ ሄዶ ለፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮ ዝርዝር ሪፖርት አቀረበ። የኩባ ኮሚኒስት ስርዓት ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ መሆኑን እዚህ ላይ ልንገነዘብ እንችላለን። ኬጂቢ ላይ እንደነቃ ሄዶ ለፊደል ሊነግረውና ምን እርምጃ እንውሰድ? ብሎ አመራር ሊቀበል ሲገባው ሶቪየት ኅብረትን ያህል ወዳጅና መከታ የሚያስቀይም እርምጃ መውሰዱ ለምን? ለምሳሌ የኮሚኒስት፣ ኢትዮጵያ የህዝብ ደህንነት ኀላፊ ለጓድ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ሳይነገር እዚህ የነበሩትን የኬጂቢ አባላት በገዛ ስልጣኑ ቢያስወጣቸው?

ፊውል እርምጃ ሳይወስድ በፊት ለፊደል ቢነግረው ኖሮ ምናልባት ፊደል ይህን እርምጃ እንዳይወስድ ይከለክለው ነበር፡፡ ነቅተንባችኋል ሁለተኛ እንዳይለምዳችሁ እንላችኋለን ይለው ነበር ምናልባት፡፡ ከዚያስ? እረስተው እንድ አመት ቆይተው እንደገና መሞከራቸው ይቀራል? ያኔ ሙከራቸው ቢሳካላቸውስ? አይ! ለሺየት ብትፈልግ ታኩርፈን እንጂ የኩባ ህዝብ ፊደል ካስትሮን ከሚያጣ የሰሺየትን እርዳታ ቢያጣ ይመርጣል፡፡

በአገራችን ላይ ፊደል ስሙ በእሱ ቋንቋ ታማኝ ማለት ነው፡፡ የኩባ ሕዝብ አማርኛ ቢያውቅ ኖሮ «ፊደል እውነትም ስምን መላክ ያወጣዋል» ይል ነበር፡፡

ዛሬም በዓለምነህ ዋሴ ድምፅ - የካስትሮና የአንክል ሰም ፍጥጫ እንደ ቀጠለ ነው፡፡

## ግንቦት 13 1987

ተስፋ አለኝ አሁንም «በቴክኒክ ጉድለት ምክንያት ሳይሆን አይቀርም» ያለፈ ጨዋታችን ውስጥ ይርጋለም ሄጄ ኩባን አግኝቻት መጣሁ ብዬ! ኩባ ውስጥ ሲነገሩ የማይችሉ ሦስት ጆኮች ነግሬያችሁ ነበር፡፡ ማስተካከያ እነሆ! ሁለተኛው ጆክ አጀማመሯ ተቆርጦ ቀርቷል፡፡ እንዲህ ይል ነበር፡፡ የሌላው አገር ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ፀሀፊ ደግሞ አገር ቤት የሚኖሩ ብዙ ድህነት ያሳለፉ አሮጊት እናቱን ልጃቸው በኑሮው ምን ያህል እንደ ቀናው አይተው ደስ እንዲላቸው ወደ ዋና ከተማው አስመጥቶ የሚኖርበትን ቤተ መንግስት አስጎብኛ ቸው፡፡ ልዩ ልዩ መኪናዎች በጋራዥ በተርታ ቆመዋል፡፡ «ይኸ ሁሉ የኔ የልጅሽ ነው» አላቸው፡፡ ዝም አሉ፡፡

የግል አውሮፕላኑ ውስጥ እያስገባቸው «ይኼም የኔ ነው» አላቸው፡፡ ዝም፡፡ (እዚህ ላይ ሳምንት ያነበባችሁት ይቀጥላል፡፡)

«እንግዲህ ካስትሮ በተከታታይ የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች ጋር የኩባን ሕዝብ ወክሎ ሲፋጠጥ ይኸው ሰላሳ ስድስት ዓመት ሆነው፡፡ የጦር ሜዳ መለዮውን እንደ ለበሰ ነው፡፡ ቦት ጫማውን ሳይቀር፡፡ ምክንያቱም የነፃ አውጭ ጦርነቱ እንደ ቀጠለ ነው፡፡ ልዩነቱ መሳሪያዎቹ የጦር ሜዳ መሆናቸው ቀረና የቢሮና የአለም አቀፍ መድረክ ሆኑ፡፡

ካስትሮ ስንል ስሙ ስለሚቀናን ነው እንጂ ከበስተኋላው እንደሱ ቆራጥና ሀገር ወዳድ የሆኑ ወደኋላ ማፈግፈግ የማይሆንላቸው ጀግኖች የተሰለፉ መሆናቸውን እያስታወስን እነካስትሮ፤ እነ ቼ እና አብዮታዊው ሰራዊት በ1959 (በነሱ) ዋና ከተማዋ ሀቫና ገቡ፡፡ ባዲስ ዓመት አዲስ ስርዓት!

«ሁዋንታ ላሜራ» የምትባለውን መዝሙራቸውን የሰማ ሊገምት እንደሚችለው የኩባ ሕዝብ ሙዚቃና ዳንስ በጣሙን ይወዳል፡፡ በጣሙን ይችልበታል፡፡ ይታያችሁ እንግዲህ ያ ህዝብ በዚያ ቀን መንገዶቹን ሞልቷቸው

እየዘፈኑ፤ እየደነሱ፤ እየተሳሳሙ:: አንድ ህዝብ አንድ ባህል አንድ ቋንቋ:: ከእንግዲህ ደሞ አንድ ፓርቲ አንድ መሪ - ፊደል ካስትሮ::

ከደስ ደስ ፌስታና ፈንጠዝያ በኋላ እነ ካስትሮ ወደየቢሮቻቸው ገቡ:: እነሆ በረከት አሉት የኩባን ህዝብ::

ስፋታቸው ማለቂያ የሌለው የሚመስሉት ላቲፋንዲያ የተባሉ የግል እርሻዎች ተወረሱና እዚያ ይሰሩ የነበሩት ቅጥረኞች ድሆች በማህበር ተደራጅተው የልፋታቸው ፍሬ ባለቤት ለመሆን በቁ:: ኩባ የአንክል - ሳም የስኳር ማምረቻ ሆሻና ደሞ የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያው ነበሩ:: አሁን የሸንኮራ ማብቀያ መሬቱም የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎቹም የኩባ ሕዝባዊ መንግስት ንብረት ሆኑ:: አንክል ሳም ደነገጠ፤ ተናደደም::

ከዚህም ጋር በፉልጄንሲዮ ባቲስቱታ ዘመን ደልቷቸው ይኖሩ የነበሩ ከቡራንና ከቡራት ኩባውያን ፈርተውም አኩርፈውም የዘጠና አምስት ማይልስ ባሕር አቋርጠው ወደ አሜሪካ ማያሚ (የፍሎሪዳ ትልቋ ከተማ) ፈለሱ:: ብዙዎቹ ከበሩ::

ይህን ሲያይ «አንክል ሳም» ወደነዚህ ስደተኞች ሲአይኤ የተባለውን የስለላ ድርጅቱን አስማራባቸው:: የማያሚ ኩባውያን ሳያውቁት ተጠንተው ተገመገሙ:: የሲአይኤ ዳይሬክተር ፕሬዚዳንት አይዘንሀወርን እንዲህ አላቸው፤ (በግምት) ሚስተር ፕሬዝዳንት ከፈቀዱለት «ሲአይኤ እነዚህን ስደተኞች በሚስጥር አሠልጥኖ አስታጥቆ በባህር ኃይላችን አሳፍሮ አገራቸው ያራግፋቸዋል:: «ቤይ ኦቭ ፒግስ» እተባለው ቦታ እነሱ የኩባን ወረራ ሲያካሂዱ እኛ እዚያ ያስታጠቅናቸው የካስትሮ ጠላቶች እሱን እንደሚሆን ያረጉታል:: እርግጠኛ አይደለንም እንጂ የእኛ ሰዎች እዚያ በሚያካሂዱት ቅስቀሳ ሕዝቡ ይነሳሳና ካስትሮ ያበቃለታል:: ይህ እንግዲህ ጊዜያዊ ጨረፍታዊ ጥናታችን እንዳለየን ነው:: ሚስተር ፕሬዚዳንት ሲፈቅዱልን ጥናቱን በዝርዝርና በጥልቀት እናካሂዳለን::»

ተፈቀደለት:: በዚህኛው ጥናት መሠረት ሙሉ ዝግጅት እንዲደረግም ሲአይኤ አስፈላጊው በጀት ተመደበለት::

በዚህ መሀል አራት ዓመቱ ሞልቶ በአሜሪካ ፕሬዚዳንት ምርጫ ይካሄድና ወጣቱና መልከ መልካሙ የባሕር ጦር ጀግናው የሚሊየኔሩ ልጅ ሴነተር ጆን ኤፍ ኬኔዲ ፕሬዚዳንት ይሆናል:: «ሚስተር ፕሬዚዳንት» ይሰዋል:: ያ የቀድሞ የሲአይኤ ዳይሬክተር በአይዘን ሀወር ፈቃድና ትዕዛዝ ፈርማና ማትተም እስካሁን የተደረገውን የኩባ ወረራ ዝግጅት በዝርዝር ይገልፅለታል:: እንቀጥል ወይስ እንተወው? የርስዎን ውሳኔ እንጠብቃለን::

ቀጥል አለ፤ ወጣቱ ኬኔዲ:: ባለ ብዙ ልምዱ ጄኔራል አይዘን ሀወር የፈቀዱት ሳይላካ አይቀርም ብሎ አስቦ ይሆን?

የበይ አብ ፒግስ ወረራ ልክ እንደ ታቀደው ተካሄደ:: እና ልክ እንደታቀደው መቶ በመቶ ከሸፈ:: አይ ቅሌት! ሰውየው ኬኔዲ ባይሆን ኖሮ ለፕሬዝዳንትነቱ በመጀመሪያው ከባድ ውሳኔ ስለተሳሳተ ለሚቀጥለው አራት ዓመት ከመንበሩ እንደከሠረ ይቆጠር ነበር::

ሲአይኤ እንዴት ከሰረ! ካስትሮስ ከታቀደለት ወድቀት እንዴት አመለጠ? መልሱ አጭር ነው:: የኩባ ህዝብ አገሩ ስትወረር ተነሳና ተዋጋ::

«አንክል-ሳም» ከዚህ ሃፍረት በኋላ የኩባን ደሴት ከማንም አገር ጋር እንዳትነግድ በወደር የለህ ባህር ኃይሉ ከበባት:: ከካስትሮ አንገት ማነቆ እንደ መሸምቀቅ ነበር:: ካስትሮ ከሶቭየት ህብረት ጋር ወዳጅነቱን ከማጠናከር ሌላ ምርጫ አልነበረውም:: ወደ አሜሪካ በመርከብ ይጫን የነበረው ስኳር ወደ ሶቭየት ኅብረት ይወሰድ ጀመር::

ከዚህ በኋላ ሳይሆን አይቀርም እነ ፊደል ካስትሮ መልዕክት ላኩ:: አውሮፓም ላቲን አሜሪካም ሌሎች አገሮችም ለሚገኙ! የራሳቸውን ህዝብ አይዋሹም ብሎ የሚያምኑባቸው የታወቁ ሰዎችን ከዚህ ቀን እስከዚህ ቀን አገራችንን እናስጎብኛችሁ:: ብታዩልን የምንወደውን እናሳያችሁ:: ልታዩት የምትፈልጉትን እናሳያችኋለን:: ከዚያ አገራችሁ ስትመለሱ ያያችሁትን ለሕዝባችሁ ትመሰክሩልናላችሁ:: ለኛም ሳታዳሉ አንክል - ሳምንም ሳትፈሩ ትናገሩላችሁ ብለን እናምናለን::

ጥሪውን አክብረው ሄደው ጎብኝተው ተመልሰው ያዩትን ፅፈው ካሳተሙት አንዱ ዣን ፖል ሳርትር ይባላል:: ከመመስከር በፊት መስካሪው ማን እንደሆን ባጭሩ መንገር ሊያስፈልግ ሆነ:: ሳርትር ከምዕራባዊው ስልጣኔ ታላቅ ፈላስፋዎች አንዱ! በልቦለዶች ባጫጭር ልብ ወለዶቹ! በትያትሮቹ ብቃት ደሞ ከፈረንሳይ ስነ-ፅሁፍ ቁንጮዎች አንዱ ነው:: የኖቤል ሽልማትን እምቢ አልቀበለውም! ኢምፔሪያሊዝም እኔን አይሸልመኝም ያለ ሰው ነው:: በሂትለር ወረራ ዘመን ኀቡዕ (ድብቅ) አርበኛ ነበረ:: ሰውየው ይሁዲ ነው:: አጭር ነው! ጠንካራ ነው! ወፍራም መነፅር ያረጋል:: ሴቶች በጣም ይወዱታል:: ከሳርትር ምስክርነት በትንሹ እነሆ:: እነ ፊደል ካስትሮ የስራ ሰዓት የዕረፍት ሰዓት ብለው አይለዩም:: አቢሮዎቻቸው ታጣፊ አልጋ አለ:: እንቅልፍ ሲመጣ እሱ ላይ ይተኛሉ:: ሲነቁ ወደ ስራ ነው:: ካስትሮን ሕዝቡ ይወደዋል:: ሕዝቡና መሪው እኩል ሲዋደዱ ብዙ ጊዜ አያጋጥምም::

አንድ ቀን ካስትሮ ሳርትርን ሲያስጎበኝ የነሱ መኪናዎች ተከትለውት የሱ መኪና ፊት ፊት እየሄደ ወደ አንድ ጫካ ገቡ:: መንገድን ተከትለው:: ብዙም ሳይሄዱ አንድ በጣም ግዙፍ የሆነ ጥቁር ሰውዬ ድንገት ከጫካው ብቅ ብሎ መንገዳቸው ላይ ቆመ:: መትረየስ ይዟል:: ቁም! አለ:: ቆሙ::

«እውቅሀለሁ:: በል አሁን አዙርና በመጣህበት ተመለስ::»

«ስማ:: እነዚህ የውጭ አገር እንግዳዎቻችን ናቸው::»

«ይሁኑ:: እነሱ ሊያልፉ ይችላሉ ከፈለጉ:: አንተ ግን ትመለሳለህ»

«እንትንን (የቦታ ስም) ላስጎብኛቸው ኮ ነው::»

«በዛኛው መንገድ ውሰዳቸው»

«ያ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥም ይኸ አቋራጭ እያለ? ጊዜያችንን ለምን እናባክናለን?»

«ይኸ ጫካ ስለሆነ:: ጠላት አደጋ ሊጥልብህ ስለሚችል:: አሁን እኔ ጠላት ልሆን እችል ነበር:: አንተስ ከሞትክ ሞትክ ነው አለቀልህ እኛ ግን ከዚያ በኋላ ምን እንሆናለን አታስብልንም?»

እነ ካስትሮ እነ ሳርትር አዙረው በዙሪያ ጥምጥሙ መንገድ መሄድ ግድ ሆነባቸው::

ፊደል ካስትሮ የዚህ ሰውዬ ነገር ሳይከነክነው አልቀረም:: ለማንኛውም ተስፋዬ ገሠሠ አጋጥሞት አይቶ የነገረኝ እነሆ:: ለተባበሩት መንግስታት ስብሰባ ወደ ኒዮርክ ሲመጡ ከፕሬዝዳንቶቹ ሁሉ የማን አጀብና ጓዝ ይበዛል? የፊደል ካስትሮ:: ሀርለም ውስጥ (ሀርለም የጥቁሮች ሠፈር) ነበር ያረፈው:: ካስትሮ ሆቴሉን በሙሉ የያዙት እነካስትሮ ናቸው:: ምክንያቱም ካስትሮን ሲአይኤን አያምንም:: ዛሬ ተበልቶ የዛሬ ወር የሚገድል መርዝ ቢያበሉትስ? ለሞትም ሳይሆን ለበሽታ ቢዳርጉትስ? ያልጠረጠረ ተመነጠረ ነው፤ ወዳጄ:: ስለዚህ በግስ፤ ዶሮስ፤ ድንችንስ ምንስ - ካስትሮ የሚበላውና የሚጠጣው ከኩባ ይዞት የመጣውን ብቻ ነው::

ካስትሮ ለሕዝቡ በሬድዮና በቴሌቪዥን ሲናገር ለሰዓታት ነው:: አንድ ጊዜ ከአስር ሰዓት በላይ ተናግሯል:: በሌላ ኮሚኒስት አገር ቢሆን ህዝቡ ፈርቶና ተገዶ ነው የሚያዳምጠው ኩባውያን ታዲያ ካስትሮ ንግግር ያደርጋል ሲባል አብዛኛውን ሌላ የግል ፕሮግራማቸውን ሠርዘው ያዳምጡታል:: ብዙ ተማሪዎች እሱን ለማዳመጥ ሲሉ ከትምህርት ይቀራሉ (ይፎርፋሉ)::

ብዙ ኩባውያን እንዲህ ይላሉ «የሶሻሊዝም ጉዳና ባይመችም ችግር ቢበዛበትም ፊደል ካስትሮ መንገዳችን ነው ብሎ እስከ መረጠው ድረስ ለኛ መንገዳችን ነው:: እሱ እንሂድ እስካለ ድረስ እንሄዳለን:: ባጭሩ ፊደል ካስትሮ ነፃ አውጭ ሳይሆን የህዝቡ ውድ መሪ ጭምር ነው::

ጋዜጠኛ ሙሼ እፍረት አያውቅም:: አንዱ ፊደል ካስትሮን «ለምን ጢምህን አይላጩትም?» ብሎ ጠየቀው:: መልስ «እኔ ጢሜን የምላጨው አገሬ ምላጭ ስታመርት ነው::»

ግንቦት 6 1997

# 12

# ቼ ጉዌቫራ

# *Che Guevara*



ምነው ያገራችንን ትምህርት ተምሬ በነበረና፣ የቼ ጉዌቫራን ታሪክ በቅዱስ ጊዮርጊስ ገድል ስልትና አሰካክ አገጣጥሜ በፃፍኩላችሁ:: ለቼ ጉዌቫራ ምንም ሊበዛበት አይችልም::

ለማንኛውም እኔ ነኝ እንጂ ቼ ጉዌቫራ ራሱ እንደሆነ ለዓለም ጭቁኖች ተዋጋ፣ እስከ ሞት ድረስ ተዋጋ እና የተቀደሰ ተልእኮውን ፈፀመ:: ማን በግጥም ህይወቱን ጣፈለት፤ ማን ዝም አለ፤ ማንስ አወገዘ፤ ስሜት አይሰጠውም::

ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር ሆነን ለጣፍነው ደሞዝ እየተከፈለን ቼ ጉዌቫራን ለአንባቢዎቻችን ማወደስ ሌላ፣ ቼ ጉዌቫራን መሆንና ሆኖ ኖሮ ለመላው የዓለም ጭቁን ተዋግቶ በጨቋኞች ላይ ስንትና ስንቱን ድል ተቀዳጅቶ ለታጋዮች ሁሉ አርማ አርአያ መሆን ሌላ::

አሁን በማደንቃቸው በአዝማሪዎች ደምብ ስለ ቼ ጉዌቫራ እዘፍንላችኋለሁ::

ጆግናችን አዝምርልኝ ብሉ ያላ||||ኝ ተነስቶም የማይሸልመኝ አዝማሪ ስለ ቼ ጉዌቫራ ለማዝመር መታደል ራሱ ትልቅ ሽልማት ነውና፤ ወደ ዘፈናችን

የፊደል ካስትሮ ቀኝ እጅ ሆኖ ለኩባ ሕዝብ ነፃነት የተዋጋው ቼ ጉዌቫራ ትውልዱ ኩባዊ አይደለም፤ አርጀንቲናዊ ነው:: በነሱ አቆጣጠር በ1928

የተጠለዩው ቼ ጉቬኀራ ጤነኛ ልጅ አልነበረም። መጥፎ የአስም በሽታ ነበረበት። (አስም ሲነሳብህ መተንፈስ ይከለክልሀል፣ እፍን እፍን ያረግሀል። የሚያዩህ ሰው ካሁን ካሁን ሞተ እያለ እስኪጨነቅ ትወራጫለህ፣ ትንፋሽን ያህል ነገር ተከልክለህ የቆም ስቅላትህን ታያለህ።) የሀገሩ ቼ አስም ሀይለኛ ከመሆኑ የተነሳ አብዛኛውን ቀን አልጋ ውስጥ ነበር የሚውለው። ተራ ልጅ ቢሆን ኖሮ በሽታውን ሰበብ ሳይሆን ምክንያት አድርጎ ቤተሰቦቹ በቂ ሀብት ስለነበራቸው እየኀታመሙ የሚያሳዝን በሽተኛ ሆኖ ይቀር ነበር።

የቼ ገድል ግን ምን ይነግረናል? ልጁ መስሀፎቹ እና የቤት ሥራዎቹ ከትምህርት ቤት እየመጡለት እያጠና የቤት ስራውንም ሠርቶ ወደ አስተማሪዎቹ እየላከ አርመው እየላኩለት፣ እንዲህ እየተማረ አደገ። በኋላም ከመንፈሱ ብርታት የተነሳ ከማንም ጤነኛ እኩል ተምሮ የህክምና ድግሪውን ተቀበለ። በኋላ በኩባና በሌሎቹም አገሮች በየጫካው በየጋራው በየሸንተረሩ በየሜዳው ሲዋጋ በአንድ ትከሻው መትረየሱን በሌላ ትከሻው የሀኪም ቦርሳውን አንግቦ ነበር - ያ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ይቀራል ተብሎ የነበረው ልጅ ዓለም ራሷ የጠበበችው ይመስላል።

ገዳዩ ቼ ጉቬቫራ መትረየሱ እስኪግል ሲታኮስ ሞት ሲያርከፈክፍ ይቆይና፣ አንዱ መጥቶ ቁስለኛ በዛ ሲለው፣ ሀኪሙ ቼ ጉቬቫራ ሞትን አውልቆ ህይወትን ሰብሶ ያሀኪም ቦርሳውን አንጠልጥሎ ወደ ቁስለኞቹ ይሮጣል። ቦርሳው ውስጥ የአስም ማስታገሻም ይገኛል። በሽታው ሲነሳበት መተንፈስ እየተሳነው እየተጣደፈ ያወጣውና እንደ ፊኛ ዓይነት በአበጠው በኩል ሲጫነው በሌላው በኩል ወደ ጉሮሮው ውስጥ መድሀኒቱን ይረጭለታል። በሽተኛው ሀኪም፣ ለሰው ፍቅር ሲል ሰውን የሚገድለው ቆራጥ!


ወጣቱ ዶክተር ቼ ጉቬቫራ የአርጀንቲና ፈላጭ ቆራጭ ዲክቴተር በነበረው በሁዋን ፔሮን ላይ ቅስቀሳ ያካሂድ ነበር። ግን ፔሮንን ተዋግቶ ለማሸነፍ ሁኔታዎች አይፈቀዱም ነበር። ግድ የለም። ጭቆናንና ብዝበዛን በብዙሀን ላይ የጥቂቶቹ መንቀባረርን ከአርጀንቲና ጠራርጐ ማስወጣት ካልሆነልን ከሌላ አገር እናጠፋዋለን። እስኪያጠፉን ድረስ እናጠፋዋለን። ቼ፣ የኩባ ኮከብ፣ አብርተህ ጥፋ!

ዶክተር ቼ ጉቬቫራ በ1953 ወደ ጓቲማላ ሄደው የጃኮሞ አርቤንዝ ጉዝምንን የግራ ክንፍ (ማለትም የድሀውን ወገን የሚደግፈውን) መንግስት ለአንድ አመት አገለገሉ። በ1954 ቼ ወደ ሜክሲኮ ዘለቀና ከፊደል ካስትሮ ጋር ተገናኘ። ከነባቸው ገጠመ።

በዲሴምበር (ታህሳስ) 1956 ሁለቱ እና ሰማንያ ሌሎች ጓዶች የኩባን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት የትጥቅ ትግልን ለመጀመር በመርከብ ወደ ኩባ ተጓዙ። ከሦስት ዓመት ውጊያ በኋላ በጃንዋሪ አንድ 1959 (ማለትም በነሱ አንቆጣጠር

ተገን የአሜሪካ ተማኞች አገልጋይና የኩባ በዘባኙ የነበረውን ባቲስታን አባረው በኋላ አድራጊነት ሀቫና ገቡ:: ዶክተር ቼ ጉቬቫራ ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የኩባ ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ሆነው የፊደል ካስትሮን ኮሚኒስት መንግስት በትጋት አገለገሉ::

በ1985 ቼ ጉቬቫራ ከሕዝብ ፊት ተሰወረ:: ወደ ቦሊቪያ ዘልቆ አገደ ሽምቅ ተዋጊ ኃይል ማሰልጠን ጀመረ:: በ1987 ሲአይኤ (የአንክል ሳም የስለላ ድርጅት) ቼ ጉቬቫራንና ጓዶቹን አስከበባቸው ጀግናው ቼ ጉቬቫራ ተያዘና ተረሸነ::



ፊደልና ቼ

መቼም ቼ ጉቬቫራን ገደልነው ብንል ማንም አያምነንም በማለት ሲአይኤ የቼ ጉቬቫራን ሬሳ ፎቶግራፍ አንስቶ በማሰራጨቱ ሸለለ ኩኩሉ አለ:: እናም የሶስተኛው አለም ወጣቶች አረሩ::

የቼ ጉቬቫራ የህይወት ታሪክና አሟሟት ብዙ ሀሳቦችን ይቀሰቅሳሉ:: ለምሳሌ የሕንዱ ማህትማ ጋንድሂ የግብፁ ገማል አብደል ናስር፣ የቻይናው ማኦ ዜዱንግ፣ የቬትናሙ ሆቺ ሚን፣ የሰሜን ኮሪያው ኪም ኢል ሱንግ፣ የኬንያው ጆሞ ኬኒያታ - እነዚህና ሌሎቹም ጀግኖች ነፃ አውጪዎች ይህን ክፍለ ዘመን አስጊጠውታል:: ግን ሁሉም ተዋግተው ነፃ ያወጡት የገዛ አገራቸውን ሰው ነው:: ቼ ታዲያ ደረቱን ለጥይት አጋልጦ ተዋግቶ ነፃ ያወጣው የሌላውን አገር ህዝብ ነው:: ጀግና ለእናት አገሩ ሲዋጋ ይሞታል:: ቼ ግን ለሰው አገር ሲዋጋ ነው የተገደለው::

ይህ ክፍለ ዘመን ማርክሲስት ሌኒኒስት ነን የሚሉ ኮሚኒስቶች በየፈርጁ ያፈራ ቢሆንም አፋችንን ሞልተን ሙሉ ማርክሲስት ነው ልንል የምንችለው ቼ ጉቬቫራን ነው:: እሱም እንደ ካርል ማርክስ ያንድ አገር ሳይሆን ያንድ አለም የጭቆናና የብዝበዛ ስርአት አስቆጥቶት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲዋጋው የተነሳ ጀግና ነው:: አስከፊው ስርአትም ያገር ድምበር አይወስነውም፣ የቼ ጉቬቫራን ውጊያም ያገር ድምበር አይከልለውም:: ባለ ፋኖሱ ዲዮጋን «የየትኛው አገር ዜጋ ነህ?» ሲሉት «የአለም ዜጋ ነኝ» አለ ይባላል ቼ ጉቬቫራም የአለም ዜጋ መሆኑን በደሙ አስመስክሯል::

የቼ ታሪክ የኩባ ኮሚኒስት ፓርቲ ከሌሎች ኮሚኒስት ፓርቲዎች በሙሉ የተለየ መሆኑን ወለል አድርጐ ያሳያል፡፡ ለምሳሌ የሶቭየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲን ብንመለከት ፀረ ዓብዮት ሀይላትን ድል ያደረገው ሊዮን ትሮትስኪን ጆዜፍ ስታሊን ከሀገር አባረረው፡፡ ትሮትስኪ በስደት በሜክሲኮ ሲኖር ተገደለ፡፡ የስታሊን እጅ አለበት ሲባል ነበር፡፡

የቻይና የመከላከያ ሚኒስቴር የፖሊት ቢሮ አባል ጓድ ሊዩ ሻዎ ቺ በአውሮፕላን ሊያመልጥ ሲሞክር የነማኦ ዜዶንግ ወገኖች ተኩሰው ጣሉት፡፡ ማለትም አብዛኛውን ጊዜ የነበረውን ስርአት እስኪገለብጡ ድረስ ኮሚኒስቶች እርስ በርስ ሲበዛ ይተማመናሉ፡፡ ስልጣን ከያዙ በኋላ ግን የመጋጨት፣ የመፈራራት፣ በአይነቁራኛ የመጠባበቅ፣ የመገዳደል ጠባይ ይታይባቸዋል፡፡ በቃኝ ብሉ ፓርቲውን ጥሉ መውጣት ያስገድላል ወይም ያሳስራል፡፡ ምስጢር እንዳያወጣ ሲባል ነው ይባላል፡፡

የኩባ ኮሚኒስት ፓርቲ ግን ስልጣን ከያዘ በኋላም አባላቱ እንደ ቀድሞው የሚተማመኑ ጓዶች እንደሆኑ ቀጥለዋል፡፡ በቼ ጉዌቫራ እንዳየነው «ጓዶች፣ ቦሊቪያ ሥራ ይጠብቀኛል፡፡ ይቅናህ በሉኝ!» ብሉ ተሳስሞ መለያየት ይቻላል፡፡ ለመሆኑ ቼ ጉዌቫራና ፊደል ካስትሮ ሲለያዩ ምን ተባብለው ይሆን?

አርጀንቲናዊው የኩባ ኮከብ የቦሊቪያ መስዋዕት ሆነ እልኳችሁ እንጂ፣ ልፅፍ ያሰብኩት እንደ ሚከተለው የሚጀምርና በዚያው ቅኝት የሚቀጥል የስድ ንባብ መወድስ ወይም መልክአ ቼ ጉዌቫራ ወይም ገድለ ቼ ነበር፡፡

ቅዱስ ቼ ገና በሕፃንነታቸው መልአከ ሞት ከጌታው ከሰይጣን ተልኮ መጣባቸው፡፡ የአስትንፋስ ተቃራኒ የሆነውን አሸከሩን አስምን ልኮ ያለ የሌለውን አየር ከሳንባቸው ሳብ ምጥጥ አርጐ ወስዶ፣ «ና እንሂድ ሰዓቱ ደረሰ» አላቸው፡፡ ሕፃኑ ቅዱስ ቼ ሳምባቸውን በመንፈሳቸው ፅናት ለጊዜው ከስራ አሰናበቱ፡፡

እነሆ፣ ሞትን እምቢ ባዩ መልአከ ሞትን አካልቦ ግራ አጋብቶ አሰናባቹ አቡዬ ጣዲቁ ወገናቸውን፣ መሣያቸውን ብጤያቸውን ያውቃሉ፡፡ (እሳቸው ግብፅ ተወልደው ወደ ጉጃም መጥተው ለምድረ ጉጃም ሃምሳ አመት ተዘቅዝቀው የፀለዩለት አይደሉምን? ጉጃምን እንደ ኩባ እንቁጠረው፡፡ ቀጥለውስ አባይን ተሻግረው ዝቋላ ድረስ መጥተው ሌላ ሃምሳ ዓመት ለተቀረችው ምድረ ኢትዮጵያ እግራቸው ትልቅ ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ በሀረግ ታስሮ እሳቸው ቁልቁል ተንጠልጥለው የፀለዩላት አይደሉምን? ስለዚህ የመንፈሳቸውን ፅናት ለቼ ላኩለት፡፡ ሕፃኑ ቅዱስ ቼ መልአከ ሞትን እንዲህ አለው፣ «አልሄድም የሚጠብቁኝ ስራዎች አሉ! አድጌ እነሱን እስከምፈፅም አልመጣልህም፡፡ ተስፋህን ቁረጥ፡፡» መልአከ ሞት ከመቶዎች ዓመታት በፊት ዝቋላ ተራራ እንደዚሁ እንደ አሁኑ እንዴት ኩባን ከምድር ወደ ሰማይ ለማድረስ ወርዶ ያጋጠመው ያ የአቡዬ እምቢታ ምክንያቱና ታወቀው፡፡ አሁንም ያው የአቡዬ ኮከብ ኮከቡ የሆነ ሰው ተወልዶ

… ጠረጠረ:: ጠለቅ ብሎም መረመረ:: አቡዬ ማንንም ፍጡር ሆን
… ስለማያውቁ! የናታቸውን ጡት እንኳ ጠብተው ስለማያውቁ!
… እምቢ ሊሉት በቁ::
… ቅዱስ ቼ ደሞ የናት ምድርና ያባት ሰማይን አየር መተንፈስን
… እያለ ነው:: መልአከ ሞትም እየተርበተበተ፣ በስፓኝኛ ቋንቋ (ያውም
… ቅኝትና ዜማ) የቼ ጉዌቫራን ኮከብ እንዲህ አለው፣
«እንደ ዝቋላ ጊዜው ጌታችንንና ዲያብሎስን ሳንጠራ ተደራድረን መግባት
አንችልም?»
«እንችላለን»
«አሁን እኔ ልወስደው ስመጣ እምቢ ማለቱ ለምን?»
«ታስታውሳለህ:: ቀድሞ በሀይማኖት ዘመን ተማባራችን እርኩስ መናፍስትን
ከምድረ ኢትዮጵያ ማስወጣት ነበር:: አስወጣናቸው::»
«አስታውሳለሁ»
«ዛሬ ደሞ እርጉም ጨቋኞችን ከምድረ ገፅ ኡፍ ብሎ እንደ ጢስ ማስወጣት
ነው::»
«በመትረየስ?»
«እና በቦምብ፣ እና በታንክ::»
መልአከ ሞት መሸነፉ ገባው:: «አሁን እምቢ ብትል ስራህ እንደሆነ ከሰው
አድሜ አያልፍ:: ስለዚህ መቼ እና የት ልምጣ?»
የቼ ኮከብም «ቦሊቪያ እንገናኝ:: በ1987» አለው::
«ይሄን መሸከምያ የአለም ልጅን መውሰጃ ነው ብዬ አስመዝግቤ ነበረ
ይዤው የወረድኩ:: ልጁን ሳልይዝ አስም ይዤ ስመለስ የሰማይ ቤት
ቢሮክራሲያዊ ዘበኞች አያስገቡኝም::»
«ስሙን ትተኸው ሂድ:: እንችለዋለን:: አስታ ላቪስታ!»
«አስታ ላ ቪስታ!» (እንገናኛለን)
በነገራችን ላይ፣ ቼ ጉዌቫራ በኩባ ተልእኮውን ፈፅሞ ወደ ቦሊቪያ ሲሄድ
ፊደል ካስትሮ ሲሰናበተው ምን ተባባሉ ይሆን? ምናልባትም ቁም ነገሩ እንዲህ
ሳይል አይቀርም፣ «አቤት እኔና አንተ ምንኛ ድንቅ ጉዞ አብረን ተጓዝን! እንኳንም
አብረን ተጓዝነው! የወደፊቱን ማን ያውቃል? ይቅናህ! አስታ ላ ቪስታ!» ማለትም
እንገናኛለን:: አልተገናኙም እንጂ::... ቼ ጉዌቫራ በቦሊቪያ ከሞተ በኋላ እነ
ፊደል ካስትሮ በኩባ የግንባታ ስራቸውን ቀጠሉ - አሜሪካም ማዕቀብ ጥላ
ለማሰናበር ማለትዋን ቀጠለች::
አንክል ሳም ለኩባ የዘጠና አምስት ማይልስ ቅርበት ባላት በማያሚ
ከተማ ሬድዮ ሆዜ ማርቲ የሚል ከፈተ:: ሆዜ ማርቲ በኩባ ህዝብ አይታን

የሚጠረድ፣ ደሴቲቱን ከአስፓኝ ግዛት ነፃ ያወጣ ጀግና ነው። በሱ ስም የተቋቋመው ያህ የሲ.አይ.ኤ እጅ ያለበት ሬድዮ ጣቢያ የሚያሰራጨው ወደኩባ ሲሆን፣ ዓላማውም የኩባ ህዝብ የካስትሮን መንግስት እንዲገለብጥ ቅስቀሳ ለማካሄድ ነበር። አንክል ሳም በሌላ አገር ጉዳይ ጣልቃ ስለማይገባ የራዲዮ ሆዜ ማርቲ ሰራተኞች በሙሉ ኩባውያን ናቸው። የካስትሮን መንግስት ጠልተው ወይ ፈርተው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የፈለሱ ኩባውያን።

ከነዚህ ኩባውያን አንዱ ግን የኩባ መንግስት ደህንነት ድርጅት (ማለትም የስለላ ድርጅት) አባል መሆን አለበት። ምክንያቱም ሬድዮ ሆዜ ማርቲ የኩባን ህዝብ ሊያደናግርና ሊያወናብድ የሚችል አደገኛ ውሸት የተቀመመበት ፕሮግራም ከረዥም ዝግጅት በኋላ ተጠናቅቆ ወደ ኩባ ሊሰራጭ ሲሆን፣ ልክ በቀጠሮ ይመስል፣ የካስትሮ ቴክኒሺያኖች ጃም አደረጉት። ጃም ማድረግ ለኔ በማይገባኝ ዘዴ በብዙ የኤሌክትሪክ ኃይል በመጠቀም ያ ሬዲዮ ፕሮግራም በዚህ እንዲደመጥ በማንፈልግበት አካባቢ ሊደመጥ እንዳይችል ማድረግ ነው።

አንድ ሙሉ ፕሮግራም እነደዚህ ጃም ማድረግ በኩባ የኢኮኖሚ አቅም ሲታይ በጣም ብዙ ወጪ ይጠይቃል። በየቀኑ ሊደረግ አይችልም። ጉዳ ሊሆን ይችላል ብለን የምንገምተውን ብቻ ነው ጃም የምናረገው። ግን ጃም ለምን እናረጋለን? ምክንያቱም ለኩባ ህዝብ እውነቱን መናገር ብቻ አይደለም ተግባራችን። ሕዝቡን ከመርዘኛ የጠላት ውሸትም ልንጠብቀው ይገባናል። በቂ ችሎታና ስልጠና ያለው አንድ ጥይት ጋዜጠኛ ግማሽ ውሸቷን ከግማሽ እውነት ጋር እየቀላቀለ የአድማጮቹን እምነት ለመስረቅ ይችላል። ባያሳምን እንኳን ጥርጣሬን ያሳድራል።...

... አንድ ቀን የኩባ ሕዝብ ከማያሚ በአየር የመጣ ከድቶ የነበረ ኩባዊ ሀቫና አየር ማረፊያ ከጋዜጠኞች ጋር ሲነጋገር በቴሌቪዥን ይመለከታል። ጥቂት ቀደም ብሎ የዚህ ሰው በዚህ ሰዓት መምጣት ተነግሮ ስለ ነበረ አሁን ሰውየውን ብዙ ሰው ከቦታል። ቃለ ምልልስ ነው በሰውየውና በጋዜጠኞቹ መሀል። ሰውየው የሬድዮ ሆዜ ማርቲ ዳይሬክተር ወይም ክፍል ሀላፊ ነው፣ ማለት የካስትሮ መንግስት ጠላት። ያን ጊዜ በቤይ ኦቭ ፒግስ ውጊያ ጊዜ ካገር ሸሽቶ አሜሪካ ገብቶ እንጀራውን አብስሉ ምናልባት እስካሁን አሜሪካዊ ዜግነት ሳይሰጡት አልቀሩም።

«ማን ነዎት?»

«እኔ አገሌ ነኝ። የሬድዮ ሆዜ ማርቲ...»

«ሬድዮ ሆዜ ማርቲ የጠላ

እችል ነበር።»

«እንግዲያው ለምን እዚያ ገቡ?»

«አገሬን ለማገልገል» (የማነው ዓይነ አውጣ? ብለው እየተናደዱ ነው እዚያ የከበቡት ሰዎች።)

«የቱን አገርዎን?»

«ኩባን ነዋ! ሌላ ምን አገር አለኝ?» (ኧረ ይሄ የሴባ አይነ ደረቅ!)

«ለጠላቶችም በመስራት ኩባን ያገለግሏታል? እስቲ ያብራሩልን እባክትን?»

«ጠላቶችዋን የማገለግል መስዬ እዚያ ሆኜ ጊዜዬን ስጠብቅ ነበረ። ይህ ፕሮግራም ሲተላለፍ ኩባን ይጎዳታል ብዬ የምገመተው ፕሮግራም ሲመጣ ባለኝ ቦታና ስልጣን ተጠቅሜ ያንን ተቀርፆ ሲተላለፍ ዝግጁ ሆኖ የተቀመጠውን ፕሮግራም ሰርቆ በእሳት ማቃጠል።»

«ከዚያስ?»

«ከዚያማ ሲ.አይ.ኤ ሳይነቃብኝ ወደ አገሬ! ይኸውና ከብዙ ናፍቆት በኋላ አገሬ ገባሁ።»

«ይህን እንዴት ልናምን እንችላለን? እስር ቤት የሚጠብቅዎት አይመስልዎትም?»

«በጭራሽ! ከዚህ ታዝገዩ ሄጄ ነው'ኮ። እኔ አገሌ የኩባ መንግስት ደህንነት ድርጅት የውጭ ኦፕሬሽን ክፍል አባል ነኝ»

ዘይገርም ነገር! ሲአይኤን ምንኛ ይገርመው? Hasta la Vista!

ሰኔ 11፣ 1987

# 13

# ሆ ቺ ሚን
# *Ho Chi Minh*



በዚህ አምድ አልፎ አልፎ ስለማህትማ ጋንድሂ እና ነጻነት ስለ እነ ፊደል ካስትሮ እና ስለ ኩባ ነፃነት ስናስነብባችሁ ቆይተናል:: ዛሬ በወጣቶች አንባቢያን ጥያቄ ተመርተን ተገዝተናል:: አንዳንድ ልዩ ሰዎች አሉ:: በቅድሚያ ጀግኖች ለሀገራቸው የነፃነት አርበኞች ሆነው ወሳኝ ሚና የተጫወቱና ጊዜ ሲያልፍ ደሞ ህዝባቸው የሚኮራባቸው አባቶች ሆነው ያልፋሉ:: የአንድ አንድ ልዩ አገር መስራቾች ናቸው ካገራቸውም አልፈው ለአለም ህዝቦች ያበራሉ:: (የምንጠቅሳቸው ዓመተ ምህረቶች በፈረንጅ አቆጣጠር ናቸው)

በስመ ፍትህ ወነፃነት ወአብዮት ስለጀግናው የቪየትናም ልጅ ስለሆ ቺ ሚን እናወሳለን:: «ቪየትናም ለቪየትናማውያን» ሳይሆን አይቀርም የሆ ቺ ሚን የኑሮና የትግል መመሪያ:: መጀመሪያ ጃፓንን ቀጥሎ ፈረንሳይን ቀጥሎ ደሞ አሜሪካንን ተለማምጦ ሳይሆን ተራ በተራ ተዋግቶ ከምድረ ቪየትናም አስወጣቸው::

በየተራ ሲያሰናብታቸውም «ቻው ቻው!» አላቸው በጠራ ቪየትናምኛ። «ከንግዳህ በንግድ ልውውጥ ለጋራ ጥቅም ወይም በባህል ልውውጥ ለጋራ ደስታ ስትመለሱ የቪየትናም ሕዝብ በክብር ይቀበላችኋል:: እንገዛለን እናስተዳድራለን ብላችሁ እንደማትመለሱ ግን መጪዎቹ ትውልዶች

ይገባኛታል ብዬ እምናለሁ።»

እኔ ነኝ እንጂ አንክል እንኳ ንግግር አያበዙም - ድርጊታቸው ነው

ሰዎች የሚናገረው። በዚያን ወቅት በእንግሊዘኛው ተናጋሪ አለም አንክል

(አጎት) የሚባሉ አራት ብቻ ናቸው። እነርሱም አንክል ጆ/የሩሲያው ጆሴፍ

ስታሊን (አንክል ሆ/የቪየትናሙ) አንክል ማኦ/የቻይናው/ እና አንክል ሳም

ናቸው። አንክል ሳም ግን ሰው አይደለም የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ

መንግስት ነው። አንክል ሳም እንኳን የአሜሪካ ለምን የሰማይ መንግስት

አይሆንም? አንክል ሆ ስሜት አይሰጣቸውም። «ቪየትናምን ለቀህ እስከወጣህ

ድረስ በፈለከው አለም ንገስ» ሳይሉት አልቀሩም በልባቸው። አቤት አንክል

ሆ ደሞ ሲያከብራቸው!

ሀ/ ሆ ቺ ሚን እድሜ - ከ1890 - 1989/ ማለት ሰባ ዘጠኝ ዓመት/

ለ/ የአንክል ሆ- የፕሬዚዳንትነት ዘመን - ከ1945- 1989 /ማለት ሃያ

አራት/

ሐ/ አንክል ሆ የተዋጉበት ዘመን ሃያ ሰባት ዓመት!

መ/ አንክል ሆ ፈረንሳይን በተዋጉበት በስምንቱ ዓመት ውስጥ ሁለት

ጊዜ ህጋዊ የሆነ የሞት ሰርቲፊኬት ተፈርሞላቸዋል። ወይም «ሆ ቺ ሚን

የተባለ ግለሰብ በዚህ ቀንና ስፍራ መሞቱን አረጋግጣለሁ» ይላል ሕጋዊው

ፈረንሳዊ ሐኪም። «እፎይ ግልግል! ያ ከይሲ ሞተልን» ይላል የፈረንሳይ

መንግስት።

አንክል ሆ ታዲያ ለተወሰነ ጊዜ ተሰውረው ይሰነባብቱና ጊዜው ልክ

አሁን ነው ብለው በሚገምቱበት ሰዓት ተታኩሰውም ተጋድለውም ጉድ ካፈሉ

በኋላ «ኢሮ! አልሞትኩም! ውሸቴን ነው!» ይላሉ። እኔ ነኝ እንጂ አንክል ሆ

እንኳ ፉከራ አላስፈለጋቸውም።

ሠ/ ሳይሞቱ መሞት ብቻም አይደለም አንክል ሆ የሚችሉት። አንድ

ቦታ እያሉ የሌሉ መምሰሉንም ያውቁበታል ሁልጊዜም ለሞት የሚጋለጡት

ታጋይ ጓዶች'ኮ አንዳንዴ የመዘናናት ስሜት ይመጣባቸዋል። በንዲህ አይነቱ

ሰዓት አንክል ሆ ተሰብስበው ቆመው በሚያወሩት ጓዶች አጠገብ ያልፋሉ።

ከጓዶቼ የሚያያቸው አይጠፋም አያውቋቸውም እንጂ!

አንክል ሆ ደሞ መልክም ልብስም አለለውጡም። ግፉ ቢል መለያቸውን

ወደ ላይ አጠፍ ትከሻቸውን ጎበጥ አድርገው ይሆናል። በቃ ነው። እልፍ ኳሉ

በኋላ መለስ ሲሉ ታዲያ ጓዶቼ አይናቸው ያከፈትና ይገረማሉ ይስቃሉ። አይ

አንክል ሆ!

ረ. ስመሆኑ እኛና አንክል ሆ ቋንቋችን አይመሳሰልም፣ ሃይማኖቶችን ... ርቀት

አይተዋወቁም፣ በገሮቻችን መሐል የስንትና ስንት ኪሎ ሜትር

ያፈርቀናል፣ እማቸው ለንጉት መዋ ት ዕድ ተቸው፣ እኔ ውጊያ የሚሉትን አላጡቀውም በጦሬ ነው እንጂ:: እንግዲያው እንዴት ተገናኙትን ነው እኔ ስለሳቸው ስለፍላጎት ኩራት ጭምር የሚሰማኝ? በላይ እንዳልኩት አንዳንድ ጀግና ላገሩ ልጆች ከመሆንም አልፎ ተርፎ ለባዳዎች ጭምር ጀግናቸው ይሆናል:: የሰው ልጅ መሆን በቂ ነው ለእንዲህ አይነቶቹ... ሆቺ ሚን ወጣት እያለ ቬየትናም የፈረንሳይ ትልቅ ሰው አጓጓዥ መርከብ ውስጥ ስራ ያዘ:: ያ ሲበቃው ለንደን ከተማ ሲደርስ ከመርከቡ ተሰናብቶ አንድ ሆቴል ውስጥ ተቀጠረ::

አንደኛው የአለም ጦርነት ሲያልቅ ሲል ሆ ቺ ሚን ወደ ፈረንሳይ ተሻገረና የሶሻሊስት ፓርቲ አባል ሆነ:: ቀጥሎ የፈረንሳይ ኮሚኒስት ፓርቲ መስራች አባል ሆነ::

ጊዜው ሲደርስ ሆ ቺ ሚን አብዮታዊ ዘዴዎችን ለማጥናት ወደ ሶቭየት ህብረት ገሰገሰ:: እዚያ ደርሶ ከመቼው የኮሚኒስት ኢንተርናሽናል (ኮሚኒተርን Comintern) አባል እንደሆነ እንጃ፣ ወደ አስራ ዘጠኝ መቶ ሃያዎቹ ማለቂያ አካባቢ ላይ ወደ ምስራቅ እስያ ተመደበ::

በ1930 ሆ ቺ ሚን ኢንዶ ቻይኒዝ ኮሙኒስት ፓርቲን መሠረተ::

በ1930 ዎቹ ሆ ቺ ሚን ሲመቸው በሶቪየት ህብረት፣ ሲመቸው በቻይና እንዳሰኘው ይኖር ነበር:: የሚያሰኘው ደሞ ውድ አገሩን ከማንም ቅኝ ገዢ ነፃ ማውጣት ሆነ:: ሁለተኛው የአለም ጦርነት ሲነሳ ጊዜ ሆ ቺ ሚን በጠራ ሩስኪኛ በቻይንኛ እንዲሁም በቪየትናምኛ «ጠራችኝ አገሬ!» አለና ወደ ቪየትናም ተመለሰ::

በ1941 ሆ ቺ ሚን «ቪየት ሚን» የተባለውን የሀገር ወዳድ ተዋጊዎች ማህበር መሰረተና የጃፓን ወራሪ ጦር ለአራት ዓመት ከተዋጉዋቸው በኋላ አስወጡዋቸውና ሲያበቁ በሴፕቴምበር ሁለት ቀን አስራ ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ዓመተ ምህረት ሆቺማን የነፃይቱን የቪየትናም ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን መመስረት ዓወጀ:: ከእንግዲማ አንክል ሆ መሆን ላይቀረለት ሆነ::

አንክል ሆ ሰሜን ቪየትናምን ነፃ አወጡ እንጂ ከተማዋ ሳይጉን የሆነችው የደቡብ ቪየትናም ገዢዎች ግን አንክል ሳምን የሙጥኝ ብለው በሰላም ለመኖር እየሞከሩ ነው:: ዳሩ ምን ዋጋ አለው? በደቡብ ቪየትናም ውስጥ ቪየት ኮንግ የተባሉ የነፃነት አርበኞች ተነሱ:: እድሜ ለአንክል ሆ ሰሜን ቪትናም አስራ አምስት ዓመት ሙሉ ከቪየት ኮንግ ጐን ተሰልፋ ተዋጋች:: በመጨረሻም አንክል ሳምን «ያንኪ ጎ ሆም!» (ያንኪ አገርህ ግባ) ብለው አባረሩት!

ለሁለት ተከፍላ የነበረችው ቪየትናም በ1976 ዓመተ ምህረት ተመልሳ ተዋሀደች:: ደግ አደረገች እንኳንም ተዋሀደች!

ሐምሌ ፱፣ 1987

# ፴ 14 ፴

# ማኦ ዜ ዱንግ
# *Mao Tse-Tung*



የሚከተለውን ስነግራችሁ የነማኦ ዜዱንግ ቲፎዞ አድናቂ ተማሪ ሆኜ ነው። ግን መዋሸት መጨመር የለም። አያስፈልግማ! ታስታውሱ ከሆነ ተደጋጋሚ ለሆኑ ሰንበቶች ስለኩባ ስለ ውድ ነፃ አውጪ ልጅዋ ስለ ፊዴል ካስትሮ በደብልጥ ደሞ አለም ሁሉ አገሬ ነው፣ ጭቁን ሁሉ ወገኔ ነው ጨቋኝ ሁሉ ጠላቴ ነው ብሎ ለኩባ ከካስትሮ ጐን ቆሞ ስለተዋጋለት የአርጀንቲና ተወላጅ ጐን የመላው አለም ልጅ ቼ ጉቬቫራ አጫውቻችሁ ነበር።

የሆነች እሳት ወይ ብልጭታ ወይ መንፈስ ወይ ቃል የሚገኝላት ነብስ ላለች። እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች ሁሉም የሚጋሯት። ስለዚህ ኢጠቃልለን የነፃነት አርበኞችን የዓለምን ሕዝብ አንድ ስድስተኛውን ነፃ ያወጣ ነው። ማኦ ዜዱንግ ይባላል።

ማን እንደ ሊቀመንበር ማኦ!?

የነማኦን ወደር የማይገኝለትን ገድል የራሳቸው ቻይናዊ ቢነግረን ኖሮ ይኼ ቀዳ ማዋደድ - ራስን መካቡ ከነማኦ ሹመት ሽልማትን ፍለጋ ብለን ንቀን እናልፈው ነበር።

ነጋሪው ባዳ ቢሆን ግን?

ኤድጋር ስኖው ይባላል። (Edgar Snow) ሪፖርተር ሆኖ፣ የቻይናን የነፃነት ትግል፣ ከጋዜጣው አልፎ በወፍራም መፅሀፍ ነገረን።

እነ ማኦ ለህዝባቸው ነፃነት ሲታገሉ መጡ፤ ኤድጋር ስኖው ሀቁን አይቶ ለዓለም ሊመሰክር መጣ:: «ቀይ ኮከብ በቻይና ላይ» (Red Star Over China) ብሎ ዕፁ መሰከረ:: እኛም አብዛኛውን ከሱ ተቀበለን ነው የምናቀርብላችሁ:: ቀጣጣሪ ጋዜጠኛ አለ፤ ለሀቅ መስካሪ ጋዜጠኛም አለ::

በ1937 ጃፓን ቻይናን፤ በወረረች ጊዜ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ከጠላቱ ከኮሚንታንግ ጋር የተባበረ ግንባር ፈጥሮ ለመዋጋት ተገደደ:: ጃፓንን ድል አድርገው ካስወጧት በኋላ ሁለቱ ወገኖች ተመልሰው ተፋጠጡ:: የማይቀር ስለነበረ የቻይና እርስ በርስ ጦርነት ተከፈተ:: ምን ይላል ሊቀመንበሩ ማኦ? «ስልጣን ከጠመንጃ አፈሙዝ ነው የሚመጣው::»

ማኦ ዜዱንግ፤ ጆ ዴህ፤ ጁ አን ላይ እና ሌሎች ነፃ አውጪው ጦር አባላት አስሩን ኪሎ ሜትር፤ በእግር ተጉዘው በኦክቶበር 1935 ሸንሲ ደረሱ:: ከ1946 እስከ 1949 የነማኦ ኮሙኒስት አርሶ አደር ሠራዊት የሻንጋይሼክን ኮሚንታንግ ሠራዊት ተዋግቶ ከቻይና፤ ወደ ታይዋን አባረረው::

በ1949 ማኦ ዜዱንግ የህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክን መሠረተ:: በነገራችን ላይ፣ በ1934 ሊቀመንበር ማኦ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ከሶቪየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆኗን አውጆ ነበር:: የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ በ1937 አርባ ሺ አባላት ነበሩት:: በ1945 የአባላቱ ቁጥር አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ሆነ::

ጥቂት ቃላት ስለ ጁ ኤን ላይ:: በ1898 ከምሁራንና ከሀብታሞች ቤተሰብ ይወለዳል:: በ1920 ለትምህርት ወደ ፈረንሳይ ይሄዳል:: እዚያ ያለው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ አባል ይሆናል:: በ1924 ወደ ቻይና ይዘልቃል:: ከ1937 ጀምሮ ሶቭየት ህብረትን ደጋግሞ ይጐበኛታል:: በ1931 ወደ አገሩ ተመልሶ ከነ ማኦ ጋር ተቀላቀለ::

ጁ ኤን ላይ ሁለት ጊዜ ከኮሚንታንግ እስር ቤት አምልጧል:: ሁለቱንም ጊዜ ያመለጠው ሾልኮ ሳይሆን የሚጠብቁትን ዘቦች ልቀቁኝ ብሎ አሳምኖ ነው:: ሁሉም አብረውት ወደ ኮሚኒስቱ ሠራዊት ገቡ:: አሳሪህን አስከትለህ ወደ ጦር ግንባር::

ጁ ኤን ላይ ቻይናን ከ1944 እስከ 1976 ማለትም ሀያ ሰባት ዓመት ሙሉ በጠቅላይ ሚኒስትርነት አገልግሏታል:: በተጨማሪም እሱ የኮሚኒስት ፓርቲው ዋና ተደራዳሪ ስለነበረ ለሀያ አምስት ዓመት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን ሥራ ደርቦ ሰርቷል:: እጅግ መልከመልካም እና የኤድጋር ስኖው የቅርብ ጓደኛ የሆነው ጁ ኤን ላይ ሀያኛው ክፍለ ዘመን ካበቀለቻቸው ጥቂት ታላላቅ ዲፕሎማቶች አንዱ ነው::

በጁ ኤን ላይ የዲፕሎማሲ ጥበብና የድርድር ችሎታ ብርታት በ1950 የቻይና እና የሶቭየት ኅብረት የወዳጅነት ስምምነት ተፈረመ:: በ1955 የገለልተኛ

ሀገሮች የባንዱን ጉባኤ ተካሄደ። በ1972 ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት ኒክሰን ጋር የሻንግሀይ ስምምነትን ተፈራረሙ። ይህም ሰላም ወዳዱን ዓለም እጅግ አስደሰተ።

ጃ ኤን ላይ ያገሩ ሰዎች የሚወዱት የሚያከብሩትና የሚኮሩበት መሪ ነበር።

ክብር ነው ለኔ፣ ላገሬ ሰዎች እኔ የማኦን ጀብዱዎች በዚህ አምድ መንገር። እድሉ ስለደረሰኝ እኔም የቻይናን ያህል ሩቅ አገር ውስጥ ያን ያህል በሩቅ ዘመን የተካሄደውን በርቀት ቋንቋ ሳጫውታችሁ። ለነሱ ሞት ሽረት ለኛ ጭቆናና አብዮት። አንዳንዴ ይገርመኛል የነማኦ ማለፍና ታሪክ ተረት ሆኖ መቅረት።

እንግዲህ ከሩቅ እንደሚታዩኝ ስነግራችሁ ማኦ ዜዱንግ እና ጃ ኤን ላይ ከዚያ ሁሉ አመታት የናታቸውን የቻይና ቀኝና ግራ እጅ ሆነው አገልግለዋል። እንደ ሁለቱ እጆቻችን ሁሉ ለማስብና ለመነጋገር ሁለት እናረጋቸዋለን እንጂ እነሱ ግን የትጥቅ ጦርነት ሲዋጉም ይሁን የፖለቲካና አገርን የማስተዳደር እንደዚሁም ከነአሜሪካ ከበባ ቻይናን የማውጣት ተግባራትን የመፈፀም ይሁን አብረው ተባብረው ነው የሚታገሉላት። ከሁለት መደብ ህዝቧ አብራክ የወጡ። ማኦ ከገበሬው ከገባሩ ከግብር ከፋዩ ከተጠቃው ጃ ኤን ላይ ከምሁሩ ከሁብታሙ፣ ሲያልበው ከተመቸው መደብ። ማኦ ለገዛ ወገኑ ተከፍቶ ተናዶ ተነሳ። ጃ ኤን ላይ ከተመቸውና ሞልቶ ከተረፈው መደብ ተወልዶ፣ ይህን የተወለድኩበትን ከእንግዲህ አልፈልገውም፣ ወገን ለውጫለሁ፣ ለጭቁኖች ጉልበቴንም ትምህርቴንም ችሎታዬንም መድቤላቸዋለሁ አለ።

እንደ ቻይና ጥንታዊትና ለሌሎች ህዝቦች አገሮች ስልጣኔ አቀባይ አውራሽ የሆነችው የቅርባችን ግብፅ ሁለት ወንዞች ይመጡላታል ተስፋንና ህይወትን እያንሳፈፉ። ከኛ ከጣና ተነስቶ ጥቁር አባይ ይደርስላታል። ከጐረቤት አገሮች ተነስቶ ደሞ ነጭ አባይ። ሁለቱ ወንዞች ናቸው የግብፅ ህይወት።

ለነዚያ ዓመታት ደሞ ማኦ ዜዱንግ እና ጃ ኤን ላይ እንደ ሁለቱ ወንዞቻችን ሁለትም አንድም ሆነው ቻይናን በፍቅርና በወኔ አገለገሉዋት።

ማኦ ዜዶንግ ከቻይና ታላላቅ መሪዎች አንዱ መሆኑን ጠላቶቹ ሳይቀሩ ያምኑበታል። በቻይና የአምስት ሺ ዓመት ታሪክ ውስጥ ሶስት የአርሶ አደር ልጆች አድላቸውና ችሎታቸው ተቀናጅተውላቸው የሙሉዋ ቻይና መሪዎች ሆነዋል። ሁለቱ እንደ ጥንቱ ቢሆን አልጋውን ለልጆቻቸው አውርሰው ስርወ መንግስት መትከሉን ትተው፣ የህብረተሰቡን ስርዓት ለወጡ።

ሊቀመንበር ማኦ ካከናወናቸው ተግባራት ዋና ዋናዎቹ፣

ሀ. ኮሚኒታንግን አባርሮ ደክማ የነበረችውን ቻይና ተመልሳ አንጿን ቀና አድርጋ እንደተደላደለው ዘመናት ታላቅና የተከበረች እንድትሆን አብቅቷታል። በአንድ ገፅታው በናየው አርጅታ የነበረችውን ቻይና እነማኦ አደሷት።

ሊ በዓለም ታሪክ ከሁሉ የሰፋና የላቀ ህብረተሰብአዊ አብዮት አካሄዱ። አብዛኛውን መሬት ከግል እርስት ወደ ማህበራዊ መሬት ለወጡት። ሀብታሙን ባለመሬት መደብ አደከሙትና የአርሶ አደሩና የፋብሪካ ወዛደሩ መደቦች ክብራቸውና ማዕረጋቸው ከፍ አለ። በየዓመቱ እስከ ስምንት ሚሊዮን ቻይናዊ በረሀብ መርገፉ የድሮ የቅድመ አብዮት ታሪክ ሆነና ቻይናዊ ሁሉ ሠርቶ የሚበላ ሆነ። ማን እንደ ሊቀመንበር ማኦ?!

የቻይናን ባህልና ታሪክ ካነፁት ከቀረፁት ታላላቅ ሰዎች አንደኛውና ዋነኛው ኩንግ ፉዞ (ኮንፉሽየስ) ነው። ይህ ድንቅ መምህር አንድ ቀን ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሲሄድ በደን በተሸፈነ ባንድ ተራራ ስር ሲያልፍ አንዲት አሮጊት አገኘ።

«እዚህ ጫካ ውስጥ ያለው ክፉ ነብር ባሌንም ሶስት ልጆቼንም ተራ በተራ በላብኝ» አሉ አሮጊቷ ከሰላምታዎች በኋላ።

«እንዳቸው ከተበሉብዎት በኋላ ለምን ወደ አገራችሁ አልተመለሳችሁም?»

«ወደ አገራችንማ ከምንመለስ መሞት እንመርጣለን» አሉ አሮጊቷ።

«ምክንያቱስ?»

«ምክንያቱ አገራችን ጨቋኝ ገዥ ነግሶባታል።»

«አስተውሉልኝ» አለ መምህር፤ ኩንግፉ ወደ ደቀመዛሙርቱ እየዞረ፣

«እመቤቴ እውነታቸውን ነው ከጨቋኝ ገዥ ክፉ ነብር ይመረጣል»

እነ ማኦ ዜዱንግ እነ ጁ ኤን ላይ ይችን ታሪክ በጣም ሳይወዷት አይቀሩም። የውድ እናት አገራቸው አፈር ይቅለላቸው።

ነሐሴ 28፣ 1987

# ፲፭ 15 ፲፭

# ዶ ጎል
# *De Gaulle*



«ውሻ በበላበት ይጮሀል» ብለዋል አበው:: ተሰፋ እናድርግና እኛም በበላንበት ለመጮሀ እንሞክራለን::

በጉርምስናችን ዘመን ያበሉንን ጀኔራል ደጎልን ልንጮሀላቸው እንሞራለን:: በጉርምስናችን ዘመን ያበሉንን ጀኔራል ደጎልን ግን የማን ጨኸት ነው በገደል ማሚቶዎች ታግዞ እንኳ ቢሆን ጀኔራል ደጉልን እንኳን አሳቸውነታቸውን ሻርል ደጉልነታቸውን ቀርቶ ጥላቸውን ያህል እንኳ ልንነግራችሁ አንበቃም::

ግን እዚህ አካባቢ እኛ ራሳችን መሞከር ይኖርብናል:: አኑሮናል አብልቶናል ያውም ለሁለት ዓመት ያህል:: ውለታ ስላለብን በዚች አምድ ጥላውን ወይም የጥላውን ጥላ ያህል እናቅርብላችሁ::

ፍራንስ በረዥም ዘመንዋ ደጉልን የሚያክሉ ታላላቅ ልጆች የወለደችው ጥቂቱ ነው:: በብዙ አላስፈለጋትማ:: ሲያስፈልጋት ግን ኩተፍ ይላል:: እንደ ጀኔራል ደጉል - እነሱ እንደሚጠሩትም ሞን ዤኔራል:: ሻርል ደጎል ፍራንስን እንደ አገሩ ብቻ ሳይሆን እንደናቱ ጭምር ነበር የሚወዳትና የሚጠብቃት:: ፍራንስ በቢስማርክ ጊዜ እንደ ተደረገው ከጀርመን ጥቃት ወረራ እንዳ ይደርስባት ድንበራቸው ላይ የማዢኖ መስመር የተባለውን የመከላከያ አጥር ዘረጋች:: ፈረንሳዮች የማዢኖን አጥር የጀርመን ሀይል በምንም ተአምር ሊጥሰው አይችልም ብለው አምነው ዘና ብለዋል:: ኮሌኔል ሻርል ደጉል ግን ነቅቷል::

ያሉን ሰዎች ሊቀሰቅሳቸው ሊያስጠነቅቃቸው አገር መሰባሰብ ሄደ። የማጂኖ አጥር የድንጋይ ነው። ለሚቀጥለው ጦርነት ቀጣዩ መከላከያ አዲስ የመጣው ታንክ የተባለው የድንጋዩን አጥር በቀላሉ ጥሶ ማለፍ የሚችል ነው። ስለዚህ ማጂኖ አጥር ትላንት ሊጠብቀን ይችል ነበር እንጂ ዛሬ ግን እንደሌለ እንቆጠረውና ፍራንስ በተቻለ ፍጥነት የታንክ ተዋጊ ኃይሏን ቅድሚያ ሰጥታው ልታጠናክረው ይገባታል። ብራቸውን ከፍተው ይተውና ሰውን ሊባ ይላሉ።

ሻርል ደጉል መልእክቱን ለፈረንሳዮቹ ነበር የገለፃቸው። ነገር ግን ነገዩ ጠገሩ አይስበርም ሆነና ፈረንሳዮች አንዝበውት ችላ አሉት። ጀርመኖቹ ናቸው ኮሎኔል ደጎልን ልብ ብለው ያደመጡት።

የታንክ ሀይላቸውን በደጉል ማስጠንቀቂያ መሰረት ቅድሚያ ሰጥተው ቶሎ ብለው አሳደጉት። ጊዜው ሲመጣ የሂትለር ታንኮች የማጂኖን አጥር በቀላሉ በጥሰውት አለፉና በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ፓሪስ ገቡ። በስተደቡብ በምትገኝ ቪሺ በምትባል ከተማ ውስጥ የሂትለርን ትዕዛዝ የሚከተል አሻንጉሊት የፈረንሳይ መንግስት ተቋቋመ።

ሻርል ደጉል ለናቱ ደረሰላት። በለንደን የፈረንሳይን የስደት መንግስት አቋቋመ። በቢቢሲ ሬድዮ ለመላው ፈረንሳይ የታወጀው ጥብጡ እንዲህ ይል ነበር። ፍራንስ አልተዝረከረከችም። የእነጀኔራል ፔተን የቪሺ መንግስት የፈረሳይን ሕዝብ አይወክለውም። የምንወክለው እኛ በለንደን የተቋቋምነው እውነተኛው የፈረንሳይ መንግስት ነን። ውጊያውን እየቀጠልነው ያለነው ኃይሎች እኛ ነን። ቪቭላ ፍራንስ!! ፍራንስ ለዘለአለም ትኑር!!! እውነቱን ነበረ። ከእንግሊዝ ከሶቭየት ኅብረት ከአሜሪካን ጉን እየተዋጋች ነፃይቱ ፍራንስ በነሱ በ1945 ዓ.ም. ድል ተቀዳጀችና ጀኔራል ሻርል ደጉል ፓሪስ ሲገቡ ህዝቡ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ እጅግ በጣም የሞቀ የድል አድራጊ ጀግና አቀባበል አደረገላቸው።

የስደት መንግስት ወደ አገሩ ተመልሶ ፍራንስን ለጥቂት ጊዜ ከመራት በኋላ በምዕራባውያን ደንብ መሰረት ህዝቡ የሰላም ጊዜ መንግስት ሊመርጥ ወጣ። ይገርማል የሰው ነገር! ሞን ገኔራል ሳይመረጡ ቀሩ።

ሞን ገኔራል በውለታ ቢሱ ህዝብ ምክንያት እናታቸውን ፍራንስን አኩረፉዋት ያባቶቻቸው መኖሪያ ወደ ሆነችው ውድ መንደራቸው ወደ ኮሎምቢይ - ሊደዜግሊዝ ገቡና አገርን ከመጠበቅ ቀጥሎ ወደ ሚወዱትና ወደ ታወቁበት ወደ ተመሰገኑበት የስነፅሁፍ ስራቸው ተሰማሩ። ልቦለድ ሳይሆን ታሪክና ፖለቲካ ነው እሳቸው የሚፅፉት። እጅግ በተደነቀ «ክላሲክ» በሚባል የቋንቋ አጠቃቀም የቃላት አወራወር የሀሳብ አፈላሰስ። በነገራችን ላይ፣ ሞን ገኔራል ለሕዝባቸው ያሁን ወይ ለምክር ቤት ንግግር ሲያደርጉ እሳቸው ራሳቸው የፃፉትን ነው የሚያነቡት። የሳቸው ውበትና ግርማ ሞገስ የሚደመጥበት ፈረንሳይኛ የመልክቶቸውን ያህል ተለይቶ ይታወቃል። በእድሜ እየገፉ ለማገዝበ መነሾር

እየከፈለጋቸው ሲሄድ ንግግራቸውን ማንበብ ተዉት። በቃላቸው እጥንተውት ይመጡና ያ ድብርታም መነፅር መልካም መልካቸውን ሳያጠፋባቸው ይናገራሉ። እዚህም ላይ እየተስተዋለ። ሞን ዤኔራል በሰዎች መሀል ሲቆሙ ሁልጊዜም ከሁሉ ረዥም እሳቸው ናቸው። በውነቱ ቁመናቸው እጅግ ያምርባቸዋል። ሕዝባቸውም በበኩሉ ይህን ያውቅላቸዋል። እንዲያውም ቀልድ (ጆክ) ያወራባቸዋል - የጥላቻ ሳይሆን የፍቅር ቀልድ ነው ግን ይባላል። ሞን ዤኔራል አይናቸቸው ከድተዋቸዋል። ወረቀቱ ላይ የተፃፉት ፊደሎች ብቻ አይደሉም የማይታዩዋቸው። የተወደዱ ታላቅ መሪ እንደመሆናቸው መጠን ለጉብኝት ወደ ወዳጅ አገር ሲሄዱ አየር ማረፊያ ሲቀበሉዋቸው የሚመጡት ሰዎችም ድምፃቸው ጩኸታቸው ይሰማቸዋል'ንጂ ሰዎቹ ራሳቸው አይታዩዋቸውም። እሳቸው ደግሞ በጭብጨባው አፀፋ ፈገግታዎችና እጅ የሚውለበለብ ሰላምታዎች ይጠበቅባቸዋል። ሞን ዠኔራል ለፈገግታ እየተዘጋጀ አጠገባቸው የቆመውን አንጋቻቸውን «ሕዝቡ በየት በኩል ነው?» ይሉታል። ታድያ የሚያውቁትን ህዝብ ለማየት ያን ድብርታም መነፅር ሊያረጉ ኖሯል'ንዴ? ሆ!

ሞን ዤኔራል ባለመመረጣቸው አኩርፈው ወደ ትውልድ መንደራቸው ሲገቡ እንዲህ ብለው ነበር «ፍራንስ ባስፈለኩዋት ጊዜ ትጠራኛለች! እኔም እመጣለሁ።»

እውነትም ሲያስፈልጉዋት ጠራቻቸውና መጡ። እንደዚህ ሆነ። እነማህትማ ጋንድሂ እንኳ ጠመንጃ ቀርቶ ዱላ ሳያነሱ ኃያሉን የእንግሊዝ መንግስት ካገራቸው ካስወጡ በኋላ ኮሎኒያሊዝም ሊያበቃላት ጀመረ። ፍራንስ ብዙ ቅኝ ግዛቶች ይኑሩዋት'ንጂ አልጀሪያ ግን በፈረንሳዮቹ አይን ቅኝ ግዛታቸው አይደለችም - የባህር ማዶ ፍራንስ ነው የሚሏት - ብዙ ፈረንሳዮች አልጀሪያ ተወልደው አድገው እዚያው የሚኖሩ ናቸው። ሦስትና አራት ትውልድ አልፏል ከፍራንስ ተሻግረው አልጄሪያውያን ከሆኑ።

አልጄሪያውያን ግን እንዲህ አሉ። ጊዜው ደረሰ ፈረንሳውያን ከምድረ አልጄሪያ ወጥተው ተመልሰው ወደ አገራቸው የሚሻገሩበት። ወደን ሳይሆን ተገደን እስከ አራት አምስት ትውልድ አስተናግደናል። አልወጣም የሚል እንግዳ እየተገፈተረ ይወጣል።

የፈረንሳይ ህዝብ ለሁለት ተከፈለ። በዚህ በኩል እውነታቸውን ነው አገራቸው ነው ካልፈለጉን እንውጣላቸው አሉ፤ በዚያ በኩል ደሞ አገራችን ነው አባቶቻችን የተቀበሩበት እኛ የተወለድንበት ርስታችን ነው አሉ።

የእርስ በርስ ጦርነት ደመና በምድር ፈረንሳይ ታንዣብብ ጀመር። ሞን ዤኔራል ሰአታቸው ደረሰ። እሳቸው ተንብየውት እንደነበረ እናታቸው ጠራቻቸው። ወደ ፓሪስ ተመለሱ። የፈረንሳይ ህዝብ ጠንካራ መሪ እንደሚያስፈልገው አወቀ። ሞን ዤኔራል ተመረጡ። ፍራንስ ለልጆችዋ የሚበቃ

ሀብትም ፍቅርም አላት አሉ ሞን ዢኔራል፡፡ በባዚህ አልጄሪያ ውስጥ ያልተፈለገከ ፈረንሳዊ ጠፍ አዝጋ ተመለሰ፡፡

አልጄሪያ ምድር ላይ የብዙ ፈረንሳዊ እና የብዙ አልጄሪያዊ ደም ከፈሰሰ በኋላ በሞን ዢኔራል አመራር ቆራጥነትና ብርቱነት አልጄሪያ ነፃ ወጣች፡፡ የፈረንሳይ ሕዝብ ሲናጋ ሲቃጣው የነበረ አንድነት ተመለሰለት፡፡ ከሞን ዢኔራል አመራር ጋር ወደፊት!

አንድ፡- ዛሬ በደረስንበት የታሪክ ሂደት ቅኝ ግዛቶች ለፍራንስ አያስፈልጉዋትም፡፡ በዚህ ጊዜ እንግዲህ እያንዳንዱ ቅኝ ግዛት የሆነ ሀገር እንደ አንድ የፍራንስ ክፍለ ሀገር ተቆጥሮ ለፓርላማ ምርጫ ጊዜ አንድ አባል መርጦ ወደ ፓሪስ ይልካል፡፡ አንድ እለት ታድያ ፕሬዚዳንት ደጉል ከነዚህ ተመራጮች አራት ሦስቱን ይሰበስቡና መመሪያ ይሰጡዋቸዋል፡፡ «ወደ የአገራችሁ ተመለሱና አገራችሁ ነፃ ስትወጣ የሚረከባትን መንግስት አዋቅራችሁ ተመለሱ፡፡ ያ እንደተጠናቀቀ ነፃነት እናውጅና ሂዳችሁ የየአገራችሁ የመጀመሪያው መሪ ትሆናላችሁ፡፡» እንደዚያ ተባለ እንደዚያ ተፈፀመ፡፡

ሁለት፡- በሁለተኛው የአለም ጦርነት እነ ሂትለር ካከተመላቸው በኋላ አለም በሁለት ተፃራሪ ሀይሎች ተከፈለች፡፡ ሰር ዊንስተን ቸርቺል እንዳሉትም በነዚህ ሁለቱ መሀል የብረት መጋረጃ ተጋረደ፡፡ በዚህ በኩል አሜሪካ የምትመራቸው የካፒታሊስት አገሮች ምዕራባዊው አለም የሚባሉት፡፡ በዚያ በኩል ራሺያ የምትነዳቸው ኮሚኒስት አገሮች - ኮሙኒስቱ አገሮች የሚባሉት፡፡ በዚህ የሀይሎች አሰላለፍ አሜሪካ - ምዕራብ አውሮፓን ከሶቭየት ኅብረት ጥቃት ወይም ወረራ ለመጠበቅ ኔቶ (NATO) የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ማህበርን አደራጀች፡፡ ከነሙሉ ትጥቁ፡፡ ኒዩክለር ኃይል ጭምር፡፡ የኔቶ እዝ ጠቅላይ መምሪያ መስሪያ ቤቱ የት ነው? ፓሪስ ነዋ!

ሶቭየት ኅብረት ምዕራብ አውሮፓን በኒዩክሊየር ቦምብ እንዳታጠቃ የአሜሪካ ጋሻ ስላለ እነዚህ የኔቶ አገሮች እንዲህ ዓይነት መሳሪያ ማምረት አይኖርባቸውም ማለት ነው፡፡ ተባለ'ንዴ? አሉ ሞን ዤኔራል፡፡ ፍራንስ የሌላ ሀገር ሀይል አይጠብቃትም የራሷ ሀይል አለላት፡፡ እና ፍራንስ የራሷን ኒክሊየር ኃይል ማምረቱን ተያያዘችው፡፡ (Force de Frappe) «ፎርስ ደፍራፕ» ይሉታል ሞን ዤኔራል «ደምሳሽ ሀይል» ማለት ነው፡፡ መች ይሄ ብቻ? ፕሬዚዳንት ደጉል ኔቶ ከፓሪስ እንዲወጣ አዘዙ፡፡ ወደ ሌላ አገር ይሂድ፡፡ ይኼም አልበቃቸው፡፡

ፍራንስ ክርስቲያን ካፒታልስት ምዕራባዊ አገር ናት እንጂ በአሜሪካ በኩልም አልተሰለፈችም፤ የሶቪየት ኅብረት ጠላትም አይደለች፡፡ ይህንኑ በድርጊት ሲያሳዩ ደሞ ብዙ አጀብ አስከትለው ወደ ሞስኮ የወዳጅ አገር ጉብኝት አደረጉ! በጣም ሞቅ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው፡፡

አሜሪካኖቹ ጭስስ! እርር! ታድያ ሞን ዤኔራልን ምን ያድርጉዋቸው?

የም የሚያደርጉትን ቢያጡ በጆክ ወረዱባቸው። አንድ ሁለቱን በሚቀጥለው እንነግራችኋለን። የሞን ዤኔራል አምላክ እድሜ ይስጠን አሜን!

«ደጎልን ምን ታረገዋለህ?» ይባባላሉ አሜሪካኖች ጭስስ እርር ድብን እያሉ። «እኛ ነን የቡድኑ አምበል» ሲሉ ሞን ዤኔራል ደሞ «እንኳን አምበል ዘጠኙን ሁኑ ከፈለጋችሁ። ቡድኑ ውስጥ ግን ፍራንስ የለችበትም። የራሷን ቤት እያስተካከለች ስለሆነ ከማንም ቡድን ጎን ለመሰለፍ ጊዜም ፍላጎትም የላት። ከዚያ የተረፈ ግን የዩናይትድ ስቴትስና የፍራንስ ቋሚ ወዳጅነት ይለምልም!»

«ደጎልን ምንም አታደርገውም። ታሪክንም ፈጠራንም እያቀናጀህ ጆክ ትወረውርበታለህ'ንጂ። ያውም እሱ በመንፈስ እንጂ በስጋ በሌለበት!»

... ሞን ዤኔራል እያረጁ ሄዱና አይኖቻቸው ከዱዋቸው! በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ታዘዘባቸውና የተባባሰ አረጋዊ ህመም አደረባቸው። ከባድ ቀዶ ህክምና ተደረገላቸው። ሁለት ሦስት ወር ማረፍ ይገባቸው ነበረ። የናት ሀገር ጉዳይ ሆነባቸውና ሁለት ሶስት ሳምንት ያህል እንዳረፉ እነዚያን የፍራንስ ቅኝ ግዛት የነበሩትን አስራ ሦስት አገሮች ጨምሮ አስራ ሰባት (?) የሶስተኛው አለም አገሮችን አከታትለው ለመጎብኘትና ከፍራንስ ጋር ያላቸውን ወዳጅነት ለማጠናከር ኤሮፕላናቸውን አስጭነው ተነሱ። እንኳን ለሽማግሌ ለጉብል አድካሚ ይሆናል በዚያ ሁኔታ ያን ያህል ብዙ አገር መጎብኘትና የዲፕሎማሲ ስራ ማካሄድ። የኛ ገመምተኛ ሽማጌ ግን ለውድ ፍራንስ እንኳን እያገገሙ እየታመሙ ቢሆንም ይጓዙላታል! በስራ ይጠመዱላታል! ቢያስፈልግም ይሞቱላታል።

«እንኳን ሞት እርጅና አለ» አለ አንበሳ በትግርኛ። ሞን ገኔራል ትዝ ሲሉኝ የማስታውሳት ምሳሌ ናት። እሳቸውም ሊናገሩዋት ይችሉ ነበረ። በምትቀጥለው ጨዋታ ላይ የአገሮቹን ስም ሳላሳስትም አልቀረም ጊዜው በጣም ስለራቀብኝ ይቅርታ።

ሞን ዤኔራል የጉዞው አድካሚነት እየተሰማቸው ድካማቸውም እየታወቀባቸው ሄደ። ለሴኔጋል ህዝብ ንግግር ሲያደርጉ «ውድ የማሊ ህዝብ ሆይ» ብለው ጀመሩና እስከመጨረሻው ቀጠሉበት። አገር አሳስተዋል ብሉ ያረማቸውም የለ እሳቸውም መሳሳታቸውን ልብ አላሉ። የአንበሳን ዲስኩር ማን ያቋርጣል? በኋላ በግል ይቅርታ እየለመኑትና እየባበሉት ይነግሩታል'ንጂ። ይህን ሲነግሩዋቸው «እድሜ አተላ!» ይሉ ነበር ሞን ገኔራል አማርኛ ቢያውቁ ኖሮ።

ሰዎች ለነብሳቸው ወደ ኢየሩሳሌም ወይም ወደ መካ አድካሚ ጉዞ ይጓዛሉ። ሻርል ደጎልም እንደነብሱ ለሚወዳት ለውቢቱ ፍራንስ የአድካሚ አድካሚ ጉዞ ይጓዝላታል። በዚህ ጉዞ ላይ አንድ ላቲን አሜሪካ አገር ጉብኝተው ሲሰናበቱ ለላቲን ህዝቦች ልማድ ሞን ዤኔራል ሸኚዎቻቸውን ተራ በተራ እያቀፉዋቸው ጉንጭ ለጉንጭ ሲስሙዋቸው ቆዩና አንዱን ከሳሙት በኋላ በቁጣ «ፓርዶን!»

ይትሮ:ታላ ብለው ወደዚያ ገፈተሩት። ለካ ሳይታወቃቸው የገዛ አንጋቾቸውን ኖሯል የስንብት የሳሙት!

በጊዜው መገናኛ ብዙኃን እንደተከታተልነው ቴሌቪዥኑም ሬድዮውም ጋዜጣውም የሚያወራው ስለዚህ አስገራሚ የፕሬዚዳንት ደጎል ጉዞ ነበር። ዓለም በሙሉ እየተቀባበሉ ስለ አገር መሪ ይህን ያህል አውርቶ አያውቅም። ምናልባት ፕሬዚዳንት ኬኔዲ በተገደሉ ጊዜ ካልሆነ። ዩሪ ጋጋሪን የጠፈር ተጓዥ፣ መሀመድ አሊ ቦክሰኛው፣ አበበ ቢቂላ ማራቶኒስቱ - ለነዚህ የተጮኸውን ያህል ነበር ለሸማግሌው ገመምተኛ ረዥሙ ጉዞ የተጮኸው።

እንግሊዝኛ ተናጋሪ ህዝቦች በጥቅል አንግሎ - ሳክሰን ይባላሉ። እነዚህ አንግሎ ሳክሰኖች ሞን ጀኔራል እንደ ትዕቢተኛ አስቸጋሪ ግማሽ እንቅፋት ግማሽ ምርኩዝ አርገው ነበር የሚያዩዋቸው። በጦርነቱ መሀል ጀኔራል ደጎል ለንደን እያሉ ከሰር ዊንስተን ቸርቺል ጋር ብዙ ግንኙነትና ንትርክ ነበራቸው። ሰር ዊንስተን በጭራሽ አልተመቻቸውም የሞን ጀኔራል ጠባይ (በነገራችን ላይ የኛ አርማ አንበሳ እንደሆነ፣ የነደጎል አርማ ደሞ የሉሬይን መስቀል ነው።) አንድ ቀን ሰር ዊንስተን ምርር ብሏቸው እንዲህ ቀለዱ፤ «ሰው ሁሉ መስቀሉን እንዲሸከም ታዟል። እኔ የታዘዘብኝ መስቀል የሉሬይን ነው።»

ከፈረንሳይ ንጉሶች ከሁሉም የገዘፈው ፈላጭ ቆራጭ ሉዊ አስራ አራተኛ ነበር «ፀሀዩ ንጉስ» ነው ቅፅል ስሙ። አንድ ቀን የገንዘብ ሚኒስትሩ ለሉዊ ለግሉ የማይመቸውን የገንዘብ ወጪ ጠየቀ።

«ለምን እንዲህ ይሆናል?» አለ ፀሐዩ ንጉስ።

«ለሀገር እንዲበጅ ነው ግርማዊ ሆይ»

«ይግባህ! ሀገር ማለት እኔ ነኝ» አለና ከፍራንስ ራሱን አስቀደመ።

አንግሎ ሳክሰኖቹ እንዳሉት ከሆነ አገሩ ሪፐብሊክ ነው መሪውም ፕሬዝዳንት ነው ደባል እንጂ የሞን ጀኔራል የመቁረጥ የመፍለጥ ስልጣን ግን ከፀሀዩ ንጉስ እንኳ ይብልጣል።

አሁን አሁንማ እንደ አግዜርነት ይቃጣቸው ጀመር።

የሞን ጀኔራል የመጨረሻ ጅብዱ አሜሪካውያን ደቀ መዛሙርታቸው እንደመሰከሩት ፍርሃት የሚባል ነገር ሲያልፍ ጨርፏቸው አያውቅም። ማን ማንን ሊፈራ ባነዘ? ሻርል ደጉል እንዴት እንደራሱ ስጋ የለበሰውን ሰው ሊፈራ ይችላል፣ የማይደረገውን!?

ግና ሞን ጀኔራል ሸምግለው ለቀዶ ህክምና ማደንዘዣ ሲደረግላቸው ክሎሮፎርም የሚባለው የሚተነፈሰው በግዳቸው እያስተኛቸው ሲሄድ ሞት ምን እንደሆነ ብልጭ ብሎ ታያቸው።

ታክመው ድነው እያገገሙ ከማርኮፓሎ የማያንስ ጉዞዎቻቸውን ፈፅመው ተመለሱ። እና ሲያስታውሱት ጊዜ - ክሎሮፎርም በትንፋሻቸው ጉትቶ ወደ እንቅልፍ

ሐዩቅ ሲናስኮማችው ከቻለ - ሞት ደሞ በዘኮሱ...

— ሞን ገኔራል ከሚኒስትሮቻቸው ጋር ስብሰባው ሲያበቃ ጠቅላይ ሚኒስትራቸውን (ከሳቸው በኋላ ፍራንስን እንዲመሩ ሲያወርሷቸው የመረጡዋቸውን) «ፖምፒዱ - ትንሽ ቆይታ እናድርግ» አሉዋቸው ሁለቱ ብቻቸውን ሲቀሩ ሞን ገኔራል እንዲህ አሉ - «ፖምፒዱ መቸስ ምንም ቢሆን ሰው ሞት አይደርስብኝም አይልም:: ስለዚህ ምናልባት እንዲያው ምናልባት እኔው ራሴ እንኳ ልሞት ስችል ወይም እንበል ከእለታት አንድ ቀን ስጋ ለባሽ'ል ስለዚህ መሞት አለብህ ብለውኝ እሺ ብዬ ስሞትላቸው ያን ጊዜ የት ነው የምቀበረው?

«ላስብበት ይፈቀድልኝ ሞን ገኔራል» አለና ፖምፒዱ ሶስት ቀን አስቦ ተመለሰ::

ፓሪስን ለማያውቋት አንባቢዎች ለጥ ያለ ሜዳ ላይ ተዘርግታ ሳለች ከሩቅ ከየትም የምትታይ ኮረብታ አለቻት:: ኮረብታዋ ላይ ደሞ በማለዳና በምሽት ሰዓት ደማቅ ዕንቁ መስላ የምትታይ ቤተክርስቲያን፤ ሴዜንቫሊድ ትባላለች፤ ከናፖሊዮን ጋር በምተው የተመሰሱ ጀግኖች የተቀበሩባት ናት:: ናፖሊዮንም የተቀበረው እዚያው ነው:: በዚች ጨዋታችን በታሪክ መድረክ ላይ ለመጀመሪያ ብቅ ሲል ናፖሊዮን የወታደር ማዕረጉ ኮርፖራል ነበር (በኛ አስር አለቃ?) እንግዲህ ፖምፒዱ ለፍራንስ ክብርና ገናናነት ከናፖሊዮንና ከወታደሮቹ የበለጠ የሰራ እንደሌለ ስለሚያምን ሞን ገኔራል ከነዚያ የናት አገር ጀግኖች መሐል መጋደም አይከፋቸውም እንዲያውም ደስ ሳይላቸው አይቀርም እያለ በልቡ «ሞን ገኔራል ያዘዙኝን ማረፊያ ቦታ አግኝቻለሁ» አለ በፈገግታ:: «እሺ ተናገር» አሉ በእርጋታ:: «ለዜንቫሊድ!» ሞን ገኔራል ንቀትና ንዴት በሚውለበለብበት ገፅታ «እንዴት አንተ?» አሉ «ከማንም ኮርፖራል ጋር?»

ፖምፒዱ በእፍረት አጉነበሰ:: «ይቅርታ ሞን ገኔራል» ይፈቀድልኝና እንደገና ልሞክር::»

«በል እስቲ ሞክር» አሉ ሞን ገኔራል - ድምፃቸው ውስጥ «ታገኘው የምትችል አይመስለኝም እንጂ» የሚል ቅላፄ አለ::

ሰባት ቀን አለፈ:: ፖምፒዱ ገብቶታል:: ለካ ሞን ገኔራል እንዲህ ማስታቸው ኖሯል:: የፍራንስ ታላቅነትና የዓለም ብርሀንነት እንዲሁም ዘላቂነት እነ ናፖሊዮን ለመላው አለም አሳይተዋል - ግን ለጥቂት ጊዜ - ለአንድ ሰው እድሜ ያህል ብቻ ነበር::

ሴዜንቫሊድ ፓሪስ ሆነን ከየትም ብንመለከት ከምንም ቀድማ ትታያለች እንጂ የፓሪስ መሀል እምብርቷ ግን ኮከብ አደባባይ ነው:: ወደ ሁሉም አቅጣጫ እስከ ፓሪስ ወሰን የሚሄዱ ሰፋፊ ጐዳናዎች መነሻቸው ኮከብ አደባባይ ነው:: (የአብዮት ሳይሆን የአቅጣጫ የዲአሜትሪ ኮከብ) እዚህ የፓሪስ መሐል መሐል

ባስሙያ ሴት የሰፋችው ሴማት ወይም ሰፌድ መሐል ያሰን ይመስላል። እዚያ ላይ ሲያዩት ቢውሉ የማይሰለች የድንጋይ ሐውልቶች የፍራንስን ታሪክን የሚያሳዩበት በታሪክ ዘላቂ ድንጋይ የተገነባ የጄኔራል ደጉልን ድል አድራጊ ሠራዊት እንኳ በመሐሉ ያሳለፈ በሌላ ጊዜም የፓሪስን ህዝብና ትራፊክ የሚያሰልፍ ግዙፍ ቅስት አለ።

እንግዲህ ከሐይማኖትና ከሌላዎቹ አላማዎች ሌላ እናት ሀገር የምትባል የእምዬ ማርያምን ያህል የሚወዷት የሚኖሩላት አለች። ለሞን ገኔራል ውቢቱ ፍራንስ ትባላለች።

ኮከብ አደባባይ ላይ ላዩን የፓሪስ ውበት! መሐሉ የትራፊክ መመላለሻ እና እንደ ሞን ገኔራል ያሉ ለናት አገር ተሟሙተው ስንቱን አብሮ ዘማች ሰውተው የተመለሱ በመሀሉ በሰልፍ ሲያልፉ አገርና ህዝብ የሚሳተፍበት ልዩ ስፍራ ነው።

ከዚያም ጋር ከሀይማኖት ውጪ ሆነን ስናየው ይህ ኮከብ አደባባይ ከፍራንስ ምድር ሁሉ የተለየ ቅዱስ ቦታ ነው። ፍራንስ እንደ ሁሉ ታላላቅ ሀገሮች እግዜርም ካዘዘላት ወንዝና መንደር ተነስታ ታላቅ ለመሆን በቃች። ነገስታት ዋና የጦር መኳንንቷ በመላው አለም ስለተዋጉላት ብዙ ብዙ ወታደሯ እዚያ ረግፎ ቀርቷል። ለትውልድ አገሩ አፈር አልበቃም። የዚህ ሁሉ ወታደር መቃብር ተምሳሌት ነው ኮከብ አደባባይ። በፈረንሳዮቹ ህሊና ያን ሁሉ ስሙም መልኩም ያልታወቀ በዚያ ሁሉ ዘመን ለፍራንስ የሞተላት ዜጋዋ እዚህ ኮከብ አደባባይ ነው የተቀበረው። እጅግ በጣም የሚያምረው ግዙፍ የድንጋይ ቅስት ስራ ያለው ቅዱስ ስፍራ «ያልታወቀው ወታደር መቃብር» ይባላል።

ፖምፒዱ አለቃውን እንደሚያስደስት እርግጠኛ እየሆነ «ሞን ገኔራል የርሶ ማረፊያ ኮከብ አደባባይ ነው» አለ።

«ምን አልክ?» አሉት በተግሳፅ ድምፅ

«ከማንም ካልታወቀ ወታደር ጋር?!»

«ይቅርታ ሞን ገኔራል።»

አስራ አምስት ቀን አለፈ። ዛሬስ ፖምፒዱ በእርግጠኝነት ደረቱን ነፍቶ

«አግኝተነዋል ሞን ገኔራል!»

«ካገኘኸው እስቲ ተናገር»

«ኢየሩሳሌም!»

«አሁንኳ ይሻላል። በል ከኤምባሲዎቸው ጋር ጉዳዩን ፈፅም።»

«ተፈፅሟል»

«ስንት አስከፈሉን?»

«ሀምሳ ሚሊዮን ፍራንክ»

«እረ እነዚህ ቀንቋና ስግብግብ አይሁድ!» ብለው ጮሁ። ሞን ገኔራል ሐምሳ ሚሊዮን ፍራንክ ያውም ለስባት ክንድ ቦታ!! ያውም ለሶስት ቀን !?

ታህሳስ ፩፣ 1989

# ዣን ፖል ሳርትርና ሌሎቹ
# Jean-Paul Sartre & Others



ስለ ፕሬዚዳንት ሻርል ደጉል ያነበቡ «ምን ገፔራል በጣም አስደስተውናል።
ስለ ፕሬዚዳንት ሻርል ደጉል ያነበቡ «ምን ገፔራል በጣም አስደስተውናል፡፡ ስለ ፕሬዚዳንት ሻርል ደጉል
ከላቸው ጉን ከተሰለፉት ሌሎች ታጋዮች ውቢቱ ፍራንስ ልጆች ስለ ጥቂቶቹ
ጨምረህ ብታወጋን ጥሩ ነበር» ባሉኝ መሰረት እነሆ፡፡

ዣን - ፖል ሳርትር (Jean-Paul Sartre 1905-1980) ፈላስፋ የልቦለድና የትያትር ደራሲ፤ እና ታጋይ ነበር፡፡ ሁለቱን የዓለም ጦርነቶች አልቂት ያዩት የሃያኛው ክፍለ ዘመን ኤውሮፓውያን በድሮው አስተሳሰብ ሊወሰኑ አልቻሉም፡፡ ኤግዚስቴንሺሊዝም የሚባል ፍልስፍና መጣ፡፡ የዚህ ፍልስፍና ዋና ድምፅ ሳርትር ሆነ፡፡

ሳርትር ኤቴይስት ነው፡፡ ማለት እግዚአብሔር የለም ባይ ነው፡፡ ለሳርትር ሰው ነው ያለው፡፡ ከሰው ጋር እንኖራለን፡፡ ጓደኝነት አለ፡፡ ፍቅር አለ፡፡ ፍቅረኛውና ደቀመዝሙሩ ጓደኛው ሲመን ደ. ቦቧር (Simon de Beauvoir) ትባላለች፡፡ እንደሱው ደራሲም ፈላስፋም ናት፡፡ ለሴቶች እኩልነት ቀንደኛ ታጋይ ነበረች፡፡ (The Second Sex) ሁለተኛው ፆታ የሚለው መፅሀፍዋ ለሴቶች ነፃነት ትግል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከማድረጉም በላይ ስለሴቶች ጥልቅ ፍልስፍና አለው፡፡ ሁለቱ ፍቅረኞች አልተጋቡም - ሳርትር እስኪሞት ድረስ ሳይለያዩ ይሁን የቅርብ ቅርበት ያለውን ግንኙታቸውን ቀጠሉት እንጂ፡፡ የህይወት ታሪኳን ፅፋለች፡፡ በዙሪያው የፍራንስን ታሪክ ያንፀባርቃሉ፡፡ ስለ ሳርትርና እሷን ራሷን ጨምሮ ስለኖሩት የፍልስፍና ደቀመዛሙርት በልቦለድ ቅርፅ ታሪካቸውን ፃፈች፡፡ (Prix Goncourt) የጎንኩር ሽልማትን ተቀብላበታለች፡፡ የጎንኩር ሽልማት የፈረንሳይ የስነፅሁፍ ሽልማቶች ቁንጮ ነው፡፡

ሳርትር ስራውን እየሰራ ለሰው ጊዜ አይሰጥም። ማንም ሰው ከሳርትር ጋር ለመነጋገር ፈልጎ ጊዜ የለኝም ተብሎ አያውቅም። ውይይቱ የፈለገውን ሰአት ወይም ሰዓታት ያህል ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ሰርትር ጊዜ አለው። አንድ እልቆ ያለ ዱርዬ ሌባ ጉረምሳ የእስር ቤቶች ደምበኛ ነበር፤ ዣን ዥኔ (Jean Genet) የተባለ። እስራት ላይ እያለ አንድ ተውኔት ፃፈና ለሳርትር ላከለት፤ አይልኝ ብሎ።

ሳርትር አነበበውና ተገረመ። ወስዶ ለሚያውቃቸው የትያትር ባለሙያዎች ሰጣቸውና አነበቡት ወደዱት ሰሩት። የፈረንሳይ ቲያትር ሰማይ ላይ አዲስ ደማቅ ኮከብ ብቅ አለ። የፈረንሳይ ትያትር አዲስ ፈር ቀደደ፤ ያ ከንቱ ዱርዬ ጉርምሳ። ሳርትርና ገርኔ በጣም ተቀራረቡ። ሳርትር ቅዱስ ዥኔ በሚል ረዕስ የፃፈው ህይወት ታሪክ ይህን ጉረምሳ ለፈረንሳይ ስነፅሁፍ የተሰጠ ትልቅ ፀጋ አድርጐ ያቀርበዋል።

ሳርትር አጭር ሆኖ ጠንጋራ ነው። ወፍራም መነፅር ያረጋል። ፈላስፋና ደራሲ ብቻ አይደለም። ጠረኛም ነው። ፍርሀት አያውቅም። ይሁዲ በዚያ ላይ ፈረንሳዊ እንደመሆኑ ከናዚ ወታደር ጋር መዋጋት የተቀደሰ ተግባር ነው። በጦር ሜዳ ቆስሎ ተይዞ ከዓነ በኋላ ከአንድ አመት እስራት አመለጠ። ውጊያውን ለመቀጠል የጥፋት ልኡካን እንደ አዶልፍ ሂትለር የአጥፍተህ ጥፋ ተልእኳቸውን ፈፅመው እንደ አንበሳ መንጋ በነፃነት ነፋስ ተበትነው አለፉ። አውሮፓ ለጊዜውም ቢሆን እፎይ አለች። ሳርትር ቤት ግን እፎይታ አይታወቅም። ለሰው ልጅ ነፃነት መዋጋት ነው። በበአር ብርሃን ይሁን ወይ በጥይት ጨለማ መዋጋት ሃያ ዓመታት ምድራቱ አንዳች እንድታበቅል የሚያደርግ መርዛማ በምብ ሰሜን ቬየትናምን መደብደብዋ ኢ-ሰብአዊ ወንጀል ነው። ስለዚህ ዩናይትድ ስቴትስ ኦቭ አሜሪካ ስቶክሆልም ከተማ ውስጥ በተሰየመው ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባታል። ዳኞች፡- እንግሊዙ ፈላስፋና የማቲማቲክስ ሊቅ በርትራንድ ራስል እና የኛ ዣን-ፖል ሳርትር። ዳኞቹ ጉዳዩን አጥንተው ምስክሮች ሰምተው የሰሁፍ ማስረጃዎች አገላብጠው በሲኒማ የተቀረፀውን የጦርነቱን አስከፊ ፋሺስታዊ ገፅታ በዓይናቸው አይተው በልባቸው ፈረዱ። አሜሪካ በፍጥነት ያሀን በአገር ደረጃ የጋንግስተር ወንጀልዋን አቁማ ጦርዋን ከሰው አገር ማስወጣት አለባት።

በነሱ 1964 ዓ.ም. ደራሲ ዣን-ፖል ሳርትር በስነፅሁፍ የኖቤል ሽልማት አልቀበልም አለ። ናቀው። ክብሩ አልፈቀደማ። ሳርትር እግዜር የሰም ቢልም ቃሉ ስምን መልእክ እንደሚያወጣው እኛ እናውቃለን። ዮሀንስ - ጳውሎስ ነው ስሙ - የአንድ ሀዋርያ የመንፈስ ፅናት ያን ሁሉ ትግልና ውጊያ ለማካሄድ አይበቃም ተብሎ የሁለት ሀዋርያ ስም ተሰጠው።

አንድሬ ማልሮ (André Malraux 1901-1976) የልበለድ ደራሲ የኪነጥበብ

ፈላስፋና እና የማይበገር ታጋይ ነበር። በጉርምስናው ዘመን ወደ ካምቦዲያ ተጓዘ። እዚያም ለመቶዎች አመታት ጫካ ውስጣቸው ጠፍተው የነበሩ የጥንት ቤተ መቅደሶችና ከተሞች እየተፈለጉ እየተገኙ ነበር። ማልሮ በገለ አዘህ ፍለጋ ውስጥ ገብቶ የአርኪኦሎጂ ቁፋሮ አካሂዶ ከቤተመቅደስ የተሰያዩ ሐውልቶችና የቅርስ እቃዎችን አገኘ። በአርኪኦሎጂ ቁፋሮ የተገኘ ንብረት ሁሉ የመንግስት ነው አሉና አገሩ ገባ።

አንድሬ ማልሮ ወደ ቻይና ሄደ። በ1927 የቻይና አብዮት ሲካሄድ በቅርብ አጥንቶና በድርጊት ተሳትፎ (Le Condition Humaine) (የሰው ልጅ ሁኔታ) የተባለውን ታላቅ ልበለድ ፃፈ። ፍልስፍናና ድርጊት በደራሲውም በገፀባህሪያቱም ውስጥ ተወራራሽ ናቸው።

የስፓኝ እርስ በርስ ጦርነት ተነሳ። ማልሮ ወደዚያ ዘመተ፤ ፋሽስቶችን ሊወጋ። እንደ ማልሮ አይነቶቹን ጦረኞች የአገር ድንበር አይወስናቸውም። የሪፐብሊካኑ ወገን አየር ሀይል ውስጥ አባሻር ሆኖ ተዋጋ። በ1940 ተማረከና ታሰረ። አመለጠ። የስፓኝ ሪፐብሊካዊ ወገን ድል ሆነ። ማልሮ ወደ አገሩ ተመልሶ የነፃይቱ ፍራንስ ጦር ኃይል ውስጥ አባሻር ሆኖ ጦርነቱ ቀጠለ።

ማልሮ ሩቅ ምስራቅን ስለሚወዳትና ስለሚያውቃት የገኔኔራል ደጉል ልዩ መልእክተኛ እየሆነ ተመላልሶባታል።

ከ1958 እስከ 1968 ማልሮ በፕሬዚዳንት ደጉል መንግስት ውስጥ የባህል ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ለውቢቱ ፍራንስ ባህል ትልቅ የግንባታ አስተዋፅኦ አድርጓል። በከፍለ ሀገሩ የባህል ተቋማትና ሙዚየሞች አስከፍቷል። (Les Voix du Silence) የዝምታ ድምፆች የሚል ትልቅ መፅሀፍ ውስጥ ለዘመኑ ሰዎች ስነጥበብ በስፋትና በጥልቀት ተንትኖባቸው አይናቸውን ከፍቶላቸው የልባቸውን አድርሶላቸዋል።

(Albert Camus 1913-1960) አልበር ካምዩ በናቱ እስፓኝ ባባቱ ፈረንሳይ የትውልድ አገሩ አልጄሪያ። ሁለተኛ ደረጃ እያለ የትምህርት ቤቱ የእግር ኳስ በር ጠባቂ ነበር። መዋኘት ነው ከሁሉ የሚወደውና የሚያዘወትረው ስፖርት።

አልበር ካምዩ ጋዜጠኛ ሆኖ ሲሰራና ድህነትን ሲሰናበታት ሳለ የአልጄሪያ ብሄራዊ ነፃ አውጪ ግንባር ፈረንሳይን ከአልጄሪያ ለማስወጣት የትጥቅ ትግል ጀመረ። ካምዩ በጋዜጣው እንዲህ ሲል ፃፈ «ምንም እንኳ እዚህ ተወልደን ብናድግና አልጄሪያን እንደ እናት አገር ብንወዳት አልጄሪያኑ በበኩላቸው እምርረው ዘርህ ከፈረንሳይ ከሆነክ ካገራችን ውጣልን ካሉ ህሊናችን እንድንወጣ ያስገድደናል። ጓደኞቹ ተቆጡት። አብደሀል? ከንቲባውን እየወከውለ» በዚች ፅሁፍ ከመታሰር ሌላ ምንም የምትፈይደው የለም። ይልቅ አምልጥ ወደ ፍራንስ ገስግስ አሉና መሄጃና ለአጭር ጊዜ መኖሪያ ገንዘብ አዋጥተው ሰጡት።

እደሜ ለወዳጆቹ፣ ከእስራት ለትንሽ አመለጠ። ገባ። ይሄ የሆነው በ1939 ነበር።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጣ። የናዚ ጦር የማገርኖ መስመር የተባለውን የፍራንስ መከላከያ ጥሶ ገባ። በሁለት ሳምንት ውስጥ ፓሪስ ተያዘች። እነ ዤኔራል ደጐል ነፃይቱ ፍራንስ ጦርነቱን ትቀጥላለች ብለው የአርበኝነት ውጊያዎችን ከለንደን ሲያውጁ፣ አልቤር ካምዩ በፓሪስ Le Combat ትግል የተባለ ህቡዕ ጋዜጣ አዘጋጅ ሆነ። ያ ካምዩ የጀመረው ጋዜጣ ከነፃነት በኋላ የፈረንሳይ ኮሙኒስት ፓርቲ ልሳን ሆነ - እስከዛሬም አለ።

ከድል በኋላ ካምዩ ወደ ስነ ፅሑፍና ወደ ትያትር ስራ ተሰማራ። አማተር የተውኔት ቡድን አቋቋመ።

ፈላስፋው ካምዩ Myth of Sisyphus (የሲዚፈስ ተረት) በምትል አነስተኛ ፅሁፍ እንዲህ ይላል። ዋናው ጥያቄ ሀቅ ምንድን ናት ወይም ተፈጥሮ ከየት መጣ አይደለም። ዋናውና አንገብጋቢው ጥያቄ ልኑረው ወይስ ልሙተው ነው። ሌላዎቹ ጥያቄዎች ለመኖር ከወሰንኩ የምደርስባቸው ናቸው/እኛ ፈላስፋ እንለዋለን እንጂ እሱ ግን ፈላስፋ አይደለሁም - ሞራሊስት ነኝ ነበር ያለው።

በዚህ በኩል፣ ይላል ካምዩ፣ እኔ ማወቅ ከመፈለግ አልፎ ማወቅ አለብኝ የምል ሰው ነኝ። በዚያ በኩል ይሄ እውስጡ ያለሁትና እፊቴ የተደቀነው አለም ደሞ በኔ በሰው የማወቅያ አቅም ሊታወቅ አይችልም። የኔ ጭልፋ አእምሮ የሁሉ ሁሉን ውቅያኖስ ቀድታ ልትጨርሰው ትችላለችን? ይሄ ነው የሰው ሁኔታ። Absurd (አብሰርድ) ይለዋል ካምዩ፣ ለእውሩ ሰው ደማቅ ፋኖስ እንደመስጠት፣ አብሰረድ። እንደ ፈላስፋዎች በሉጂክ ተጠየቅ ዘዴ ሳስበበት ኖርኩ አልኖርኩ ምንም ልዩነት ስለማያመጣ ብኖረውም ያው አብሰርድ ኑሮ ነው ብሞተውም ያው አብሰርድነቱ አይወጣም።

ኑሮ ሌላ ፍልስፍና ሌላ። እኔ እየኖርኩ ነው ያለሁት። ካለመኖር ወደ መኖር ስነቃ ከልጅነት ወደ አዋቂነት ስነቃ ያው እየኖርኩ ነው ያለሁት ስለዚህ መኖሩን ልቀጥልበት ነፃ ምርጫ ወስጃለሁ። ስኖር ደሞ በነፃነት ነው። በባርነት ከመኖር ለነፃነት ብዋጋላት እመርጣለሁ።

አልቤር ካምዩ በ1957 የኖቤል ሽልማት ሲቀበል ምን አለ? ክብር ይሰማኛል አመሰግናለሁ። እንደኔንደኔ ቢሆን ኖሮ ግን እቺ ሽልማት ለጓደኛዬ ለአንድሬ ማልሮ ነበር የምትገባው።

ጥር 4፣ 1989

# 16

# ማርክ ትዌን
# *Mark Twain*



ሳሙኤል ላንግሆርን ክሌመንስ (በነሱ 1835-1910) የኖረውንና ያስተዋለውን ያስላሰለውን ማን ጣፈው ቢባል ማርክ ትዌን ራሱ በገዛ እጁ። ሳም ክሌመንስ ባስራ አንድ አመቱ አባቱ ስለሞቱ ከትምህርቱ በኋላና ቅዳሜ እሁድ እየሰራ የቤተሰቡን ገቢ ይደጉም ነበር።

ባስራ ሶስት አመቱ ትምህርቱን አበቃና አንድ አሳታሚ ድርጅት ውስጥ እንደ ሰልጣኝ ሠራተኛ ሆኖ ተቀጠረ። ስልጠናውን ሲጨርስ ዛበር አመት የሚበልጠው ታላቅ ወንድሙ ጋዜጣ ስለነበረው የዚያ ጋዜጣ ህትመት ሰራ ሆኖ አልፎ አልፎም አጫጭር ፅሁፎችን እያቀረበ ይታተምለት ነበር። በየተራ ዕቃዎች አድራሽ ተላላኪ፣ የምግብ ሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ሻጭ፣ የብረት ቀጥቃጭ ረዳት ሆኖ ሠርቷል።

ቀልድ የተቀላቀለባቸው ፅሁፎቹ ቀስ በቀስ ይወጡ ጀመር። ከአስራ ሰምንት አመቱ ጀምሮ ተጓዥ ሆነ። አንድ ቦታ ረግቶ መኖር አይሆንለትም። ለስድስት አመት ያህል ሚሲሲፒ ወንዝ ላይ ሰልጣኝ ፓይለት (መርከብ ነጂ) እና በኋላም እራሱን የቻለ ፓይለት ሆኖ ኖረ። የሰው አይነት እየተመለከተ በትውስታው መዘገበ።

በእርስ በርስ ጦርነቱ ምክንያት የሚሲሲፒ የመርከብ ንግድ ሲቋረጥ ወደ ምዕራብ አሜሪካ እንደ ተጓዥ ጋዜጠኛ ሆኖ ሄደ።

...ከዳን በኋላ ሳም ክሌመንስ ገንዘቡን በልዩ ልዩ ቢዝነስ ወይም ኢንተርፕራይዝ ወይም የንግድ ድርጅት ላይ ኢንቨስት አድርጓል። ማለት አክሲዮን ይገዛና ከአመታት በኋላ ትርፍ ማግኘት ይጀመራል የሚል ነው ሀሳቡ። በማዕድናት፣ በጫካ ዛፎችና ለመርከብ ይሁን ለቤት ወይም ለወንበር ጠረጴዛ ወዘተ በሚያውሉዋቸው ሙከራዎች ለሚገኝ ሀብት፣ በኋላም ወርቅና ብር ማዕድናት ለማግኘት አደን ወይም ፍለጋ በዚህ በዚህ ላይ ገንዘቡን ያፈሰውና ዞሮ ዞሮ ሳንቲሙ አይመለስለትም።

ወደ ኋላ ጊዜ ፊደሎችን ራሱ ለቅሞ ራሱ የሚያስተካክል ማሽን ከሚሰሩ ሰዎች ጋር ብዙ ብዙ ሺ ዶላር አወጣ። አልሆነለትም።

... ይህን ሁሉ ገንዘብ ከየት ያመጣዋል? አንደኛ ከልቦለድ መፅሀፎቹ ሽያጭ ከዚያ በፊት በህይወት እያለ ከማርክ ትዌን እኩል መፅሀፎቹ የተሸጡ ደራሲ አልነበረም።

አንደኛ ንግግሮች። ሁለተኛ ከደብዳቤዎቹና እየተከፈለው ከሚያደርጋቸው ንግግሮች። ይህ ሁለተኛው የገቢ ምንጭ ትንሽ ማብራሪያ ይጠይቃል።

በ1886 (በነሱ) ከሳን ፍራንሲስኮ ወደብ ተነስታ ወደ ሆኖ ሉሉ (ሀዋይ) የምትጓዝ መርከብ የመጀመሪያ ጉዞዋን ስትሄድ ሳክራ ሜንቶ ዩንየን (Sacramento Union) የተባለ ጋዜጣ ማርክ ትዌንን በሷ መርከብ ሄዶ እንዲመለስና በጉዞው ላይ ስለሚያጋጥሙ ነገሮች ጋዜጣው አንባቢያን ደብዳቤዎች እንዲፅፍ ቀጥሮ ላካው። እነዚህ ብዙ ማስተዋልና ሳቅ የታመቀባቸው ደብዳቤዎች እጅግ ተወዳጅ ሆኑ። አንድ ሁለተኛው ደሞ ከጉዞው መልስ አዳራሽ እየተከራየ ከፍለው ለሚገቡ ሰዎች ስለጉዞዎቹ ያወራላቸዋል። የጋዜጣው ደብዳቤዎቹ የጣሙአቸውና በወሬ የሰሙዋቸው ሰዎች የማርክ ትዌንን ገለፃዎች ለመስማት እየተንጋጉ ይመጡ ጀመር።

ዳሩ ምን ያረጋል? ከተሰፋ በቀር ምንም የሌለው ጀማሪ የንግድ ወይም የፋብሪካ ድርጅት የተጠራቀመውን ገንዘብ ይበላውና ትርፍ ኪሣራ ይሆናል። ደግነቱ አንድ ሮጀርስ የተባለ የአንድ ትልቅ የነዳጅ ዘይት ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የማርክ ትዌን የልብ ጓደኛ ሆነ። እና በሮጀርስ ዕቅድና እርዳታ ማርክ ትዌን ከአሜሪካ ውጭ እየዞረ ንግግር እያደረገ ገንዘብ አጠራቅሞ እዳዎቹን ሁሉ ለመክፈል በቃ። ከለንደን እስከ አውስትራሊያ፣ (ኤውሮፓ ጨምሮ) ዓለምን ዞራት - አድማጮቹን ስላያቸው አገሮችና ሕዝቦች እያሳወቀና በሳቅ እያንከተከተ። እነዚያ ደብዳቤዎቹና እነዚህ ንግግሮቹ ለመፅሀፎቹ ገዥዎችን ያዘጋጅላቸዋል - መፅሀፎቹ ደሞ በበኩላቸው ለንግግሮቹ አድማጮችን ያስገኙላቸዋል። «እነና

ራሴ ስንቶ ጋገዙ ይል ነበር ማርክ ትዌን አማርኛ ቢያውቅ። ሚስተር ሳሙኤል ላንግሆርን ክሌመንስ ጉዞ ስለሚወዱ ይጓዛሉ። ያስተውላሉ። ማርክ ትዌን ከሌሎ ተቀብሎ ለጋዜጣዎቹ ደብዳቤዎችን ይልካል። ደብዳቤዎቹ በማንበያ የቀበሏቸውን ገጠመኞችና ሳቆች ንግግሮቹ በዋንጫ ያጠጡዋቸዋል።...

...ለንደን ደርሰ የመጀመሪያው ንግግር ሲከፈት አዳራሹን የጨናነቁትን አድማጮች ግር አሰኝቷቸው ነበር። «ከቡራንና ክቡራት፣ «ሼክስፒር» አዝማሪው ሞቷል (ይህንን'ኮ ማንም አድማጭ ያውቀዋል፤ አዝማሪው ሰራሱ ከሞተ ሰስት መቶ አመት አልፎታል። ማርክ ትዌን ባዘነ ድምፅ ይቀጥላል) «የሚልተን፣ የእንግሊዝኛ ቅኔ ጥበብ እውሩ ፋናችን ሞቷል እውሩ ሚልተንም ከሞተ ዘመን የለውም። ሰውየው ዞሮበታል? ግን አልሰከረም ያስታውቃል። ማርክ ትዌን ከመቶዎች ዓመታት በፊት የተነሳ እስከ ሃያ ዓመት በፊት የሞቱትን የእንግሊዝኛ ሥነ ፅሁፍ እንቁዎችን እያደነቀ፣ የመሞታቸውን የጠነዛ የዛገ መርዶ ሲናገር ደቂቃዎች አለፉ። አድማጮች እያዘኑለት በትዕግስት ሲያዳምጡ ማርክ ትዌን ይቀጥላል።

«ቻርልስ ዲክንስ፣ ያ ሳቅና እንባ የሚያፈራርቅብን አንጋፋ ልቦለድ ደራሲያችን ሞቷል። እና እኔም እራሴም ብሆን ከሠሞኑ ጤና አጥቻለሁ»

(አዳራሹ በሳቅ ፈነዳ)...

...ሚስተር ክሌመንስ ድሮውንም ትዕግስት የላቸው፣ ዕድሜ እየጨመሩ ሲሄዱ ቶሎ ቶሎ ቱግ ማለት አመጡ። ያን ሁሉ ሳቅ እየሳቁና እያሳሳቁም ኑሮ መራራ ሆናባቸዋለች። እነሆ ለመሰናበቻ ቅምሻ የማርክ ትዌን «ንግግሮች»

1. ስለ ስታቲስቲክስ። «ውሸት አለ፤ የውሸት ውሸትም አለ። ከዚያ በላይ ስታቲስቲክስ»

2. ሲጋራ ማጨስ ስለመተው «ሲጋራ መተው ቀላል ነው። እኔ እራሴ መቶ ጊዜ ትቼዋለሁ»

3. ስለ አዳም «አዳም የመጀመሪያው ባለ ውለታችን - ሞትን ያስገኘልን»

4. ስለ አሜሪካን ኮንግረስ። «ውድ አንባቢ ሆይ፣ እስቲ የኮንግረስ አባል ነኝ ብለህ አስብ። እንደ ገናም ደደብ ነኝ ብለህ አስብ ሁለቱም ያው ናቸው።»

5. ቃላቱ ሳይሆን ሐሳቡ እነሆ። አዳምን ሔዋን አሳተችውና እፀ በለሱን አበላችው? ነገሩ እንኳ እንደዚያ አልነበረም። አዳም ከኤደን ሲመለስ ሔዋን ሮጣ ተጠመጠመችበትና እያለቀሰች ትነግረዋለች። እፀ በለስ በላሁ እንግዲህ መሞቴ ነው። ፈራሁ ትለዋለች።

አይዞሽ ሂዋንዬ፣ ሞት ቢመጣም አይለየንም፣ አለና ሆን ብሎ ራሱ በላ እጁ እፀ - በለሲቱን ቀጥፎ ገመጠ! አይ አዳም! አይ ማርክ ትዌን! አይ እኛ ም ራሳችን ሰሞኑን ጤና አለመሆናችን...

# ገማል አብደል ናስር
# *Gamal Abdel Nasser*



አንዳንድ ሰው በልጅነቱ የሚያልመውንና የሚመኘውን ሲያድግ በድርጊት ይፈፅመዋል። ግብፃዊው ገማል አብደል ናስር እንዲህ አይነት ሰው ነበር። ከ1918-1970 (በፈረንጅ አቆጣጠር)

ንጉስ ፋሩቅ ለስሙ የግብፅ ንጉስ ነው እንጂ አገሩን የምትገዛው እንግሊዝ ናት። ገማል በልጅነቱ የእንግሊዝን አገዛዝ ይቃወም ነበር። ምኞቱ ፀሎቱ ከእለታት አንድ ቀን ግብፅን ነፃ ማውጣት ነበር። ሰላሳ አመት ሲሆነው ማለትም በ1949 «ነፃ መኮንኖች» የተባሉ ህቡዕ ማህበር አቋቋመ። ከሶስት አመት ስውር ድርጅትና ዝግጅት በኋላ ኮሎኔል ናስር ነፃ መኮንኖች የተሳካ መፈንቅለ መንግስት አካሄዱ። ንጉስ ፋሩቅን ገደሉት ወይ? ምን ይገሉታል! እነ ናስር እኮ የተነሱት አገራቸውን ነፃ ለማውጣት ነው እንጂ፣ ማንንም ለመግደል ወይ ለማሰር አይደለም። ፋሩቅ ከዚያ በኋላ ወደ ግብፅ አልተመለሰም።

ጄኔራል መሀመድ ናጊብ በመላ ግብፅ እጅግ የተወደደ የተከበረ ሰው ነበር። ነፃ መኮንኖች ጄኔራል ናጊብን ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገው ሹመዋቸው ከሁለት አመት በኋላ በ1954 አሰናበቱዋቸውና ናስር ራሱ ስልጣኑን በደፋ ያዘ።

በ1956 ነፃ መኮንኖች አዲስ ሕገ መንግስት አርቅቀው ሕዝቡን አፅድቅልን አሉት፣ ብዙ በሆነ ድምፅ አፀደቀላቸው። ወዲያውም ናስር ፕሬዚዳንት ሆነ።

ናስር አረባዊ ሶሻሊዝም የሚባል የኢኮኖሚ ስርአት አመጣ:: ከሀብታም ባለመሬቶች ላይ 243 ሺህ ሄክታር መሬት ወረሰና ለደሀ ገበሬዎች አከፋፈለ::

ግብፅን ነፃ ከማውጣት ቀጥሎ የናስር ዋና አቅድ አስዋን የሚባለው ቦታ ላይ አባይን በትልቁ ገድቦ ለአገሪቱ አስተማማኝ የውሃ ክምችት ለማስገኘት ነበር:: እንግሊዝና አሜሪካ ታድያ እንተባበርሃለን እንገድብልሃለን ሲሉት ከቆዩ በኋላ ሐሳባቸውን ቀየሩ፤ በጉዳዩ የለንበትም አሉ:: አንዳንዴ አገሮችም እንቁልልጭ ይጫወታሉ:: ናስርን እንቁልልጭ ማለት ግን አደገኛ ጨዋታ ነበር - ያን ጊዜ ገና አልታወቀም እንጂ::

ያን ጊዜ ስዊዝ ካናል ኩባንያ አብዛኛው አክሲዮን በእንግሊዝ ነበር:: ስዊዝ ካናል ሜዲቴራኒያን ባህርና ቀይ ባህርን ያገናኛል:: የአውሮፓ ንግድ ከምስራቁ ዓለም ጋር የሚካሄደው አብዛኛው በዚህ ካናል በሚያልፉ መርከቦች እየተጫኑ ነበር::

ስዊዝ ካናል ኩባንያን የግብፅ መንግስት ወረሰው:: ጉድ ፈላ:: ናስር አበደ ተባለ:: የእንግሊዝ የፈረንሳይና የእስራኤል ነገስታት ተማከሩ በዚህ በኩል:: እስራኤል የሲና ባህረ ሰላጤን ወረረች:: በዚህ በኩል ደሞ እንግሊዝና ፈረንሳይ ስዊዝን ወረሩ:: ዓለም በጭንቀት ተወጠረች::

ወረራ አይፈቀድም ተባለ:: አሜሪካ በተለይ ሽንጧን ገትራ ተከራከረች:: የተባበሩት መንግስታት አባላት አገሮች ተባብረው ሌላውን የተባበሩትን መንግስታት አባላት አገር ከወረሩትማ የተባበሩት መንግስታት ለምን ተቋቋመ?

እስራኤል፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ጦሮቻቸውን ከምድር ግብፅ ሲያስወጡ ዓለም እፎይ አለ:: ዓለም ናስር ላይ አተኮረ:: በዓለም ዓይን እየገዘፈ ሄደ::

ናስር ፊቱን ወደ ሶቭየት ሕብረት አዞረ:: አግዙኝ የአስዋን ግድብን እንገንባው:: የግብፅ ሕዝብ አስተማማኝ ውሃ ያስፈልገዋል:: ያው እንገብጋቢው የዳቦ ጥያቄ ነው:: ሶቪየት ሕብረት ሳታመነታ ኢንጅነሮቿን ላከች:: ግብፅን ያህል የሶስተኛው ዓለም ትልቅ አገር ከምዕራቡ ጋር ስትኮራረፍ ሶቭየት ሕብረትን ወዲያውኑ የወዳጅነት እጇን መዘርጋቷ የማይቀር ነው::

የአስዋን ግንብ ዘመናዊ ቴክኒዎሎጂ ከፈጠራቸው ታላላቅ ተአምራት አንዱ ነው:: ከሰባቱ የአለም መደነቂያዎች አንዱ እዚያው ግብፅ ጊዛ ውስጥ የሚገኘው የኩፉ ፒራሚድ ነው:: የአስዋን ግድብ መጠኑ ወይም ትልቅነቱ የጊዛ ፒራሚድን አስራ ሰባት ጊዜ ይበልጠዋል:: ለዚያውም ያ የአንድ ፈርኦን መቃብርያ ይሄ የአንድ ሕዝብ መመገቢያ:: በግድቡ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ አንድ መቶ ሺህ ኑቢያውያን መንግስት ወደ ሰራላቸው ሌሎች መንደሮች ተዛውረዋል:: ይሄ እንግዲህ ግድቡ ለሚያከማቸው ሰው ሰራሽ ሐይቅ ቦታ ለመልቀቅ ነው:: ናስር ሀይቅ ተባለ ከነስሙ:: በዐለም ሁለተኛው ትልቁ ሰው ሰራሽ ሃይቅ እሱ

ነው።

በሦስተኛው ዓለም ውስጥ በተለይም በሙስሊሞቹ ዘንድ ገማል አብደል ናስር ከሀገር ወዳድ ጀግና ነፃ አውጪዎች አንዱ ሆነ።

እነ ማሀትማ ጋንዲ ህንድን ከአራት መቶ አመት ቅኝ ግዛት በኋላ ነፃ አወጡ።

እነ ማኦ ዜዱንግ ቻይናን ከውስጣዊና ከውጫዊ አገዛዝ ነፃ አወጡ።

እነ ገማል አብደል ናስር ግብፅን ከሁለት ሺህ ዓመት ልዩ ልዩ የባዕድ አገዛዝ በኋላ ነፃ አወጡ።

ነፃ መውጣት ብቻም አይደል። ግብፅ የአረቡ ዓለም መሪ ሆነች።

እንደ ብዙዎቹ የዘመኑ ተራማጅ አረቦች ሁሉ ናስርም የአረቡ አለም አንድ የሚሆንበት ቀን ይናፍቀው ነበር። ስዚህ የአረብ አለም መዋሃድ የመጀመሪያው እርምጃ በ1958 ግብፅና ሶርያ ተዋሀዱና የተባበረው የአረብ ሪፐብሊክ ተባለ። የዚህ የአዲስ አገር ፕሬዚዳንት ናስር ሆነ። ሌላ ማ ሊሆን ኖራል!?

ከስዊዝ ካናሉ ግጭት በኋላ ናስር እያደር በሶቭየት ህብረት ላይ መተማመንን እያበዛ ሄደ። ሶቭየት ህብረትም የጦር መሳርያ በገፍ ትሸጥለት ገባች።

ጀግና ሄዶ ሄዶ መደናቀፍ አይቀርም፤ ናስርም ተደናቀፈ። በ1967 በጋዛ ሰላጤ ተሰማርቶ የነበረውን የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ሀይል አስወጣ። ኤላት የተባለችውን የእስራኤል ብቸኛ የቀይ ባህር በር የነበረችውን የወደብ ከተማ ዘጋት።

እስራኤል ተነሳች። አንድ አይናው ጀኔራል ሞሼ ዳያን በስድስት ቀን ጦርነት ግብፅን ድል አደረገ። (አቤት ስንትና ስንቱን አንድ አይና ልጅ ነው ከዚያ በኋላ ቅፅል ስሙን ሞሼ ዳያን ያሉት!)

ሌላ መሪ ቢሆን ውድቀቱ ነበር። ናስርም ውድቀቴ ነው ብሎ ከስልጣን ተሰናበተ። አይሆንም አለ የግብፅ ህዝብ፤ ብዙቱ ታይቶ ተሰምቶ የማያውቅ ሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ወጣ። «ገማል አብደል ናስርን እንደግፋለን! ለዘለዓለም ይኑር!»

ናስር ወደ ስልጣኑ ተመለሰ።

በ1970 ገማል አብደል ናስር በልብ ህመም ሞተ። ግብፅ ሰውድ ልጅዋ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

ልዩ ማስታወሻ፤ ኮሎኔል ናስር ፕሬዚዳንት ከሆኑ በኋላ መኖርያ ቤታቸውን አልቀየሩም። እስኪሞቱ እዚያው ነው የኖሩት።

«የምን ቤተ መንግስት ነው?» አለ ናስር «ይልቅ ግድብ እንስራ»

ሐምሌ 17፤ 1986

ጋሽ ስብሐት ባልተገደበ ነፃ አስተሳሰባቸውና በሰላ አይናቸው ብዙ ሰውቀቶችንና ጥበቦችን አንብበዋል፣ መርምረዋል።

ከ40 ዓመታት በላይ ሳያቋርጡ መፃፍ የመቻላቸው ሚስጥር ለኔ ሲመስለኝ ለተፈጥሮና ለሰው ልጅ በግልጽ ታማኝ የሆነ ስብዕና ያላት ነብስ ተሸላሚ በመሆናቸው ጥምር ነው።

በዚህ መድበል 18 የሀገራችን፣ የአፍሪካና የዓለም ባለታሪኮች ተካተዋል። ታሪኮቻቸውን ስንመረምር የጋሽ ስብሐትም አገባበፅ ከባለታሪኮቹ እኩል አስደሳች ሆኖ እናገኘዋለን።

ጋዜጠኛ ሰንዱ አበበ

... «ፖምፒዱ መቸስ ምንም ቢሆን ሰው ሞት አይ
ነገርም ስለዚህ ምናልባት እንዲያው ምናልባት
እንኳ ልሞት ስችል ወይም እንበል ከእለታት አንድ
ለዓለሁ ስለዚህ መሞት አሉብህ ብለውኝ እሺ ብዬ ስ
ያን ጊዜ የት ነው የምቀበረው?
ላስብበት ይፈቀድልኝ ሞን ዤኔራል» አለና ፖምፒ
ቀን አስባ ተመለሰ::
... «ሞን ዤኔራል ያዘዙኝን ማረፊያ ቦታ አግኝቻ
በፈገግታ:: «እሺ ተናገር» አሉ በእርጋታ:: ለዜንቫሊ
ዤኔራል ንቀትና ንዴት በሚውለበለብበት ገፅታ
እንተ?» አሉ «ከማንም ኮርፖራል ጋር?»
ፖምፒዱ በእፍረት አጉነበሰ:: «ይቅርታ ሞን
ይፈቀድልኝና እንደገና ልሞክር::»
... ፖምፒዱ አለቃውን እንደሚያስደስት እርግጠኛ እየ
ዤኔራል የርሶ ማረፊያ ኮከብ አደባባይ ነው» አለ::
«ምን አልክ?» አሉት በተግሳፅ ድምፅ
«ከማንም ካልታወቀ ወታደር ጋር?!»
«ይቅርታ ሞን ዤኔራል::»
አስራ አምስት ቀን አለፈ:: ዛሬስ ፖምፒዱ በእ
ደረቱን ነፍቶ
«አገኝተነዋል ሞን ዤኔራል!»
«ካገኛችሁ እስቲ ተናገር»
«ኢየሩሳሌም!»
«ሁሉንም ይሻላል:: ግን ከኤምባሲያቸው ጋር ጉዳዩን
ተፈፅሟል»
«ስንት አስከፈሉን?»
«ሀምሳ ሚሊዮን ፍራንክ»
«እረ እንዚህ ቆንቋና ስግብግብ አይሁድ!» ብለው ጮ
ዤኔራል ሐምሳ ሚሊዮን ፍራንክ ያውም ለሰባት ክ
ያውም ለሶስት ቀን !?

ከመጽሐፉ ውስጥ

ዋጋ 13.00 ብር